አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ

በ

ደግሰው ጥላሁን

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ሰነ ጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት

ሰኔ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ

በ

ደግሰው ጥላሁን

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ መርሀግብር

ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ

በ

ደግሰው ጥላሁን

ሰኔ 2003 ዓ.ም

የፊተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዘሪሁን ገሰሰው	
አማካሪ	ፊርማ
ንታቸው ካህሀመሳርያው	
ፈታኝ	ፊርማ

ርዕስ ማውጫ

ርዕስ **ማውጫ**

ማውጫ i

ምስጋና v

የቃላት መፍቻ vi

የፎቶ ማውጫ vii

የቡሬ ወረዳ ካርታ ix

የወንበርማ ወረዳ ካርታ x

አጠቃሎ xi

1. መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ 2

1.4 የጥናቱ ወሰን 2

1.5 የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ አሰባሰብ 3

1.6 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች 5

1.7 የመስክ ተሞክሮ 7

2.ክለሳ ድርሳን 10

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 10

2.2 ንድፈሀሳባዊ ቅኝት 17

2.2.1 የቁሳዊ ባህል ምንነት 17

2.2.2 የቁሳዊ ባህል ጥናት የትኩረት ነጥቦች 19

2.2.3 ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (ሀገረሰባዊ ቅርፃቅርፅና ጌጣጌጥ) 20

2.2.4 የቁሳዊ ባህል ምደባ 21

3 የቡሬ እና የወንበርማ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ 24

3.1 መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት 24

3.2 የሕዝቡ መተዳደሪያ 26

3.3 ሐይማኖትና ልዩ ልዩ ሃገረሰባዊ ዕምነቶች 27

4. የመረጃ ትንተና በቡሬና በወንበርማ ወረዳ የቆዳና የሸክላ ስራ ላይ 29

4.1. የቆዳ ሥራ 29
4.1.1 የቆዳ ቁሶች ዓይነትና አገልግሎት 29
4.1.1.1 ለመኝታነት፣ ለልብስነትና ለትራስነት የሚያገለግሉ ቁሶች.. 30
4.1.1.2 ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉ የቆዳ ቁሶች 35
4.1.1.3. የተለያዩ ቁሶችን ለመሸፈን/ለመያዝ/ የሚያገለግሉ ቁሶች... 36
4.1.1.4 ለልጅ ማዘያና ማጫወቻ የሚያገለግሉ ቁሶች 40
4.1.1.5 ለእህል መያዣነት የሚያገለግሉ ቁሶች 42
4.1.1.6. የቆዳ ቁሶች ባህላዊ ጠቀሜታ 44
4.1.2 የቡሬ እና የወንበርማ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች መስሪያ ጥሬ ዕቃዎችና መሳሪያዎች 48
4.1.2.1 የቆዳ ቁሶች መስሪያ ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች 48
4.1.2.2 ለመፋቅና ለመቆራረጥ የሚያገለግሉ ቁሶች 49
4.1.2.3 ለመወጠር/ለመቃቃት/ የሚያገለግሉ ቁሶች 51
4.1.2.4 ለማለስለስና ለፀጉር ማስለቀቂያ የሚያገለግሉ ጥሬ እቃዎች 52
4.1.2.5 የቆዳ ቁሶችን ለማስጌጥ የሚውል ጥሬ ነገር 54
4.1.3 ባህላዊ የቆዳ ውጤቶች የአሠራር ሂደትና ዘዴ..... 54
4.1.3.1 ለቁሶች መስሪያ የሚያስፈልገውን ቆዳ ማዘጋጀት 55
4.1.3.2 መዘፍዘፍ ወይም መንከር 56
4.1.3.3 መፋቅና መቃቃት 57
4.1.3.4 መደበን 59
4.1.3.5 ማሸት/ማልፋት/ 60
4.1.3.6 ቀለም መቀባት ፣መቆራረጥና መስፋት..... 61
4.1.3.7 መተልተል/መሸንሸን/ እና ማጠር 63
4.1.4 ባህላዊ የቆዳ ሥራ ሙያ ለመዳ 64
4.1.5 የቆዳ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ..... 65
4.1.6 ከቆዳ ሙያ ጋር የተያያዙ እምነቶች እና አመለካከቶች..... 68
4.1.7 የቆዳ ባለሙያዎችን ያጋጠሙ ችግሮች 69
5. በቡሬ ወረዳ የሸክላ ቁሶች ስራ 73

5.1. የቡሬ ወረዳ የሸክላ ቁሶች የአሠራር ሂደት 73
5.1.1 የሸክላ አፈርን የመቆፈር ሂደት 73
5.1.2 የሸክላ አፈርንና ገልን ለስራ የማዘጋጀት ሂደት 77
5.1.3 የሸክላ ቁሶችን ለመስራት መጀመር እና ቅርጽ ማስያዝ 79
5.1.3.1 የጀበና አሠራር ሂደት 82
5.1.3.2 የሰታቴ /የትልቅ ድስት/ አሠራር ሂደት 85
5.1.4 የሸክላ ቁሶችን ማስጌጥና ማድረቅ 86
5.1.5 የሸክላ ቁሶችን መተኮስ 93
5.2 የሸክላ ውጤቶች ጠቀሜታና ወቅታዊ ሁኔታ 95
5.2.1 እስካሁን የሚመረቱ እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ቁሶች 95
5.2.2 መሰራትና ማገልገል ያቆሙ የሸክላ ቁሶች 96
5.2.1.3 ተፈላጊነታቸው በመቀነሱ በትዕዛዝ ብቻ የሚሠሩ የሸክላ ቁሶች 98
5.3 የሸክላ ቁሶች ጠቀሜታ 102
5.3.1 የሸክላ ቁሶች ማህበራዊ ጠቀሜታ 103
5.3.1.1 ለጠላ እና ጠጅ ማዘጋጃና ማቅረቢያ የሚሆኑ ቁሶች 103
5.3.1.2 ለአረቄ ማውጫ የሚያገለግሉ የሸክላ ቁሶች 105
5.3.1.3 ለወጥ መስሪያ፣ ለወተት፣ለውሃ ማፍሊያና ማሞቂያ የሚያገለግሉ የሸክላ ቁሶች 107
5.4 የሸክላ ቁሶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ 108
5.5 የሸክላ ቁሶች ባህላዊ ፋይዳ 109
5.6 የሸክላ ባለሙያዎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ 114
5.6.1 የሸክላ ስራ ሙያ ለመዳ 117
5.6.2 የሸክላ ሙያ ላይ የተጋረጡ ችግሮች 118
6.ያታዊ ተሳትፎ በባህላዊ የሸክላ እና የቆዳ ሥራ 121
7. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች 124
7.1 ማጠቃለያ 124
7.2 የይሁንታ ሃሳብ 127
ዋቢ ጽሁፎች 129
አባሪዎች

መታሰቢያነቱ

መታሰቢያነቱ የእሱን ፍላጎትና ምኞት ገድሎ እኔን በማስቀደም ለስኬቴ ሁሉ መሰረት ለሆነኝ አባቴ አቶ ጥላሁን ገላው ይሁንልኝ። አባቴ ከምድራዊ አባቶች ሁሉ አቻ የሌለው ፍቅርህና ውለታህ በእድሜዬ ሙሉ ከውስጤ ስለማይወጣ ወደ አንተ እስክምመጣ ድረስ አልረሳህም።

ምስጋና

በመጀመሪያ ዲግሪዬ ላይ ከስነጽሁፍ ጋር እንደተዋወቅ ላደረጉኝና በሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ቆይታዬ ደግሞ በርካታ ስነጽሁፋዊ ጉዳዮችን እንድገነዘብ ያስቻሉኝ መምህሬና አማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያለመሰልቸት በማረም እና አቅጣጫ በማስያዝ የዘወትር ምክራቸውና ማበረታታቸው ሳይለየኝ እዚህ ስለደረስኩ ከልቤ አመሰግናቸዋለሁ።

ጥናቱ ከታሰበለት ግብ ይደርስ ዘንድ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን በማገናኘትና መረጃ በመስጠት በመስክ ቆይታዬ ያጋጠሙኝን ችግሮች ያቃለልሽልኝ እናቴ ወ/ሮ መድሀኒት ዘገየ አንችን የማመሰግንበት ቃል ስለሚያጥረኝ እግዚአብሔር ረጅም እድሜ ይስጥሽ።

ለጥናቱ ግብአት የሆኑ መረጃዎችን በመስጠትና ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን በማገናኘት ቀና ትብብር ያደረጋችሁልኝ እና ስማችሁ በአባሪው የተጠቀሳችሁ መረጃ አቀባዮቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ የትወራ መጽሀፍትን በማዋስ እና በመጠቆም ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝና በልዩ የማስተማር ክሂላቸው የፎክሎር ፍቅር በውስጤ እንዲሰርጽ ያደረጉት መምህሬ ወንድወሰን አዳነ ከልብ አመሰግናለሁ።

ውድ ጊዜህን ሰውተህ የጥናታዊ ጽሁፉን የአርትኦት (የኤዲቲንግ ሥራ) ያለመሰልቸት በማገዝ ግልጽ ያልሆኑ ሀሳቦችን በማቅናት ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከጎኔ ያልተለየህው ጓደኛዬ ብሩክ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስህ።

ለኤዲቲንግ ስራ (ላፕቶፕ) ኮምፒውተር በማዋስ፣ የፊደልና የሀሳብ ግድፈቶችን በማረም ጥናቱ በታቀደው ጊዜ እንዲያልቅ ከፍ ያለ የሞራል ድጋፍ ያደረግሽልኝ በሁለት አመት ቆይታዬ ያፈራሁሽ ጓደኛዬ ደነቀ አበረ (ደኒ) አመሰግንሻለሁ።

ላፕቶፕ በማዋስ የኤዲቲንግ ሥራው እንዲቀላጠፍ በማድረግ የተባበርሽኝ ጓደኛዬ ሀመልማል ተሻለ ምስጋናዬ ይድረስሽ።

ሙዳየ ቃላት


መቀነቻ	የዝናር ማጥበቂያ
መወዘት	ማሞቅ
መከርከር	መድረቅ
መክላት	ማስወገድ
መግላሊት	የድንጉኝ ክዳን
ማቆጨት	ማርካት
ማቋደስ	ለመናፍስቶች (ዛሮች) ምግብና መጠጥ የማቅመስ ሥርዓት
ማዕዘንት	ለእንስራ እና ለገንቦ ማስቀመጫ የሚሠራ ከፍ ያለ ቦታ
ማድጋ	እንስራ
ሞሳ	ህፃን
ሠታቴ	ትልቅ ድስት (በገ ፈጅ)
ሠኔል/አንኩቲ	ከዘንባባ የሚሠራ ምንጣፍ
ሸቦ	የገብስ ገለባ
ሸንክላ	ከእንስራ አነስ ያለ የውሃ መቅጃ የሸክላ ዕቃ
ቀርበታ	ስልቻ
ቆረንጮ	የሻጉዲ ቁራጭ
ቡሆ	ሊጥ
ቶፋ	ለህፃናት ውሃ መቅጃ የሸክላ ዕቃ
አንዲር	ቡናው የሚቀዳበት የጀበና ክፍል
ኮሾ	የዳፕ ማዳበሪያ መያዣ ላስቲክ
ወደል	ትልቅ
ደበል እንሳ	ማህበረሰቡ ለ ሸክላ ባለሙያዎች የሠጣቸው ስያሜ
ደፊጫ	ዳጉሳ የተባለ እህል ገለባ
ዳ ማለት	መዘግየት
ድንጉኝ	ለውሃ እና ለወተት መቅጃ እና ማሞቅያ የምታገለግል የሸክላ ዕቃ
ገል	የሸክላ ቁስ ስባሪ
ጉችማ	ለበርበሬ ወይም አዋዜ ማስቀመጫ
ፍራ	የቆዳ ባለሙያዎች ሙያዊ ቃል ሲሆን ፍቺውም ቀዳዳ ማለት ነው፡፡
ፍንጃል	ስኒ

የፎቶ ማውጫ

ፎቶ 1 ገርንዲ በገበያላይ 31
ፎቶ 2 ላምነት 31
ፎቶ 3 የግርግዳ ጌጥ አጎዛዎች 32
ፎቶ 4 መጠጊያዎች በገበያ ላይ 35
ፎቶ 5 የተጠቀለለ መጫኛ- 36
ፎቶ 6 ምራኖች 36
ፎቶ 7 ሱቅ ላይ የተንጠለጠሉ ማህደሮች 37
ፎቶ 8 ዝናር 40
ፎቶ 9 ጀበርና 40
ፎቶ 10 አንቀልባዎች በገበያላይ- 41
ፎቶ 11 ቆዳ በመጥረቢያ ሲፋቅ 50
ፎቶ 12 ስፌት በወስፌ ሲለጎም 52
ፎቶ 13 የድንቡሻቡሽ ፍሬ 53
ፎቶ 14 የተወቀጠ ድንቡሻቡሽ 53
ፎቶ 15 በባለሙያዎች ግቢውስጥ የተጠራቀሙ ቆዳዎች 56
ፎቶ 16 አቶ በላይ ደነቀው ቆዳ በመዘፍዘፍ ላይ 57
ፎቶ 17 የተቃቁ ቆዳዎች 59
ፎቶ 18 ቀለም ተቀብቶ የተቃቃ ቆዳ 62
ፎቶ 19 አቶ አስማማው ለእንቀልባ የሚሆን ቆዳ ሲቆራርጡ 62
ፎቶ 20 የባጉና ቀበሌ ሸክላ አፈር መገኛ- 75
ፎቶ 21 የሻኳ ቀበሌ የሸክላ አፈር መገኛ 76
ፎቶ 22 የሸክላ አፈር ሲቢካ 78
ፎቶ 23 ወ/ሮ ቦሰናና አባባ ጀበና በመስራት ላይ 83
ፎቶ 24 ባለ ሶስት ና ባለ ሰባት እንዲር ጀበናዎች 85
ፎቶ 25 ሰታቴዎች በገበያላይ 86
ፎቶ 26 ጠንቋይ ያልሆኑ ሰዎች ማጤሻ 88
ፎቶ 27 የጠንቋዮች ማጤሻ 88
ፎቶ 28 ማእዘንት ላይ የተቀመጠ ገንቦ 91

ፎቶ 29 ከቤት ውጭ በመድረቅ ላይ ያሉ የላቀች ምድጃዎች 92
ፎቶ 30 ድስት ሲሚሽ 93
ፎቶ 31 ማሰሮ 98
ፎቶ 32 ጉልቻ የሌላት ላቀች 101
ፎቶ 33 ጉልቻ ያላት ላቀች 101
ፎቶ 34 ገበያ ላይ የቀረቡ ተንከርተቶች 102
ፎቶ 35 ሽንክላዎች 104
ፎቶ 36 ቧድና 104
ፎቶ 37 ጋን 104
ፎቶ 38 ለአረቄ ማውጫ የሚያገለግሉ የሸክላ ቁሶች 106

የቡሬ ወረዳ ካርታ


Kebele Map of Burie woreda
Ageni Ferda
Wohini Durbete
Jib Gedel
Arebsi Menefesawit
Ambaye Woynma
Shakuwa
Burie town Administration
Tiyatiya
Denbun Fuati Galabed
Wadra Gndiba
Adilgata
Alefa Basi
Gulem Derjin
Zelma Shembekuma
Sertegez
Fezel
Ziyiw Shiwa Kuch Town
Gedame Lijemur
Feteme Senetom
Boko Tabo
0 2.5 5 10 KM
Source - GIS Team of ANRS BoFED
CSA map is used as base map

የወንበርማ ወረዳ ካርታ

አጠቃሎ

ይህ ጥናት “ባህላዊ የሸክላ እና የቆዳ ሥራ በቡሬ እና ወንበርማ ወረዳ” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሲሆን የሸክላ እና የቆዳ ውጤቶችን የአሠራር ሂደት እና ጠቀሜታ መመርመርን ዋነኛ ዓላማ ያደረገ ነው። በተጨማሪም የባለሙያዎች ህይወትና ባለሙያዎቹ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና በሙያቸው ያገኙት እና ያጡት ጉዳይ ተዳሷል። እንዲሁም ቁሶችን ከባህል መገለጫነታቸው አንፃር በመተንተን ማህበረሰቡ በቁሶቹ ራሱን ምን ያህል እንደሚገልጽ ለመመርመር ጥረት ተደርጓል።

የጥናቱን ዓቢይ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የቃል መጠይቅና ምልከታ በመረጃ መሠብሰቢያነት ጥቅም ውለዋል። መረጃዎቹን በእነዚህ ዘዴዎች በመጠቀም ከተፈጥሯዊ መቼቱ ለመሠብሰብ ተችሏል። በዚህ መንገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ትዎራዎች ጋር በመጣመር ተተንትነዋል። በዚህም መሠረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውጤቶች ላይ ለመድረስ ተችሏል።

በሁለቱ ወረዳዎች የሚገኙት ባለሙያዎች ቀደም ባሉት ጊዜያት የተለያዩ ቁሶችን በማበጀት ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ያቀርቡ ነበር። የቆዳ ባለሙያዎች ሃያ ሶስት አይነት ቁሶችን የሸክላ ባለሙያዎች ደግሞ ሀያ ሁለት የሸክላ ቁሶችን ያመርቱ ነበር። ባሁኑ ጊዜ ግን ሁለቱም ባለሙያዎች እየሰሩ ለገበያ የሚያቀርቧቸው ቁሶች አይነትና ቁጥር እየቀነሰ መምጣቱን ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል። የቆዳ ባለሙያዎች ሰባት ያህል ቁሶችን ብቻ የሚያመርቱ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አራቱ ወቅት እየጠበቁ በሠርግ እና በእርሻ ሥራ ጊዜ ብቻ የሚበጁ ናቸው።በአካባቢው የሚበጁት የሸክላ ቁስ አይነቶች ቁጥራቸው ወደ አስራ ሶስት ቀንሷል። አንዳንድ የሸክላ ቁሶች ደግሞ መሰራት አቁመዋል።

ከጥናቱ እንደተገኘው የቆዳ ሥራ በስምንት ተከታታይ የሥራ ሂደቶች አልፎ የሚከወን ሲሆን የሸክላ ሥራ ደግሞ አምስት ሂደቶችን በማለፍ ይሠራል። የሁለቱም ሙያዎች የአሰራር ሂደቶች አድካሚ ሲሆኑ የባለሙያዎችን ጥበብ እና ክህሎት በእጅጉ ይጠይቃሉ።

በጥናቱ የተተነተኑት የሸክላ እና የቆዳ ቁሶች ከሚሠጡት አገልግሎት ባሻገር የተጠቃሚዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን በመጠቆም እና አንዳንድ ባህላዊ ክዋኔዎችን ለመከወን እና የተጠቃሚዎች እምነት መገለጫ በመሆን ያገለግላሉ።።

ከጥናቱ ግኝቶች መረዳት እንደሚቻለው የቆዳ እና የሸክላ ሥራ ውጤቶች የተለየ ጥበብን እና ክህሎትን በመጠቀም የሚሰሩ ሲሆን ለተጠቃሚው እና ለባለሙያዎቹ ከፍ ያለ ጥቅም ይሰጣሉ።። ነገር ግን ለእነዚህ ቁሶችና ባለሙያዎች በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እምብዛም ትኩረት የተሰጣቸወው አይደሉም።። በመሆኑም ቢሮው የአካባቢውን የቆዳ እና የሸክላ ቁሶች ማጥናት ይጠበቅበታል፤ የእጅ ባለሙያዎችንም ከሚደርስባቸው መገለል ለማዳን ለማህበረሰቡ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ቢሰጥ፤ ቁሶቹ በተሻለ ሁኔታ የሚሠሩበት መንገድ ሊፈጠር ይቻላል የሚል ሃሳብ አለኝ።። ከዚህም በተጨማሪ የቁሶቹን ጥቅም በተለያዩ ማህበራዊ እና ባህላዊ አጋጣሚዎች የማስተዋወቅ ሥራ ቢሠራ ማህበረሰቡ ለቁሶች እና በተለይም ለባለሙያዎች ያለው አሉታዊ አመለካከት ሊቀየር ይቻላል ብዬ አምናለሁ።።

1. መግቢያ

ይህ ክፍል ስምንት ንዑሳን ጉዳዮችን አካቶ ይዟል፡፡ እነሱም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ናቸው::

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ተወልጄ ያደግሁት፣ ትምህርቴንም እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የተማርኩት ቡራ አካባቢ በመሆኑ የቆዳ ፣ የሸክላ፣ የሽመናና የአንጥረኝነት ስራ ሲከናወኑና ማህበረሰቡም ከእነዚህ ሙያ ውጤቶች የሚገኙ ቁሶችን ለእለት ከእለት ኑሮ ማከናወኛ በስፋት ሲጠቀምባቸው አስተውል ነበር፡፡

ቦታው ምንም እንኳን ተወልጄ ያደግሁበት አካባቢ ቢሆንም ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ኑሮዬ ከዚህ አካባቢ ውጪ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ወደ ቦታው የምሄደው በአመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ሲሆን የምቆየውም ከሳምንት እስከ አንድ ወር ብቻ ነው፡፡ ወደ ቦታው በምሄድበት ጊዜ የእነዚህ ቁሶች በተለይም የሸክላና የቆዳ ስራ ውጤቶች ተግባር ላይ የመዋል ሁኔታ ከአመት ወደ አመት እየቀነሰ መሄዱን ተመልክቻለሁ፡፡

በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የማስተርስ ዲግሪ የአንደኛ አመት ዓመት ትምህርቴ ስለ ቁሳዊ ባህል ያገኘሁት ግንዛቤ ለእረፍት ወደ ቦታው በሄድኩበት ወቅት ይበልጥ ነገሩን እንዳተኩርበት አደረገኝ፡፡በዚህም ምክንያት ጥናቴን በቁሶች ማህበራዊ እና ባህላዊ አገልግሎት ላይ ለማድረግ ተነሳሳሁ፡፡በተጨማሪም የሙያው ባለቤቶች ዋናው መተዳደሪያቸው የተመሠረተው እንደሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች በእርሻ ላይ ቢሆንም አሠፋፈራቸው ግን ከሌሎች ኗሪዎች የተገለሉና በአንድ አካባቢ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ይህ ሁኔታና ባለሙያ ያልሆነው ማህበረሰብ ስለባለሙያዎቹ በተለያዩ አጋጣሚዎች አመለካከቱን ሲገልጽ መስማቴ ጉዳዩን ይበልጥ እንዳጠናው አነሳስተውኛል ::

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ ባህላዊ የሸክላና የቆዳን አሠራር ሂደትና ጥቅም ማሳየትና መቅረስ፣ የባለሙያዎችን የህይወት ልምድ መዳሰስ ነው። ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት።

- የሸክላና የቆዳ ሥራ ሙያ ለመዳን ማሳየት፣
- ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹና ለዕቃዎቹ ያለውን አመለካከት ማሳየት፣
- የሁለቱን ባለሙያዎች የእርስበእርስ ግንኙነት መርምሮ ማሳየት፣
- የአካባቢውን የሸክላና የቆዳ ሥራ ወቅታዊ ሁኔታ መዳሰስ፣
- በሁለቱ ሙያዎች የሚታየውን ጸታዊ ተሳተፎ ማሳየት፤

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

- ከሸክላና ከቆዳ የተሠሩ የቤት ቁሶችን የአመራረት ሂደት እና ተግባር ያሳውቃል።
- ከሸክላና ከቆዳ ቁሶች አጠቃቀም አንፃር የአካባቢው ማህበረሰብ ባህል እና እምነት ምን እንደሚመስል መረጃ ይሰጣል።
- ከሸክላና ከቆዳ የሚሰሩ የቁሳቁስ ዓይነቶችን ቀርሶ ለማቆየት ይጠቅማል።
- ቁሳዊ ባህሎች ወደፊት በተሻለ መንገድ የሚሰሩበትን ሁኔታ ይጠቁማል።
- በቡሬ እና በወንበርማ ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ የቆዳ እና የሸክላ ባለሙያዎች ያላቸውን የህይወት ልምድ ያሳያል።
- በአካባቢው ወደፊት በቁሳዊ ባህል ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ሠዎች የተወሰነ መረጃ ይሰጣል።

1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፎች መካከል በተለይ ዕደ ጥበብ ተብሎ በሚታወቀው ዘርፍ ስር ከሚገኙት ንዑሳን ዘርፎች /በባህላዊ የሸክላ እና የቆዳ ስራ/ ላይ ብቻ ያተኩራል።

ጥናቱ በ ሁለት ወረዳዎች ላይ የተወሰነ ነው። ይኸውም የሸክላ ስራው ቡሬ ወረዳ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች (ባጉናና ሻኳ) ላይ ሲያተኩር የቆዳ ስራው ደግሞ

በወንበርማ ወረዳ ሻምብላበር በምትባል አካባቢ እና በቡሬ ወረዳ ባጉና ሀና ቀበሌ ላይ ብቻ ያተኩራል። ቦታዎቹ የተመረጡት መረጃ ለማግኘት ካላቸው ምቹነት (እኔ ወይም ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ የሚያውቋቸው አካባቢዎች መሆናቸው) እና ካላቸው የትራንስፖርት አመቺነት አንፃር ነው።

1.5 የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ አሰባሰብ

የጥናቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ምልከታና ቃለመጠይቅ በዋናነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ቀጥሎም እነዚህ ዘዴዎች በምን አይነት ሁኔታ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ይገለፃል።

ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት ሠዎች በተለይም ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በአካባቢው ሠዎች ጥቆማ ቁሶችን በመስራት፤ በመጠቀም፣ ከረዥም ጊዜ የህይወት ልምዳቸው ባለመ.ያዎችን ጠንቅቆ በማወቅ፣ እንዲሁም የቁሶችን ታሪካዊ አመጣጥ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ጥቅም ከማወቅ አንፃር የተመሠከረላቸው ሠዎች ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ በተለያዩ አጋጣሚዎች ማለትም በሆቴል፣ ሻይ ቤት፣ ዘመድ ቤት፣ መንገድ ላይ ተዋውቂያቸው ጥሩ መረጃ የሰጡኝ ግለሰቦች አሉ።

በቃለ መጠይቁ የተካተቱ የዕደ ጥበብ ሠራተኞች፤ የቁሶቹ ተጠቃሚዎች፤ ታሪክ እና ባህል አዋቂ የሃገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት ሠዎች፤ ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸው የወረዳው አስተዳደር እና ሌሎች ኃላፊዎች እና ባለመ.ያዎች ናቸው። መረጃ አቀባዮቼ ወንዶችም ሴቶችም ሲሆኑ እድሜያቸው ከ ሀያ አምስት እስከ ሰማኒያ ነው።

ቃለ መጠይቁ ለመረጃ አቀባዮች የቀረበው በሁለት አይነት መንገድ ነው። አንደኛው መንገድ ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት የተዘጋጁ ጥያቄዎች ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡበት መንገድወይም መደበኛ ቃለመጠይቅ የሚባለው ሲሆን ሌላው እና በብዛት የተጠቀምሁበት መንገድ ደግሞ ኢመደበኛ ቃለመጠይቅ የተባለው ነው።

የቃል መጠይቆቹ የቀረቡበት ቦታ መኖሪያ ቤት፣ ገበያ፣ የህዝብ መዝናኛዎች (ሻይ ቤት፣ ሆቴል፣ አረቄ ቤት)፣ መንገድ ላይ እና የቁሶች መስሪያ ቦታ ላይ ነው። ቦታዎቹ የተመረጡት መረጃ አቀባዮች አዘውትረው የሚገኙባቸው በመሆናቸው እና ጥያቄዎችን ለማቅረብ የተሻሉ አማራጮች ሆነው በመገኘታቸው ነው። በቃለ መጠይቅ መረጃዎች በምሰበስብበት ወቅት ማስታወሻ ደብተርና መቅረፀ ድምጽ ተጠቅሚያለሁ። ነገር ግን አንዳንድ መረጃ አቀባዮች በመቅረፀ ድምጽ ደምጻቸው እንዳይቀረፅ በመፈለጋቸው ምክንያት በዋነኛነት የተጠቀምሁት ማስታወሻ መፃፍን ነው። አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ፈቃደኛ ሆነው ሲገኙ ደግሞ መቅረፀ ድምጽን ተጠቅሚያለሁ።

ምልከታ የቁሶችን የአሠራር ሂደት፣ የቁሶችን መገኛ ቦታ፣ አገልግሎት ፣ የመስሪያ ንጥረ ነገሮችን መገኛ ቦታ፣ የቁሶችን ግብይት ለመመልከት የተጠቀምኩበት ዘዴ ነው። በተጨማሪ የቁሶች መሸጫ ቦታ ከሌሎች ቁሶች ጋር ያለውን ቅርበት እና እርቀት ለማወቅ በቦታዎቹ በመገኘት ምልከታ አካሂጃለሁ። ምልከታዬም በፎቶ እና በቪዲዮ ካሜራ እንዲሁም በማስታወሻ የታገዘ ነው። ይኸውም በፎቶ የቁሶችን ቅርጽ፣ መስሪያ እና ማዘጋጃ ቦታ፣ የቁሶች የአገልግሎት እና የመቀመጫ ቦታ፣ ቀለም፣ እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመቅረጽ የአገለገለ ሲሆን ቪዲዮ ደግሞ የቁሶችን የአሠራር ሂደት፣ እና የመስሪያ ጥሬ ነገሮችን መገኛ ቦታ እንዲሁም የባለሙያዎችን መኖሪያ እና መስሪያ አካባቢ ቀርጸ ለመያዝ አገልግሏል።

የተሰበሰቡት መረጃዎችጥናቱ በአላማነት ይዞት የተነሳውን ጉዳይ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ ተተንትነዋል። በትንተናው ሂደት በመጀመሪያ የመስኩ ምሁራን እንደሚመክሩት ቁሶቹን በምድብ በምድብ አስቀምጫለሁ። የቆዳ ቁሶችን ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር ለልብስነት፣ ለእርሻ ስራ፣ ለልጅ ማዘያና ማጫወቻ ወዘተ የሚያገለግሉ በሚል፣ የሸክላ ቁሶችን ደግሞ ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መሰራትና ማገልገል ቆመ፣ ተፈላጊነታቸው በመቀነሱ በትእዛዝ የሚሰሩ፣ ወዘተ በማለት ክፍፍሉን ካደረግሁ በኋላ። Prown (1982) ከአብራሪያቸው ሶስት የመተንተኛ ሂደቶች መካከል ገለፃንና ትርጓሜን በመጠቀም መረጃዎችን ተንትኛለሁ።

ገለፃ፡- አጥኝው ለትንተና የመረጠውን ቁስ እሱ ባየበት መንገድ አጠቃላይ ገፅታውን በመግለፅ ቁሱን አይተውት ለማያውቁ ሰዎች ምናባዊ ምስል መፍጠር ነው፡፡ ማለትም በውጫዊ ገፅታው ላይ በማተኮር ቀለሙን፣ ክብደቱን፣ ልስላሴና ሸካራነቱን፣ ወፍረት እና ቅጥነቱንን፣ የተሠራበትን ንጥረ ቁስ፣ ቅርፁንና ጌጣጌጡን ወዘተ በማብራራት በአንባቢ ዓይነ ህሊና ምስል ለመፍጠር በሚያስልችል ሁኔታ መግለፅ ነው፡፡ በአጠቃላይ ገለፃ በአይን ታይቶ ሊገለፅ በሚችለው የቁሱ ገፅታ ላይ ብቻ በማተኮር የሚከናወን የትንታኔያችን የመጀመሪያ ተግባር ነው፡፡

ትርጓሜ፡- የቁሱን አጠቃላይ ገፅታ እና ጠቀሜታ ገለፃ ካደረግን በኋላ የሚቀጥል ሁለተኛው የትንታኔ ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት አጥኝው የቁሱን ገፅታ ከመግለፅ ባለፈ በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት (Reaction) በመመርመር ወደ ትርጓሜ ያመራል፡፡ በዚህም መሰረት ገለፃው ከላይ የዘረዘራቸውን መረጃዎች መነሻ በማድረግ ቁሱ የያዘውን ገፅታ እንዴት እና ለምን ሊያገኝ እንደቻለ በማጤን፣ቁሱ በዚህ ወቅት እና ቀደም ባሉት ጊዜያት ሲሰጥ የነበረውንና እየሰጠ ያለውን አገልግሎት እንዲሰጥ የተመረጠበትን ምክንያት በመመርመር የመተርጎም ስራ ያከናውናል፡፡

1.6 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመስክ ቆይታዬ ወቅት በመጀመሪያ ያጋጠመኝ ችግር ወደ መስክ ከወጣሁበት ወቅት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ወደ መስክ የሄድኩበት ጊዜ የፋሲካ በዓል ዋዜማ በመሆኑ የቢሮ ሀላፊዎችንም ሆነ ባለሙያዎችን በወቅቱ አግኝቼ የምፈልገውን መረጃ በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ እንዳልሰበስብ አድርጐኛል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች እና ሌሎች የወረዳው አስተዳደር ኃላፊዎች በበዓሉ ምክንያት የአንድ ሳምንትና ከዚያ በላይ የሆነ ጊዜ ፈቃድ ስለወሰዱ በወረዳው በቁሳዊ ባህል በተለይም በቆዳና ሸክላ ዙሪያ የተደረጉና፣ እየተደረጉ ያሉ እንቅስቃሴዎችን፣ ማለትም የተሠበሰቡ መረጃዎች ወይም የተጠኑ ጥናታዊ ጽሁፎች መኖራቸውን የሚያሳውቅ መረጃ በጊዜው ማግኘት አልቻልኩም ::

በጥናቱ አካባቢ የፋሲካ በዓል በከፍተኛ ቅድመ ዝግጅት ከሚከበሩት በዓላት አንዱ በመሆኑ ባለሙያዎች ቀድመው የሠሯቸውን ቁሶች ሸጠው ሌሎች የበዓል ዝግጅቶችን የሚያደርጉበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ እንዳሰብኩት ባለሙያዎችን አግኝቼ የቁሶችን አሠራር ሂደትም ሆነ ሥለ ህይወታቸው ማናገር አልቻልኩም፡፡ በነዚህ ችግሮች ምክንያት የመስክ ሥራዬን ለአንድ ሳምንት /በዓሉ እስከሚያልፍ/ ሳልጀምር ለመቆየት ተገድጃለሁ፡፡

ሌላው ያጋጠመኝ ችግር ደግሞ ከቆዳ እና ሸክላ ባለሙያዎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ገና ሲያዩኝ የእኔን ዓላማ ከመንግስት ጋር በማያያዝ ግብር ሊጣልብን ነው በሚል ፍራቻ በተለይም ከቁሶች ዋጋ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በግልጽ ለመናገር አለመፈለጋቸው ነው፡፡ባለሙያዎቹ የኛን ጥበብ ለሌላ ሃገር ልታስተዋውቂብን እና የኛን ገበያ ልትዘጊብን ነው የሚል ሥጋትም ነበራቸው፡፡

ሊጠኑ ከተመረጡት ሙያዎች ባህሪ የመጣ ችግርም ተከስቷል፡፡ ለምሳሌ የሸክላ ሥራ ብዙ ሂደቶችን የሚያልፍ የዕደ ጥበብ ሥራ ነው፡፡ ከሂደቶቹ ውስጥም የሸክላ አፈር መቆፈር የመጀመሪያው እና ዋናው ሥራ ነው፡፡ ይህ ሂደት በጣም አድካሚ በመሆኑ በአካባቢው የሚኖሩ የሸክላ ባለሙያዎች ተነጋግረው በረኸም ጊዜ ልዩነት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ነው ወደ ቁፋሮ የሚሄዱት፡፡የአተኮርሁበት ቀበሌ የሸክላ ባለሙያዎች እኔ ወደ መስክ ከመድረሴ አንድ ቀን ቀድመው ቁፋሮውን አካሂደዋል፡፡ ለአንድ ወር እና ከዚያ በላይ ሊያገለግላቸው የሚችል የሸክላ አፈር በማጠራቀማቸው ይህን ሂደት በቪዲዮም ሆነ በፎቶ መቅረጽ አልተቻለም፡፡

በዚህ ጥናት ካጋጠሙኝ ችግሮች በጣም ፈታኝ የሆነብኝና መፍተሄ ሊገኝለት ያልቻለው ችግር ከሁለቱ የእደጥበብ ዘርፎች ጋር ተያይዘው የሚዜሙ የስነቃል ዘሮችን ማግኘት አለመቻሌ ነው፡፡ ለዚህም ሁለት ነጥቦች በምክንያትነት ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው ስነቃሎቹ ታስበው የሚባሉ ሳይሆኑ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎችና ባጋጣሚ የሚከወኑ መሆናቸው፤ ሁለተኛው ደግሞ ባለሙያዎቹ ስራችንን እንጂ ጭቃ እየጠፈጠፍን ቆዳ እየፋቅን ዘፈን ምን ያደርግልናል (ወንዴ አምባው እና አበባ ደመላሽ ቃለመጠይቅ፣ግንቦት፣9፣2003፣) በማለት ስነቃሎቹን ከምንም አለመቁጠራቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የመስክ ሥራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ከላይ የተገለፁትን ይመስላሉ፡፡ የተፈጠሩትን ችግሮችም እንደ ፎክሎር አጥኚ የተለየዩ አማራጭ መንገዶችን በመጠቀም ለመቅረፍ እና የተጠበቀውን መረጃ ለመሠብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡መፍተሄዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡ ከጊዜ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ችግሮችን ከባለሙያዎች ጋር የምገናኝባቸውን ቀናት በመጨመር ችግሩን የቀረፍኩ ሲሆን በባለሙዎች የተፈጠሩትን የግብር ይጣልብናል እና ጥበባችንን ወደ ሌላ አገር ይወሰድብናል የሚሉ ስጋቶችም አላማየን ደጋግሜ በማስረዳት እና በማሳመን የሚፈለገውን መረጃ መውሰድ ችያለሁ፡፡ከመቅረፀ ድምጽ ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን ችግር ደግሞ ከመረጃ አቀባዮች የንግግር ፍጥነት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ አካሄድ ማሰታዎሻ በመጻፍ ችግሩ ተቀርፏል፡፡

1.7 የመስክ ተሞክሮ

የጥናቴ ቦታ ወደሆኑት ቡሬና ወንበርማ ወረዳ የተጓዝኩት ለመረጃ መሠብሠቢያነት የሚያግዙ መሳሪያዎችን ማለትም መቅረፀ ድምጽ/ቴኘ/፣ የቴኘ እና የቪዲዮ ካሴቶች፣ ባትሪ ድንጋይ፣ የጽህፈት መሳሪያዎች፣ ፊልም፣ ሜትር በመያዝ ነው፡፡ ጉዞውን የጀመርኩት በሚያዚያ 09/03 ሲሆን ከአዲስ አበባ በቀጥታ ቡሬ የሚመደብ አውቶቡስ ባለመኖሩ በመጀመሪያው ዕለት ፍኖተሰላም አረፍኩ፤ በማግስቱ ቡሬ ወረዳ ደረስኩ፡፡

ጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮ ውስጥ በሚሠሩ አቶ የሸዋስ ተመስገን በሚባሉ ግለሰብ አማካይነት ወደ እምፊልጋቸው ቢሮዎች /ባህልና ቱሪዝም፣ አስተዳደር ቢሮዎች/ ለመሄድ ተዘጋጀሁ፡፡ አቶ የሸዋስ ወረዳው ከተማ እና ገጠር ዙሪያ መስተዳደር ተብሎ ስለተከፈለ የትኛው ጋ በመሄድ እንደምፈልግ ጠየቁኝ፡፡ አላማዬን ገለጽኩላቸውና ወደተለያዩ ቢሮዎች ከእሳቸው ጋር ሄድኩ፡፡

በሚያዚያ 10፣2003 ዓ.ም ገጠር ዙሪያ በመሄድ ኃላፊውን ለማግኘት ሙከራ አደረግሁ፡፡ ነገር ግን ኃላፊው ለሥብሰባ ሌላ ወረዳ እንደሄዱ እና ሊገኙ የሚችሉት ከፋሲካ በዓል በኋላ መሆኑን ገለፁልኝ፡፡ በቢሮ ውስጥ ላገኘኋቸው ባለሙያዎች ዓላማዬን በግልጽ አስረዳሁ፡፡ እነሱም በኔ ርእስ ዙሪያ የተሰራ አለመኖሩን ገልፀው ምንአልባት ቢሰራ እንኳን ከሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት /ማስታወቂያ ቢሮ/ ነው

የሚገኘው በማለት እዚያ ብጠይቅ የሚሻል መሆኑን ገለፁልኝ፡፡ እኔም ወደ ተባለው ቢሮ አመራሁና አላማዬን አስተዋውቄ የተሠራ ነገር ካለ እንዲገልፁልኝ ጠየኳቸው፡፡ እነሱም ምንም እንዳልተሠራ ነገሩኝ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ጉዞዬን ወደ ከተማ መስተዳደር ሴቶች ጉዳይ ቢሮ አደረግሁ፡፡ ወደ ቢሮ ስደረስም የሴቶች ጉዳይ ሃላፊዋ በስብሰባ ምክንያት ቢሮዋ ውስጥ አልነበሩም፡፡ ነገር ግን ሴቶች ጉዳይ ቢሮ የሥርዓተ ፆታ ሥርጸትና የሥራ ክትትል ባለሙያ የሆኑትን ወ/ሮ አሊማን አገኘሁ፡፡ ለእሳቸውም ዓላማዬን ገለጽኩላቸው፡፡ ወ/ሮ አሊማን በሸክላና በቆዳ ሥራ ዙሪያ ባለሙያዎች ተደራጅተው የሚሠሩበትን እድል ከጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮ ጋር ለማመቻቸት እንደሞከሩ እና በሸክላ ዙሪያ እንድትሰለጥን የተላከችው ሴት ሠልጥና መጥታ ልምዷን ሳታካፍል መሞቷን ገለፁልኝ፡፡ በወረዳው ለእነዚህ ሙያዎች የሚሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ፣የግንዘብ ችግርም በመኖሩ ሌላ ዕድል በድጋሚ ማመቻቸት እንዳልተቻለ በዕቅድ ደረጃ ግን መያዙን ነገሩኝ፡፡ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ደግሞ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊዋን ወ/ሮ ወለትን ማናገር እንዳለብኝ እና የማገኛቸውም ከበዓል በኋላ መሆኑን ገለጹልኝና ከወይዘሮ አሊማ ጋር የነበረኝ ቆይታ በዚሁ አበቃ፡፡

በሚያዚያ 12፣ 2003 ዓ.ም ወደ ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት በመሄድ የወረዳውን ምክትል ከንቲባ ለማግኘት ሙከራ አደረግሁ፡፡ ነገር ግን በስብሰባና በሌሎች ሥራዎች ምክንያት ቢሯቸው ውስጥ ላገኛቸው ስላልቻልኩ ከትምህርት ክፍሉ ይገፍው የሄድኩትን የትብብር ደብዳቤ ለፀሐፊያቸው በመስጠት ከበዓል በኋላ ማለትም ማክሠኞ ሚያዚያ18፣ 2003 እንድምመለስ ነግሬያቸው ባለሙያዎቹ ወደ ሚገኙበት ገጠር ቀበሌ በሚያዚያ13፣2003 አመራሁ፡፡ ከዚያም የሸክላ እና የቆዳ ባለሙያዎመኖቹ መኖሪያ አካባቢ፤ የቆዳ መዘፍዘፍያ ወንዞችን፣ የሸክላ አፈር መቆፈሪያ ቦታዎችን ተመልክቼ ስንት ባለሙያዎች እንዳሉ እና የታዋቂ ባለሙያዎችን ሥም ጠይቄ ወደ ቤተሰቦቼ ተመለስሁ፡፡ እናቴም ሸክላ ሠሪ ደንበኞች እንዳሏትና እነሱን በቀላሉ ማግኘት እንደሚቻል ነገረችኝ፡፡ የቆዳ ባለሙያዎችን ደግሞ እነሱ አካባቢ የሚኖሩ ነገር ግን ባለሙያ ያልሆኑ ዘመዶች እንዳሏትና በእነሱ አማካይነት ማግኘት እንደምችል ነገረችኝ፡፡ ነገር ግን ወቅቱ የበዓል ሰሞን በመሆኑ ሸክላ ሠሪዎች እንደማይሠሩ ነገረችኝ፡፡ ቆዳ ሠሪዎችም ያም

በመሆኑ ቆዳ አያገኙም፤ በዓል ስለሆነም እነሱም አይሠሩም በማለት፤ እኔም በአመት በዓል ከሰው ቤት አልሄድም ስለሆነም ከበዓል በኋላ በሚያዚያ 19 እና 20 ይዛኝ እንደምትሄድ ገለፀችልኝ። ከዚያም ቀጠሮ ይዛ ከባለሙያዎች ጋር አገናኘችኝ።

ባጉና ሃና ቀበሌ ይሠሩ የነበሩት የቆዳ ባለሙያዎች መስራት ስለተዉ የቆዳ ሥራን ጥበብ እና የአሠራር ሂደት በበለጠ ለመመርመር ወደ ወንበርማ ወረዳ መሄድ እንዳለብኝ እናቴና ሌሎች የአካባቢው ተወላጆች ስለጠቆሙኝ ወደዚያው በመሄድ የማውቃቸውን የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሠራተኞች ከመረጃ አቀባዮች ጋር በቀላሉ እንዲያገናኙኝ ይገዙ በመሄድ የሚፈለገውን መረጃ ለመሰብሰብ ቻልሁ።

ከመስክ ተሞክሮዬ የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር፣ አንድ የፎክሎር አጥኚ ለጥናት የመረጠው ቦታ የትውልድ ቦታው ካልሆነ ቀደም ብሎ የማህበረሰቡን ባህል፣ እምነትና ፍላጐት፣ ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ወደ መስክ ከመሄዱ በፊት መረጃ አቀባዮችን የሚያገናኝ ቁልፍ ሰው ማግኘቱ ተቀዳሚ ተግባሩ ሊሆን ይገባል።

2.ክለሳ ድርሳን

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ አጭር ቅኝት ከቁሳዊ ባህል ዘርፎች አንዱ በሆነው ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ሥራ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ይቃኛሉ፡፡ በዚህ ክፍል የሚቃኙት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል እና በሌሎች ትምህርት ክፍሎች ለቢኤ ዲግሪና ለ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የተደረጉ ጥናቶች፣ እንዲሁም የዲግሪ ማሟያ ያልሆኑ ሌሎች ጥናቶች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡት አስራ ሁለት የቁሳዊ ባህል ጥናቶች ውስጥ ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራን በጨረፍታ የነካው የደስታ ሎሬንሶ ጥናት ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ “የከምባታ ሕብረተሰብ ባለእጆችና ስነቃሎቻቸው” በሚል ርዕስ በ1982 ዓ.ም ቀርቧል፡፡ አጥኚው በዚህ ጽሁፍ ሌሎች ሙያዎችን ጨምሮ ቆዳና ሸክላን በሚመለከት የተዜሙ ስነ ቃሎችንም ዳሷል፡፡ አጥኚው ቃለ መጠይቅን ለመረጃ መሰብሰቢያነት እንደተጠቀመ ገልጿል፡፡ ስነ ቃሎችን ሰብስቦ ከተነተነ በኋላ በከምባታ ማህበረሰብ ዘንድ ሽመናና የብረታ ብረት ስራዎችን ማንኛውም የብሔረሰብ አባላት የሚሰራቸው ሲሆን የሸክላና የቆዳ ሥራ ግን በዝቅተኛው ማህበረሰብ የሚሰራ ተደርጎ ስለሚታይ ባለሙያዎቹ እንደሚገለሉ ገልጿል፡፡

በጥናቱ ያቀረባቸውና ትንተና ያደረገባቸው ሥነ ቃሎች በከፊል ስለ ሸክላ ሰሪዎች እና በጥቂቱ ስለ ቆዳ ባለሙያዎች የተዜሙ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበትም ምክንያት ሌሎች ሙያዎች የሁሉም ህብረተሰብ ሥራዎች ስለሆኑና ስለነሱ የተነገሩ ስነ ቃሎች ባለመገኘታቸው ነው በማለት ገልጿል፡፡ የሸክላ ሰራተኞች ስነ ቃል መበርከቱ ደግሞ የሸክላ ሰራተኞች ከቆዳ ባለሙያዎች ይበልጥ ስለሚናቁ ነው በማለት ገልጿል፡፡ ስለቆዳ ሰራተኞች የተነገሩ ስነቃሎች ይዘትም የባለሙያዎችን አመጋገብ ስርዓትና ማህበራዊ ሕይወትን የሚያንቋሽሹ እንደሆኑ አስረድቷል፡፡

ይህ ጥናት የባለሙያዎችን ህይወት መዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ሆኖም ግን በኔ ጥናት የሸክላና የቆዳ ቁሶችን ያሰራር ሂደት፣ ጠቀሜታ፣አይነት የሚሉትንና ሌሎችን ጉዳዮች በጥልቀት መዳሰሱ የኔን ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ድህረምረቃ መርሐግብር የተደረጉ የተወሰኑ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ የኔን የጥናት ርዕሰ ጉዳይ በጨረፍታም ይሁን በሰፊው የሚነኩት የሚከተሉት አራት ጥናቶች ናቸው፡፡ እነዚህም፡- ሔለን አላምረው "በህላዊ የሽመናና የቆዳ ሥራ በደምበጫና አካባቢዋ" (1999)፣ አስቴር ሙሉ "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረሰላጤ" (2000)፣ ታምራት ህይሉ "የብራና መፃህፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ" (2000)፣ እና ህብታሙ እንግዳው "በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሻሞ ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድኃኒዓለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና" (2001) ናቸው፡፡ ቀጥዬ እነዚህን ጥናቶች በዝርዝር እቃኛለሁ፡፡

"ባህላዊ ሽመናና የቆዳ ሥራ በደምበጫና አካባቢዋ" በሚል ርዕስ በሔለን አላምረው በ1999 ዓ.ም የቀረበው ጥናት ዋነኛ ዓላማ በደምበጫና አካባቢዋ የሚገኙ ባህላዊ የሽመናና የቆዳ ሥራዎችን አሰራር ሂደት ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱ ባለሙያዎቹ በሥራቸው የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎችና የአሰራር ሂደቶች ከማንና እንዴት እንደሚያገኟቸው ተዳሰዋል፡፡ አጥኚዋ የቁሳዊ ባህልንና የህገረሰባዊ እጅስራዎችን ምንነትና ባህሪያት የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጥቀስ አብራርታለች፡፡

አጥኚዋ የባለሙያዎችን ማህበራዊ የሕይወት ገጽታ ለማሳየት ሞክራለች፡፡ ነገር ግን በትወራዊ ቅኝቷ የባለሙያዎችን ህይወት በተመለከተ ያቀረበችው ነገር የለም፡፡ በትንተናውም ይህን በሚመለከት ቲዎሪዎችን ከመስክ መረጃዎች ጋር በማጣመር አልተነተነችም፡፡ይህም በዚህ ጥናት አንድ ክፍተት የሚታይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ አጥኝዋ ቃለ መጠይቅና ምልከታን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅማለች፡፡ እነዚህን ዘዴዎች በመጠቀም የሰበሰበቻቸውን መረጃዎች ገላጭ ዘዴን በመጠቀም ተንትናለች፡፡ በዚህ መሰረት መረጃዎችን ከሰበሰበችና ከተነተነች በኋላ የሚከተሉትን ነጥቦች በግኝት መልክ አስፍራለች፡፡ ባለሙያዎች በስራቸው

የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎችና የአሰራር ሂደት ችሎታን የሚያገኙት ቤተሰቦቻቸው ሲሰሩ በመመልከትና ቀስ በቀስ በሥራዎቹ በመሳተፍ እንደሆነ ገልፃለች፡፡ ባለሙያዎቹ ለሥራቸው የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች በአካባቢያቸው በቀላሉ ከሚገኙ ነገሮች ማለትም ከእንጨት፣ ከቀርከሀ እና ከመሳሰሉት ነገሮች የሚሰሩ መሆናቸውን ገልጻለች፡፡

በማህበራዊ ህይወታቸው በኩል ሽማኔዎቹም ሆነ የቆዳ ባለሙያዎቹ ከህብረተሰቡ በተወሰነ ደረጃ የተገለሉ ሲሆን በተለይ የቆዳ ሰራተኞች ከሽመና ሰራተኞች በበለጠ እንደሚገለሉ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ከደምበጫና አካባቢዋ ነዋሪዎች እና ከራሳቸው ከባለሙያዎቹ የተሰበሰቡት ቃላዊ ግጥሞች በአብዛኛው ባለሙያዎች የፍቅር ስሜታቸውን የሚገልፁባቸው፣ ስለፈታይ ሴቶች የተነገሩና ባለሙያዎቹ ከሌላው ማህበረሰብ ለሚደርስባቸው ነቀፋ ምላሽ የሚሰጡባቸው መሆናቸው ተገልፁዋል፡፡

አጥኚዋ ጥናቱን ለማካሄድ የመረጠቻቸው ዘዴዎች ተገቢ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ የቁሳዊ ባህል ጥናት እንደመሆኑ መጠን ምልከታን በመጠቀም የአሰራር ሂደቶችን ማጤን ይገባል፡፡ በምልከታ መሰብሰብ የማይቻለውን የባለሙያዎችን ማህበራዊ ህይወት ለመመርመርና ስነቃሎችን ለመሰብሰብ ደግሞ ቃለመጠይቅን መጠቀሚ ተገቢ ነው፡፡ የመተንተኛ ዘዴዋን ገላጭ ማድረጓም ተገቢ ምርጫ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙዎቹ የመስኩ ምሁራን እንደሚሉት ይህ ዘዴ ለቁሳዊ ባህል ጥናት ተስማሚ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ዘዴው ገለፃን፣ ትንታኔንና ትርጎማን አካቶ የያዘ በመሆኑ ነው፡፡

ጥናቱ የቁሶችን የአሰራር ሂደት ለማሳየት መሞከሩ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላልል፡፡በተጨማሪም በእኔ ጥናት ባህላዊ የሸክላ ሥራ መካተቱ፣ የቁሶችን ቅርፅና መጠንን መሰረት በማድረግ ትዕምርታዊ ትርጓሜ መሰጠቱ ሌላው ልዩነታችን ነው፡፡ እንዲሁም የቆዳና የሸክላ ሥራ ወቅታዊ ሁኔታን መመልከቴ የእኔን ጥናት ከሔለን ጥናት ይለየዋል፡፡

አስቴር ሙሉ “ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ” (2000) ያቀረበችው ጥናት አላማ በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ የአጠናን መንገድ መግለጽ፣ መቅረስ፣

መሰነድና እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ህልውናቸው ፈጽሞ ከመጥፋት ተቆጥቦ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚሰጡበትን መንገድ መጠቆም ነው። የጥናቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታና በጥናቱ የተነሱት ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ቀዳማይ መረጃዎች ከመስክ በቃለ መጠይቅና በምልከታ፣ ካልዓይ መረጃዎች ደግሞ ከቤተመፃሕፍት እና ከድረ ገጽ (internet) ተሰብስበዋል።

በዚህ መንገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ባህላዊ ቤቶች ማህበረሰቡ ቅርፁን ተከትሎ በሰጣቸው ስያሜ መሰረት፤ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ደግሞ በተግባራቸው ተመድበው ከመስክ የተገኙ መረጃዎች በትወራው ከቀረቡ ንድፈ ሀሳቦች ጋር በመገናዘብ በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል። ከትንታኔውም የባለሙያዎችን ህይወት፣ ማህበረሰቡ ለባለሙያዎች ያለውን አሉታዊ አመለካከት፣ የቁሶቹን ማህበራዊ ፋይዳ፣ በትርጓሜ አሳይታለች።

ይህ ጥናት የቁሶችን የአሰራር ሂደት፣ የባለሙያዎችን ማህበራዊ ህይወት፣ የባለሙያዎችን የሙያ ለመዳ፣ በመመርመሩ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። የእኔ ጥናት ባህላዊ የቆዳና የሸክላ ስራን ጎን ለጎን በማምጣት ማጥናቱ ከአስቴር ጥናት ይለያል። በተጨማሪ የሁለቱን ሙያዎች ወቅታዊ ሁኔታና የባለሙያዎችን የእርስ በእርስ ግንኙነት የሚመረምር መሆኑ ከአስቴር ጥናት የሚለይበት ሌላው ገጽታ ነው።

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ በሶስተኛነት በዚህ ቅኝት የተካተተው ታምራት ሀይሉ "የብራና መፃህፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ" 2000 ዓ.ም በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ነው። ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ በቅኝቱ ያካተትኩበት ምክንያት በቁሳዊ ባህል ላይ በማተኮሩ ብቻ ሳይሆን ከባህላዊ የቆዳ ሥራ ውጤቶች አንዱ የሆነውን የብራና መፃህፍ አዘገጃጀት በመመርመሩ ነው። ጥናቱ በዓላማነት ይዞት የተነሳው ጉዳይ የብራና አዘገጃጀትን በሚመለከት ሂደቱንና የሚዘጋጁትን ቁሶች መግለጽና ቀርፆ በቅርስነት ማቆየት ነው። ትውፊቱ ተለይቶ በእስቴ ማህበረሰብ ውስጥ በቋሚነት አሁንም ድረስ ሳይጠፋ እንዲቆይ ያስቻለውን ምክንያት ለይቶ መግለጽ ሌላው ዓላማ ነው። አጥኚው እነዚህን አላማዎች በመያዝ ምልከታና ቃለመጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት በመጠቀም ቀዳማይ

መረጃዎችን ከመስክ የሰበሰበ ሲሆን ያነሳውን ርዕሰ ጉዳይ በሚመለከት ደግሞ የተለያዩ ትውሮችን በማካተት ጥናቱን አካሂዷል። በንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቱ የቁሳዊ ባህል ምንነት በአጭሩ አብራርቷል። ከዚያም የጥናቱ ዋና ርዕሰ ጉዳይ የሆነውን የብራናን ምንነት፣ ታሪካዊ አመጣጥና የብራና መስሪያ ጥሬ እቃዎችን ምንነት አስረድቷል። ቲዎሪዎችንም ከመስክ ካገኛቸው መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ትንተናውን አካሂዷል።

የታምራት ጥናት ከእኔ ጋር የሚመሳሰልበት ገጽታ ቢኖረውም የሚለያይበት ገጽታ ግን ብዙ ነው። በእኔ ጥናት ባህላዊ የቆዳ ስራ ውጤቶች የሆኑትን የቤት ቁሶች የአሰራር ሂደት እና ጥቅም ከተለያየ አንፃር በሰፊው ይዳሰሳል። በእኔ ጥናት ባህላዊ የሸክላ ስራ ከቆዳ ጋር ጎንለጎን ይመረምራል።

በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ከተደረጉ ጥናቶች መካከል በመጨረሻ የምቃኘው ሀብታሙ እንግዳው "በደቡብ ጉንደር አስተዳድር ዞን በሊበ ከምከም ወረዳ በሻሞ ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒያለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና" በሚል ርእስ ያቀረበውን ነው።

የዚህ ጥናት አላማ የሸክላን ስራ የአሰራር ሂደት፣ የሸክላ ስራ ውጤቶች የሆኑ ቁሶችን መሰብሰብ፣ መሰነድ እናም ከዛም ባለፈ ቁሶች ያላቸውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ መርምሮ ማሳየት ነው። ይህን ጉዳይ ከዳር ለማድረስም በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በተተኳሪ ቡድን ወይይት ዘዴዎች ሰብስቧል። ካልዓይ መረጃዎችን ደግሞ ከቤተ መፃህፍት፣ ከድረ ገጽ (internet) እና ከታዋቂ መፅሄቶች መሰብሰቡን ይገልፃል። በዚህም መሰረት በትወራው የቁሳዊ ባህል ምንነት እና ባህሪያት፣ የቁሳዊ ባህልን ምደባ ሁኔታ፣ የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሂደቶችንና ዘዴዎችን በሚመለከት ሰፊ ማብራሪያ አቅርቧል።

አጥኝው ጥናቱን ለማካሄድ የመረጣቸው የአጠናን ዘዴዎችም ሆነ ንድፈ ሀሳባዊ መነሻዎች ተገቢና አስፈላጊ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። እንዲሁም በዚህ ጥናት

የቀረቡት ትውሮች ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር ማስረገጫ ሆነው ለመተንተኛነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

የሀብታሙ ጥናት የሸክላ ስራን ከአሰራር ሂደት፣ ከባህላዊና ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር መመርመሩ፤ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የእኔ ጥናት በተጠኝ ማህበረሰብ መገኛ፣ የሸክላ ስራን ከቆዳ ስራ ጋር ጎን ለጎን ማጥናቱ፣ የሁለቱ ባለሙያዎች የእርስ በርስ ግንኙነት እና የሙያዎቹ ወቅታዊ ሁኔታ መዳሰሱ ከሀብታሙ ጥናት ይለያል።

ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነዕሁፍ ክፍልም ውጭ የተደረጉ ባህላዊ የሸክላና የቆዳ ስራ ጥናቶች አሉ። ጥናቶቹ እነዚህን የእጅ ሙያ ዘርፎች ያጠኑበት መንገድ ሲታይ በአንድ በኩል አንዳቸውን ነጥሎ በማምጣት በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ሙያዎች ከሌሎች የእጅ ስራዎች ጋር በማጣመር ያቀረቡ ናቸው።

በሌሎች ትምህርት ክፍሎች የተሰሩና በእኔ ጥናት የተነሱ ርዕሰ ጉዳዮችን የተመለከቱ ጥናቶች በቁጥር ሁለት ብቻ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ገድፍ አብዋ. "An Ethno Archeological Investigation of Pottery Making Among Traditional Potters of Gonder" (2005) በሚል ያቀረቡት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ታከለ መርድ"Gender Culture Pottery as Women Activity in Ethiopia: A Case Study of Selected Sites in Addis Ababa and Its Surroundings." (2007) በሚል ርዕስ ያቀረቡት ነው። ጥናቶቹ በቀደምት ጥናቶች የተከለሱ በመሆናቸው ይዘታቸውን ብቻ ባጭሩ አቀርባለሁ።ሁለቱም ጥናቶች ሸክላ ላይ ብቻ በማተኮር የተሰሩ ሲሆ የሸክላ ስራን የአሰራር ሂደት፣ የሰራተኞችን ማህበራዊ ህይወት እና ያታዊ የስራ ክፍፍል ዳሰዋል። እነዚህን ጉዳዩች በማሳየታቸው ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ሲሆን በሚከተሉት ነጥቦች ደግሞ የእኔ ጥናት ከእነሱ ይለየዋል።

ባህላዊ የቆዳ ስራ የጥናቱ አንድ አካል በመሆኑ የሁለቱ ሙያዎች(የቆዳ እና የሸክላ ስራ) ወቅታዊ ሁኔታ እና የባለሙያዎቹ የእርስ በርስ ግንኙነት ምን ይመስላል የሚሉት ጉዳዮች ተመርምረዋል።

ከዚህ ሌላ በታዋቂ መፅሄቶች ላይ የወጡ ሁለት ጥናቶች በዚህ ቅኝት ተዳሰዋል። እነዚህም አንደኛ Gallegher.J "The Preparion of Hides with Stone Tools in South Central Ethiopia." (1974)፣ ሁለተኛው ደግሞ Alula Pankhurst "Decline, Survival and Development of Class Comparisons of Tanning, Iron Work, otters, Wood Work and Weaving with Particular Reference to South Western Ethiopia" (2000) በሚል ርዕስ ያቀረቡት ነው።

እነዚህም መጣጥፎች በቀደምት ጥናቶች የተቃኙ በመሆናቸው ይዘታቸውንና የእኔ ጥናት ከእነሱ የሚለይበትን ገፅታ በአጭሩ በመግለፅ አልፋለሁ። ጥናቶቹ ባህላዊ የሸክላና የቆዳን ስራን ከሌሎች ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ጋር በማጣመር እንዲሁም ለየብቻቸው ነጥሎ በማምጣት አጥንተዋል። በጥናቶቹ የታዩት ጉዳዮችም የሙያዎቹ (የሸክላና የቆዳ) የአሰራር ሂደት የባለሙያዎቹ ማህበራዊ ህይወት፣ የሙያዎቹ የተፈላጊነት ደረጃ፣ ባህላዊ የቆዳ መሳሪያዎች ጥቅም እና የቁሶቹ የገበያ ሁኔታ በንፅፅር ተመርምረዋል። በአሰራር ሂደቱም ሆነ ከቁሶቹ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚታየው ባህላዊ ክዋኔ እና መሰል ጉዳዮች አልተተነተኑም።

የእኔ ጥናት በዚህ መጣጥፍ ከተዳሰሱት በተጨማሪ ሌሎችንም ጉዳዮች ይመለከታል። ማህበረሰቡ ለቁሶቹና ለባለሙያዎቹ ያለው አመለካከትና በባህላዊ የቆዳ እና የሸክላ ስራ የሚታየው ጾታዊ ተሳትፎ በንፅፅር ተመርመሯል።

በዚህ ጥናት የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት በቆዳና በሸክላ ስራ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉና የታተሙ ጥናታዊ መፃህፎችም ተካተዋል። እነዚህም Richard Pankrust A Social History of Ethiopia (1990)፣ እና Tsehai Berhane Seleassie (1991 እና 1999)፣የሚሉት ይጠቀሳሉ። የ ፓንክረስት ጥናት የሸክላና የቆዳ ስራን ከእንጨት ስራዎች፣ከቤት አሰራር ሂደት እና ከሌሎች የዕደ ጠበብ ዘርፎች ጋር በንፅፅር አይቷል። በዚህም መሰረት የሸክላና የቆዳ ስራን አሰራር ሂደት፣ የባለሙያዎቹን ህይወት፣ የሙያው ውጤቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው የተፈላጊነት ደረጃ እና ሌሎችም ጉዳዮች ከብረት፣ ከእንጨት እና ከቤት አሰራር ጋር በማነፃፀር ቀርበዋል።የፀሀይ ብርሃነ ስላሴ ጥናት ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በወላይታ ማህበረሰብ ሸክላ ሰራተኞች ላይ ያተኮረ ሲሆን በጥናቱ

መጨረሻም በአካባቢው የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወን መሆኑን፤ ባለሙያዎቹም ችናሻ ተብለው እንደሚጠሩ እና ባለሙያ ባልሆነው ማህበረሰብ ዘንድ ዝቅ ተደርገው እንደሚታዩ ተብራርቷል።

2.2 ንድፈሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ክፍል ባነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የመስኩ ምሁራን ያስቀምጧቸው ትውሮች ቀርበዋል።ትዎራዎቹ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ሲተነተኑ ማገናዘቢያ በመሆን አገልግለዋል።

2.2.1 የቁሳዊ ባህል ምንነት

ስለቁሳዊ ባህል ምንነት አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ የተገኘለት አይመስልም። የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ በይነውታል። ይሽውም ከፊሎቹ ቁሳዊ ባህል ማለት የቁሶች ስብስብ ብለው ሲያብራሩት ሌሎች ደግሞ ቁሶች የሚጠኑበት የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ይገልፃሉ። ፈቃደ Dorson- ንን ጠቅሰው እንዲህ ብለውታል።

> *ቁሳዊ ባህል በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ. አሰራርን ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸው መሳሪያዎችንና ሌሎችን ተመሳሳይ ጉዳዪች ያጠናል ማለት ነው። (ፈቃደ 1991፣15)*

ፈቃደ የቁሳዊ ባህልን ምንነት ከመግለፅ በተጨማሪ በስሩ የሚካተቱትን ዘርፎችም ህገረሰባዊ እጅ ስራ (Folk Carafts)፣ ህገረሰባዊ ስዕል (Folk Art)፣ ህገረሰባዊ ምህንድስና (Folk Architecture)፣ ህገረሰባዊ ልብስ (Folk Costume) እና ህገረሰባዊ የምግብ አሰራር (Folk Cookery) እንደሚባሉ በበነ።

Glassie ም ቁሳዊ ባህልን እንደሚከተለው በይኖታል።

> *Material culture is the culture made material; it is the inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things, but not ending wtith them, the study of material culture uses objects to approach human thought and action (1999:41)*

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ቁሳዊ ባህል ተጨባጭ ለሆኑና የሰው ልጅ ባህልን መሰረት አድርጎ ለዕለት ከዕለት ኑሮው ማከናወኛ የሚሰራቸውን ቁሶች የሚመለከት መሆኑን ነው። ከፈቃደ ብያኔ የቁሶችን ምንነትና የተሰሩበትን ዘዴ የሚመረምር መሆኑን ለማወቅ ሲቻል ከGlassie ብያኔ ደግሞ ፅንሰ ሀሳቡ የቁሶች ባለቤት የሆነውን የሰው ልጅን አስተሳሰብ እና ፍልስፍና በቁሶች አማካይነት መመርመር የሚቻል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። Jones ደግም David Prown ንን ጠቅሰው The study through artifacts of the belief values, ideas, attitudes, and assumption of a particular community or society at a given time (Jones፡ 1987, 3) ብለዋል። ከዚህም የምንረዳው ቁሳዊ ባህል ተብሎ የሚጠራው የፎክሎር ዘርፍ በቁሶች አማካይነት የአንድን ማህበረሰብ እምነት፣ እሴት፣ አመለካከት ፣ በአጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤው የሚጠናበት የእውቀት ዘርፍ መሆኑን ነው።

እስከ አሁን ያየናቸው ሀሳቦች ባአብይነት ቁሳዊ ባህልን ከጥናት ዘርፍ አኳያ በማየት የበየኑ ናቸው። Cleary ደግሞ ቁሳዊ ባህልን በተለየ መንገድ እንዲህ ይለዋል። "...The term material culture represents the "thing" or the "stuff" which we creat and use on daily basis, the "material products of culture" (2004:2) ከዚህ ብያኔ ቁሳዊ ባህል በባህላዊ መንገድ የተሰሩና በዕለት ተዕለት ተግባር የምንገለገልባቸው ቁሶችን ወይም የቁሶችን ስብስብ የሚያሳይ እንጂ የጥናት ዘርፍ አለመሆኑን እንገነዘባለን።

Prown; 1982:2 ቁሳዊ ባህል እንደተጠኚ ጉዳይ ቁስ ተብሎ የተበጀለትን ሰፊ የቁሶችን አለም ይይዛል" በማለት ቁሳዊ ባህል ሰዎች በእጃቸው ባህላዊ እውቀታቸውን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸውን ቁሶች የሚመለከት መሆኑን ገልፀዋል።

ከዚህ በተጨማሪም Jones(2000፡9) ቁሳዊ ባህል ባህልን የሚያንፀባርቅ፣ ሰው ሰርቶ ለዕለት ኑሮ የሚጠቀምበት መሆኑን ጠቅሰዋል። ከዚህም አገልግሎታቸውና ጥቅማቸው ባሻገር አሁን ካለውም ሆነ በታሪክነት ሊወሳ ከሚችለው የሰው ልጅ እሴት፣ አመለካከትና ፍላጎት ጋር የዘመንን መንፈስ፣ የማህበረሰብንና የተወሰነን

ቡድን፣ የግለሰቦችን የህይወት ልምድ የማንፀባረቅ ጥቅም ያላቸው ናቸው ብለዋል።።

ከቀረቡት ብያኔዎች መገንዘብ እንደተቻለው ቁሳዊ ባህል ሰዎች ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ባህላዊ እሴቶቻቸውን፣ እምነታቸውን፣ ንፅረተ አለማቸውን፣ ለስነ ውበት ያላቸውን አመለካከት የፈጠራ ችሎታቸውን ለማሳየት ሲሉ የሚያበጇቸውን ቁሳዊ ነገሮች ሁሉ የሚያካትት ፅንሰ ሀሳብ ነው።። በዚህ መሰረት ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ወደ ባህላዊ ስፍራነት እና ወደ ባህላዊ ቁስነት የተለወጡ ወይም የሚለወጡ ተፈጥሮዊ ስራዎችንና ተፈጥሯዊ ቁሳዊ ነገሮችን ያካትታል ማለት ነው።። ባጠቃላይ ቁሳዊ ባህልን ማጥናት ማለት በቁሳዊ ነገሮች አማካይነት የሰው ልጅን አዕምሮ ማጥናት (ሰውን ማጥናት) ማለት ነው።።

2.2.2 የቁሳዊ ባህል ጥናት የትኩረት ነጥቦች

አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ቁሶችን አጥንቶ የቁሶቹ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ እውቀት፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ የአኗኗር ዘይቤ ለማወቅ የጥናቱን ትኩረት ከላይ የተገለፁትን የሰው ልጅ እሴቶች ለማወቅ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ማድረግ አለበት።። የባለሙያዎቹን እውቀት አመጣጥ፣ የቁሶቹን የአሰራር ሂደቶች መመልከት ይኖርበታል።። የእጅ ስራ ውጤቶች ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ለማወቅም ቁሶችን የሚጠቀምባቸው ማህበረሰብ ውስጥ ገብቶ የአጠቃቀም ሁኔታውን ማጤን ይኖርበታል።። ይህን ጉዳይ በሚመለከት "የአንድ ግለሰብ ፈጠራ ከባህል ጋር ያለው ዝምድና በእጅ ስራዎች የአሰራር ሂደት ውስጥ የሚታዩ ስልቶች፣ ባለሙያው ከባህሉ ያገኛቸውን የአሰራር ስልቶች ወይም ዘዴዎች እና የእጅ ስራ የአንድ ህብረተሰብ መገለጫ ሊሆን የቻለበትን መንገድ በትኩረት መመርመር አለበት።።" (Vlach 1983፤301)

ሀብታሙ (2001፣ 15) Schlerthን ጠቅሶ "ምሁሩ የቁሳዊ ባህል ትኩረት መሆን ያለበት ነገሮች ለምን ተሰሩ? ለምንስ ቅርፃቸው ይህን መስሎ ተሰራ? እንዲሁም ቁሶች ምን ምን ማህበራዊ፣ ግልጋሎታዊ፣ ጥበባዊ ወይም

ትዕምርታዊ አላማን ለማመላከት ተወከሉ? የሚሉትን ጉዳዮች ከማብራራት ላይ መሆን እንዳለበት በአፅኖት ይገልፃል፡፡" ብሏል፡፡

በቁሳዊ ባህል ጥናት የሚመረቱት ቁሶች የተሰሩበትን አላማ፣ ቁሶች የተሰሩት የትኛውን ፍላጎት ለማሟላት እንደሆነ ከሰሪዎቹ በመጠየቅ ቁሶችን ለመስራት ያነሳሱ ምክንያቶችን ለማወቅ ይቻላል፡፡ ቅርፃቸውን በመመልከት ምን ትዕምርታዊ አላማ እንዳላቸው መመርመር ይቻላል፡፡

የቁሳዊ በህል ምንነት በሚለው ርዕስ ስር ከተጠቀሱት አምስት የቁሳዊ ባህል ዘርፎች መካከል የእኔ ጥናት ሚያተኩረው ሃገረሰባዊ የእጅ ስራ በሚለው ላይ በመሆኑ ስለ እሱ ጥቂት ነጥቦች ማንሳቱ ተገቢ ነው፡፤፤

2.2.3 ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (ሀገረሰባዊ ቅርፃቅርፅና ጌጣጌጥ)

የእጅ ስራ የሚለው ፅንሰ ሀሳብ የአሰራር ሂደትንና ጥበብን የሚገልፅ ነው፡፡ በስሩም በባህላዊ መንገድ የሚሰሩትን ሸክላ ስራን፣ ሽመናን፣ ስፌትን፣ ቆዳ ስራን ወዘተ. አካቶ ይይዛል፡፡ "ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ደግሞ ባህልን መሰረት አድርገው የሚሰሩ የእጅ ስራዎችን ይመለከታል፡፡" (Roberts ውስጥ Dorson 1972፣233) ፡፡ Roberts ቁሶችን ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ የሚያስብላቸው የሙያው ባለቤት የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ሙያውን የሚለምዱት በዘመናዊ ትምህርት ሳይሆን ይገልጻሉ፡-

> *One can say generally that folk crafts are traditionall crafts. It is indeed in the crafts that one can observe with special clarity the operation of traditional until relatively recent times. Craft techniques and designs were passed down with on family for many generation or were transmitted by the apprentice system where a boy learning the craft served for as long as seven years under a master crafts man (232)*

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ሀገር በቀል እውቀትን መሰረት በማድረግ የሚሰሩ ቁሶችን የአሰራር ሂደትና ቴክኒክ የሚዳስስ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ቁስ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ነው ለመባል ቁስ አምራቹ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ቁስ የማምረት ክህሎቱን ያገኘው በዘመናዊ ትምህርት

ሳይሆን በልምድ ከቤተሰብ በማየትና በተደጋጋሚ በመለማመድ ከሆነ ነው የሚለው ጉዳይ ጎልቶ ይታያል፡፡

ቅርፃቅርፅ አንዳች ተግባራዊ አገልግሎት ለመስጠት አላማ የሚበጁ ቁሳዊ ነገሮችን ያካትታል፡፡ ጌጣ ጌጥ ደግሞ ለማጌጫ ወይም ለማስጌጫ አላማ በአጠቃላይ ለስነ ውበታዊ ዋጋቸው ሲባል የሚበጁ ቁሳዊ ነገሮችን ይመለከታል፡፡ ቅርፃቅርፅ አንዳንዴ ለማጌጫ ወይም ለማስጌጫ አገልግሎት ሲውሉ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ አገልግልን ብንወስድ ተግባራዊ አገልግሎቱ ስንቅ መያዣ ነው፤ ነገር ግን አንዳንድ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤቶችና ባህላዊ ምግብ ቤቶች ውስጥ ደግሞ እንደ ጌጥ ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡ ጌጣ ጌጦችም እንደዚሁ አንዳንዴ ለተግባራዊ አገልግሎት ሲውሉ ይታያሉ፡፡ የአንገትና የጆሮ ጌጦች ባለቤቶቹን ከማስዋብ በተጨማሪ ባህላቸውን በማንፀባረቅ ያገለግላሉ፡፡ ከቅርፃቅርፅ መካከል የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከእንጨት የሚሰሩ (ዛቢያ፣ አልጋ፣ ወንበር፣ ማንኪያ፣ መቀጫ፣ ገበታ፣) የመሳሰሉ ቤት እቃዎች መጥቀስ ይቻላል፤ከሸክላ ዕቃዎች ምጣድ፣ ጉልቻ፣ ድስት፣ ጀበና፣ እንስራ፣ ጋን፣ ጊርጌራ፣ ዋዲያትን መጥቀስ ሲቻል ከብረት እቃዎች ደግሞ ቢላ፣ ማጭድ፣ ምሳር፣ ሞረድ፣ ዘነዘና፣ አንካሴ፣ ሰይፍ፣ ጎራዴ፣ ገጀራ፣ ወገል፣ ማረሻ፤ ከቀንድ እቃዎች ዋንጫ፣ ማንኪያ፣ ጭልፋ፣ አዝራር፣ ዋገምት፤ ከቆዳ የሚሰሩ እቃዎች አጎዛ፣ ጀንዲ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ጌጣጌጥ የሚባሉት ደግሞ የፀጉር ጌጥ (ወለባ)፣ የቅንድብ ጌጥ፣ አፍንጫ ተበስቶ የሚንጠለጠል ወይም የሚለጠፍ ጌጥ፣ ከሸክላ የሚሰራ የከንፈር ጌጥ፣የጆሮ ጌጥ ከብር፣ ከወርቅ፣ ከንሀስ፣ ከመዳብ ወዘተ የሚሰሩ ጉትቻዎች ይጠቀሳሉ፡፡

2.2.4 የቁሳዊ ባህል ምደባ

በዚህ ክፍል በቁሳዊ ባህል ዙሪያ ጥናት በሚደረግበት ጊዜ ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎችን በቀላሉና ባልተወሳሰበ መንገድ ለመተንተን ያመች ዘንድ የመስኩ ምሁራን ያቀረቧቸውን የመመደቢያ (የማወገኛ) መስፍርቶን አንመለከታለን፡፡ በዘርፉ የሚጠኑት ቁሶች የተለያየ ገፅታ፤ የአሰራር ዘዴ፣ ጥቅም እና በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው በመሆኑ በቀላሉ ለመመደብ እና ያለምንም ችግር ወደ ትንታኔ እና ትርጓሜ መምራት ቀላል ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም Prown እና ሌሎችም

የመስኩ ምሁራን የተለያዩ የመመደቢያ መስፍርቶችን በመዘርዘር መስፈርቶቹ ላይ የሚታየውን የ ኢ- ምሉዕነት ባህሪ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

Prown (1982፡2) በቁሳዊ ባህል ጥናት ምደባ አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ቁሶችን ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ (Sorting by physical materials)፣ የተሰሩበትን ዘዴ methods of fabrication) እንዲሁም የቁሶችን አገልግሎች (function) መሰረት በማድረግ መመደብ እንደሚቻል እና በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም መስፍርቶች ከችግር ያልፀዱ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የተሰሩበትን ንጥረ ቁስ እንደ መስፈርት ስንወስድ አንድ ቁስ ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ሊዘጋጅ ይችላል፤ የአሰራር ዘዴን ብንወስድ ደግሞ ዘዴው እደባለሙያዎቹ ፍላጎትና ዓላማ፣ እንዲሁም እንደ ወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ሊለዋወጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም አገልግሎት የተሻለ መመደቢያ መስፍርት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም አንድን መስፈርት ብቻ በመጠቀም ለመመደብ ከመሞከር ይልቅ የተለያዩ መስፈርቶችን በማሰባጠር መጠቀም በትንታኔያችን ሂደት ሊያጋጥመን የሚችለውን ችግር ያቀለዋል ብለዋል፡፡

Ames (1978: 20) Prown ከዘረዘራቸው መስፍርቶች በተጨማሪ “ቅርፅ”፣ “ዘመን” እና “ባለሙያ” የሚሉትን ጉዳዮች እንደ መስፈርት በመውሰድ ቁሶችን መመደብ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ Ames- ም ቢሆን መስፈርቶቹ ምሉዕ አለመሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ ይኸውም ቅርፅን መስፈርት በማድረግ የቁሶቹን ለመመደብ ሲሞከር ብዙዎቹ ቁሶች ተመሳሳይ ገፅታ ላይኖራቸው ሥለሚችል ጉዳዩን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ “ዘመንን”መስፈርት ስናደርግ ደግሞ ቁሶች የተመረቱበትን እና፣ አገልግሎት መስጠት የጀመሩበትን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን የማወገን ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህም ቢሆን ጊዜውን ከትክክለኛ የመረጃ ምንጭ ማግኘት ካልተቻለ ምደባውን ሰንካላ ያደርገዋል፡፡ ሌላው መስፈርት ደግሞ ባለሙያዎችን መሰረት አድርጎ የሚከናወን የምደባ አይነት ነው፡፡ ይህ ዘዴ ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ በምድቦቹ መካከል መወሳሰብ ሳይፈጠር ልዩነቱ በግልፅ ሊታይ በሚችል ሁኔታ ለማከናወን የሚረዳ የምደባ ተግባር ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በ Ames እና በ Prown የተዘረዘሩት ነጥቦች ከመስክ የተሠበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎችን በቀላሉ ለመመደብ የሚያስችሉ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሆኖም ሁሉም መስፍርቶች ምሉዕ አለመሆናቸውን መገንዘብ ይገባል፡፡የመስፈርቶች

ጠንካራ እና ደካማ ጎን ጠንቅቆ በማወቅ እንደሚጠናው ርዕስ ጉዳይ የተለያዩ መመደቢያ መስፈርቶችን በማሰባጠር መጠቀሙ የተሻለ ነው፡፡ እኔም በትወራው የቀረቡትን መስፍርቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባርን እና መስሪያ ንጥረ ቁስን በስፋት በመጠቀም፣ ሌሎችን ማለትም ቅርፅን፣ የአሰራር ስልትንና ዘመንን ደግሞ በከፊል በመጠቀም ከመስክ የሰበሰብኳቸው መረጃዎች በመመደብ ትንተናና ትርጓሜ ሰጥቻለሁ፡፡

በዚህ ምዕራፍ የትናቱን አካሄድ የሚመሩ ንድፈሃሳባዊ ነጥቦች አንዲሁም ካነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመዱ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡በሚቀጥለው ምዕራፍ ጥናቱ የተካሄደባቸው የቡሬ እና የወንበርማ ወረዳዎች አጠቃላይ ገጽታ ይቀርባል፡፡

3 የቡሬ እና የወንበርማ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ

ቡሬ ወረዳ በ1994 ዓ.ም በተደረገው የህዝብ እና ቤቶች ቆጠራ መሰረት በገጠር123 ,037፣በከተማ ደግሞ 4705 ህዝብእንደሚኖር ታውቋል፡፡በገጠር የሴቶች ቁጥር61,167 ሲሆን ወንዶች ደግሞ 61,870 ናቸው::በከተማ ደግሞ2460ሴቶች እና 2245 ወንዶች መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ በወረዳው ወስጥ ከሚኖረው ህዝብ 98 %የሚሆነው የአማረኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆን 2% ያህሉ ደግሞ የኦርምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነው፡፡

3.1 መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት

ቡሬ ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ጎጃም መስተዳደር ዞን ከሚገኙ የከተማ አስተዳደሮች አንዷ ስትሆን ለከተማውም ሆነ ለገጠር ዙሪያ ወረዳ ዋና ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ ከዙሪያ ወረዳዎች ጋር በጥቅል ስትታይ በምስራቅ የጃቢጠህናን ወረዳ፣ በደቡብ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፣ በምዕራብ የወንበርማ ወረዳ እና በሠሜን የአዊ ዞን ያዋስኗታል፡፡ ከዋና ዋና ከተሞች ያላት እርቀት ሲታይም ከአዲስ አበባ በ400 ኪ.ሜ ከባ/ዳር 155 ኪ.ሜትርና ከነቀምት ደግሞ በ250 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ (ቡሬ ዳሞት የጎጃሚ እሸት የንግድ ትርኢትና ባዛር መጽሔት 2001)

ከወረዳው ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ወረዳው ከተማ እና ገጠር ዙሪያ አስተዳደር ተብሎ የተከፈለ ነው፡፡ ከተማ አስተዳደሩ በአራት የገጠርና በአራት የከተማ ቀበሌዎች የተከፋፈለ ሲሆን 1376 የቆዳ ሥፋት ይሸፍናል፡፡ የገጠር ዙሪያ ወረዳው ደግሞ አንድ የከተማ እና አስራ ዘጠኝ የገጠር ቀበሌዎችን አካቶ የያዘ ሲሆን የወረዳው ጠቅላላ ስፋት 72.379 ሄክታር ወይም 727.39 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋት አለው፡፡ /ከዕቅድ ዝግጅት ክትትል እና ግምገማ ኦፊሠር ቢሮ የተገኘ መረጃ/

ቡሬ ከተማና የዙሪያ ወረዳው መልካም ምድራዊ አቀማመጥ 76% ሜዳማ፣ 10% ተራራማ፣ 7% ሸለቆሚ 7% ወጣ ገባ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የአፈር አይነቶቹ ደግሞ ቀይ አፈር 63% ቡናማ 20% እና ጥቁር 20 ፐርሰንት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የመሬት አጠቃቀም ሁኔታውን ስናይ 34606 ሄክታር ለቋሚ ተክል ፣740 ሄክታር

ለግጦሽ ፣4348 ሄክታር በደን የተሸፈነ፣ 6142 ሄክታር ለግንባታ ሥራዎች፣ 4850 ሄክታር ጥቅም የማይሰጥ፣ በውሃ የተሸፈነ ደግሞ 186 ሄክታር መሆኑን ከወረዳው ማስታወቂያ ጽ/ቤት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ቡሬ ወረዳ ሶስት የአየር ንብረት አይነቶች እንዳሉት ያሳያል፡፡ ይኸውም አንድ በመቶ ደጋ፣ 77.23% ወይና ደጋና 21.77 በመቶ በቆላማ የአየር ንብረት የተሸፈነ ነው፡፡ የቡሬ ወረዳ አመታዊ አማካይ የሙቀት መጠን ከ17 እስከ 25 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይደርሳል፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ደግሞ ከ1000 እስከ 1500 ሚ.ሊ ሜትር ዝናብ እንደሚያገኝ ይገመታል፡፡(የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትል እና ግምገማ ኦፊሠር ቢሮ የወረዳው አጠቃላይ ገጽታ በሚል ርዕስ ካዘጋጀው ያልታተመ ጽሑፍ የተወሰደ)

የወረዳው ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ከባህል ወለል በላይ ከ700 እስከ 2350 ሜትር ከፍታ አለው፡፡ ወረዳው በአመት ሁለት ጊዜ ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን ከሰኔ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚኖር ሲሆን መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ደግሞ ከየካቲት እስከ ግንቦት አጋማሽ እንደሚዘልቅ ገልፀዋል፡፡ (አለማየሁ ሞላ ቃለ መጠይቅ፣ሚያዚያ 28፣2003)

ስለ ወንበርማ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ በቂ መረጃ ማግኘት አለተቻለም፡፡ሊገኝ የቻለው የወንበርማ ወረዳ ሁለንተናዊ ገጽታ በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ያልታተመ ጽሁፍ ብቻ ነው፡፡ከዚህ ምንጭ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ወንበርማ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ አስራ ሶስት ወረዳዎች አንዷ ናት፡፡ ከወረዳው ማስታወቂያ ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደ ሚያመለክተው ወንበርማ በምስራቅ ቡሬ ወረዳ፣ በደቡብ ምስራቅ ወለጋ፣ በምዕራብና በሰሜን አዊ ዞን ያዋስኗታል፡፡ ከባህር ዳር ከተማ 172 ኪ.ሜትር ወጣ ብላ ትገኛለች፡፡ ጠቅላላ የቆዳ ሥፋቷ 135,675 ሔክታር ነው፡፡ የወረዳው የአየር ንብረትም 68% ወይና ደጋ 32% ደግሞ ቆላማ ነው፡፡

3.2 የሕዝቡ መተዳደሪያ

የቡሬ ወረዳ ህዝብ ኑሮ የተመሠረተው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ነው። እነዚህም እርሻ፣ ንግድ፣ ንብ እርባታ፣ የመንግስት ሥራ፣ ዶሮ እርባታ፣ የዕደ ጥበብ ሥራዎች /ቆዳ፣ ብረት፣ ሽመና፣ሸክላ፣ ዋንጫ/ ናቸው።አብዛኛው የወረዳው ህዝብ 81.63% ያህሉ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን ቀሪው 18.36% ደግሞ በመንግስት ሥራ፣ በንግድና በመሳሰሉት ስራዎች ላይ ተሰማርቶ ኑሮውን ይመራል። የግብርና ሥራ ለአብዛኞቹ የገቢ ምንጭ እንዲሆን ካስቻሉት ዋናው ጉዳይ የወረዳው ተስማሚ የአየር ፀባይ እና ጥሩ መልካም ምድራዊ አቀማመጥ መሆኑን "ቡሬ ዳሞት የጐጃሚ እሸት ንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲህ በማለት ገልጿል።

> *አካባቢው የአየር ንብረቱና የመልካም ምድራዊ አቀማመጡ ካሉት እምቅ ሊለሙ ከሚችሉ ሀብቶች ጋር ተዳምሮ ለልማት እንቅስቃሴ ምቹ እንዲሆን አድርጐታል። ይህም በመሆኑ በአካባቢው የተለያዩ የእህል አይነቶች እንደ በቆሎ፣ ጤፍ፣ በርበሬ፣ ማር፣አብሽ፣ ሰንዴ፣ ዳጉሳ፣ ድንች፣ ሽንኩርት፣ የጓሮ አትክልቶች በስፋት ሲመረቱ ከእነዚህ ምርቶች ውስጥ የበቆሎ ምርት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል /ገጽ 13/*

ከእርሻ ሥራ ጐን ለጐን በወረዳው የቤት እንስሳት እርባታም በሠፊው ይታያል። ከአካባቢው ሠፊ የእንስሳት ሃብት ውስጥ 74,708 የቀንድ ከብቶች 6,296 የጋማ ከብቶች፤54,499 በግና ፍየል፣ 42,415 ዶሮዎች እና 13,729 በንብ የተሞሉ ቀፎዎች በወረዳው እንደሚገኙ ከቡሬ ዙሪያ ወረዳ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የወረዳው ህዝብ መተዳደሪያ በዋናነት የተመሰረተው በተስማሚው የአየር ፀባይ ላይ መሆኑን እና ወረዳዋ ለሁሉም የገቢ ምንጭ ዘርፍ አመቺ መሆኗን የቡሬ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት "መልክተ ግብርና" በሚል ርዕስ በቡሬ ዳሞት የጐጃሚ እሸት መጽሔት ላይ እንደሚከተለው አብራርቷል።

> *የቡሬ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት በ2000 ዓ.ም ስራ ሲጀምር በስሩ አራት የከተማና አራት የገጠር ቀበሌዎች ይዞ በጥቅሉ 1000 ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የግብርና ሥራዎችን በማካሄድ ላይ ይገኛል። አሁን ኢኮኖሚያችን ለማንኛውም ዓይነት ሥራ*

ያመቻል። በሰብል ልማት ዘርፍ ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የሠብል ምርቶች፣ የቅባት እህል ምርት እንዲሁም ለስኳር ምርት የሚሆን ድንች ምርት ተሞክሮ ውጤታማ ሆኗል። በእንስሳት ምርትም በኩል አሳ እርባታ እና ድልብ ዓሳ በኩሬ ማምረት፣ በግና ፍየል እርባታ በግልም ይሁን በኢንቨስተሮች እየተሰሩ ይገኛሉ። በተፈጥሮ ሃብት ልማት በኩልም ከሚሠሩ ሥራዎች አንዱ ቧርቧር ሰራ፣ ከተር ሥራ በመንግስትም ሆነ በማህበራት እንዲሁም በግል የችግኝ ጣቢያዎች በመስራት ላይ ይገኛሉ። ከላይ የተገለፁት የገቢ ምንጮች በዚህ ወረዳ በተሳካ ሁኔታ ሊኖሩ የቻሉበት ምክንያት የአካባቢው ተስማሚ የአየር ንብረት ሁኔታ በመሆኑ ወረዳዋ ወደፊትም ከዚህ በተሻለ ሁኔታ የመልማት ዕድሏ ሠፊ ነው። /ገጽ 3፣ ቡሬ ዳሞት የጐጃም እሸት መጽሔት/

በአጠቃላይ የወረዳዋ ዓቢይ የገቢ ምንጭ ግብርና ሲሆን ከግብርና ሙያ ዘርፎች ውስጥ ደግሞ እርሻ እና እንስሳትን በዘመናዊ እና ባህላዊ መንገድ ማርባት ትልቁን ስፍራ የሚይዙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። (3፣2001)

3.3 ሐይማኖትና ልዩ ልዩ ሃገረሰባዊ ዕምነቶች

የቡሬ ወረዳ ህዝብ በአብዛኛው የክርስትና እና የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ ነው። ከህዝቡ 80% ያህሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትያን ሀይማኖት ተከታይ ሲሆን ቀሪው 20% ደግሞ የእስልምና እና የፕሮቴስታንት እምነትን ተከታይ ነው።

ከእነዚህ ሐይማኖቶች ጐን ለጐን ዛር እና ቆሌ የሚባሉ እምነቶችም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሲተገበሩ ይስተዋላል። እነዚህ ሐይማኖትና እምነት ተብለው የተገለፁት ሥርዓቶች በሚከበሩበት ወቅት ሁለቱም ስርዓታቸው እንደሚፈቅደው የተለያዩ ቁሶችን በመጠቀም ይታጀባሉ። የወረዳው የክርስትና እምነት ተከታዮች በወር በዓላት፣ በገና፣ በፋሲካ፣ በጥምቀት፣ በሥሌ ሚካኤል፣ ግንቦት ልደታ በእንቁጣጣሽ ወቅት ከምግብ ጀምሮ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጨምሮ ከእነሱ የተለዩ ቁሶችን በመጠቀም አስፈላጊው ሥርዓት ይከናወናል። ቆሌ፣ አውሊያ/ዛር/ ደግሞ በሌላ በኩል ሁለቱ መንፈሶች በሚፈልጉት መንገዶች እና የቁስ

አይነቶች ሥርዓታቸው ይከናወንላቸዋል፡፡ የወንበርማ ወረዳ አብዛኛው ህዝብ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እና የእስልምና ሀይማኖቶች ተከታይ ነው፡፡

በአጠቃላይ የወረዳዎቹ የእምነት እና ሐይማኖት ሁኔታ ከላይ የተገለፀውን ይመስላል፡፡ ርዕሰ ጉዳዩ እንደ አንድ ንዑስ ርዕስ ሆኖ የቀረበበት ምክንያትም ወደፊት በዚህ ጥናት ትንተና ውስጥ የተካተቱና ከተለያዩ እምነት እና ሐይማኖቶች ጋር የተያያዘ አገልግሎት ያላቸው ቁሶች ሊኖሩ ሥለሚችሉ ነው፡፡

4. የመረጃ ትንተና በቡሬና በወንበርማ ወረዳ የቆዳና የሸክላ ስራ ላይ

በዚህ ምእራፍ የጥናቱ ዋና ጉዳይ የቀረበ ሲሆን የሸክላ ሥራን በሚመለከት ከቡሬ ወረዳ የቆዳ ሥራን በሚመለከት ደግሞ ከቡሬ እና ከወንበርማ ወረዳ የተሠበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ንድፈ ሃሳባዊ መነሻዎች ጋር እየተናበቡ ትንተናና ትርጓሜ ይሰጥባቸዋል።

4.1. የቆዳ ሥራ

በዚህ ክፍል ስለባህላዊ የቆዳ ሥራ ውጤቶች ዓይነት እና ጠቀሜታ፣ ስለባህላዊ የቆዳ ቁሶች የአሠራር ሂደት፣ ስለ ባለሙያዎቹ ማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም የቆዳ ቁሶቹ ማህበራዊ እና ባህላዊ አገልግሎት ተዳሷል። በተጨማሪም ባህላዊ የቆዳ ቁሶችን በቆዩበት ነባራዊ ሁኔታ እንዳይቀጥሉ ያደረጉ ችግሮች፤ ከቆዳ ባለሙያዎች ጋር የተያያዙ አመለካከቶች እና እምነቶች ቀርበዋል።

4.1.1 የቆዳ ቁሶች ዓይነትና አገልግሎት

Ames (1978) እና Prown (1982) የቁሶችን ምደባ በተመለከተ ቁሶቹ በተግባራቸው /በሚሰጡት አገልግሎት/፣ በሚሠሩበት ጥሬ ነገር፣በአሰራር ስልታቸው፣ በባለሙያዎቹ ስያሜ ፣በቅርጻቸው፣ እንዲሁም ማህበረሰቡ ለቁሶቹ የሰጣቸውን ሙያዊ ስያሜ መሠረት በማድረግ መመደብ እና መተንተን ይቻላል በማለት ገልጸዋል። በዚህ ጥናት የሚዳሰሱትን የቆዳ ቁሶች ዓይነትና ጠቀሜታ ለማሳየት የተሻለ ሆኖ የተገኘው የቁሶችን ተግባር መሠረት አድርጎ መመደቡ ነው። በመሆኑም በዚህ ክፍል ቁሶች በሚሠጡት አገልግሎት ተመድበው ይተነተናሉ።

በሁለቱ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙት የቆዳ ሥራ ውጤቶች ዓይነታቸውም ሆነ አገልግሎታቸው በርከት ያለ ነው። እነሱም ገርንዲ፣ ላምነት፣ አጐዛ፣ አንቀልባ፣ መጫኛ፣ ምራን፣ ለምድ፣ መርገጫ፣ ማህደር/የመጽሐፍ ቅዱስ የጸሎት መጻፍ መያዣ/፣ ዝናር/እንግት/ ፣ጀበርና፣ የጐራዴ እና የሳንጃ ማስገቢያ/አፎት/፣ የፈረስ ልጓም፣ ዳውላ/አቆማዳ/፣ ስልቻ/ቀርበታ/፣ የጠፍር አልጋ፣ አለንጋ፣ ነት፣ የወረንጦ ማስገቢያ፣ መከዳ፣ የልጆች ማጫወቻ/አምባር/ እና መጠጊያ ናቸው።

4.1.1.1 ለመኝታነት፣ ለልብስነትና ለትራስነት የሚያገለግሉ ቁሶች

ዠርንዲ፡- ከላም ወይም ከበሬ ቆዳ የሚሠራ ከላይም ከውስጥም ምንም አይነት ፀጉር የሌለው በእጅ ሲነካ የሚለሰልስ ገጽታ ያለው መደብ ወይም አልጋ ላይ ተነጥፎ ለመኝታነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ እንደ አቶ ሽታ ደነቀው ገለጻ የዠርንዲ ዋጋ ቀደም ባሉት ጊዜያት ከ15-20 ብር የነበረ ሲሆን ከሁለት ዓመት ወዲህ ግን በአማካይ እስከ 60 ብር በመሸጥ ላይ ይገኛል (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 05፣ 2003)፡፡ ዋጋው ከሌሎች አቻ አገልግሎት ከሚሠጡ እና ከጭፍር ወይም ከቁጠማ ከሚሠሩ ምንጣፎች ማለትም ሠሌል/አንኩቲ/፣ ዳውጃ አንፃር ሲታይ ዋጋው ከፍ ያለ በመሆኑ የሚገኘው መካከለኛ የኢኮኖሚ አቅም ካላቸው ሰዎች ቤት ነው፡፡

ላምነት፡- የሚሠራው ልክ እንደ ዠርንዲ ከበሬ ወይም ከላም ቆዳ ሲሆን በመጠንም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ላምነት ከዠርንዲ በተለየ መንገድ ፀጉር ያለው ሲሆን ላምነት ለመስራት የሚውለው ቆዳም ዥንጉርጉር ቀለም ያለው ሊሆን እንደሚገባ ደነቀው አባተ (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 05፣ 2003) ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም የቁሱ አገልግሎት እንደ ዠርንዲ አልጋ ላይ ወይም መደብ ላይ ተነጥፎ ለመተኛነት ሲሆን ከዚህም ባለፈ ግድግዳ የማስጌጥ ተግባርም አለው፡፡ ይሄኛው ተግባሩ ከአሠራሩ እና ከቆዳው ቀለም የተያያዘ ነው፡፡ ላምነት ፀጉሩ ሳይለቅ/ሳይረግፍ/ የሚሠራ ሲሆን ከነፀጉሩ ለአገልግሎት የሚዘጋጅበት ምክንያት ደግሞ የቆዳው ቀለም በራሱ የተለያዩ ቀለማቶችን አካቶ የያዘ በመሆኑና አይን የሚስብ/ማራኪ/ በመሆኑ ነው በማለት ያስረዳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ እንደላይኛው)፡፡



(ፎቶግራፍ 1) ዣንዲ በገበያ ላይ



(ፎቶግራፍ 2) ላምነት

አጎዛ፡- ከበግ፣ ከፍየል እና አልፎ አልፎም ከሚዳቋ ቆዳዎች ከእነ ፀጉሩ ተዘጋጅቶ መደብ ላይ በመደረግ ለምንጣፍነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡አጎዛ ከላምነት እና ከዣንዲ ጋር ሲነጻጸር የአገልግሎት አድማሱ ሳይጠብ በአካባቢው ማህበረሰብ በሰፊው ግልጋሎት ላይ እየዋለ የሚገኝ ቁስ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አጎዛ የሚዘጋጀው በቆዳ ሥራ ባለሙያዎች ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በግ፣ ፍየል፣ ወይም ሚዳቋ ማግኘት የቻለ ሰው እንስሳቶቹን አርዶ ቆዳቸውን በጥንቃቄ በመግፈፍ እና ፀሐይ ላይ ወጥሮ በማድረቅ የሚያዘጋጀው የቆዳ ቁስ አይነት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ባለሙያዎችም ሆኑ ሌላው ማህበረሰብ በቀላሉ በማዘጋጀት የሚጠቀሙበት ሲሆን እንደ ሌሎች ቁሶች በብዙ ሂደቶች ማለፍንና የተለየ ክህሎትን አይጠይቅም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደሌሎች የቆዳ ውጤቶች ገበያ ላይ ለሽያጭ የማይቀርብ ሲሆን ማንኛውም ሠው ቤቱ ውስጥ በቀላሉ አዘጋጅቶ ሊጠቀምበት የሚችል ቁስ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በማዘጋጀት ሂደቱ አሰራሩን ከሌሎች መቅሰምንና መመልከትን የማይሻ እና በዘፈቀደ የሚሰራ ነው፣ ማለት እንዳልሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

አጐዛ ከምንጣፍነት በተጨማሪ እንደ ላምነት የግርግዳ ጌጥ በመሆን አገልግሎት ይሰጣል ነገር ግን ሁሉም አጐዛዎች ለዚህ ተግባር አይመረጡም፡፡ ይኸውም ግርግዳ ላይ የሚንጠለጠሉት አጐዛዎች የሚመረጡት በቀለም ዓይነታቸው ነው፡፡ ከመስክ ሥራው መመልከት እንደተቻለው ብዙ ቤቶች ላይ ለዚህ ተግባር

የተመረጡት ዥንጉርጉር እና ሙሉ ነጭ ወይም ቀይ ቀለም ያላቸው አጦዛዎች ናቸው።



(ፎቶግራፍ 3) የግርግዳ ጌጥ የሆኑ አጦዛዎች

የጠፍር አልጋ፡- የጠፍር አልጋ ከጠፍር የሚሠራ አልጋ ሲሆን አገልግሎቱም ከእንጨት እና ከሸቦ እንደሚሠሩት አልጋዎች ለመኝታነት የሚውል ነው። የአልጋው ቅርጽ ከሸቦ የሚሠሩትን /"ፋሚሊ" አልጋዎች/ አይነት ቅርጽ ሲኖረው፤ የሚሠራበትን ንጥረ ነገሮች ስንመለከት የፍራሽ ማስቀመጫ ርብራቦቹ በቀጫጭን ተሠንጥቀው ከተዘጋጁ ቆዳዎች (ጠፍሮች) የሚሰራ ሲሆን የአልጋው እግር ደግሞ ከእንጨት ይዘጋጃል። ይህ የአልጋ አይነት በዚህ ወቅት በሁለቱም ወረዳዎች መሠራትም ሆነ አገልግሎት መስጠት ያቆመ መሆኑን የአካባቢው ተወላጅ አበበ መልኬ እና ሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች ይገልፃሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 16፣2003፣ ዓም)። ምክንያቱም ጠፍርን የሚተካ ላስቲክ ወይም ደግሞ ሲባጎ ገመድ በመገኘቱ እና እነዚህን ቁሶች ተጠቅሞ በቀላሉ አልጋ ለማዘጋጀት በመቻሉ ነው።

የጠፍር አልጋን ሲያዘጋጁ የነበሩ የቆዳ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት፣ የሚሸጠው ገበያ ቀርቦ ሳይሆን ባለሙያዎች ቤት ውስጥ ብቻ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ከባድ በመሆኑና ለመሸከም ስለሚያስቸግር ነው። ከዚህ በተጨማሪም አልጋው ተፈላጊ በነበረበት ጊዜም ቢሆን የቆዳ ባለሙያዎች እንደ ሌሎች ቁሶች

በራሳቸው ተነሳሽነት አያበጁትም፡፡ ምክንያቱም ተጠቃሚው የሚፈልገው መጠን/ስፋት/ ተዘጋጅቶ ከተቀመጠው አልጋ ጋር አንድ ላይሆን ስለሚችል ነው፡፡ በመሆኑም ይህ አልጋ ለተጠቃሚ የሚደርሰው በትዕዛዝ እንዲሠራ ሲደረግ ብቻ መሆኑን ቁሱ ተፈላጊ በነበረበት ጊዜ ይሠሩ የነበሩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡

እስካሁን የተገለፁት ቁሶች በሁለቱ ወረዳዎች በምንጣፍ /በመኝታነት/ እንዲሁም በግርግዳ ጌጥነት አገልግሎት የሚሠጡ ሲሆን ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የሚለበሱ የቆዳ ቁሶችን እንመለከታለን፡፡

ለምድ፡- ከበግ ቆዳ ከነፀጉሩ የሚሠራ ሲሆን ከአጐዛ የሚለየውም ለመለበስ እንዲያመች ተብሎ በሚጨመርበት ማሰሪያ ነው፡፡ የሚለበሰው እንደ ካባ ትከሻ ላይ በመደረብ ሲሆን ዋነኛ አገልግሎቶቹም በእርሻ ወቅት በተለይም በክረምት ወራት ጭቃ የነኩ ሞፈሮችን ለመሸከም እንዲሁም ብርድና ዝናብን ለመከላከል ናቸው፡፡


ለምድ በሁለቱ ወረዳዎች ውስጥ ከላይ የተገለፁትን ተግባራት በማከናወን በሠፊው አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ የቆዳ ውጤት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ግን ለምድን ለብሶ የሚያርስ ሰው አይታይም፡፡ ምክንያቱም የለምድን አገልግሎት ሊተካ የሚችል "ጐጃም አዘነ" ተብሎ የሚጠራው በፋብሪካ የሚመረት ጨርቅ በሰፊው መመረት በመጀመሩ እንደሆነ በለምድ ሲጠቀሙት የነበሩት አቶ ባይህ ግዛቸው ይገልጻሉ፡፡ አቶ ባይህ ግዛቸው ቡሬ ወረዳ ከበሳ አቦ በምትባል የገጠር ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩና በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ይህ ሠው ለምድን በእርሻ ሥራ ወቅት በብዛት ሲጠቀሙ የነበሩ ሲሆን በዚህ ወቅት የለምድ አገልግሎት በፎጣ መተካቱ ያስቆጣቸው በሚመስል ንግግር ለለምድ ያለቸውን ፍቅር "ለምድማ በጣም አገልግሎን ነበር፡፡ እድሜ ለጎጃም አዘነ አሱ መጥቶ ድራሹን አጠፋው እንጅ ፤ድሮማ ለምድ የሌለው ገበሬ ምኑን ገበሬ ነው፡፡ አይ ለምድ ሙቀቱ ነው ለሸክም መምጠኑ፤ ሥንቱ ይወራል ይሄ ጥላ የለሽ ፎጣ መጣና አጠፋው እንጂ" *(ቃለመጠይቅ ሚያዚያ ፣18፣2003፣)* ገልጸውልኛል፡፡

ነት፡- ሌላው ከቆዳ ተሠርቶ በልብስነት የሚያገለግለው ቁስ በአካባቢው አጠራር ነት በመባል ይባላል፡፡ የዚህ ቁስ አገልግሎት ከሃይማኖት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡

የሚጠቀሙበት ሰዎችም በመንፈስም ሆነ ባካል ራሳቸውን ካለማዊ ኑሮ ያራቁ ናቸው። አለም በቃኝ ብለው ኑሯቸውን በዱር እና በጫካ ያደረጉ ሠዎች እንደ ካባ ደርበው በመልበስ ለብርድ እና ለፀሐይ መከላከያ አድርገው የሚጠቀሙበት መሆኑን መሪ ጌታ ዘማሪያም ያስረዳሉ። ነት ከዣንዲ የሚዘጋጅ ሲሆን በካባ ቅርጽ ተሠርቶ በእጅ ይሰፋል። ዳር ዳሩ ላይ አንዱን ጠርዝ ከሌላኛው ለማያያዝ የሚያገለግሉ ቁልፎች ይተከሉበታል።

ለትራስ የሚያገለግሉ ቁሶች፡- በትራስነት የሚያገለግሉ የቆዳ ስራዎች መጠጊያ እና መከዳ በመባል ይታወቃሉ። መጠጊያና መከዳ አሰራራቸው አንድ አይነት ሲሆን የሚለያዩት በተግባራቸው እና በመጠናቸው ነው። መጠጊያ አነስተኛ መጠን ያለው ሲሆን አገልግሎቱም በመኝታ ጊዜ ትራስ በመሆን ጭንቅላትን ደገፍ አድርጐ ለመያዝ ነው። መከዳ ደግሞ ከመጠጊያ ከፍ ያለ መጠን/ቢያንስ የአንድ መጠጊያን ስድስት እጥፍ ያህል ግዝፈት አለው/ ሲኖረው አገልግሎቱም የቤት አባዋራዎች ከስራ፣ ከገበያና ከሌሎች ቦታዎች ውለውና ደክሟቸው ሲመጡ ከሚዘጋጅላቸው ምንጣፍ ላይ ተቀምጠው ወገባቸው ዘና እንዲል ደገፍ የሚሉበት ቁስ ነው። መከደ የሚሠራው በትዕዛዝ ሲሆን ክፍያውም ውድ በመሆኑ የሚገኘው እና ጥቅም የሚሠጠው ሀብት ባላቸውና በተከበሩ ሠዎች ቤት ነው።

መጠጊያ ግን በማንኛውም ሰው ቤት ውስጥ ሊገኝ የሚችል ነው። አገልግሎቱም ለአዲስ ተጋቢዎች (ሙሽሮች) በትራስነት ነው። መጠጊያ እስካሁን ድረስ አገልግሎት መስጠቱን ያላቆመ ሲሆን፤ በተለይም በበጋ ወራት ሠርግ ስለሚበዛ ገበያ ላይ በብዛት ይቀርባል።



(ፎቶግራፍ 4) መጠጊያዎች (ትራሶቸ) በገበያ ላይ

4.1.1.2 ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉ የቆዳ ቁሶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ በበሬ የእርሻ ሥራን ለማከናወን የሚያግዙ ቁሶችን እንመለከታለን፡፡ እነሱም ምራን፣ ጅራፍ እና መርገጫ ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ የግብርና ውጤት የሆኑ የእህልና የአትክልት ዘሮችን በከረጢት ከትቶ በአህያ ጭኖ ለማሰር የሚያገለግለውን መጫኛ የተባለውን ቁስም አብረን እንመለከታለን፡፡

ምራን፣መርገጫና ጅራፍ፡- ምራንና መርገጫ ሙሉ በሙሉ ከቆዳ የሚሠሩ ቁሶች ሲሆኑ ጅራፍ ግን ብዙው ክፍል ከገመድ የተሰራ ሲሆን የተወሠነው ክፍል ማለትም ጅራፉን አንጠልጥሎ ለመያዝ ያመች ዘንድ ለእንጨት ማስገቢያ የሚሆነው ጀሮ ብቻ ከቆዳ ይሠራል፡፡ ጅራፍ ገበሬው በሬዎቹን ለመንዳትና የእርሻ ስራን በፍጥነት እንዲያከናውኑ ለማድረግ የሚጠቀምበት ወይም በሬዎቹ በተፈለገው አቅጣጫ እንዲሄዱ የሚያደርግበት ነው፡፡ ምራን ደግሞ በበሬዎች ትከሻ ላይ የሚቀመጠውን ቁስ/ቀንበርን/ እና ማረሻውን ለመያዝ ከሚያግዘውና በከፊል መሬት ላይ ከሚነተተው ሞፈር ጫፍ ጋር ለማያያዝ የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ መርገጫ የሚባለው ቁስ ደግሞ ማረሻ ብረቱ የተገጠመበትን እርፍ የሚባል እንጨት ከሞፈሩ ጋር ለማያያዝ የሚያግዘውን ወገል የተሠኘ ብረት ከሞፈር ጋር አያይዞ ለማሠር የሚያግዝ እንደ ዣንዲ ከተዘጋጀ የላም ወይም የበሬ ቆዳ በቀጫጭኑ እየተሠነጠቀ የሚሠራ ቁስ ነው፡፡ የእነዚህ ቁሶች ወቅታዊ ሁኔታ ሲታይ ምራንና ጅራፍ በሌሎች

የፋብሪካ ውጤት ያልተተኩ መሆኑን ከመረጃዎች ለማወቅ ተችሏል። መርገጫ ግን ገበሬዎች ከአጐበር ጨርቅ እየተገመደ በሚዘጋጅ ገመድ እየተተካ መሆኑን በወንበርማ ወረደ ሻምበል በር አካባቢ የሚኖሩት አቶ ደነቀው አባተ ይገልፃሉ።

መጫኛ፡- መጫኛ ዝንዲ ሲሰራ የሚያልፍባቸውን የአሠራር ሂደቶች አልፎ /ሙሉ በሙሉ ባይመሳሰልም/ የሚሠራ ሲሆን፤ በቀጫጭኑ ተሠንጥቆ የሚዘጋጅ ቁስ ነው። ዋነኛ አገልግሎቱም በከረጢት (በማዳበሪያ) ወይም በኩንታል ያለን እህል ወይም አትክልት በአህያ ወይም በፈረስ ጭኖ ከጀርባቸው ላይ ተንሸራቶ እንዳይወድቅ ለማሰሪያነት የሚያግዝ ዕቃ ነው። መጫኛ ከጠፍር ጋር የሚለያየው በእርዝመቱ ሲሆን መጫኛ ከጠፍር ቢያንስ አራት እጥፍ ያህል እርዝመት እንዳለው ባለሙያዎች እና ተጠቃሚዎች ይገልፃሉ።



(ፎቶግራፍ 5) የተጠቀለለ መጫኛ



(ፎቶግራፍ 6) ምራኖች

4.1.1.3. የተለያዩ ቁሶችን ለመሸፈን/ለመያዝ/ የሚያገለግሉ ቁሶች

በዚህ ክፍል የሚጠቀሱት ቁሶች መጽሐፍ፣ ጥይት፣ ገንዘብ (ብር) ለመያዝ ወይም ለመሸፈን የሚያገለግሉ የቆዳ ውጤቶች ሲሆኑ እነሱም ማህደር፣ ዝናርና ጀበርና ናቸው።

ማህደር፡- ሐይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን መፃህፍት ከጉዳት ወይም ከመቀደድ ለማዳን የሚያገለግል ከከብት ቆዳ የሚሠራ ቁስ ነው። የማህደር መጠን እንደ ሚያዙት መፃህፍቱ መጠን የተለያየ ነው። ማህደር መፅሀፍ የሚቀመጥበት/የሚያዘበት/ ሲሆን በትከሻ አንጠልጥሎ ለመያዝ የሚያገለግል ማንገቻ

አለው። በዚህ ቁስ የሚገለገሉት ባብዛኛው ቄሶች ሲሆኑ ዲያቆናት እና የቆሎ ተማሪዎችም የተለያዩ የፀሎት መፅሀፎችን ለመያዘ ይገለገሉበታል።

አርሶ አደር የሆኑና ኑሯቸውን ገጠር አካባቢ ያደረጉ ቄሶች ወደ ቤተክርስቲያን ለቅዳሴ ረዥም መንገድ አቋርጠው ስለሚሄዱ ማህደር ተመራጭ የመፅሀፍ ቅዱስ እና የፀሎት መፃህፍት መያዣ እንደሆነ ይገልፃሉ። ማህደር ለመንፈሳዊ መጻህፍት መያዣነት የተመረጠው ከተሠራበት ጥሬ ዕቃ አንፃር ለአያያዝ አመቺ በመሆኑ እንጂ ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ ምንም አይነት ትዕምርታዊ ትርጉም የሌለው መሆኑን መሪ ጌታ ዘማሪያም እና ሌሎች የአካባቢው ቄሶች ጨምረው አስረድተውኛል። (ቃለመጠይቅ ግንቦት 1፣ 2003 ዓም)



(ፎቶግራፍ 7) ሱቅ ውስጥ የተንጠለጠሉ ማህደሮች

ማህደር ጥናቱ ባተኮረበት አካባቢ በሚገኙ ባለሙያዎች አይሠራም። ምክንያቱም ለዚህ መስሪያ የሚሆኑ ቁሶች አለመገኘታቸው እና መስራት የሚችሉ ባለሙያዎችም አለመኖራቸው ነው። ማህደር ከደንበጫና ከሌሎች አካባቢዎች በነጋዴዎች አማካይነት የሚመጣ ነው።

ዝናር እና ጀበርና፡- እነዚህ ሁለት ቁሶች በአካባቢው ስያሜ መሠረት የተለያዩ ጠመንጃዎችን ለምሳሌ የዲሞትፈር፣ የውሹግራ፣ የአብራራው፣ የወጨፎ ፣ የአልቢን፣ የምኒሽር ጥይቶች በወገብ ለመያዝ ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው።ቁሶቹ ቀደምት

አርበኞች ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ ጥይቶችን ወገባቸው ላይ ደርድረው ይይዙባቸው እንደነበር የቡሬ ወረዳ አባት አርበኛ የሆኑት አባ አማረ ነግረውኛል(ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 9፣2003 ዓም)። ከዚህም ባሻገር ጦር ሜዳ ሄዶ ከጠላት ጋር ሲዋጋ የነበረ ሰው በሠላም ከተመለሰ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በመገኘት አጋጣሚውን ለማጀብ እና የእሱን ክብር እና ጀግንነትም ለመዘከር ይጠቀምባቸዋል።

ጥናቱ ባተኮረባቸው አካባቢዎች ጀበርና ወይም ዝናር ያለው ሰው የተከበረ እና አርበኛ የነበረ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ወይም ደግሞ የወታደር እና የአባት አርበኞች አመታዊ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ዝናሩን ወይም ጀበርናውን በጥይቶች ሞልቶ፤ ጠብመንጃ ካለው አንግቦ፤ በቅሎ ወይም ፈረስ ላይ ተቀምጦ ለለቅሶው ወይም ለክብረ በአሉ ድምቀት ይሰጣል። ማህበረሰቡም የዝናሩን ዙር (ወገብ ላይ ምን ያህል እንደሚዞር) እየቆጠረ፤ የበቅሎውን አነዳድ እያደነቀ ጀግንነቱን እና ክብሩን በተለያዩ አጋጣሚዎች ስሙን እየጠራ ያሞግሳል።

ከመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት እነዚህ ሁለት ቁሶች በማንኛውም ሰው እጅ አይገኙም። ጀበርና እና ዝናር የሚገኙት ከአባት አርበኞች እና ከመሳፍንት ዘር ከተወለዱ ሠዎች ቤት ብቻ ነው። በዚህ ወቅት ቁሶቹ ያሏቸው ሠዎች በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ ያላቸው ተሠሚነት እና ክብር ከፍ ያለ ነው። ምክንያቱም የቁሶቹ አገልግሎት ከጦርነት እና ከአርበኝነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ማህበረሰቡ ለቁሶችም ሆነ ለቁሶቹ ባለቤት የተለየ ክብርና ቦታ ይሰጣቸዋል።

ጀበርና 36 ሳ.ሜ ርዝመት ሲኖረው የውስጥና የውጭ ክፍሎች አሉት። የውስጠኛው ክፍል/አስሮ የያዘውን ያነገተውን ሰው ወገብ የሚነካው ክፍል/ ልሙጥና ለስላሳ ሲሆን ውጨኛው ክፍል ደግሞ አስር አስር ጥይቶችን ባንድነት ለመያዝ የሚችሉ ኪሶች አሉት። የኪሶቹ ስፋት 3 ሳ.ሜ ሲሆን ቁመታቸው ደግሞ 4 ሳ.ሜ ነው። የጀበርና ቅርጽ ከወንዶች ቀበቶ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ለመታጠቂያነት የሚያገለግለው ብረት እና የብረት ማስገቢያ ቀዳዳዎች ከዚህ ቀበቶ ጋር ያመሳስለዋል። ጀበርና ከዝናር ጋር ሲነፃፀር የተወሰኑ ልዩነቶች አሉት። ይኸውም ጀበርና አንድ ዙር ርዝመት ብቻ ሲኖረው ዝናር ግን ከአንድ ዙር እስከ ሁለት ዙር

ተኩል ርዝመት ኖሮት ሊሠራ እንደሚችል የቁሱ ተጠቃሚ የሆኑ መረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል። እኔም በመስክ ቆይታዬ አንድ ዙር ጀበርናና ሁለት ዙር ተኩል ርዝመት ያለው ዝናር ለማየት ችያለሁ። በመስክ ያገኘሁት ዝናር 180 ጥይቶችን፣ ጀበርናው ደግሞ 100 ጥይቶችን ይይዛል። የሁለቱ ቁሶች የጥይት አቀማመጥ የተለያየ ነው። ይኸውም ጀበርና ላይ የሚገኙ ጥይቶች ቁልፍ ባላቸው ኪሶች ይቀመጡና ይቆለፋሉ /ሙሉ በሙሉ ይሸፈናሉ/ ዝናር ግን አንዳንድ ጥይቶችን በመደዳ የሚያስቀምጥ ሲሆን ጥይቶቹ ሙሉ በሙሉ አይሸፈኑም።

ጀበርናንና ዝናርን የሚያለያያቸውን ገጽታ ስንመለከት ዝናር በየዙሮቹ መጨረሻ ላይ የተቀጠሉ 11ሳ.ሜ ርዝመት ያላቸው መቀነቻ ወይም ማጥበቂያ ተብለው የሚጠሩ ስስ ቆዳዎች ይገኙበታል። ጀበርና ደግሞ መሃል ላይ የተቀጠለ እና በኪሶቹ ተከተው በወገብ የተያዙትን ጥይቶች ሚዛናዊ አድርጐ ለመያዝ የሚያስችል እና ወገብ ላይ ከሚታሰረው ከጀበርናው ዋና ክፍል ተነስቶ በአንድ ትከሻ የሚገባ ማንገቻ አለው። በእነዚህ ክፍሎች ልዩነት ሳቢያም ዝናር በመቀነቻዎቹ እየጠበቀ ወገብ ላይ ብቻ የሚታሰር ሲሆን ጀበርና ደግሞ ሸክሙን ሚዛናዊ ለማድረግ ወገብ ላይ ከመታጠቅ በተጨማሪ በአንድ ትከሻ አስገብቶ መያዝን የሚጠይቅ ነው።

እነዚህ ቁሶች በማህበረሰቡ ዘንድ በጣም የተከበሩ እና የተወደዱ ቁሶች ቢሆኑም በአሁኑ ጊዜ ግን በቆዳ ባለሙያዎቹ ሲበጁ አይታዩም። ምክንያቱም እነሱን ለመስራት የሚያስችሉ መሳሪያዎች አለመኖራቸውና ቁሶቹን ሲሰሩ የነበሩ አባቶች በመሞታቸውና ተተኪ በአለመገኘታቸው ነው። በዚህም ምክንያት በዚህ ወቅት ቁሶቹ የሚገኙት ከጥቂት ሰዎች እጅ ላይ ብቻ በመሆኑ በቀላሉ ለማግኘት ይከብዳል። እኔም ቁሶቹን ለማየትና ገጽታቸውን በፎቶና በቪዲዮ ለመቅረጽ ባለቤቶቹ ለዕቃዎቹ ካላቸው ከፍተኛ ክብር እና ፍቅር ለማንኛውም ሰው ስለማይሰጡ ለማግኘት ተቸግሬ ነበር። ሆኖም በስተመጨረሻ አካባቢው የትውልድ ቦታዬ በመሆኑ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ በሆነችው በእናቴ በኩል ለማግኘት እና የቁሶቹን አካላዊ ገጽታ ለመቅረጽና ፎቶ ለማንሳት ችያለሁ።



(ፎቶግራፍ 8) ዝናር



(ፎቶግራፍ 9) ጀበርና

4.1.1.4 ለልጅ ማዘያና ማጫወቻ የሚያገለግሉ ቁሶች

አንቀልባ፡- አንቀልባ በሁለቱ ወረዳዎች የሚገኘው የገጠር ነዋሪ ማህበረሰብ ከወር እስከ ሶስት አመት ከስድስት ወር ዕድሜ ያላቸውን ህፃናት በጀርባ ለማዘልና ለማስተኛት እንዲሁም ህፃን አዝሎ የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን በስፋት የሚጠቀምበት የቆዳ ውጤት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ቁሱ የሚሸጥበት ዋጋ በአማካይ 160 ብር ነው፡፡ እንደባለሙያዎቹ ገለፃ በግምት ከ10 ዓመት በፊት የአንድ አንቀልባ ዋጋ 20 እና 30 ብር እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ የአንቀልባ ዋጋ ጭማሪ ያሳይበትን ምክንያትም ወንዴ አንባው የተባሉት የረዥም ጊዜ የቆዳ ባለሙያ "የገበያው ሁኔታ ሲያገኝ ሲያጣ ነው፤ አንድ ቀን ደህና ይሆናል እንደ ቀን ይረክሳል፡፡ አሁን በጣም የሚፈለገው ዕቃ አንቀልባ ነው፡፡ እሱም ያው ጌጣጌጥ ስለበዛበት ነው የተወደደው"፡፡ (ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዚያ 22 ፤2003 ዓ.ም.) በማለት ስለአንቀልባ ተፈላጊነት ገልፀዋል፡፡

አባ ወንዴ እና የአንቀልባ ተጠቃሚ የገጠር ሴቶችም ጨምረው እንደገለፁልኝ አንቀልባ ገበያ ላይ ከሚሸጡት የቆዳ ቁሶች ሁሉ በውድ ዋጋ የሚሸጥና ተፈላጊነቱም በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣ ቁስ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በመስክ ለማየት እንደቻልኩት በተዘጋጀው አንቀልባ ላይ የሚጨመሩት የዛጐል ጌጣጌጦች ውበቱ እንዲጨምር ስለአደረጉት እና ቀልብ ሳቢ ቁስ እየሆነ በመምጣቱ ነው፡፡

ቡሬና ሽንዲ ገበያ ላይ በአደረግሁት የስድስተ ቀን ምልከታ አንቀልባ በዛሎች በተለያየ ቅርጽ ተውቦ በሰፊው ለገበያ ቀርቦ አይቻለሁ፡፡

አንቀልባ የልጅ ማዘያ በመሆን ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የአዛዮቹን/ የልጅ እናቶችን/ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ወይም ሐብት የመጠቆም ትዕምርታዊ ፋይዳም አለው፡፡ ይኸውም በዚህ አካባቢ ልጇን በጫቅማ ቅባት በደንብ በለሰለሰና ጥሩ የቆዳ ቀለም በተቀባ እንዲሁም በብዙ ዛጐሎች ባጌጠ አንቀልባ ያዘለች እናት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንደ ሐብታም ትቆጠራለች፡፡ በሌላ በኩል ጌጣጌጥ ባልበዛበት እና በደንብ ባለሰለሰ አንቀልባ የሚያዝሉ እናቶች ደግሞ አነስ ያለ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አንቀልባ ለልጅ ማዘያ በመሆን ከሚሠጠው አገልግሎት በተጨማሪ የአንቀልባ ተጠቃሚዎችን ኢኮኖሚያዊ ደረጃ በመግለጽ የሚጠቅም መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል፡፡



(ፎቶግራፍ 10) አንቀልባዎች በገበያ ላይ

ከላይ በቀረበው ማብራሪያ ባካባቢው ለልጅ ማዘያ በመሆን የሚያገለግለውን አንቀልባ ገጽታና አገልግሎት ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ለልጆች ማጫዎቻ በመሆን የሚያገለግለውን የቆዳ አምባር እናያለን፡፡ ይህ የህፃን ማጫወቻ አምባር የሚሠራው በቆዳ ባለሙያ ሴቶች ሲሆን በህፃኑ/ኗ የእጅ ውፍረት መጠን ተለክቶ የሚሠራ ነው፡፡ የቁሱ ቅርፅ ከብር ወይም ከሌላ ንጥር ቁሶች እንደሚሠሩት ማጌጫ አምባሮች ክብ ሲሆን የሚለየው ደግሞ አምባሩ ላይ የሚንጠለጠሉት ዛጐሎች መጨመራቸው ነው፡፡ የአምባሩ አገልግሎት የሚመነጨው ከእነዚህ ዛጐሎች ከሚወጣው ድምጽ ነው፡፡ የዚህን ቁስ ጥቅም በተመለከተ ወ/ሮ ምንታምር ገዛኸኝ እንዲህ ብለውኛል፡፡

ሶስት ወር እና ከዚያም የበለጠ ዕድሜ ያላቸው ህፃናት በእጃቸው ልክ ዛጐል ያለበት የቆዳ አምባር እናሠራላቸዋለን፡፡ እናም ሞሳዎች ተንተው እጃቸውን ሲያወዛውዙ ሹዋሹዋ ስለሚልላቸው ይጫወታሉ፡፡ እናቴን ብለው አያለቅሱም፡፡
(14/08/03)

ከወ/ሮ ምንታምር ንግግር መረዳት እንደሚቻለው የአምባር ተግባር ህፃኑ ሆን ብሎም ይሁን በአጋጣሚ እጆቹን ሲያወዛውዝ በሚፈጠረው የዛጐሎች የግጭት ድምጽ ራሱን እንዲያዝናና ማድረግ ነው፡፡ ይህ የቆዳ አምባር ህፃኑን በማዝናናቱ ለህፃኑ ከሚሰጠው ደስታ በተጨማሪ እሱን ለማባባል የሚጠፋውን ጊዜ በመቆጠብም ትልቅ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

4.1.1.5 ለእህል መያዣነት የሚያገለግሉ ቁሶች

ጥናቱ በአተኮረበት አካባቢ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማለትም ዘመናዊ የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ቁሶች እስከ መጡበት ጊዜ ድረስ ከላም፣ ከበሬ፣ እንዲሁም ከፍየል ቆዳ እየተሠሩ የተለያዩ የእህል ዘሮችን ከትቶ ለማስቀመጥ፣ ወደ ገበያ እና ወደ ሌላ ቦታ ተሸክሞ ለመውሰድ የሚያገለግሉ ከረጢቶች አሉ፡፡ ከላምና ከበሬ ቆዳ የሚሠሩት አቆማዳ ወይም ዳውላ ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ከፍየል ቆዳ የሚሠሩት ከረጢቶች ደግሞ ስልቻ ወይም ቀርበታ ተብለው እንደሚጠሩ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑት አቶ የኔሁን ዘገየ እና አቶ ባይህ ግዛቸው ይገልፃሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 17፣ 2003 ዓም)

የእነዚህ ቁሶች አገልግሎት ተመሳሳይ ሲሆን ባካባቢው የሚመረቱ የእህል ዘሮችን ማለትም ጤፍ፣ዳጉሳ፣በቆሎ፣ ባቄላ አተርና ሌሎችንም እህሎች ለመያዝ ያገለግላሉ፡፡ አቆማዳ ወይም ዳውላ የሚባለው ቁስ ግዙፍ አካል ካላቸው እንስሳት የሚዘጋጅ እንደመሆኑ መጠን ትልቅ ሲሆን እንደመረጃ አቀባዮቼ ገለፃ በጣም ትልቅ የሚባለው አቆማዳ እስከ መቶ ኪሎ ግራም እህል የመያዝ አቅም እንዳለው ይናገራሉ፡፡ ስልቻ ወይም ቀርበታ ተብሎ የሚታወቀው ደግሞ ከአቆማዳ ያነሰ መጠን ሲኖረው በግምት እስከ 30 ኪ.ግ ሊይዝ ይችላል፡፡

አቆማዳ ቤት ውስጥ እና ከቤት ውጪ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ሌላም ትዕምርታዊ ፋይዳ አለው፡፡ ይኸውም በየአመቱ ብዛት ባላቸው እና በትልልቅ አቆማዳዎች ምርቱን በሰፊው የሚያስገባ ገበሬ ታታሪ እና ሀብታም ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ታታሪ ያልሆነና ደሃ ገበሬ ሊኖረው የሚችለው አቆማዳ አንድ ብቻ ወይም ደግሞ ጭራሹን ላይኖረው ይችላል፡፡ የሚያገኘውን ትንሽ ምርት ወደ ቤቱ የሚየስገባበት የእህል መክተቻ አቆማዳ ስለማይኖረው ከሀብታሙ ገበሬ ይዋሳል፡፡ ከዚያም ለስላሳና እና ተለቅተለቅ ያለ አቆማዳ ካዋሰው 'እከሌ እኮ የልጅ ገላ የመሳሰለውን ወደል ወደል አቆማዳ ሠጠኝ፤ የለመደውን ምርት ደግሞ ደጋግሞ በሰፊ እጁ ይስጠው' በማለት ሐብታሙን ገበሬ ያወድሳል፡፡ ሐብታሙ ገበሬም ይህን መሰል ምስጋና እንዳይቀርበት የተሻሉ የሚላቸውን አቆማዳዎች መርጠ ከአደራ ጋር ያውሳል፡፡

ባጠቃላይ አቆማዳ ባካባቢው ከፍተኛ ማህበራዊና ባህላዊ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ቁስ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በሌሎች የፋብሪካ ቁሶች በመተካቱ ሲበጅም ሆነ አገልግሎት ሲሰጥ አይታይም፡፡ አስማማው ተረፈ የአቆማዳን አሰራርና ወቅታዊ ሁኔታ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> *አቆማዳ አሁን ቀርቷል፡፡ ሰው ተወው ካልገዛን ሠርተን ምን እናረገዋለን? ማዳበሪያ እና ኩንታል መጠቀም ስለጀመረ ትቶታል፡፡ አሠራሩማ ያው አንድ ገጉንዲ ተሠርቶ ለሁለት ይቀደዳል፡፡ ከዚያ የተቀደደው በሲር ወየም በማዳበሪያ ክር አገጣጥሞ ይሠፋሉ፡፡ መጠኑን በክንዳችን ነው የምንለካው፡፡ ቁመቱን ሁለት ክንድ ወርዱን ደግሞ አንድ ክንድ ተሰንዝር አድርገን እንሠራው ነበር፡፡* (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 5፣ 2003 ዓ.ም)

ከባለሙያዎቹ እና ከሌሎችም የአቆማዳ ተጠቃሚ ከነበሩ ሰዎች ጠይቄ መረዳት እንደቻልኩት የአካባቢው ማህበረሰብ አቆማዳም ሆነ ስልቻን ከመጠቀም ይልቅ በፋብሪካ የሚመረቱትን ማዳበሪያ እና ኩንታል የሚባሉትን የእህል መያዣዎችን ይጠቀማል፡፡

እስካሁን የቆዳ ቁሶችን ዓይነት እና የሚሰጡትን ተግባር ተመልክተናል፡፡ በዚህም በሁለቱም ወረዳዎች በባህላዊ መንገድ የሚበጁት ቁሶች አይነትና ተግባር በርከት ያሉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸው

ቁሶች ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ ሲታይ ብዙዎቹ ከአገልግሎት ውጪ ለመሆን የተቃረቡ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በፋብሪካ የሚመረቱ ቁሶች መበራከት መሆኑን ከመረጃ አቀባዮች ንግግር እና እኔም መስክ ላይ ካደረግሁት ተደጋጋሚ ምልከታ ለማወቅ ችያለሁ፡፡

4.1.1.6. የቆዳ ቁሶች ባህላዊ ጠቀሜታ

በቡሬ እና በወንበርማ ወረዳ በሚኖሩ ባለሙያዎች የሚበጁት የቆዳ ቁሶች ቤት ውስጥ ከሚሰጡት ሰፊ አገልግሎት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት ባህላዊ ጥቅም እንዳለም በጥናቱ ሂደት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቁሶቹ በባህላዊ አገልግሎታቸው የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያሳያሉ፤ እምነቱን እንዲሁም የህይወት ፍልስፍናውን ይገልጻሉ፡፡በዚህ አካባቢ እነዚህን አገልግሎት በመስጠት የሚታወቁት ቁሶች ዝንዲ፣ መጠጊያ፣ ላምነት እና አጎዛ ናቸው፡፡ ዝንዲና መጠጊያ ለሠርግ ስርአት መከወኛ በመሆን ሲያገለግሉ ላምነትና አጎዛ ደግሞ የተጠቃሚውን ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ በውክልና የመጠቆምና የመግለፅ ትእምርታዊ ፋይዳ አላቸው፡፡

በአካባቢው ዝንዲና መጠጊያ አንድ ቤተሰብ ሴት ልጁን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲድር ለጥሎሽ በተከፈለው ገንዘብ ቀደም ብሎ ከገበያ በመግዛት ለሰርጉ ቀን ባህላዊ ስርአቱን መከወኛ ያደርጋቸዋል፡፡ ይኸውም ቁሶቹን በሰርግ ወቅት የመግዛት ግዴታ ያለባቸው የሴቷ ቤተሰቦች ናቸው ፡፡ ቁሶቹ የሚያስፈልጉት ልጅቷ ለመጀመሪያ ጊዜ የምታገባ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የልጅቷ ቤተሰቦች በህግ ሳያደርጉ ቢቀሩ ቁሶቹን ባይገዙ የባል ቤተሰቦች በህገር ሽማግሌ እስከ መክሰስ የዘለቀ ወቀሳና ነቀፌታ ያደርሱባቸዋል፡፡ የሴቷ ቤተሰቦች የተከፈላቸው የጥሎሽ ብር በተለያየ ምክንያት ቁሶቹን ለመግዛት በቂ ሳይሆን ቢቀር እንኳን ከሚደርስባቸው ወቀሳ ለመዳን ተበድረውም ቢሆን ይገዛሉ ፡፡ ከዚያም የሰርጉ እለት ሚዜዎች ቁሶቹን ከሙሽራዋ ጋር ይዘው እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ወደ ባል ቤት ከተወሰዱ በኋላ ለሙሽራዎቹ መተኛ እና ትራስ በመሆን የሚያገለግሉ ሲሆን ሙሽራዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚፈፀሙት ግብረስጋ ግንኙነት (የክብረ ንፅህና ወሰዳ) ስርአትም በነዚህ ቁሶች ላይ እንዲሆን ልማዱ ያስገድዳል፡፡

ቁሶቹ በሰርግ ጊዜ ከላይ ከተገለፀው ተግባር ያለፈ ፋይዳ አላቸው።።ይኸውም በሙሽሮቹ የጫጉላ ጊዜ ቆይታ የሚከናወነውን የደገም ወይም ኩርኩም ተብሎ የሚጠራውን የድብድብ ጨዋታ ለማከናወን ያገለግላሉ።። ከዚህ ጨዋታ ጋር ተያይዞ ሙሽራው ሙሽሪትን በመጠጊያ ካልመታት ትንቀዋለች ስለሚባል ባል ሚስትን በመጠጊያ በመምታት የበላይነቱን ያስመሰክራል።። ባካባቢው የሰርግ ስርአት የሙሽሮቹ የጫጉላ ቆይታ ሲያበቃ ሙሽሪት ከባሏ ቤተሰቦች ጋር ፊት ለፊት መተያየት ትጀምራለች።። ባልም ወደ እርሻና ወደ ሌሎች የስራ ቦታዎች በመሄድ ስራ መስራት ይጠበቅበታል ።።

እነዚህ ሽግግሮች ከመደረጋቸው በፊት ግን ሌላ መከወን ያለበት ስርአት አለ።። ስርአቱም ግልጫ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፤ ሥርዐቱ ከሚፈፀምባቸው ቁሶች ውስጥም ሙሽሮቹ በጫጉላ ውስጥ ለተለያየ አላማ ሲጠቀሙባቸው የነበሩት ዣንዲ እና መጠጊያ ዋነኞቹ ናቸው።። በመሆኑም የግልጫ ስርአት ሲከወን ሽማግሌዎችና የባል ቤተሰቦች ተሰብስበው ወለል ላይ ከስር ዳውጅ ከላይ ደግሞ ዣንዲ ተደርቦ ይነጠፋል።። በተነጠፈው ዣንዲ ላይ ደግሞ መጠጊያ ይጨመራል።። ከዚያም ሙሽሮቹ መጠጊያው ላይ ቁጭ ብለው እግራቸውን ደግሞ ዣንዲው ላይ አሳርፈው በአንድ ዋንጫ የተሞላ ጠላ እንዲቀምሱ ይደረጋል።።ከዚያም ሙሽሮቹ ተቀምጠውበት የነበረውን መጠጊያ እየጎተቱች ወደ ጓዳ እንድትገባ ይደረጋል ከዚህ ስርአት በኋላ ሙሽራዋ ከባል ቤተሰብ ጋር መነጋገር እና ፊት ለፊት መተያየት እንዲሁም የጓዳ ስራዎችን መስራት ትጀምራለች።። ባጠቃላይ በዣንዲና በመጠጊያ የግልጫ ስርአቱ ከተከወነ በኋላ ሙሽራዋ በባል ቤተሰብ ውስጥ እንደ አንድ አባል (ልጅ) መቆጠር ትጀምራለች፤ በማለት በሥርአቱ ያለፉ የአካባቢው ተወላጆች አቶ ቢዘንጋው አናጋው እና ወይዘሮ መልካም አለማየሁ አስረድተውኛል።።(ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 21፣ 2003 ዓም) ይህን ክዋኔ ሳይፈፅሙ የቀሩ የባል ቤተሰቦችም ባካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንደነውረኛ ይቆጠራሉ።።

መጠጊያና ዣንዲ ከመጋባት ጋር ብቻ ሳይሆን ከመፋታት ጋር የተያያዙ ባህላዊ ክዋኔዎችን የመፈፀም ተግባርም አላቸው ።። ይኸውም ተጋቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች ግንኙነታቸው ሳይሰምር ቀርቶ ከተፋቱ በአካባቢው የፍቺ ስርአት መሰረት የቤት እቃዎችን የማካፈል ሂደት ይከናወናል።። በዚህ ሂደት ሙሽሮቹ

መጠጊያና እና ገርንዲ የሚካፈሉበት ህግና ደንብ አለ። ምንም እንኳን ቁሶቹ የተገዙት በልጅቱ ቤተሰቦች ቢሆንም ሁሉንም የመውሰድ መብት ግን የላትም። በመሆኑም ገርንዲውን ሚስት ትራሱን ደግሞ ባል እንዲወስዱ የአካባቢው የፍቺ ስርአት ያስገድዳል። የሀገር ሽማግሌ የሆኑት አባ ገላው አበጀ "በፍቺ ጊዜ ወንዱ ገርንዲ ይዞ አይሄድም ነውር ነው። ለእሱ የሚሆነው መጠጊያና ዋንጫ ብቻ ነው። ገርንዲ አወስዳለሁ ብሎ አሻፈረኝ ቢል እንኳ እንደወንድ አይቆጠርም፤ መሣቂያ መሳለቂያ ይሆናል፤ የሚስት ቤተሰቦችም በሀገር ሽማግሌ ይከሱታል።" ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 9፣ 2003 ዓ.ም) በማለት ገልፀውልኛል።

ቁሶች ከሰርግና ከፍቺ ስርአት ጋር የጠበቀ ቁርኝት ስላላቸው አንድ ሰው አዲስ መጠጊያ ገዝቶ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከታየ ያሰው በቅርቡ ሴት ልጁን እንደሚድር ይታወቃል። በአጠቃላይ እነዚህ ሁለት ቁሶች ማህበረሰቡ ከሠርግ ጋር ተያይዞ ያለውን እምነት እና ስርአት መግለጫ ናቸው ማለት ይቻላል።

አጎዛ እና ላምነት የሀብትና የደረጃ መለኪያ ተደርገው ይወሰዳሉ። ትልልቅና ብዙ አጎዛዎችን ቤቱ ውስጥ ያነጠፈና ግድግዳው ለይ ያንጠለጠለ አባወራ በማህበረሰቡ ዘንድ ሀብታም ተደርጎ ይወሰዳል።በመሆኑም ማህበረሰቡ በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚሰበሰብበት ጊዜ ትልልቅ አጎዛዎችን ቤቱ ውስጥ የአንጠለጠለውን ሰው ስም በመጥራት " እከሌ እኮ ቀላል ሰው እንዳይመስልህ ቤቱ ውስጥ ያለው የሙክት እና የሽሽር አጎዛ ተቆጥሮ አያልቅም" በማለት ቤቱ ውስጥ የሚነጠፉት አጎዛዎች በውድ ዋጋ ከሚገዙ እንስሳቶች የሚገኙ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ሰውየውም በአካባቢው ማህረሰብ የሚሰጠው ምስጋና እና ውዳሴ እንዳይቀርበት በማሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚያርዳቸውን በጎችና ፍየሎች ቆዳ ወደ ገበያ አውጥቶ ከመሸጥ ይልቅ እራሱ ቃቅቶ እና አድርቆ ቤቱ ውስጥ ለምንጣፍነትና ለግድግዳ ጌጥ በማድረግ ይጠቀምባቸዋል፡

የአጎዛን የቤት ውስጥ አገልግሎት ስንመለከት ለዘወትር ምንጣፍ በመሆን የሚያገለግሉት ትንንሽ መጠን ያላቸው አጎዛዎች ናቸው። ትልልቆች እና ደስ የሚል ቀለም ያላቸው (በአካባቢው ደስ ይላል የሚባለው የአጎዛ ቀለም ሙሉ ነጭ ሙሉ ቀይ እንዲሁም ኧርንጉርጉር ነው)። ትልልቆቹ እና ማራኪ ቀለም ያላቸው

ደግሞ ለግድግዳ ጌጥ በመሆን የሰውየውን ክብር የሚገልፁ ናቸው። አጎዛዎቹ የተከበረ ሰው በእንግድነት በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ ከግርግዳ ወርደው ምንጣፍ በመሆን ያገለግላሉ። የቤቱ ባለቤት የተሻለ የሚለውን አጎዛ በማንጠፍ ለእንግዳው ያለውን ክብር እና ፍቅር ያሳያል። እንግዳውም የተደረገለትን አቀባበል መሰረት አድርጎ የሰውየውን ስም እየጠራ የተቀመጠበትን የአጎዛ መጠንና ቀለም እየጠቀሰ በተለያዩ አጋጣሚዎች ያመሰግነዋል።

በዚህ አካባቢ ማህበራዊ ደረጃንና ክብርን በመግለፅ የሚታወቀው ሌላው የቆዳ ቁስ ላምነት ነው። ይህ ቁስ ለግድግዳ ጌጥነት እና ለምንጣፍነት የሚያገለግል ነው። ነገር ግን ላምነት ከዚህ ያለፈ ባህላዊ አገልግሎት ያለው መሆኑን ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል። በዚያ አካባቢ አንድ ሰው ከሁለት በላይ ላምነት ለግድግዳ ጌጥነት ወይንም ለምንጣፍነት ከተጠቀመ ሰውየው የተሻለ ሀብት ያለው መሆኑ ይታወቃል። ምክንያቱም ላምነት ከዣንዲና ከሌሎች በባህላዊ መንገድ ከሚበጁ የምንጣፍ ዘሮች ዋጋው ከፍ ያለ በመሆኑ ነው ።ይህን ውድ ቁስ ገዝቶ የሚጠቀም ሰው አለው የሚባል ሰው መሆኑን በመስክ ቆይታዬ ተዘዋውሬ ከተመለከትኳቸው እና በቃለመጠይቅ ካገኘኋቸው መረጃዎች ለማወቅ ችያለሁ ። "ትልልቅ ላምነት እና ዣንዲ ፣ብዙ አጎዛ ያለው ሀብት ያለው እና የደህና ሰው ዘር የሆነ ነው የሌለውማ ለመተኛም ቁራጭ አንኩቲ ያነጥፋል እንጅ ላምነት ከሽት አምጥቶ በ80 ብር ገዝቶ ያነጥፋል" (ቃለ መጠይቅ፣ የኔሁን ዘገየ፣ ሚያዚያ16፣ 2003 ዓ.ም)

በአጠቃላይ በአካባቢው በባህላዊ መንገድ የሚበጁት የቆዳ ቁሶች ከማህበራዊ አገልግሎታቸው በተጨማሪ ባህላዊ ግልጋሎት መስጠታቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ክብርና ቦታ እንዲኖራቸው አስችለዋቸዋል። በዚህም መሰረት እቃዎቹ የተለየ እሴት ባለቤት መሆናቸው ሊተኳቸው የሚችሉ የፋብሪካ ቁሶች ቢመረቱም መበጀታቸውና በ አገልግሎት የመስጠታቸው ሁኔታ ፊዕሞ ሳይቀር እስካሁን ድረስ እንዲዘልቁ አስችሎአል። ለዚህም ነው በአካባቢው ከሚበጁትና የተለያዩ የቤት ውስጥ አገልግሎቶች ከሚሰጡት ቁሶች ውስጥ የእነዚህ አራት ቁሶች ተፈላጊነት ደረጃ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሳይቀንስ ሊዘልቅ የቻለው።

4.1.2 የቡሬ እና የወንበርማ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች መስሪያ ጥሬ ዕቃዎችና መሳሪያዎች

በመስክ ቆይታዬ ወቅት በሁለቱ ወረዳዎች የሚኖሩ የቆዳ ባለሙያዎች ቁሶችን ለመስራት የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎችና ዕቃዎችን ተዘዋውሬ ተመልክቻለሁ፡፡ ለቆዳ ቁሶች መስሪያ የሚሆነው ቆዳ ከተለያዩ እንስሳት የሚገኝ ሲሆን መስሪያ መሳሪያዎችም በአካባቢው በቀላሉ ከሚገኙ ቁሶች የሚዘጋጁ መሆናቸውን ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኙት ባለሙያዎች የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች እና ጥሬ ዕቃዎች ተመሳሳይ መሆናቸውንም ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

4.1.2.1 የቆዳ ቁሶች መስሪያ ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች

በቡሬ እና በወንበርማ ወረዳ የሚገኙ የቆዳ ባለሙያዎች ከሠጡት የቃል መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የቤት እንስሳትን ቆዳ ለተለያዩ ቁሶች መስሪያ በማድረግ በጥሬ ዕቃነት ይጠቀማሉ፡፡ በመሆኑም ባለሙያዎች ከቤት እንሰሳት የበሬ፣ የላም፣ የበግ፣ የፍየል ቆዳን የሚጠቀሙ ሲሆን አልፎ አልፎ ማለትም አዳኞች ገድለው ካመጡላቸው የሚዳቋ ቆዳንም ለመስሪያነት ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት እንስሳት በአካባቢው በሠፊው ሥራ ላይ የሚውለው ከበሬ እና ከላም የሚገኘው ቆዳ እንደሆነ ባለሙያዎቹ ይገልፃሉ፡፡

የቆዳ ባለሙያዎች ለመስሪያነት የሚጠቀሙባቸውን ቆዳዎች የሚያገኙት በሁለት አይነት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው መንገድ የደረቁ ቆዳዎችን ከገበያ በመግዛት ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች /ለድግስ፣ ለማህበር በሬ ወይም ላም ሲታረዱ ወይም በሬዎቻቸው ታመው ለመሞት ሲቃረቡ/ አርደው ቆዳዎቻቸውን ለተለያዩ ቁሶች መስሪያ ያውሏቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠቃሚው ማህበረሰብ አንድ የቆዳ ቁስ ማሠራት ሲፈልግ ቆዳ ከገበያ ገዝቶ ወይም አርዶ ባለሙያዎች ቤት ድረስ በመውሰድ እንዲሰራለት ያደርጋል፡፡ ባለሙያዎች ቁሶችን ለመስራት የሚያስፈልጋቸውን ቆዳ የሚያገኙባቸውን ገበያዎች ስንመለከት፡- ወንበርማ ወረዳ የሚገኙ የቆዳ ባለሙያዎች ሽንዲ ከተባለች የወረዳው ዋና ከተማ በመሄድ ሲገዙ፣ የቡሬ ወረዳ የቆዳ ባለሙያዎች ደግሞ ከቡሬ ከተማ

ገበያ ይገዛሉ፡፡ ማህበረሰቡ ለባለሙያዎች ለመሸጥ ገበያ የሚያወጣው ቆዳ ደረቅ በመሆኑ ባለሙያዎችም በትከሻቸው በመሸከም ወደ ቤታቸው ይወስዳሉ፡፡

አንዳንዴ ባለሙያዎች ገበያ ሄደው እንደልባቸው ቆዳ የማያገኙባቸው ወቅቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከነዚህም ወቅቶች መሀከል የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች የጾም ወቅት ዋነኛው ነው፡፡ ምክንያቱም በሁለቱ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖረው ማህበረሰብ አብዛኛው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በጾም ወቅት ብዙ ልኳንዳ ቤቶች ስለሚዘጉ እና በእርድ (በስጋ) የሚታጀቡ ማህበራዊ አጋጣሚዎችም በዚህ ወቅት ስለማይከናወኑ ለተለያዩ ቁሶች መስሪያ የሚሆነው ቆዳ ገበያ ላይ እንደልብ አይገኝም፡፡ በዚህም የተነሳ ባለሙያዎች ስራቸውን ለማቆም እንደሚገደዱ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በበጋ ወራት በተለይም ከገና እና ከፋሲካ በዓል በኋላ የተትረፈረፈ ቆዳ ገበያ ላይ ስለሚገኝ የሚፈልጉትን ያህል እየገዙ የተለያዩ ቁሶችን ይሠራሉ፡፡

ጥናቱ በአተኮረባቸው አካባቢዎች ለባህላዊ የቆዳ ቁሶች መስሪያ በመሆን የሚያገለግሉት ቁሶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተመርተው የተገኙ ሳይሆን በአካባቢው ከሚገኙ ተፈጥሯዊ ወይም ሠው ሠራሽ ነገሮች በቀላሉ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ቁሶቹ ለመፋቅና ለመቆራረጥ፣ ለመወጠርና ለመቃቃት፣ ለማለስለስና ፀጉር ለማስለቀቅ እና ለማስጌጥ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

4.1.2.2 ለመፋቅና ለመቆራረጥ የሚያገለግሉ ቁሶች

በዚህ ስር የሚካተቱት ቁሶች የተለያዩ ቁሶችን ለመስራት የሚዘጋጀውን ቆዳ በሚፈለገው መጠን ለመቆራረጥና ለመፋቅ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነሱም ካራ/ቢላዋ፣ መጥረቢያ/ምሳር፣ እና ሞረድ ናቸው፡፡

ካራ/ቢላዋ ይህ ቁስ የቆዳ ቁሶች መስሪያነት በዋናነነት ከሚያገለግሉ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የሚሰራውም በአካባቢው በባህላዊ መንገድ ብረት በማቅለጥና በመቀጥቀጥ ስለታማ ነገሮችን በሚያበጁ ባለሙያዎች ነው፡፡ በመስክ ቆይታዬ ለማየት እንደቻልኩት ካራ/ቢላዋን የቆዳ ባለሙያዎች ለስራ ያዘጋጁት ቆዳ እርጥብ ከሆነ ከመዘፍዘፉ በፊት ደረቅ ከሆነ ደግሞ ከተዘፈዘፈ በኋላ ቆዳው ላይ የተጠበቁ አላስፈላጊ /ትርፍ/ ሥጋዎችን ለማንሳት ይገለገሉበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቆዳውን

ፀሐይ ላይ ወጥሮ ለማድረቅ ያመች ዘንድ ለመወጠሪያ እንጨቶች ማስገቢያ የሚሆኑ ጀሮዎች/ቀዳዳዎች/ ለመብሳት ይጠቅማል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ትንንሽ የቆዳ ቁሶችን ለመስራት የተዘጋጀን ቆዳ ለመቆራረጥም ያገለግላል፡፡

መጥረቢያ/ምሳር ይህ በመስክ ምልከታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት ባለሙያዎቹ ውሃ ውስጥ የተዘፈዘፈውን ቆዳ አውጥተው ተገቢውን የውፍረት መጠን እንዲይዝ ለማድረግ ሲባል በቆዳው ውስጠኛው ክፍል የሚገኙትን ትርፍ ሥጋዎች ለማስወገድ የሚጠቀሙበት ቁስ ነው፡፡ ቁሱንም መጥረቢያ ወይም ምሳር በማለት ይጠሩታል፡፡ ቁሱ በአካባቢው የሚሠጠው መደበኛ አገልግሎት እንጨት መፍለጥ ነው፡፡ ሥያሜውን በተመለከተ ሌላው ማህበረሰብ ተለቅ ያለውን ምሳር በማለት የሚጠራው ሲሆን አነስ ያለውን እና ለቀጫጭን እንጨቶች መፍለጫነት የሚያገለግለውን ደግሞ መጥረቢያ በማለት ይጠራዋል፡፡ እኔም በመስክ ምልከታዬ የቆዳ ባለሙያዎች ሲገለገሉበት ያየሁት ማህበረሰቡ መጥረቢያ በማለት የሚጠራውን ቁስ ነው፡፡



(ፎቶግራፍ 11) ቆዳ በመጥረቢያ ሲፋቅ

ሞረድ፣ ሌላኛው እና ሶስተኛው ለቆዳ ባለሙያዎች ሥራ አጋዥ የሆነው መሳሪያ ሞረድ ነው፡፡ ሞረድ እንደቢላዋና መጥረቢያ በቀጥታ ከቆዳው ጋር ግንኙነት ያለው ሥራ አይሠራም፡፡ ይልቁንም እነዚህ መሳሪያዎች ተግባራቸውን በፍጥነትና

በተገቢው መንገድ እንዲያከናውኑ ማድረጊያ ነው፡፡ ሞረድ ለትርፍ ሥጋ ማስወገጃና ለመቆራረጫ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች የስለትነታቸው መጠን ሲቀንስ የመቁረጥ ብቃታቸውን ለመመለሰ የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ ባለሙያዎችም ካራውና መጥረቢያው/ምሳሩ ሲዶሎዱሙባቸው በሞረድ እየሳሉ ሥራቸው ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

4.1.2.3 ለመወጠር/ለመቃቃት/ የሚያገለግሉ ቁሶች

ችካል/ ካስማ፣ ችካል ወይም ካስማ ቆዳውን ለመወጠረ የሚያግዙና ከእንጨት የተሰሩ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የእንጨቶቹ ቅርጽም ከላይ ወፍራም ሲሆን ከጫፍ መሬት ለመብሳት የሚያስችል ሹል ክፍል አላቸው፡፡ አገልግሎታቸውም በሚወጠረው /በሚቃቃው/ ቆዳ ዙሪያ በመሰካት እና ቆዳውን ከመሬት ጋር አጣብቀው በመያዝ ቆዳው ሙሉ በሙሉ ፀሐይ እንዲያገኘው ማስቻል ነው፡፡ ባለሙያዎቹ እንደገለጹልኝ እና እኔም በመስክ ምልከታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት የበሬ ወይም የላምን ቆዳ ለመቃቃት/ለመወጠር/ 40 ችካሎች ያስፈልጋሉ፡፡

ወስፌ፣ ይህ ቁስ ተነክሮ/ተዘፍዝፎ/ ተፍቆ ለስልሶና ተቆራርጦ የተዘጋጀን ቆዳ እንደሚሠራው የቁስ አይነት አገጣጥሞ ለመስፋትና ተገቢውን ቅርጽ እንዲይዝ ለማድረግ የሚያግዝ ነው፡፡ ወስፌ የተቆረጡ ቆዳዎችን አገጣጥሞ ከመስፋት በተጨማሪ የተለያዩ የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ለምሳሌ ሥፌቶችን፣ ቅሎችን በቆዳ ለመሸፈን/ለመለጎም/ እና ለማስዋብ ያገለግላል፡፡ ለዚህ አገልግሎት የሚውሉት ወስፌዎች የተለያየ መጠን ያላቸው መሆኑን ተመልክቻለሁ፡፡ በመስክ ተገኝቼ ያየሁት ወስፌ እርዝመት 1.3 ሳ.ሜ ሲሆን ውፍረቱ ደግሞ 2 ሳ.ሜ ነው፡



(ፎቶግራፍ 12) ስፌት በወስፌ ሲለጐም

4.1.2.4 ለማለስለስና ለፀጉር ማስለቀቂያ የሚያገለግሉ ጥሬ እቃዎች

ለዚህ ተግባር የሚውሉት ጥሬ ዕቃዎች፣ ጫቅማ/ጉሎ፣ ድምቡሻቡሽ፣ የከብት ሽንት ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም የሚከተለው ነው፡፡

ጫቅማ/ጉሎ፣ ጫቅማ/ጉሎ ማንኛውም ሠው ዘርቶት ሊበቅል የሚችል ትልቅ ግንድ እና ቅርንጫፍ ካለው ዛፍ የሚገኝ ድፍን ቀይ እና ኧርንጉርጉር ቀለም ያለው ፍሬ ነው፡፡ የፍሬው ሽፋን ደረቅ ሲሆን ውስጡ ነጭ ቀለም አለው፤ ሲወቀጥ/ሲጨቀጨቅ/ የመቅለጥና የመቡካት ባህሪ ያለው ጠፍጣፋ ፍሬ ነው፡፡ ጫቅማ በተፈጥሮው ቅባት ያለው በመሆኑ የቆዳ ቁሶችን ከመቃቃት ጀምሮ አልቆላቸው አገልግሎት መስጠት እስኪደርሱ ድረስ እንዲለሰልሱ ያደረጋል፡፡ ለማለስለሻነት የሚውለው ጫቅማ በመፍጫ ተወቅጦ ከደቀቀ በኋላ በውሃ ቀጠን ተደርጎ ተቦክቶና ተፍቆ በተወጠረ ቆዳ ላይ በመቀባት ለማለስለሻነት ይውላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሶች ረዥም ጊዜ በማገልገላቸው ምክንያት የሚመጣባቸውን መድረቅና ውበት ማጣትን ሁኔታን በማስወገድ እንዲለሰልሱና ውበታቸው እንዲጨምር ያስችላል፡፡

ድምቡሻቡሽ፣ ድምቡሻቡሽ ልክ እንደ ጫቅማ ሁሉ ተፈጥሯዊ ተክል ሲሆን፤ ኧንጉርጉር ቀለምና ክብ ቅርጽ ያለው ፍሬ ነው፡፡ ይህ ፍሬ እንደሌሎቹ/ለምግብነት እንደሚውሉት ተክሎች/ ተዘርቶ ሳይሆን እንዲሁ ወንዝ አካባቢ እና ዱር ውስጥ በቅሎ የሚገኝ ተክል ነው፡፡ የቆዳ ባለሙያዎችም በአካባቢያቸው ከሚገኝ ወንዝ ዳር ወይም ዱር ውስጥ በመሄድ ቆርጠው /ቀጥፈው/ በማምጣት ይጠቀሙበታል፡፡ ፍሬው በድንጋይ ተቀጥቅጦ ከከብት ሽንት ጋር በመቀላቀል ከላምነት ውጪ ለሚሠሩ የቆዳ ቁሶች መስሪያ የተዘጋጀውን ቆዳ ፀጉር ለማስለቀቅ ያስችላል፡፡ ይህ ፍሬ በተፈጥሮው ያሲድነት ባህሪ ስላለው ቆዳው ላይ ያለውን ፀጉር ለመምለጥ የሚያስችል መሆኑን አባ ወንዴ ገልፀዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ ግንቦት 27፣2003 ዓም)



(ፎቶግራፍ 13) የድምቡሻቡሽፍሬ



(ፎቶግራፍ 14) የተወቀጠ ድምቡሻቡሽ

የከብት ሽንት፣ የከብት ሽንት ከተወቀጠ ድንቡሻቡሽ በመቀላቀል ፀጉር ለማስለቀቅ ያገለግላል፡፡ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሂደት በተመለከተም ባለሙያዎቹ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፤ የከብት ሽንት ከድንቡሻቡሽ ጋር ቀላቅሎ ፀጉሩ እንዲለቅ በታሰበው ቆዳ ላይ ይቀባል፡፡ ከዛም ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ጉድጓድ ውስጥ በማስቀመጥ ወይም በመደበን ፀጉሩ እንዲለቅ ይደረጋል፡፡ ሁሉም በመረጃ አቀባይነት የተካተቱት የቆዳ ባለሙያዎች በሙሉ የከብት ሽንትንና ድምቡሽቡን ቀላቅሎ የቆዳ ፀጉርን የማስለቀቅ ብልሃት ከቀደምት አባቶቻቸው የወረሱት መሆኑን

ገልፀውልኛል፡፡ (አባ ወንዴ፣አቶ አስማማው፣አቶ ሽታ ደነቀው እና ሌሎችም ፣ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት5፣ 2003 ዓም)

4.1.2.5 የቆዳ ቁሶችን ለማስፔጥ የሚውል ጥሬ ነገር

የቆዳ ቁሶችን ለማስፔጥ የሚውለው ጥሬ ነገር ቀለም ነው፡፡ የቆዳ ባለሙያዎች የቆዳ ቀለምን በሁለት አይነት መንገድ ያገኙታል፡፡ አንድም በቤት ውስጥ በማዘጋጀት ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከሱቅ በመግዛት ነው፡፡ በአካባቢው ተዘውትረው ለቆዳ ማስዋቢያ የሚውሉት ደማቅ ቀይ እና ጥቁር ቡኒ የቀለም አይነቶች ናቸው፡፡ ደማቅ ቀዩ ከሱቅ የሚገዛ ሲሆን ጠቆር ያለው ቡኒ ቀለም ደግሞ የቆዳ ባለሙያ ሚስቶች ጫቅማን/ጉሎን/ አሳርረው በመቁላት የሚያዘጋጁት ነው፡፡ የእነዚህ ሁለት ቀለሞች አገልግሎት አንድም ለአንቀልባ/ለልጅ ማዘያ/ ሌላው ደግሞ ተቆራርጠ ለመለጐሚያነት የሚውለውን ቆዳ በመቀባት ውበት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡

እስካሁን የባህላዊ የቆዳ መስሪያዎችንና ጥሬ እቃዎችን አይነትና አገልግሎት ተመልክተናል፡፡ ከቀረበው ገለፃ መረዳት የሚቻለው ከቀዩ የቆዳ ቀለም በስተቀር መስሪያ ቁሶቹም ሆኑ ጥሬ እቃዎቹ ቤት ውስጥ በባለሙያዎቹ የሚዘጋጁ መሆናቸውን ነው፡፡

4.1.3 ባህላዊ የቆዳ ውጤቶች የአሠራር ሂደትና ዘዴ

በቡሬ እና በወንበርማ ወረዳ የሚሠሩ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች የመጨረሻ ቅርፃቸውንና ጥንካሬያቸውን ለመያዝ በቅድሚያ የሚያልፉባቸው የተለያዩ ሂደቶች አሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ባለሙያዎች የተለያዩ የቆዳ ቁሶችን ለመስራት የሚከተሏቸውን ሙያዊ ብቃት የሚጠይቁ ያሰራር ሂደቶችን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ በመስክ ቆይታዬ ባደረኩት ምልከታና ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ባህላዊ የቆዳ ሥራ በስምንት ተከታታይ ሂደቶች ያልፋል፡፡ እነሱም ለቁሶች መስሪያ የሚሆነውን ቆዳ ማዘጋጀት፣ መዘፍዘፍ ወይም መንከር፣ መፋቅ እና መቃቃት፣ መደበን፣ ማሸት/ማልፋት፣ ቀለም መቀባት፣ መተልተል መቆራረረጥ፣ መስፋት እንዲሁም መፍተል እና ማጠር የሚባሉት ናቸው፡፡

እነዚህ ሂደቶች በመሉ በሁሉም የቆዳ ቁሶች ላይ አይተገበሩም። ምክንያቱም ያንዳንዶቹን ቁሶች የማበጀት ሂደት ስንመለከት እስከ ማሸት/ማልፋት/ ባለው ሂደት ብቻ የሚጠናቀቁ ናቸው። ይህን በባህላዊ የቆዳ ቁሶች ላይ የሚታየውን የአሠራር ሂደት ልዩነት እስከአሁን ድረስ በዘላቂነት የሚሠሩትን ቁሶች በምሳሌነት በመውሰድ እንመለከታለን። ከዚህ ጋር በማያያዝና ያሠራር ሂደት ተብለው የተጠቀሱት ጉዳዮች ምን ምን ተግባሮች ይከናወኑባቸዋል? እንዴትስ ተግባራዊ ይሆናሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በዝርዝር እናያለን።

4.1.3.1 ለቁሶች መስሪያ የሚያስፈልገውን ቆዳ ማዘጋጀት

በባህላዊ የቆዳ ቁሶች ሥራ የመጀመሪያው ተግባር ለሥራ የሚያስፈልገውን ቆዳ ማዘጋጀት ነው። በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኙት ባህላዊ የቆዳ ሥራ ባለሙያዎች እንደገለፁት ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ቁሶቹን ለመስራት የሚያስፈልገውን ቆዳ የራሳቸውን ከብቶች በማረድ ወይም ከገበያ በመግዛት ያዘጋጃሉ።

ቆዳውን እነሱ ካዘጋጁ ወይም ተጠቃሚው ማህበረሰብ ቤታቸው ድረስ ካመጣላቸው በቀላሉ ቀጣዩን ሥራ ይጀምራሉ። ከዚያ ወጪ ግን ገበያ በመሄድ እንደሚያዘጋጁት የቁስ አይነት የቆዳውን የድርቀት መጠን እና ቀለም በመምረጥ በአማካይ ከ30-35 ብር በመግዛት ተሸክመው ወደቤታቸው ያመጡታል። ለመሰራት የተፈለገው ላምነት ተብሎ የሚጠራው ቁስ ከሆነ ቫርንጉርጉር ቀለም ያለው ቆዳ ሲመርጡ በጣም የደረቀ መሆን እንደሌለበት አቶ ደነቀው የተባሉት የወንበርማ ወረዳ የቆዳ ባለሙያ ይገልፃሉ። አቶ ደነቀው ከ20 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያላቸው እና በአካባቢው የሚያገለግሉ የቆዳ ቁሶችን ጥራት ባለው መንገድ በመስራት የሚታወቁ ናቸው። ለላምነት የሚሆን ቆዳ ቀለሙ የሚያምር እና ሁለት አይነት ቀለማትን የያዘ መሆን እንደሚገባው፤ በፀሐይም በጣም መድረቅ እንደሌለበት ይገልፃሉ። ምክንያቱም ቆዳው በጣም ከደረቀ ቅባት እየተደረገ በእግር የሚታሸበት ሂደት ላይ ሲደርስ ፀጉሩ በቀላሉ ስለሚረግፍ ውበቱ ስለሚቀንስ ለዚህ ቁስ መስሪያ የሚውል ቆዳ በጣም መድረቅ የለበትም። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 25፣ 2003 ዓ.ም)

ከላምነት ውጪ ለሆኑ ቁሶች መስሪያ የሚሆነው ቆዳ ግን ከቀለም ምርጫም ሆነ ከርጥበትና ድርቀት አኳያ ብዙም ጥንቃቄ የማያሻው መሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

ምክንያቱም ሌሎች ቁሶች የሚሠሩት በቅድሚያ የቆዳውን ፀጉር በማስለቀቀ ስለሆነ ነው፡፡ ከላይ በተገለፀው መንገድ ለሥራ የሚያስፈልገው ቆዳ ከተዘጋጀ በኋላ ቀጣዩ ስራ የደረቀውን ቆዳ መዘፍዘፍ ወይም መንከር ነው፡፡



(ፎቶግራፍ 15) በቆዳ ባለሙያዎች ግቢ ውስጥ የተጠራቀሙ ደረቅ ቆዳዎች

4.1.3.2 መዘፍዘፍ ወይም መንከር

ባለሙያዎች ያዘጋጁትን የደረቀ ቆዳ የተለያዩ ቁሶችን ለመስራት ያመች ዘንድ ወንዝ ውስጥ ይዘፈዝፉታል፡፡ እንደ ባለሙያዎቹ ገለፃ ቆዳ የሚዘፈዘፍበት ወንዝ ፏፏቴ የሌለው መሆን አለበት ፡፡ ወንዙ ፏፏቴ ያለው ከሆነ የተዘፈዘፈውን ቆዳ ሊወስደው ስለሚችል በተቻለ መጠን ፏፏቴ የሌለውና አነስተኛ የውሃ እንቅስቃሴ ያለው ወንዝ ውስጥ መዘፍዘፍ እንደሚያስፈልግ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡

ቆዳው ውሃ ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ቆዳው ድርቀት ይወሰናል፡፡ ይህን በተመለከተ በቡሬ ወረዳ ባጉና ሃና ቀበሌ ማህበር ውስጥ የሚኖሩት የ67 ዓመት አዛውንት የሆኑት አባ ወንዴ "የደረቀ ከሆነ እስከ አምስት ቀን ድረስ ወንዝ ውስጥ ሲቆይ፤ እርጥብ ከሆነ ደግሞ ከአንድ እስከ ሁለት ቀን ድረስ ብቻ ይነከራል" ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 8፣ 2003 ዓ.ም.) ብለዋል ፡፡ አባ ወንዴ እና ሌሎችም ባለሙያዎች እንደሚገልፁት በቆዳ ሥራ ሂደት ውስጥ የመዘፍዘፍ ተግባር ሁለት

ጊዜ ይካሄዳል። ይኸውም በመጀመሪያ ከላይ እንደተገለፀው ከገበያ የተገዛው ወይም ቤት ውስጥ የተዘጋጀውና የደረቀው ቆዳ በቀጥታ ወንዝ ውስጥ ይዘፈዘፋል፣ ከዚያም እንደ ቆዳው የድርቀት ሁኔታ ታይቶ ከወንዝ ከወጣ በኋላ ተቃቅቶ/ተወጥሮ/ አንድ ቀን ሙሉ ፀሐይ ላይ እንዲውል ከተደረገ በኋላ ለአንድ ቀን ወይም ለሁለት ቀን ያህል እንደገና ወንዝ ውስጥ ይገባና ይዘፈዘፋል። ቆዳው የሚዘፈዘፍበት ዋነኛ ምክንያት ቆዳው ላይ የሚገኘውን አላስፈላጊ ስጋ በቀላሉና ቆዳው ሳይቀደድ ለማስወገድ ነው።



(ፎቶግራፍ 16) አቶ በላይ ደነቀው ቆዳ በመዘፍዘፍ ላይ

4.1.3.3 *መፋቅና መቃቃት*

የተለዩ ቁሶችን ለመስራት የተመረጠው ቆዳ ወንዝ ውስጥ ከተዘፈዘፈና ተገቢውን የእርጥበት መጠን ካገኘ በኋላ ቀጣዩ ሥራ መፋቅ እና በችካል ወይም በካስማ መቃቃት ነው። "እንደቆዳው አይነት ወንዝ ውስጥ ተነክሮ ተቆየ በኋላ በምሳር እየተፋቀ ስጋው ይከላል ተዚያም በካስማ ፍራ እየተበደጀ ይቃቃል። ተቃቅቶ ለመድረቅ አንድ ቀን ይበቃዋል። ተደረቀ በኋላ ደግሞ ውሃ እየተርከፈከፈ ይፋቃል። (አባ ወንዴ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 22፣ 2003)

ከአባ ወንዴ እና ከሌሎቹም ባለሙያዎች የተገኘው የቃል መረጃ እንደሚያሳየው የመፋቅ ተግባር ሁለት ጊዜ ይከናወናል። ይኸውም ለመጀመሪያ ጊዜ ወንዝ ውስጥ የቆየው ይወጣል፣ በመጥረቢያ እየተፋቀ ቆዳው ላይ ያለው ሥጋ እንዲወገድ

ይደረጋል፤ ከዚያም ዙሪያውን በቢላዋ ተበስቶ በችካል/ካስማ ይወጠራል/ ይቃቃል። የተቃቃው ቆዳ አንድ ቀን ሙሉ ፀሐይ ላይ ከዋለና ከደረቀ በኋላ እንደገና ውሃ እየተርከፈከፈበት ይፋቃል።

እነዚህ መፋቅና መቃቃት የሚባሉት ተግባራት ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ሠው ሊሰራቸው የሚችሉ ሳይሆን ሙያዊ ብቃት እና ጥንቃቄን የሚጠይቁ ናቸው። ይኸውም መፋቅ የሚባለውን ተግባር ሥናይ ከቆዳው ጋር የተጣበቀውን ሥጋ በውሃ በማራስ ከቆዳው ማላቀቅ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ የመጥረቢያውን አጣጣል ሚዛናዊ ማድረግን፣ ቆዳው ላይ የሚያርፈውን ኃይል ከመጥረቢያው የስልነት ደረጃ ጋር አመጣጥኖ መስራትን የሚጠይቅ ከባድ ሥራ ነው። ምክንያቱም አንድ ባለሙያ በሚፍቅበት ጊዜ ለመፋቂያነት የያዘው መጥረቢያ በጣም ሥል ከሆነና ባለሙያው ደግሞ ይሄን ሳያውቅ መጥረቢያውን በከፍተኛ ኃይል ቆዳው ላይ የሚያሳርፍበት ከሆነ ይቀደዳል። ስለዚህ አንድ ባለሙያ በሚፍቅበት ጊዜ ከላይ የተገለፁትን ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ሊፍቅ እንደሚገባ ልብ ይሏል። ጥሩ የመፋቅ ችሎታ የሚገኘው በረዥም ጊዜ ልምምድና አንክሮ በተሞላበት ምልከታ መሆኑን ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ።

መቃቃት ወይም መወጠር የሚባለው ከንዋኔም ከመፋቅ ያላነሰ ጥንቃቄ እና ብልሃት እንደሚገባው ባለሙያዎቹ ይናገራሉ። መቃቃት ወንዝ ውስጥ ተዘፍዝፎ የቆየን ቆዳ ከተፋቀ በኋላ ተገቢውን ፀሐይ ያገኝ ዘንድ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሂደት ነው። ይህን ተግባር በተገቢው መንገድ ለማከናወን ሸል ሆነው ከእንጨት የተዘጋጁ ችካሎችን ማዘጋጀት፣ ከዚያም የቆዳውን ጠርዝ በጥንቃቄ በቢላዋ በመብሳት ችካሎቹ የሚገቡበትን ቀዳዳ ማዘጋጀት ይጠይቃል። ይህ ከተደረገ በኋላ ደግሞ ቆዳውን ሚዛናዊ አድርጐ እየሳቡ በመወጠር ሁሉም የቆዳ ክፍል ሙሉ በሙሉ ፀሐይ እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል።



(ፎቶግራፍ 17) የተቃቁ/የተወጠሩ ቆዳዎች

4.1.3.4 *መደበን*

ይህ የቆዳ ሥራ ሂደት ከመዘፍዘፍ፣ ከመፋቅና ከመቃቃት ቀጥሎ የሚከናወን ነው፡፡ መደበን የሚሠራው ቁስ ፀጉር የማያስፈልገው ከሆነ ለሥራ የተዘጋጀውን ቆዳ ፀጉር አልባ የማድረግ ሂደት ነው፡፡ ሊሰራ የታሰበው የቁስ ዓይነት የፀጉሩን መኖር የሚፈልግ ከሆነ መደበን አያስፈልግም፡፡ የተፋቀውና የተቃቃው ቆዳ በቀጥታ ወደ ቀጣዩ ሂደት ይሸጋገራል፡፡

የሚበጀው ቁስ ፀጉር እንዲኖረው የማይፈለግ ከሆነ ቆዳው የተቦካ ድምቡሻቡሽ ይቀባና በማዳበሪያ ተከቶ ጉድጓድ ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ያህል ይቀመጣል /ይደበናል/፡፡ ይህን ሂደት በተመለከተ አቶ ሽታ ደነቀው የተባለው የወንበርማ ወረዳ ነዋሪ የቆዳ ባለሙያ "የተፋቀው እና የተቃቃው ቆዳ ሁለት ቀን ድንቡሻቡሽና የከብት ሽንት ተቀብቶ በማዳበሪያ ውስጥ ተደርጎ ጉድጓድ ውስጥ ሁለት ቀን ይደበናል፡፡ ከዚያ ጠጉሩ ከለቀቀ በኋላ ጫቅማ ተቀብቶ ይታሻል፡፡" /ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 23፣ 2003/ በማለት ገልፀውልኛል፡፡ ዋንጫ ሠፈር በሚባለው የቡሬ ወረዳ ቀበሌ 03 ነዋሪ የሆነው ወጣት የቆዳ ባለሙያ አስማማው ተረፈ ደግሞ ሂደቱን እንዲህ በማለት ገልፆታል፣ "አንድ ቆዳ ከተቃቃና ከተፋቀ በኋላ ደምቡሻቡሽ ተጨቅጭቆ/ተወቅጦ/ ከከብት ሽንት ጋር ይቀላቀልና በቆዳው

ላይ ተቀብቶ ጉድጓድ ውስጥ ይደበናል፡፡ ተዚያም ጠጉሩ ለመላቀቅ አንድ ሙሉ ቀን ብቻ ያስፈልገዋል፡፡" /ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 23፣ 2003/

በሁለቱ ወረዳዎች በባህላዊ መንገድ ከሚሠሩ የቆዳ ቁሶች ውስጥ ሳይደበን የሚሠራው ላምነት የሚባለው ቁስ ሲሆን ሌሎቹ ግን መደበን የሚባለውን የቆዳ ስራ ሂደት በማለፍ የሚበጁ ናቸው፡፡

4.1.3.5 ማሸት/ማልፋት/

ይህ ተከታታይ ሶስት ሂደቶችን አልፎ ጉድጓድ ውስጥ ለአንድ ቀን ወይም ለሁለት ቀን ያህል የተደበነው ቆዳ እንዲለሰልስ ማድረጊያ ክንዋኔ ነው፡፡ የማልፋት/የማሸት/ ሥራ የሚከናወነው በእግር ሲሆን ለማለስለሻነትም ጫቅማ የሚባለው ፍሬ ተወቅጦ ይጨመርበታል፡፡ አንድን ቆዳ ለማሸት የሚወስደው ጊዜ ሊሠራ በታሰበው የዕቃ አይነት ይወሰናል፡፡ ይኸውም ዝንዲ የተባለውን ቁስ ለመስራት በአማካኝ ከአንድ ሠዓት እስከ ስድስት ሰዓት የሚሆን ጊዜ ወስዶ ማሸትን ሲጠይቅ፣ ላምነትን ለማዘጋጀት ደግሞ ከአንድ እስከ ሁለት ሠዓት ብቻ መታሸት እንደሚኖርበት አቶ በላይ ደነቀው ይገልጻሉ፡፡ ቆዳ ለብዙ ሰአት ከለፋ ፀጉሩ የመልቀቁ መጠን ይጨምራል፡፡ ላምነትም ደግሞ ለግድግዳ ጌጥነት ስለሚያገለግልና ፀጉሩ እንዲለቅ ስለማይፈለግ ለአጭር ጊዜ ብቻ እንዲለፋ ይደረጋል፡፡ ከቁሶች ሁሉ ረዥም ጊዜ ወስዶ ማሸትን የሚጠይቀው ደግሞ መጫኛ ነው፡፡ መጫኛ በጋማ ከብቶች ላይ ያለን እቃ ለማሰር ስለሚጠቅም ጥንካሬ እንዲኖረው ሲባል ለረዥም ጊዜ የሚታሸ መሆኑን በቃለመጠይቅ እና በምልከታ ካገኘሁዋቸው መረጃዎች ለማወቅ ችያለሁ፡፡

ማሸት ወይም ማልፋት ለስራ የሚፈለገው ቆዳ እንዲለሰልስ እና ጥንካሬ እንዲኖረው ማድረጊያ ሲሆን ከቆዳ ስራ ሂደቶች ውስጥ ባድካሚነቱ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡ የሥራው አድካሚነት መጠንም እንደሚሠሩት ቁሶች አይነት የሚለያይ መሆኑን ባለሙያዎች ገልፀውልኛል፡፡

እንደባለሙያዎቹ ገለፃ ዝንዲ እና ላምነት የተባሉት ቁሶች ሲሰሩ የማልፋቱ ወይም የማሸቱ ተግባር ከተከናወነ በኋላ ገበያ ለመቅረብ የሚቀረው ሂደት ለተወሰነ ሠዓት/በግምት ለ30 ደቂቃ ያህል/ ፀሐይ ላይ መቆየት ብቻ መሆኑን ለማወቅ


ችያለሁ፡፡ ሌሎች ቁሶች ግን አገልግሎት መስጠት ለመጀመር ቀለም መቀባት፣ መተልተል እና መቆራረጥ፣ መስፋት እንዲሁም ማጠር የሚባሉ ሂደቶችን ማለፍ ይኖርባቸዋል፡

4.1.3.6 ቀለም መቀባት ፣መቆራረጥና መስፋት

በቆዳ ስራ ሂደት ውስጥ ቀለም የመቀባት ሂደት የሚከናወነው ቁሱ ከዝንዲና ከላምነት ውጪ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም አንድ ቆዳ እስከ መታሸት ድረስ የሚዘልቀውን ሂደት ካለፈ በኋላ ቀለም የሚቀባው የሚበጀው ቁስ አንቀልባ ወይም መጠጊያ ከሆነ ብቻ መሆኑን በምልከታዬ ካየሁትና በቃለመጠይቅ ካገኘኋቸው መረጃዎች ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ አንድ ባለሙያ አንቀልባ ወይም መጠጊያ ለመስራት ካሰበ በጫቅማ እየታሸ የለሰለሰውን ቆዳ ቀለም ይቀባና ለአንድ ሰዓት ያህል ወጥሮ ፀሐይ ላይ ማቆየት እንደሚገባው፤ አንቀልባ ለመስራት ቀለም ቀብተው የወጠሩትን ቆዳ ሲቆራርጡ ያገኘኋቸው አስማማው ተረፈ እንዲህ በማለት ገልፀውኛል፡፡

> *አንቀልባ የሚሠራ ተሆነ በጫቅማ በደንብ የታሸው ቆዳ ቀለም ይቀባል፡፡ ተዚያ ልክ እንዲዚህ (ቀለም ተቀብቶ የተወጠረውን ቆዳ እየጠቆመ) ፀሐይ ላይ ለአንድ ሠዓት ያህል ይወጠራል፡፡ ፀሐይ ሲበቃው ደግሞ ልክ እንደዚህ በካራ ይቆራረጣል፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 25፣ 2003/ (ቅንፉ ውስጥ ያለው ሀሳብ የኔ ነው)*

እኔም የወጠረውን እና አድርቆ በቢላዋ የቆራረጠውን ቀለም የተቀባ ቆዳ በማየት ከአንድ ቆዳ ምን ያህል አንቀልባ ሊሠራ እንደሚችል ጠየቅሁት፣ እሱም "እንደ ቆዳው መጠን ይለያያል፡፡ አንዳንዱ ሁለት አንዳንዱ ደሞ ሶስት ይሆናል፣ ይሄ አሁን ሁለት ሆንዋል (ለሁለት አንቀልባ እንዲሆን አድርጎ ያዘጋጀውን ቆዳ እየጠቆመ) " /ከላይኛው ጋር በተመሳሳይ ጊዜ/ በማለት ለአንቀልባ የሚሆን ቆዳ ቀለም ከተቀባ በኋላ የሚከናወኑ ሂደቶችን ገልያልኛል፡፡ (ቅንፉ የራሴ ነው)



(ፎቶግራፍ 18) ቀለም ተቀብቶ የተወጠረ ቆዳ



(ፎቶግራፍ 19) አስማማው ተረፈ ላንቀልባ የሚሆን ቆዳ ሲቆራርጥ

አንልባ ሲሰራ ቀለም ከመቀባት መተጨማሪ መቆራረጥን ይፈልጋል። ከአስማማው ፈጠነ ንግግር እና ከሌሎችም ባለሙያዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው አንቀልባ በሚበጅበት ጊዜ ቀለም የተቀባው እና ፀሐይ ላይ ተወጥሮ የቆየው ቆዳ እንዳለው ስፋትና ጥበት ለሁለት ወይም ለሶስት አንቀልባ እንዲሆን ተደርጐ ይቆራረጣል። ከዚያም በኋላ አላስፈላጊ የሆኑት የቆዳው ጠርዞች በቢላዋ እየተቆረጡ ይወገዳሉ። በመጨረሻም ለዛጐል ማስገቢያ የሚሆነው ክፍል በቀጫጭኑ ይተለተላል። ይህ ክፍል ከተሰራ በኋላ ደግሞ የሚታዘለውን ህፃን ጭንቅላት በሚሸፍነው የቀኝ ጠርዝ በኩል ማሰሪያ ይቀጠልበታል። ይህ ሁሉ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ባንቀልባው የውጨኛው አካል ላይ ዛጐሎች በተለያየ ቅርፅ እየተደረደሩ ይሰፋሉ።

በሁለቱም ወረዳዎች በሚገኙት ባለሙያዎች የአሠራር ሂደት መሠረት የቀለም መቀባትንና ቆራርጦ የመስፋትን ሂደት የሚያልፈው መጠጊያ ተብሎ የሚጠራው እና ለትራስነት የሚያገለግለው ቁስ ነው። ለመጠጊያ መስሪያ የሚውለው ቆዳ ቀለም መቀባቱ እና መቆራረጡ ከአንቀልባ ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን የሚለየው ገፅታ ሠፋ እንደሚል በምልክታ አረጋግጫለሁ።

ይህ ቁስ በአማካይ 40 ሳ.ሜ ስፋትና 65 ሳ.ሜ ቁመት ያለው በአራት ማዕዘን ቅርጽ የተዘጋጀ ቆዳ ነው። በውስጡም እንደይጨማደድና ሞላ ብሎ ጥሩ ትራስ እንዲሆን የዳጉሳ ወይም የጤፍ ጭድ /ገለባ/ ይደረግበታል። ከዚያም ዙሪያውን

በሲር፣ በጭፍር ወይም በቀጭኑ በተሠነጠቀ ቆዳ ይሠፋል። በዚህ ሁኔታ ያሰራር ሂደቱ ይጠናቀቃል።

4.1.3.7 መተልተል/መሸንሸን/ እና ማጠር

በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከአንድ ቆዳ መጫኛ እና ምራን የሚባሉትን ቁሶች ለማበጀት ከተፈለገ፣ ሌሎች ቁሶች ሲሠሩ ከሚደረገው በተለየ ሁኔታ ከመቃቃት ውጪ ያሉ ሂደቶች በሙሉ ሊተገበሩ ይገባል። የመጫኛንና የምራን የአሠራር ሂደት እንዲያስረዳኝ የጠየቅሁት በላይ ደነቀው እንዲህ በማለት ሂደቱን ገልያልኛል።

> *መጫኛ እና ምራን ሲሠራ ያው እንደ ሻጉዲ እና አንቀልባ ነው። ልዩነቱ የመጫኛና የምራን ቆዳ አይቃቃም። ከተቃቃ ደረቅ ሥለሚሆን ለመሸንሸንና ለማጠር አይመችም። ተደብኖ ጠጉሩ ከለቀቀ በኋላ መጫኛ የሚሆን ተሆነ በመጫኛ ልክ ተሸንሽኖ በባህር ዛፍ ላይ ይወጠርና ጫቅማ እየተቀባ ይታሻል። ተዚያ ለገቢያ ማቅረብ ነው። /ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 25፣ 2003/*

ከዚህም በተጨማሪ ለነዚህ ቁሶች የሚሆነው ቆዳ ሲዘጋጅ ፀጉሩን ለማስለቀቅ ጉርጓድ ውስጥ የሚቆይበት/የሚደበንበት ጊዜ ከሌሎች ቁሶች የበለጠ መሆኑን ባለሙያው ገልፀዋል። ለሻጉዲ የሚሆነው ቆዳ አንድ ቀን ብቻ የሚደበን ሲሆን ለመጫኛ እና ለምራን መስሪያ የሚሆነው ቆዳ ግን ከሶስት እስከ አራት ቀን ጉድጓድ ውስጥ ቆይቶ ፀጉሩ በደንብ መልቀቅ ይኖርበታል።

የምራንና የመጫኛ አሰራር ሂደት ብዙ ተመሳሳይ ገፅታዎች ቢኖሩትም ልዩነቶችም ያሉት መሆኑን ባለሙያዎች ይገልፃሉ። በወንበርማ ወረዳ ልዩ ስሙ ሻምብላ በር ተብሎ በሚጠራው ሠፈር ቆዳ በመስራት የሚተዳደረው አቶ ሽታ ደነቀው የምራንንና የመጫኛን የአሠራር ሂደት ተመሳስሎና ልዩነት "ምራንና መጫኛ ሥራው አንድ ነው። ምራን ከመጫኛ ተቆርጠ ነው ሚሠራ የሚለየው ምራን ስለሚጠር ነው። ምራን ስንሠራ ለሁለት በመተጋገዝ ነው። እና ርዝመትና ስፋቱ ታይቶ ለሁለት፣ አንዳችን ይዘን አንዳችን እንፈትለዋለን።" /ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 02፣ 2003/ በማለት ገልያታል።

ባጠቃላይ ምራንና መጫኛ ተብለው የሚጠሩት ቁሶች ከሌሎች ቁሶች በተለየ ሁኔታ በመተልተል፣ በመፍተል እና በማጠር ለአገልግሎት ዝግጁ የሚሆኑ ቁሶች ሲሆኑ

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው ባለሙያዎች ከሚሰሩት እቃዎች ውስጥ ለመዘጋጀት ረዥም ጊዜ በመውሰድ የሚታወቁ ናቸው። ይኸውም ከእነዚህ ውጪ ያሉ ቁሶች ገበያ ለመቅረብ በአማካኝ ከስድስት እስከ ስምንት ቀን የሚፈጁ ሲሆን እነዚህ ቁሶች ግን ቢያንስ ከ8-11 ቀን በመዘጋጀት ሂደት ላይ ይቆያሉ።

እስከ አሁን በቀረበው ማብራሪያ በሁለቱ ወረዳዎች የሚሠሩትን ቁሶች የአሠራር ሂደትና ዘዴ ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም በአካባቢው የሚሠሩት ቁሶች የአሠራር ሂደትና ዘዴ እንደ ቁሶቹ አይነትና የአገልግሎት ሁኔታ የሚለያይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኙት ባለሙያዎች የሚከተሏቸው ያሰራር ሂደቶች ተመሳስሎ እንዳላቸው ለማየት ተችሏል።

4.1.4 ባህላዊ የቆዳ ሥራ ሙያ ለመዳ

ከሁለቱ ወረዳዎች ተመርጠው በጥናቱ ከተካተቱት ሶስት ቀበሌዎችና ሁለት መንደሮች ውስጥ የሚገኙትን ባለሙያዎች የሙያ ለመዳ ተመሳሳይ ነው። በመረጃ አቀባይነት የተመረጡት ስምንቱም ባለሙያዎች ሙያውን የለመዱት የአባት ስራ ነው ብለው ስላመኑና ስለተቀበሉት መሆኑን ይገልፃሉ። ቤተሰቦቻቸው ሲሰሩ ደጋግሞ በመመልከት እና የቆዳ መስሪያ ቁሶችን በማቀራረብ ቀስ በቀስ ወደ ሙያው ገብተው እንደቀሩ ይገልፃሉ።

የ25 ዓመቱ አስማማው ተረፈ ሙያውን የለመደበትን ሁኔታ "ሙያውን መስራት የጀመርሁት ተአስር አመት በላይ ሆኖኛል። የእናት የአባት ሥራ ሰለሆነ እነሱ ስለማሠሩ ቆዳ አወጣለሁ አገባለሁ፣ በዚያዉም ሲሠሩ አያለሁ፣እንዲህ እንዲህ እያልሁኝ ገባሁ ቀረሁ" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 05፣ 2003) በማለት ገልያታል።
ከአስማማው ተረፈ ጋር በእድሜ አቻ የሆነውና ወንበርማ ወረዳ የሚኖረው በላይ ደነቀው ወደ ሙያው የገባበትን ሁኔታ እንዲህ ይገልፀዋል። "የአባት ሥራ ስለሆነ እነሱን እያየሁ ነው መስራት የጀመርሁ። አሁን ደግሞ በተራዬ የሚተካውን ማለማመድ ስላለብኝ ወንድሞቼን እያለማመድሁ ነው። ሁለት ወንድሞች አሉኝ እነሱን መፋቅና መቃቃት እያሳየሁዋቸው ነው።" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 05፣ 2003) ።

የ67 አመት አዛውንት የሆኑት አባ ወንዴም እንዲሁ "ሥራውን የጀመርሁት በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ነው። የአባት ሥራ ሁኖብኝ ከአባት ከእናቴ የተማርሁት ነው" (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 08፣ 2003) በማለት ለረዥም ዘመናት ሲሰሩት የቆዩት የቆዳ ሙያ የአባቶቻቸው ሥራ ስለነበረ ከቤተሠቦቻቸው የተቀበሉት መሆኑን ይናገራሉ።

ከሁለቱ ወረዳዎች በቃለ መጠይቅና ምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ባለሙያዎቹ ሙያውን የለመዱት ቤተሰቦቻቸው ሲሠሩ በማየትና የአባት ሥራ ነው ብለው በመቀበል ነው።

4.1.5 የቆዳ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ

ሂለን አላምረው (1991)፣ አስቴር፣ (2000)፣ ሃብታሙ እንግዳው (2001) እና በሌሎች የዲግሪ ማሚያ ጥናቶች ግኝት ላይ ባለሙያ ያልሆነው ማህበረሰብ የቆዳ ባለሙያዎችን የሚበሉትና የሚለብሱት ነገር ከቆሻሻ ያልፀዳ ነው። የሸክላ ባለሙያዎችን ደግሞ ሠዎችን ሊጎዳ የሚችል መንፈስ አለባቸው (ቡዳዎች ናቸው) በሚል ሰበብ ሲያገላቸው እንደነበረ እና በተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት እንደማያሳትፉቸው ተገልፀዋል።

ከዚህ አንፃር በቡሬ እና በወንበርማ ወረዳ የሚገኙ የቆዳ እና የሸክላ ባለሙያዎችን ህይወት ስናይ ከዚህ የተሸለ ገፅታ አይታይበትም። የተለየው በዚህ አካባቢ የሚኖሩ የሸክላ ባለሙያዎች ቡዳዎች ናቸው ተብሎ አለመታሰቡ ነው።

ይሸውም በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ ከሌላው ማህበረሰብ ያነሰ እና ዝቅ ያለ ሆኖ ይገኛል። በአካባቢው የሚኖረው ባለሙያ ያልሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች ባለሙያዎችን ከሚሠሩት ሥራ በመነሳት የሚያንቋሽሿቸው፣ የሚሰድቧቸው እና ከተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት የሚያገሏቸው መሆኑን ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ማህበረሰብቡ የቆዳ ባለሙያዎችን ማንቋሸሽ የሚጀምረው ከሙያቸው ባህሪ ተነስቶ ከሠጣቸው ስያሜ ነው። በሁለቱም ወረዳዎች የሚገኘው ማህበረሰብ የቆዳ ባለሙያዎችን ፋቂ ብሎ

ይጠራቸዋል፡፡ ይህንን ስያሜ በመጠቀምም በተለያዩ አጋጣሚዎች እነሱ ከሌላው ማህበረሰብ ያነሰ ደረጃ እንዳላቸው ሲገልፅ የታያል፡፡

ይህ ባለሙያዎችን የማግለል እና የማንቋሸሽ ልማድ የቆዳ ቁሶች መሠራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ/ ምንም እንኳን በዚህ አካባቢ ቁሶች መቼ ጀምረው መስራት እንደጀመሩ የሚገልጽ መረጃ ባይኖርም/ እስከ አሁን የዘለቀ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ይህ የማህበረሰቡ መጥፎ ልማድ ረዘም ያለ ዕድሜ ቢኖረውም፤ በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የማግለልና የማንቋሸሽ ደረጃ ከጥንቱ ጋር ሲነፃፀር፤ ተገቢው ለውጥ መጥቷል ለማለት ባያስደፍርም የቀነሰ መሆኑን ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ቀደም ባሉት የቆዳ ባለሙያዎች ባለሙያ ካልሆነው ማህበረሰብ ጋር ዕቁብ፣ እድር፣ አበልጅነት፣ ማህበር፣ ጋብቻ፣ በጋራ መብላት፣ መጠጣት ወዘተ በሚባሉት ማህበራዊ ተቋማትና ባህላዊ ክዋኔዎች ውስጥ በፍፁም መሳተፍ አይችሉም ነበር፡፡ ከደርግ ዘመነ መንግስት ወዲህ ከሥርዓቱ መለወጥ ጋር ተያይዞ በመጡ የአመለካከት ለውጦች ሳቢያ ባለሙያዎቹ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ዕቁብ፣ ዕድር ማህበር፣ በሚባሉት ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ የመሳተፍ ዕድል እንዳገኙ የሃገር ሽማግሌዎች እና የአካባቢው ተወላጅ (አባ አማረ እና አባ ገላው ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን በጋብቻ በኩል ያለው ችግር እስካሁን ድረስ ያልተቀረፈ መሆኑን ከመስክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት እንዲያስረዱኝ የጠየኳቸው አባ ገላው አበጀ የሚከተለውን ምላሽ ሠጥተውኛል፡፡

> *በሃይለ ስላሴ ግዜ እንኳን ለመጋባት ይቅርና እነሱ በበሉበት ዕቃ እንኳን አንበላም ነበር፡፡ በማህበር፣ በእቁብ ብር አጠራቅመን በሬ ሰናርድ ፋቂ ቆዳውን ገዝቶ ይሄዳል እንጅ ተኛ ጋር ቁጭ ብሎ አይበላም፤ ሸማኔ ይሻላል ንፁህ ነው፤ ፋቂዎች እንኳን ንጽህና ስለሚጐላቸው ተእነሱ ጋር መገናኘት ይከብደናል፡፡(ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 08፣ 2003)*

አባ ገላው እና ሌሎች መረጃ አቀባዮች እንደሚገልፁት ከደርግ አገዛዝ ወዲህ ግን የዘመኑ መንግስት የዕደ ጥበብ ሥራዎችን ለማስፋፋት ባደረገው እንቅስቃሴ ማህበረሰቡ የተወሰነ የአመለካከት ለውጥ በማምጣቱ ባለሙያዎች ከጋብቻ ውጪ ባሉት ማህበራዊ አጋጣሚዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ይሳተፋሉ፡፡

በጋብቻ በኩል የሚደርስባቸውን የመገለል ሁኔታ ስናይ የሸክላ ሠሪዎች ማህበራዊ ህይወት በሚለው ንዑስ ርዕስ እንደተገለፀው ለጋብቻ የማይፈለጉት ባለሙያ ባልሆነው ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን በሸክላ ባለሙያዎችም ጭምር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቆዳ ባለሙያዎች ከስራ አጋሮቻቸው ውጪ ከሌሎች ባለሙያዎችና የማህበረሰብ ክፍሎች ጋብቻ መመስረት እንደማይፈልጉ በመስክ ቆይታዬ ካገኘኋቸው መረጃዎች ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በዚህ ጥናት የተካተቱት ስምንቱም ባለሙያዎች በዚህ ዙሪያ ስጠይቃቸው ካላባታችን/ካለዘራችን/ አንጋባም፤ እንደኛ ሙያ የምትችለዋንና የቆዳ ባለሙያ ልጅ የሆነችውን እንጂ ከሌላ ጋር አንጋባም የሚል ተመሳሳይ መልስ ሰጥተውኛል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ችግሩ ተቀርፏል ለማለት ባይቻልም የተወሰነ ለውጥ እየታየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ ልጆችና አንዳንድ የቆዳ ሙያ ጥቅም የገባቸው የአካባቢው ተወላጆች ማህበረሰቡ ያስቀመጠውን ገደብ በመጣስ ከቆዳ ባለሙያ ልጆች ጋር በፍቅር በመጣመር እስከ ጋብቻ እንደሚዘልቁ መረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው የቆዳ ባለሙያዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት መልካም ገጽታ ያልነበረው ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በቂ ባይባልም የተወሰኑ ለውጦች እየታዩ ናቸው፡፡ የቆዳ ባለሙያዎች ህይወት ከሌሎች የዕደ ጥበብ ሠራተኞች አንፃር ሲታይ በሚሠሩት ሙያ ባህሪ /በቆዳው መጥፎ ሽታ ምክንያት/ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ መገለል ደርሶባቸዋል፡፡

የሚገርመው ጉዳይ ማህበረሰቡ ባለሙያዎቹን ከሙያቸው ባህሪ ጋር አያይዞ በያጋጣሚው ቢያንቋሽሻቸውም የሚሰሯቸውን ቁሶች ግን ከቤት ውስጥ አገልግሎት ጀምሮ እስከ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ማንነቱ መገለጫ በማድረግ በሰፊው ሲጠቀምባቸው መታየቱ ነው፡፡ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት (መረጃዎች በተሰበሰቡበት ጊዜ) የቁሶቹ አገልግሎት ላይ የመዋል ደረጃ በተለያዩ ምክንያቶች እየቀነሰ የመጣ መሆኑ ቢታወቅም፤ ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያለው ከፍ ያለ ግምት ለባለሙያዎቹ ካለው መጥፎ አመለካከት አንፃር ሲታይ ባለሙያዎቹ የልፋታቸው ውጤት የሆነውን ማህበራዊ ደረጃ እና ክብር እንዳላገኙ በይፋ ያሳያል፡፡

4.1.6 ከቆዳ ሙያ ጋር የተያያዙ እምነቶች እና አመለካከቶች

ቀደም ሲል የቆዳ ቁሶች ባህላዊ ጠቀሜታ በሚለው ርዕስ የአጐዛ ባህላዊ ጥቅም ተወስቷል። በዚህ አካባቢ በትጭጭት ወቅት ማለትም አንድ ቤተሰብ ወንድ ልጁን ለማጋባት ሲፈልግ ወደተመረጠችው ልጅ ቤተሰብ የሚላኩ ሽማግሌዎችን ይመርጣል። ሽማግሌዎቹም በቀጥታ ወደ ልጅቷ ከመሄዳቸው በፊት የሆነ አጋጣሚ (ገበያ፣ ቤተ-ክርስቲያን ወዘተ.) በመጠቀም የሴቷ ቤተሰቦች ጉዳዩንና የሚመጡበትን ቀን እንዲያውቁ ያደረጋሉ። የልጅቷ ቤተሰቦች በሰሙት ጉዳይ ላይ ተወያይተው ልጃቸውን ለመዳር ከወሰኑ ሽማግሌዎቹ በሚመጡበት ቀን አጎዛ አንጥፈው ይቀበሏቸዋል። ባንፃሩ የልጅቷ ቤተሰቦች መዳር ካልፈለጉ ደግሞ ሽማግሌዎቹ ሲመጡ በጉዳዩ አለመስማማታቸውን ገልጸው ሳይቀመጡ እንዲመለሱ ያደርጓቸዋል። ሽማግሌዎቹ በቁም የሚሸኙበት ምክንያት አጎዛው ላይ ተቀምጠውና በጋብቻው ሳይስማሙ ቀርተው አጎዛው ታጥፎ ቢነሳ የልጅቷ እድል ይታጠፋል (ባል አታገኝም) ተብሎ ስለሚታመንና የመጥፎ ምልክ መገለጫ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው።

የአጎዛው ቀለምም ከእምነት ጋር የተያያዘ ትርጓሜ አለው። ነጭ፣ ቀይ እና ዥንጉርጉር ቀለም ያላቸው አጎዛዎች ተመራጮች ሲሆኑ የመመረጣቸው ምስጢር ከውቃቢ ጋር የተያያዘ ነው። ይህን በሚመለከት አቶ የኔሁን ዘገየ እና አቶ ባይህ ግዛቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል። አቶ የኔሁን "እኔ ነጭ አጎዛ ላይ ደስ ይለኛል። ግርግዳ ላይም ሆነ መደብ ላይ ሳየው ውቃቢዬን ደስ የሚለው ነጭ ተሆነ ነው። ጥቁር ምናምን እንኳን ሥጋውንም ስበላው ደስ አይለኝም፤ አጎዛውንም አልወደውም።" (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 16፣ 2003 ዓ.ም) ።

አቶ ባይህ ግዛቸውም አቶ የኔሁን ያሉትን ካደመጡ በኋላ "አንተ አሞ ነጭ ነው ደስ የሚልህ እኔ እንኳን ነጭም ቀይም እወዳለሁ ብቻ ጥቁር አይሁን እንጅ ሌላው ጥሩ ነው። ጥቁር እንኳን ደስ አይለኝም፤ ሰው እንደውቃቤው ነው ጥቁርም የሚጠቀም ይኖራል፣ ግን በዚህ አካባቢ ለደስታ ነጭ አጎዛ ነው የሚነጠፍ" (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 16፣ 2003 ዓ.ም) በማለት ለአጎዛ ቀለም ያላቸውን አመለካከት ከውቃቢና ከውስጣዊ ደስታ ጋር አያይዘው ገልፀዋል።

ቁልፍ መረጃ አቀባዬ የሆኑት ወ/ሮ መድሃኒት ዘገየ እንዲሁ "ጥቁር አጓዛ መማማያ ነው ለደስታም ለውቃቤም ጥሩው ነጭ ሲሆን ወይም ደግሞ ዝንጉርጉር ቢሆን ይሻላል"። ብለውኛል።

መማማያ ማለት እንደ ወ/ሮ መድሃኒትና ሌሎችም የአካባቢው ተወላጆች ገለፃ ከእርቅ ባህላዊ ክዋኔ ጋር የተያያዘ ትርጉም አለው። ይኸውም ሁለት ሠዎች ተጣልተው ከተገዳደሉ የሀገር ሽማግሌዎች የተጣሉትን ቤተሰቦች ጥቁር አጓዛ ላይ አስቀምጠው ደም መመላለሳቸውን እንዲያቆሙ ቃል ያስገቧቸዋል። ይህ የማስታረቅ ሂደት መማማያ ተብሎ ይጠራል። ጥቁር አጓዛ ቤት ውስጥ ከመነጠፍ ወይም ግድግዳ ተንጠልጥሎ ክብርን ከማሳየት ይልቅ ለዚህ ተግባር ብቻ የሚመረጥ ሲሆን ቀለሙም በአካባቢው ሠው ዘንድ እንደማይወደድ ከመረጃ አቀባዮች ካገኘሁት ተደጋጋሚ መረጃ ለማወቅ ችያለሁ።

4.1.7 የቆዳ ባለሙያዎችን ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ ባተኮረባቸው አካባቢዎች የቆዳ ቁሶች ሰፋ ያለ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ሲሰጡ ኖረዋል። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ቁሶች ቀድሞ የነበራቸውን አገልግሎት ሲሰጡ አይታዩም ። ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱ ሶስት ዋና ዋና ሁኔታዎች አሉ። አንደኛው፣ የእነዚህን ቁሶች አገልግሎት ሊተኩ የሚችሉ ቁሶች በፋብሪካ መመረታቸው ሁለተኛው፣ ማህበረሰቡ ለሙያውና ለባለሙያዎቹ ያለው መጥፎ አመለካከት ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር መኖር ነው። እነዚህ የተጠቀሱት ሶስት ሁኔታዎች በቁሶቹ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ አለ።

ቀደም ሲል የባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት በተዳሰሰበት ርእሰ የቆዳ ባለሙያዎች ህይወት ዝቅተኛ እና ከማህበረሰቡ የተገለለ ኑሮ የሚመሩ መሆናቸውን አይተናል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ባለሙያዎች ወደው ሳይሆን ተገደው ሙያቸውን በመተው በሌሎች የስራ መስኮች ተሰማርተዋል ። ለዚህም ማስረጃ በቡሬ ወረዳ ባጉና ህና የሚገኙት ባለሙያዎች ወቅታዊ ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። እንደ መረጃ አቀባዮች ገለጻ በዚህ ቀበሌ 10 የሚደርሱ የቆዳ ባለሙያዎች በቆዳ ስራ ይተዳደሩ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ነገር ግን በዚህ ወቅት በመስራት ላይ የሚገኙት አባ ወንዴ የተባሉ የ67 አመት አዛውንት ብቻ ናቸው። ሌሎቹ ዘጠኝ ሰዎች ግን

በደረሰባቸው የመገለልና የማንቋሸሽ ድርጊት ሳቢያ ከፊሎቹ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄዱ ከፊሎቹ ደግሞ የቀን ስራ በመስራት ኑሮአቸውን መምራት ጀምረዋል። ይህም የማህበረሰቡ መጥፎ አመለካከት በሙያው ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳያል።

በዚህም ሳቢያ በቀበሌው ይከናወን የነበረው ባህላዊ የቆዳ ስራ ቆሟል ከሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ምክንያቱም በመስራት ላይ የሚገኙት አባ ወንዴም የሚሰሩት ዝንዲ ብቻ ሲሆን ይህንንም የሚሰሩት ተጠቃሚዎች ቆዳ ገዝተው ቤታቸው ድረስ ካመጡላቸው ብቻ ነው። ምክንያቱም ሰውየው አሁን ባሉበት የዕድሜ ደረጃ ከገበያ ቆዳ ገዝተው እና ተሸክመው ለማምጣት የሚያስችል ጉልበት የሌላቸው በመሆኑና ለማገዝ ፈቃደኛ የሆነ ልጅም ስለሌላቸው ነው። ሰውየው አቅማቸውን የሚመጥን ስራ ካገኙ የቆዳ ስራን ሙሉ በሙሉ ለመተው ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸውልኛል። ምክንያቱም ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ተነጥለው እንዲሰሩ ያስገደዳቸው ጉልበታቸው የእርሻ ስራ ለመስራት ስላላስቻላቸው እንጂ የቆዳ ስራውን መስራት ፈልገው አይደለም። ከልጆቻቸውም ሆነ ከሌላው ማህበረሰብ የሚደርስባቸው ነቀፌታ ካለባቸው የጉልበት መድከም ችግር ጋር ተዳምሮ ሙያውን በቀጣይነት እንዳይሰሩ ያስገደዳቸው መሆኑን ካቀረብኩላቸው ቃለመጠይቅ ተረድቻለሁ።
ሌላው በቆዳ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ላይ መሰናክል የሆነባቸው ጉዳይ በፋብሪካ የሚመረቱ ቁሶች መብዛት ነው ። እነዚህ በዘመናዊ መንገድ የሚመረቱ ቁሶች ለአጠቃቀም ምቹ በመሆናቸው እና የቆዳ ቁሶችን ጥቅም እንዲረሳ ማድረጋቸው ባለሙያዎቹ የሚያመርቷቸው የቆዳ ቁሶች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ተፈላጊነት እንዲያሽቆለቁል አድርጎታል። በሁለቱ ወረዳዎች በስፋት ሲበጁ የነበሩት ቁሶች በዚህ ወቅት ግን ከፊሎቹ ፈላጊ አጥተው ፈጽሞ መመረት ያቆሙ ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ በመቅረት አዝማሚያ ላይ የሚገኙና ተፈላጊ በሆኑበት ጥቂት ወራት ብቻ የሚበጁ ናቸው። የሚከተሉት ሁለት ሰንጠረገሮች ዝርዝሩን ያሳያሉ።

ሀ. መመረት ያቆሙ ቁሶችና የተኳቸው የፋብሪካ ቁሶች

ተ/ቁ	መመረት ያቆሙ ቁሶች	የተኳቸው የፋብሪካ ቁሶች
1	ዝናር	-
2	ጀበርና	-
3	ጠፍር አልጋ	የጥጥ እና የሳር ፍራሽ
4	ለምድ	ጐጃም አዘነ/ፎጣ
5	ዳውላ/አቆማዳ/	ኩንታል
6	ስልቻ/ቀርበታ/	ማዳበሪያ
7	የህፃናት ማጫወቻ አምባር	ከላስቲክ የሚሰሩ አምባሮች
8	መከዳ	የእንጨት ወንበር

ለ. ወቅት ጠብቀው የሚመረቱና የተኳቸው የፋብሪካ ቁሶች

ተ/ቁ	ወቅት ጠብቀው የሚመረቱ ቁሶች	የሚበጁበት/የሚመረቱበት ወቅት	የተኳቸው የፋብሪካ ቁሶች
1	ምራን	በእርሻ ወቅት	ከአጐበር ጨርቅ የሚፈተል ገመድ
2	መርገጫ	በእርሻ ወቅት	ከአጐበር ጨርቅ የሚፈተል ገመድ
3	መጠጊያ	በሠርግ ወቅት	የስፖንጅ ትራስ
4	ገቦንዲ	በሠርግ ወቅት	አንሶላ እና ስጋጃ

በአጠቃላይ ጥናቱ በአተኮረባቸው አካባቢዎች ሲመረቱ የነበሩ እና አሁንም በመመረት ላይ የሚገኙ ቁሶችን ቀጣይ ህልውና ስንመለከት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ቁሶች በተሻለ የፋብሪካ ቁሶች ተተክተዋል፡፡ በመሆኑም ብዙዎቹ መመረት ወይም መበጀት ያቆሙ ሲሆን በመበጀት እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት ጥቂት ቁሶችም የሚበጁት የእነሱን መኖር/መገኘት/ በሚያስገድድ ባህላዊ ክዋኔ እና የሥራ ወቅት ብቻ ነው፡፡ ቁሶቹ ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ ማሻሻያ ተደርገውባቸው መሠራት ካልቻሉ ወደፊት ሙሉ በሙሉ መበጀትም ሆነ አገልግሎት መስጠት ማቆማቸው አይቀሬ ነው፡፡

ባለሙያዎችን የገጠማቸው ችግር የጥሬ ዕቃ እንደልብ አለመገኘት ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት ስራችሁን በአግባቡ እንዳትሠሩ ያደረጋችሁ እንቅፋት አለ ወይ? ብዬ የጠየቅሁዋቸው የቆዳ ባለሙያ አቶ ሽታ ደነቀው እንዲህ በማለት ችግሩን ገልጸውልኛል፡፡

> እንዳንሠራ ያደረገን ያው ሠው ከከተማ የሚገዙ ዕቃዎችን እየገዛ የእኛን መተዉ ነው። ሌላው ደግሞ የጫቅማ ውድነት ነው። ፈጪቅማ እንደ ድሮው አይደለም ነጋዴ ገብቶታል። ድሮ አንድ ሠሀን ሁለት ብር ሶስት ብር ነበር፤ አሁን አስራ አምስት ብር ገብቷል። እኛም ከምንተወው ና ችግር ውስጥ ተምንገባ ብለን ነው ያዝ ለቀቅ እያረግን የምንሠራ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 05፣ 2003) ።

ይህ ለማለስለሻነት ጥቅም ላይ የሚውለው ጉሎ/ጫቅማ/ መወደዱ በስራቸው ላይ ጫና መፍጠሩን በላይ ደነቀው የተባለው የ25 አመቱ የቆዳ ባለሙያም ችግሩን ከወቅቱ የገቢያ ሁኔታ ጋር አነፃፅሮ "ከገበያው ይልቅ እኛን ያስቸገረን የጉሎ መወደድ ነው። 100 ኪሎው ጉሎ 200 ምናምን ብር ነበር፤ አሁን ግን 1000.00 ምናምን ገባ ተቦዘን (ተመቦዘን) ነው እንጂ ምንሞክረው እየከሠርን ነው። ሥራው ታለጫቅማ የማይሆን ነገር ነው፤ እና የጉሎ ነገር በጣም አስቸግሮናል" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 05፣ 2003) (ቅንፉ የኔነው) ገልፆታል።

በሁለቱ ወረዳዎች ከሚኖሩት ባለሙያዎች የተገኘው የቃል መረጃ እንደሚያሳየው ከገበያው ቀጥሎ የጉሎ /የጫቅማ/ ዋጋ መናር ባለሙያዎቹ ለፍተው እና ደክመው ባበጇቸው ቁሶች ትርፋማ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። ባጠቃላይ ባለሙያዎቹን በአጋጠሚቸው ችግሮች በሁለቱም ወረዳዎች የሚከናወነው ባህላዊ የቆዳ ሥራ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ የደረሰ መሆኑን እንገነዘባለን።

5. በቡሬ ወረዳ የሸክላ ቁሶች ስራ

በዚህ ምዕራፍ የወረዳው ባህላዊ የሸክላ አሠራር ሂደት፣ የሸክላ ቁሶች አይነት እና ጠቀሜታ፣ የሸክላ ቁሶች መጠንና ቅርጽ ያለቸው ትዕምርታዊነት፣ የባለሙያዎቹ ህይወት፣ በሙያው ላይ የሚታዩ ችግሮች፣ ያታዊ ተሳትፎ፣ ከሸክላ ሙያ ጋር የተያያዙ እምነቶች እና አመለካከቶች፣በዝርዝር ይቀርባሉ።።

5.1. የቡሬ ወረዳ የሸክላ ቁሶች የአሠራር ሂደት

በመስክ ቆይታዬ ለማየት እንደቻልኩት የሸክላ ቁሶች ወደ ገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያልፉባቸው የአሠራር ሂደቶች /ቅደም ተከተሎች/ አሏቸው።። አነዚህ ሂደቶችም ሂደት የሚባለውን ነገር ለማሟላት ብቻ የሚከናወኑ ሳይሆን ጉልበትን፣ ክህሎትን እና ጊዜን የሚጠይቁ ተግባሮች ናቸው።። ጥናቱ የተደረገው በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች ሲሆን ባለሙያዎች የሚከተሏቸው የአሠራር ሂደቶችም ተመሳሳይ ሆነው ተገኝተዋል።። በእነዚህ ቀበሌዎች የሸክላ ሥራ አምስት ሂደቶችን ያልፋል።። እነሱም የሸክላ አፈር መቆፈር፣ አፈሩን ለስራ ማዘጋጀት፣ ሥራ መጀመር፣ የተሠሩትን ቁሶች ማድረቅና በመጨረሻም በእሳት መተኮስ ወይም ማቃጠል ናቸው።። ከጥናቴ ዋና ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የቁሶችን አሠራር ሂደት ማሳየት እንደመሆኑ መጠን እነዚህን ሂደቶች ከመስክ ባገኘሁት መረጃ መሠረት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው አቀርባለሁ።።

5.1.1 የሸክላ አፈርን የመቆፈር ሂደት

ይህ ሂደት በሸክላ ቁሶች ሥራ የመጀመሪያው ተግባር ሲሆን ቁሶችን ለማዘጋጀት ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል በአድካሚነቱ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።። ለዚህም ምክንያት ለሸክላ መስሪያ የሚያገለግለው አፈር የሚገኝበት ቦታ ከፍተኛ ቦታ /ተራራ/ ሥር፣ ወይም ደግሞ ሚዳማ ቦታ ላይ ሆኖ ውሃ የሚበዛበት /ከበጋ እስከ ክረምት ድረስ ውሃ የማይጠፋበት ቦታ/ ላይ መሆኑ ነው።። ባለሙያዎቹ በአንድ አካባቢ ሠብሰብ ብለው የሚኖሩ ከሆነ በህብረት ይቆፍራሉ።። ምክንያቱም ስራው በጣም አድካሚ በመሆኑ በአንድና በሁለት ሠው ብቻ በቀላሉ ሊሠራ ባለመቻሉ ነው።። ነገር ግን ሸክላ ሠሪዎች ሰብሰብ ብለው የማይኖሩ ከሆነ እና በሌላ በኩል ደግሞ የማይግባቡ ከሆነ እንደሚያደክማቸው ቢያውቁም በተናጠል እየሄዱ ይቆፍራሉ።።

ይህንንም ጉዳይ ከሁለቱ ቀበሌዎች አንፃር ሥናይ ባጉና ሃና የሚባለው ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚገኙት ሸክላ ሠሪዎች ቁጥራቸው በዛ ያለ በመሆኑ /በቁጥር ስድስት ናቸው/ ::ከዚህም በተጨማሪ በመካከላቸው አንድነት ስላላቸው፤ የሚኖሩትም በአንድ አካባቢ በመሆኑ ተነጋግረው ሁሉም በሚመቻቸው ቀን በወር አንድ ጊዜ ብቻ ይቆፍራሉ:: በሻኳ ዮሐንስ ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩት ሸክላ ሠሪዎች ግን በቁጥር ሶስት ብቻ ሲሆኑ እነሱም በተራራቀ መንደር የሚኖሩ ናቸው:: በዚህ ቀበሌ የሸክላ አፈር የሚገኘው ቦታም ሶስት አካባቢዎች ላይ ሲሆን አፈሩ የሚገኝበት ቦታ ተራራ ስር ነው::የባለሙያዎቹ የቁፋሮ ልምድ ሲታይ በመካከላቸው ካለው የመኖሪያ ቤት መራራቅ እና አለመግባባት የተነሳ ሁሉም በተመቻቸው ወቅት በሚቀርባቸው ቦታ በተናጠል በመሄድ ይቆፍራሉ::


በሁለቱም ቀበሌዎች የሚገኘው የሸክላ አፈር ዓይነት ጥቁር ቀለም ያለው ዋልካ ሲሆን ሲቆፈር የሚወገደው አላስፈላጊ ነገር ግን ይለያያል:: ይኸውም ባጉና ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩት ሸክላ ሠሪዎች ሚዳማ እና ዘወትር ውሃ የሚመነጭበት ቦታ ላይ የሚቆፍሩ በመሆኑ፤ አቆፋፈራቸውም ከላይ ሳሩን በማንሳት ይጀምራል:: ከዚያም ቀጥሎ የሚገኘውን አላስፈላጊ አፈር ያስወግዳሉ:: በመቀጠል ደግሞ እስከ መጨረሻ ማለትም የሸክላው አፈር ወጥቶ እስከሚያልቅ ድረስ የማይጠፋውን ውሃ በያዙት መቅጃ ከጉድጓድ እያወጡ ይደፉታል:: በዚህ መሠረት ውሃውን ያለማቋረጥ እየደፉ እና ለሸክላ ስራ ጠቃሚ ያልሆነውን ቀይ አፈር ካስወገዱ እና ብዙ ከደከሙ በኋላ የሚፈለገው ጥቁር የዋልካ አፈር ይገኛል፤ ከዚያም በቅርጫት ወይም በማደበሪያ ተደርጎ ይመታል:: ይህን ሂደት በሚመለከት መረጃ የሰጡኝ እማ አበባ የ50 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ሲሆኑ በስራው 20 ዓመት ልምድ አላቸው፤ ባለቤታቸው በሞት በመለየታቸው አምስት ልጆቻቸውን ለብቻቸው ያሳደጉ ሲሆን ሂደቱን በሚመለከት እነዲህ ብለውኛል::

> *እኛ ባጉናዎች የሸክላ አፈር ምንቆፍረው በወር አንድ ጊዜ ብቻ ነው:: ለብቻማ ሚገፍ አይደለም:: ሥለዚህ ተረዳድተን ሁላችንም የግብርና ሥራ በማይኖረን ጊዜ መቆፈር እንወጣለን፤ ተዚያ ግማሻችን ውሃውን እየጠለቅን እንደፉለገ፤ ግማሻችን አፈርን እንከላለን:: እንደዚያ ታልሆነማ ያስቸግረናል የዚህ ቀበሌ ሸህላ አፈር ቦታው አስቸጋሪ ነው:: እንደሌላው አንድ ግዜ ተቆፈረንበት ቦታ ደግመን ለመቆፈር ውሃው ስለሚሞላበት ያስቸግራል /27/08/03/*



(ፎቶግራፍ 20) የባጉና ቀበሌ የሸክላ አፈር መገኛ

የሻኳ ቀበሌ ባለሙያዎች የአፈር አቆፋፈር ሂደት ከባጉናዎች የተለየ ነው፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የዚህ ቀበሌ የሸክላ አፈር መገኛ ተራራ ስር ሲሆን የሚያስቸግረው ቀዩን አፈር /የማያስፈልገውን/ በማስወገድ ጥቁር ቀለም ያለውን የሸክላ አፈር ማግኘት ሲሆን እንደ ባጉናዎች በቁፈራው ሂደት የውሃ ጣልቃ ገብነት አይታይም፡፡ በዚህም ምክንያት አንድ ጊዜ ከተቆፈረው ጉድጓድ ሌላ ጊዜም በተደጋጋሚ በመቆፈር ተፈላጊውን የዋልካ አፈር ማግኘት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተራራ ስር በአስቸጋሪ ሁኔታ ስለሚገኝ በዚህ ቀበሌም ቢሆን የቁፈራው ሂደት ቀላል አይደለም፡፡



(ፎቶግራፍ 21) የሻኳ ቀበሌ የሸክላ አፈር መገኛ

በሁለቱም ቀበሌ የሚኖሩት የሸክላ ባለሙያዎቹ በወር በዓላት እና በሠንበት አይቆፍሩም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ ተዘጋጅቶ የተቀመጠውንም ጭቃ ተጠቅመው አይሠሩም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ባለሙያዎች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች በመሆናቸው እና በዓላቱ ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በከፍተኛ ጥንቃቄ (ከሥራ በመታቀብ) የሚከበሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ሸክላ ሠሪዎች ለመቆፈሪያነት መጥረቢያን የሚጠቀሙ ሲሆን ውሃውን ለማስወገድ ደግሞ ከእንጨት የተሠራ ገበታ እና ከላስቲክ የተሠሩ ሠሃኖችን ይጠቀማሉ፡፡ ለሸክላ መስሪያነት የሚያገለግለው አፈር መገኛ ቦታ ከመንግስትም ሆነ ከግለሰብ ይዞታ ነፃ የሆነ እና ምንም አይነት ክፍያ የማይጠየቅበት ነው፡፡ ባለሙያዎች በነፃነት ጉልበታቸውን ተጠቅመው የሚፈልጉትን ያህል አፈር መውሰድና የሚፈልጉትን ቁስ መስራት ይችላሉ፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ባጉና ቀበሌ የሚኖሩት እና ከግብርና ሥራ ጐን ለጐን በሸክላ ሥራ የሚተዳደሩት የ60 አመቷ ወ/ሮ መልካም ጤናው ለአፈሩ ክፍያ ትጠየቃላችሁ?ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ "ምኑን አመጣሽብኝ እቴ፤ እንኳን ለአፈሩ ተከፍሎ ሥራው ከጥቅሙ ይልቅ ልፋቱ ያመዝናል፡፡ አፈሩንማ ልጄ ማንም አያስከፍለንም የህዝብ ነው፡፡ እኔ አልፋለሁ የሚል በግል የያዘው የለም፡፡" (ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዚያ 25፤ 2003 ዓ.ም) በማለት መልስ ሰጥተውኛል፡፡

ባለሙያዎቹ እንደገጹልኝ በዚህ አካባቢ የሸክላ ቁስ ለመስራት ጥቅም ላይ የሚውለው የአፈር አይነት ጥቁር ዋልካ ሲሆን የመቆፈር ሂደቱም አድካሚና አስቸጋሪ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ተከታዩን የሸክላ የስራ ሂደት አቀርባለሁ።

5.1.2 የሸክላ አፈርንና ገልን ለስራ የማዘጋጀት ሂደት

ይህ ሂደት ከብዙ ድካም በኋላ ተቆፍሮ ወደ ቤት የመጣውን የሸክላ አፈርና ገልን ለሥራ ብቁ የማድረግን ሂደት አካቶ ይይዛል።

> *የሸህላ አፈር ጽዳት ይወዳል። ከጉድጓድ ከወጣ በኋላ በንጠህ ኮሶ ወይም ቅርጫት ተደርገሞ ይመጣል። እቤትም አንራው በደንብ ተጠርገሞ በመጣበት ወይም በሌላ ንጠህ ኮሶ ተዘርግቶ ይቀመጣል። ተዚያም ተተፈጨው ገል ጋር ገሉ ተሰር ጭቃው ተላይ ሆኖ ቢያንስ ለሁለት ሰዓት ያህል በእግር ይታሻል።*/ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 24፣ 2003 ዓ.ም/

እንዲህ ያሉኝ የ40 ዓመቷ ወ/ሮ ምንትዋብ ስማቸው ናቸው።ወይዘሮዋ ሁለት ሴት ልጆችዋን በሸክላ ስራ የሚያስተዳድሩ ባለሙያ ናቸው። ቁልፍ መረጃ አቀባዬ የሆኑት ወ/ሮ አበባም እንደዚሁ የሸክላ አፈር በጽዳት መያዝ እንዳለበት እንዲህ በማለት ነግረውኛል።

> *የሸህላ አፈር ንጥህና ባለው ቦታ መቀመጥ አለበት ሲታሸም በንጠህ ኮሶ ላይ ሆኖ ምንም ትቢያ፣ የውሻና የሰው ሽንት፣ ወጥ፣ የጠላ አተላ በማይደርስበት ቦታ ላይ መሆን አለበት። እንደዚያ ታልሆነ ሲደርቅና ሲተኮስ ወይ ይፈርሳል ወይም ሊጥ ይሆናል። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 24፣ 2003 ዓ.ም)*

ከእነዚህ ሁለት ባለሙያዎች እና ከሌሎች የሸክላ ባለሙያዎች ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው የሸክላ አፈር ከፍተኛ ጥንቃቄ እና ንጽህና የሚያስፈልግው መሆኑን ነው። የሸክላ አፈር ንጽህና ከመጠየቁ በተጨማሪ ቁስ ሆኖ ከመሰራቱ በፊት ከተፈጨ ገል ጋር በእግር መቦካትና መታሸትን የሚጠይቅ መሆኑን ከወ/ሮ ምንትዋብ ስማቸው ቃል መረዳት ይቻላል። እንደ ባለሙያዎቹ ገለፃ የሸክላ አፈር ንፁህ ቦታ ላይ ይቀመጣል። ከአፈር ጋር ሊቀላቀል የተዘጋጀው ገል በድንጋይ ይከሰከስ እና ገል ለመፍጨት ብቻ በምታገለግለው የድንጋይ ወፍጮ ተደጋግሞ ይፈጫል። የገሉ ድቀትም እንደ እቃው አይነት ይለያያል።

ግንቦ ለመስራት የደቀቀ ገል ሲያስፈልግ ማድጋ እና ምጣድ ደግሞ ሸርከት ያለውን /በጣም ያልደቀቀውን/ ይወዳል በማለት ባለሙያዎች ገልጸዋል፡፡ ከዚያም ለማቡኪያነት በተነጠፈው ላስቲክ ወይም ኮሶ ላይ የተፈጨው ገል ከስር ጭቃው ደግሞ ከላይ እየተጨመረ ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት ለሚሆን ጊዜ በእግር ይታሻል፡፡ በእግር ከታሸ በኋላ ደግሞ እንደገና በድንጋይ ላይ ይታሻል፡፡ በዚህ ሂደት ተቀላቅሎ የሚታሸው ገልና ጭቃ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ ካለበለዚያ አፈሩ በዝቶ ገሉ ካነሰ ወይም ደግሞ ገሉ በዝቶ አፈሩ ካነሰ ይሰበራል፡፡ ስለዚህ የማመጠኑ ሂደት ጥንቃቄ እንደሚገባው በሸክላ ስራ የረዥም ጊዜ ልምድ /የ20 ዓመት ልምድ/ ያላቸው እማ አበባ ገልጸዋል፡፡

የሸክላ ቁሶችን ለመስራት የሚዘጋጀው ጭቃ ሁለት አይነት ገጽታ አለው፡፡ አንደኛው ከጉድጓድ ተቆፍሮ እንደመጣ ሳይደርቅ የሚሰራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሸክላ ሰሪዎች አንድ ጊዜ አምጥተው ቢያንስ ለአንድ ወር ስለሚጠቀሙበት እና በውስጡ የያዘው ውሃ ስለሚተን አፈሩ ይደርቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ የደረቀውን የሸክላ አፈር በውሃ እያራሱ በእግራቸው አሽተው ለመስራት ያዘጋጁታል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ፎቶ መጋቢት 30 ቀን ቆፍረው ያስቀመጡትን የሸክላ አፈር ውሃ እያራሱ ሲያቦኩ የሚያሳይ ነው፡፡



(ፎቶግራፍ 22) የሸክላ አፈር ሲቦካ

እስካሁን የተመለከትነው የሸክላ አፈርን መቆፈርና የተቆፈረውን አፈር ለስራ የማዘጋጀቱን ሂደት ሲሆን ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የተዘጋጀውን አፈርና ገል

በመጠቀም ስራው እንዴት እንደሚጀምር ፤ቁሶቹ ቅርፃቸውን እንዴት ባለ ሁኔታ ይይዛሉ የሚለውን እናያለን፡፡

5.1.3 የሸክላ ቁሶችን ለመስራት መጀመር እና ቅርጽ ማስያዝ

በሁለቱ ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኙት የሸክላ ባለሙያዎች የሰጡት መረጃ እንደሚያሳየው የሸክላ አፈሩና ገሉ ተመጥኖ ከታሸ በኋላ ቀጣዩ ስራ የተዘጋጀውን ጭቃ በላስቲክ ወይም በሌላ ንፁህ ዕቃ በማቅረብ ፀሐይ በማይደርስበት ቦታ ወይም ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ መስራት ነው፡፡ ባለሙያዎቹ እንደነገሩኝ እና እኔም እንደተመለከትሁት ቁሶችን ለመጀመርም ሆነ ቅርጽ ለማስያዝ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ሁሉም ከዘመናዊ ቴክኖሎጅ ውጤቶች የራቁ ናቸው፡፡ ሸክላ ሰሪዎች እቃዎችን ለመስራት በአብዛኛው የሚጠቀሙት እጃቸውን ሲሆን ከዚህ በተረፈ ደግሞ ዕቃዎችን ለማለስለስ እና ውፍረት እና ቅጥነታቸውን ተመጣጣኝ ለማድረግ የተሰነጠቀ ሸምበቆ ሲጠቀሙ የቁሶችን አፍ ለመስራትና እንዲሁም ለማለስለስ ደግሞ የገጉንዲ ቁራጭ ወይም ቆሮንጮ ይጠቀማሉ፡፡ እንዲሁም እንደ ቁሶቹ ቅርጽና መጠን የተለያየ ግዝፈት ያላቸው የቁሶች የመጀመሪያ ክፍል ማስቀመጫ ወይም መወጠኛ ዕቃ አላቸው፡፡

የእነዚህ ቁሶች አይነትም እንደባለሙያዎች ፍላጐት ይለያያል፡፡ አንዳንዶቹ የሚሰሯቸውን ቁሶች መጠን መሠረት አድርገው ከጭቃ ይሰራሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የስፌት እቃዎችን እንዲሁም የአገለገሉ የእንጀራ መብያ ሰሀኖችን ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ ቁሶችን ለመጀመር የሚያገለግሉ ዕቃዎችን ከሚሰሩባቸው ቁሶች አንፃር ስናያቸው የጀበና እና የማንደጃ ማስቀመጫዎች ተመሳሳይ መጠን አላቸው፡፡ የማድጋ ዘሮች ደግሞ እንደዚሁ ተመሳሳይ ሲሆኑ ከጀበናዎች እና ከማንደጃዎች ከፍ ያለ መጠን አላቸው፡፡ የጋን ደግሞ ከማድጋዎች ሰፋ ያለ ነው፤ ከሁሉም የሚበልጠው ግን የምጣድ ሲሆን የምጣድ የመወጠኛ ቁስ ስፋት በሚሠራው ምጣድ ልክ ነው፡፡ ከምጣዱ አነስ ያለ ከሌሎች ቁሶች መስሪያ ደግሞ ሰፋ ያለ መጠን ያላቸውን እቃዎች የሚጠቀሙት ደግሞ ለድስቶች ነው፡፡ የድስቶችም ቢሆን እንደመጠናቸው (የመያዝ አቅማቸው) የጀመሩባቸው ቁሶችም ይለያያሉ፡፡ ይኸውም

የትንንሽ ድስቶች መጀመሪያ ቁሶች ከጀበናዎች ጋር እኩል መጠን ያላቸው ሲሆን የትልልቅ ድስቶች ወይንም ሰታቴዎች መጀመሪያ ደግሞ ከጋን ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

በዚህ አካባቢ የሁሉም አይነት የሸክላ ቁሶች ስራ የሚጀመረው ከታች "ከቂጣቸው" ነው፡፡ ከታች ይጀመሩና ወደ ላይ እያደጉና አስፈላጊ የሆነው የአካል ክፍላቸው ማለትም ጆሮ፣ አንገት፣ ጌጣጌጥ ወዘተ እየተጨመረባቸው የስራው ሂደት ይቀጥላል፡፡ የቁሶቹ መስሪያ ጊዜም እንደ ዕቃዎቹ መጠን ይለያያል፡፡ ይኸውም ትንንሽ ቁሶች አንዴ ተጀምረው በአንድ አፍታ የሚያልቁ ሲሆን ትልልቆቹ ግን ከሰዓታት እስከ ቀናት ሊጨርሱ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ትልልቅ የሸክላ ቁሶች የመጀመሪያ የታችኛው ክፍላቸው ይሠራ እና በነፋስ ወይንም በፀሐይ ጠፈፍ ካሉ በኋላ ነው ቀጣዩ ክፍላቸው የሚሰራው፡፡ ስለዚህ አንድን ትልቅ ቁስ ሠርቶ ለመጨረስ ከሁለት እስከ ስድስት ጊዜ ቆም ማለትን ይጠይቃል፡፡ ከባለሙያዎቹ የቃል መረጃ እንደተረዳሁትና እኔም በመስሪያ ቦታዎች ተገኝቼ እንደተመለከትሁት አንድን ቁስ ጀምረው ጠፈፍ እንዲል ፀሐይ ላይ ወይንም ነፋስ ላይ ሲያስቀምጡ የተጀመረው እቃ ደረቅ እስኪል እነሱ ሌላ ቁስ ጀምረው ይሰራሉ እንጂ ቁጭ ብለው አይጠብቁም፡፡ በዚህም ሁኔታ እንደባለሙያዎቹ ክህሎትና እንደሚሰሩት ቁሶች ግዝፈት በቀን እስከ አምስት ቁሶች ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ወ/ሮ አበባ ቁሶችን ሲሰሩ ምን ያህል ጊዜ ይወስድበወታል? ብየ ላቀረብሁላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል፡፡

> *ሠሀቱ ያው እንደ ዕቃው መጠን ይለያያል፡፡ እኔ ድሮ ሁሉን እሠራ ነበር፡፡ አሁን ግን ማንደጃዎችን እና ዥቦናዎችን ነው የምሰራው፡፡ ትልልቁ ጉልበቴ ስለደከመ ተውሁት፡፡ በዚያ ላይ ብዙ ሰዓት ይወስዳል፡፡ ጋን እና ትልቅ ማድጋ ተሆነ አራት ጊዜ አምስት ጊዜ ዳ እያልሁ ነው የምሰራው፡፡ ዥቦና እና ማንደጃ ግን በቀን አምስት እና ሰድስት እሠራለሁ፡፡/ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 26፣ 2003 ዓ.ም/*

በሸክላ ስራ ሂደት ውስጥ የሚታየው ሌላው ጉዳይ ከአንድ ቦታ የሚገኘው እና አንድ ጊዜ የተዘጋጀው ጭቃ ለሁሉም እቃ መስሪያነት የማያገለግል መሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ቁሶች ለስራ ዝግጁ ሆነው አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት የሚያልፉበት ማሟሸት የሚባል ሂደት መኖሩ ነው፡፡ የሚሟሸበት ንጥረ ቁስ ደግሞ እንደሚሰጡት አገልግሎት ይለያያል፡፡ በመሆኑም ቁሶቹ ይህንን ሂደት አልፈው

ስራቸውን በብቃት ለመወጣት የተሠሩበት የአፈር አይነት ወሳኝ ነው። ከዚህ አንፃር የሁለቱን ቀበሌዎች የሸክላ አፈር አይነት ስናይ ባጉና ቀበሌ የሚገኘው አፈር ለሁሉም ቁስ መስሪያነት ሲያገለግል በማሟሸቱ ሂደትም ችግር አይፈጠርም። ሻኳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን አፈር ግን በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙት ሶስት የሸክላ አፈር መገኛ ቦታዎች አንዱ ብቻ በተለየ ሁኔታ ለምጣድ መስሪያነት የሚያገለግል ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለቱ ግን ከምጣድ ውጭ የሆኑ ቁሶቹን ለመስራት የሚያገለግል አፈር የሚገኝባቸው ቦታዎች ናቸው። የቀበሌው ነዋሪ የሆኑትና ከግብርና ስራ ጐን ለጐን ለ28 ዓመት ምጣድን ጨምሮ ሌሎች ቁሶችን በጥራት በመስራት በአካባቢው የሚታወቁት ወ/ሮ ውበት ከበደ ለምጣድ መስሪያነት የሚያገለግለው አፈር ያለበትን ሁኔታ እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡ ፡

> *ምጣድ ከድሮ ጀምሬ እሰራ ነበር አሁን ትቸዋለሁ። አፈሩ አንድ ቦታ ብቻ ነበር የሚገኘው፤ ችርካ ከሚባል ቦታ ነበር የምናገኘው፤ እሱም ተራራው ተንዶ አዳፈነው። ለመቆፈር አስቸጋሪ ስለሆነብኝ ተውሁት ያ ቦታ ተተዳፈነ ወዲያ ሌላ ቦታ ላይ እየሄድሁ አመጣ ነበር። ምጣድም በእሱ መስራት ጀምሬ ነበር። ግን የሸጥሁላቸው ሰዎችም እኔም ሳሚሸው ገና ማሰሻ ሲነካው ይፈርሳል። እና ከንቱ ድካም ሲሆንብኝ ጊዜ ተውሁት። ምጣድ ንፁህ ገል ስለሚያስፈልገው እሱን ማግኘትም አስቸጋሪ ነው። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 21፣ 2003 ዓ.ም)*

ሁሉም የሚሰሯቸውን ቁሶች መስራት የለመዱት ቀስ በቀስ ከቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከጐረቤቶቻቸው በማየት መሆኑን ይገልፃሉ። ከዚህ በተጨማሪም እማ ውበት የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደገለጹልኝ የወረዳው ጥቃቅንና ኢንዱስትሪ ስራዎች ማስፋፊያ የሚያዘጋጀውን ስልጠና በመውሰድ ለወጥና ለእንጀራ መጋገሪያ የሚያገለግሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን እንደሚሰሩ ተገንዝቤአለሁ።

እስካሁን ከቀረቡት ማስረጃዎች እና ማብራሪያዎች ጥናቱ ባተኮረባቸው ቀበሌዎች የሚሠሩት የሸክላ ቁሶች አጀማመርና አጨራረስ ተመሳሳይ መሆኑን አይተናል። የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎችም ባለመሥያዎቹ በቤታቸው ውስጥ ከጭቃ፣ከእንጨት ከሌሎች ጥሬቃዎች የሚያበጇቸው ናቸው። ቅርጽ ለማውጣትና በቁሶቹ ዋና አካል ላይ የሚጨመሩ ክፍሎችን ለመስራት እና ለማሳደግ ደግሞ እጃቸውንና ሸምበቆ ብቻ እንደሚጠቀሙ ለማየት ተችሏል። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ልዩነት ያለው ቁሶቹ ሲጀመሩ በሚቀመጡበት ወይም በመወጠኛ እቃዎች መጠን ብቻ ነው።

ምንም እንኳን የሚሠሩት ቁሶች አይነት ቢለያይም የአሠራር ሂደታቸው ተመሳሳይ በመሆኑ ሁሉንም ቁሶች በዝርዝር ማሳየቱ አላስፈላጊ መደጋገም ስለሚሆን ባለሙያዎቹ በትንሽ ማስቀመጫ እና በትልልቅ ማስቀመጫ የሚወጠኑ ብለው በከፋፈሉዋቸው መሠረት መጠናቸውን ዋና ጉዳይ በማድረግ የአሠራር ሂደታቸውን አሳያለሁ፡፡ ለዚህም ያመች ዘንድ ትንሽ የመወጠኛ እቃ ከሚጠቀሙት የሸክላ እቃዎች ውስጥ ጀበናን፣ ትልቅ የመወጠኛ እቃ ከሚጠቀሙት ውስጥ ደግሞ ትልቅ ድስት/ሰታቴን በመምረጥ የአሠራር ሂደታቸውን አሳያለሁ፡፡


5.1.3.1 የጀበና አሠራር ሂደት

በዚህ ጥናት የመስክ ቆይታ ወቅት ለማየት እንደተቻለው ሁሉም የሸክላ ባለሙያዎች ጀበናን የመስራት ችሎታ አላቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የጀበና ስራ ቀላል እና የተለየ ክህሎትን የማይጠይቅ ሆኖ ሳይሆን መጠኑ ትንሽና ጌጣጌጥ የሚበዛበት መሆኑ ቀልብ እንዲስብ ስላደረገው ነው፡፡ የሚሠሩት ጀበናዎች ከአንድ ሊትር እስከ ሁለት ሊትር ከግማሽ ውሃ የመያዝ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ትልቅ ጀበናዎች ተፈላጊነታቸው በአብዛኛው በገጠሩ ህዝብ ዘንድ መሆኑን ባለሙያዎቹ ነገረውኛል፡፡ እኔም ተዘዋውሬ ባየኋቸው ሁለት የገጠር ቀበሌዎች ይህንኑ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በአካባቢው የሚሠሩ ጀበናዎች በመጠን ብቻ ሳይሆን በቅርጽም ይለያያሉ፡፡ ልዩነቱም በመቅጃዎች ወይም በአንዲሮች ብዛት መሆኑን ከመስክ ምልከታው ለማወቅ ችያለሁ፡፡ በዚህ አካባቢ የሚኖረው የከተማውም ሆነ የገጠር ነዋሪ የሚጠቀመው ጀበና አንድ መቅጃ ወይም አንዲር ብቻ ያለው ሲሆን በጥንቆላ የሚተዳደሩ ሰዎች ደግሞ ከሁለት እስከ ሰባት አንዲር ያለውን ጀበና ይጠቀማሉ፡፡ የእነዚህ ሁለት ጀበናዎች አሠራር ሲታይ ከመቅጃዎች ቁጥር መብዛት በስተቀር ተመሳሳይ ነው፡፡

ጀበናዎች በሚሰሩበት ጊዜ ሌሎች ቁሶች ሲሰሩ እንደሚደረገው ሁሉ በንፁህ ላስቲክ ተዘጋጅቶ የተቀመጠው ጭቃ ከባለሙያዎቹ በስተቀኝ በኩል ይደረጋል፡፡ በሰሃን ውሃና የሸምበቆ ስንጣቂ ደግሞ ከፊለፊት ይቀመጣል፡፡ ከዚያም ለመወጠኛ የምታገለግለው ከጭቃ ወይም ከስፌት የተሠራችው ቁስ ላይዋ ላይ የተፈጨ ገል ተነስንሶባት ከባለሙያዎች ፊት ትቀመጣለች፡፡ እነዚህ ሁሉ ከተዘጋጁ በኋላ ባለሙያዋ የሸክላ መስሪያ ጭቃ እያድቦለቦለች የጀበናውን የታችኛው ክፍል /ቂጡን/

መወጠኛዋ ላይ መስራት ትጀምራለች /ትወጥናለች/፡፡ ይህን ክፍል መስራት ስትጀመር የምትጠቀመው ምንም አይነት መስሪያ ዕቃ የሌለ ሲሆን ባለሙያዋ ለሆዱ መስሪያ የሚበቃውን ያህል ጭቃ መጥና ከውስጥ በግራ እጇ ከላይ ደግሞ በቀኝ እጇ እያስተካከለች የጀበናውን ሆድ ቅርጽ ሞለል አድርጋ ትጀምራለች፡፡ ከዚያም የጀበናውን ሆድ ለመስራት ጭቃ መጨመር ካስፈለገ የሚሰራው ጀበና የተስተካከለ ውፍረት እንዲኖረው በተዘጋጀው የሸምበቆ ስንጣቂ እያስተካከለችና እየወሰወሰች ጭቃ እየጨመረች የጀበናውን ቁመት ታሳድጋለች፡፡ ጐን ለጐን ደግሞ በውስጥ በኩል በሚገኘው ግራ እጇ ስፋቱን ትጨምራለች፡፡

በዚህም መሠረት የጀበናው ሆድ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ አንገት፣ መቅጃና ጆሮ ለመስራት እንዲያመች ለሰላሳ ደቂቃ ያህል ነፋስ ላይ ወይም ፀሐይ ላይ ቁጭ ይላል፡፡ ጅምሩ ጀበና ጠፈፍ እስኪል ባለሙያዋ ሌላ ጀበና ትጀምራለች ወይም ትወጥናለች፡፡ ይህ ጀበናም በመጀመሪያው ሂደት ያልፍ እና ቀጣዩ ጀበና ጠፈፍ ብሎ እስከሚሠራ እንደገና ሌላ ይጀመራል፡፡ ይህንን ሂደትም እማ አበባ ከጐረቤታቸው ወይዘሮ ቦሰና ጋር ሲሰሩ ለአንድ ሰአት ከሰላሳ ደቂቃ ያህል ቁጭ ብዬ ተመልክቻለሁ፡፡



(ፎቶግራፍ 23) የጀበና አሰራር ሂደት

ሆዳቸው ተሠርቶ ጠፈፍ እንዲሉ የተቀመጡ ጀበናዎች ደረቅ ማለታቸው ከታወቀ መጀመሪያ አንገት ከዚያም ከማተቡ ወረድ ብሎ ይበሳና ለብቻው ተዘጋጅቶ የተቀመጠው ጆሮ በተበሳው ክፍተት ይገባል። በቀላሉ እንዳይገነጠልም ከውጪና ከውስጥ ተዳፍኖ ይለሰናል። ስለ ጀበና አሠራር እማ አበባን ጠይቂያቸው የሚከተለወን ነግረውኛል።

> *ጀበና ጭቃ ከተዘጋጀ በኋላ ቆንጆ መወጠኛ አለችኝ በእሷ ላይ የደቀቀ ገል ነስንሼ መስራት እጀምራለሁ። ጀበና ያው መጠኑ ቢያንስም የሚጀመረው ግን እንደሌሎች ከቂጡ ነው። ተዚያ መጀመሪያ በእጄ በኋላ ደግሞ በሸምበቆ እየላግሁ እና እየወሰወስኩ አስተካክላለሁ። እንደዚህ እያደረግሁ ሆዱን ሰርቼ እጨርሰዋለሁ። ትንሽ ዳ ብዬ ደግሞ አንገቱን መቅጃውን ጆሮውን እሠራለሁ። በመጨረሻም ጌጣጌጥ አደርግበታለሁ። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 21፣2003 ዓ.ም)*

በዚህ አካባቢ የሚያገለግሉት ሁለቱም የጀበና አይነቶች የአሠራር ሂደት ተመሳሳይ ነው። የሚለያዩት በሚወስዱት ጊዜ ብቻ ነው። ይኸውም ብዙ አንዲር ያለው ጀበና አንዲሩን ለመቀጠል ስለሚያስቸግር ብዙ ሰዓት ይወስዳል። የሚወስደው ሰዓት ደግሞ ሶስት ባለአንድ አንዲር ጀበናዎችን መስሪያ ሰዓት ያክላል፤ በማለት ብቸኛዋ ባለብዙ አንዲር ጀበና አምራቿ እማ አበባ ይገልፃሉ። ከሚወስደው ጊዜ እና ከስራው አስቸጋሪነት የተነሳ በጥናቱ ከተካተቱት ባለሙያዎች ውስጥ ከእማ አበባ ውጪ ማንም ይህንን ጀበና የመስራት ችሎታ ያለው የለም። ሌሎች ጀበናዎች አምስት እና ስድስት ብር ሲሸጡ እሱ ግን ከሰላሳ እስከ አርባ ብር እንደሚሸጥ፣ የመሸጫ ቦታውም ገበያ ሳይሆን በትዕዛዝ ብቻ የሚበጅ በመሆኑ ያዘዙ ሰዎች ወይንም ጠንቋዮች እቤታቸው ድረስ በመምጣት እንደሚወስዱት እማ አበባ ጨምረው ነግረውኛል። ከዚህ ውጪ ግን እንደሌሎቹ ጀበናዎች ገበያ ላይ ይታዩም።በመሆኑም ከጠንቋዮች እና በማስጠንቆል ከሚጠቀሙት ሰዎች ውጭ ሌላው ማህበረሰብ አይቶት እንደማያውቅ ለማረጋገጥ ችያለሁ።



(ፎቶግራፍ 24) ባለ ሶስት እና ባለ ሰባት አንዲር (መቅጃ) ጀበናዎች

5.1.3.2 የሰታቴ /የትልቅ ድስት/ አሠራር ሂደት

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሰታቴ ሰፋ ያለ የመወጠኛ እቃ ከሚያስፈልጋቸው የሸክላ ቁሶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሰታቴ አገልግሎቱ እንደ ትንሾቹ ድስቶች ለወጥ መስሪያ ሲሆን የሚሠራባቸው የወጥ አይነት ግን የተለያየ ነው፤ የልዩነቱ ምንጭም መጠናቸው ነው፡፡ ይኸውም ትንንሾቹ ለሽሮ እና ለሌሎች አነስ ብለው ለሚሠሩ የወጥ አይነቶች ሲያገለግል ሰታቴ ግን ለማህበር፣ ለሠርግ እና ለመሳሰሉ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ወጥ ለመስራት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ የሰታቴን የአሠራር ሂደት ስናይ መጀመሪያ በመወጠኛው ቁስ ላይ የተፈጨ ገል ይነሰነሳል፡፡ ከዚያ ለሥራ ከተዘጋጀው ጭቃ ተቀንሶ የተፈጨው ገል በተነሠነሠበት መወጠኛ ላይ ይጀምራል፡፡ መጀመሪያ ጭቃው የሚጠፈጠፈው /የሚዘረጋው/ በእጅ ሲሆን ድስቱ እኩል ውፍረት እንዲኖረው ደግሞ በሸንበቆ እየተላገ እንደገና ይስተካከላል፡፡

ከዚያም የተዘረጋው ጭቃ ከመወጠኛ ቁሱ ጋር እኩል ለመሆን ሁለት ሳ.ሜ ሲቀረው ወደ ላይ በእጅ እየተቀለበሰ በሸንበቆ እየተስተካከለ ሊይዝ እንደተፈለገው የወጥ ብዛት የሆዱ ስፋት ተገምቶ ይሠራል፡፡ በመጨረሻም የአፉ ጠርዝ/ከንፈሩ/ ይሠራል፤ይህ ክፍል የሚሰራው በተሠነጠቀው ሸንበቆው ጠርዝ ነው፡፡ በመቀጠልም እንደ ባለሙያዎቹ ፍላጐት፤ በትዕዛዝ የሚሠራ ከሆነ ደግሞ በአሠሪዎቹ ፍላጐት ሁለት ጉጦች ለመያዣነት ወይም ለጌጥ/ውበት እንዲኖረው ሲባል/ ከግራና ከቀኝ ይቀጠልበታል፡፡

ሠታቴ መወጠኛው እና መጠኑ ትልቅ ቢሆንም ለመስራት የሚወስደው ጊዜ ግን እንደ ሌሎች ትልልቅ ቁሶች /ማድጋ፣ጋን፣ቧድና/ አይደለም፡፡ ወይዘሮ መልካም ጤናው "አይ ሠታቴ እንኳን ቀላል ነው፡፡አንድ ጊዜ እንወጥነዋለን ከዚያ ቀልብሠን እየወሰወስን እናሳድግና ወዲያው እንቆርጠዋለን፡፡ እንደ ማድጋ እና ጋን ጠፈፍ ይበል ፡ይቆይ አይባልም፡፡ እዚያው ተኸምሮ እዚያው ነው ሚያልቀው፡፡ ብዙ ጌጥ፣ አንገት፣ ጆሮ፣ ቁመትም ስለሌለው አያቆይም በማለት ስለ አሰራሩ ገልጸውልኛል፡፡(ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 26፣2003ዓ.ም)

ሠታቴ /ትልቅ/ ደስት መጠኑ ከሌሎች አነስተኛ ድስቶች ሥለሚበልጥ ትልቅ መወጠኛ ላይ የሚሠራ ቁስ ቢሆንም የሚወሰደው ጊዜ እና ጉልበት ግን ከሌሎች ትልልቅ ቁሶች የአነሠ ነው፡፡



(ፎቶግራፍ 25) ሰታቴዎች በገበያ ላይ

እስካሁን ከቡሬ ወረዳ በተመረጡ ሁለት ቀበሌዎች ላይ የሚከናወነውን የሸክላ አሠራር ሂደት ሁለት የተለያየ መጠን ባላቸው ቁሶች ማስረጃነት ተመልክተናል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በአካባቢው የሸክላ አሠራር ሂደት በተከታታይነት የሚከናወኑትን ተጨማሪ ሂደቶች እናያለን፡፡

5.1.4 የሸክላ ቁሶችን ማስጌጥና ማድረቅ

የሸክላ ቁሶችን የማስጌጥ ስራ ቁሱ እንደሚሰጠው አገልግሎት ሌሎች ክፍሎቹ /ጆሮው፣አንገቱ፣ አፉ፣መቅጃው/ ተሠርቶ ካበቃ በኋላ የሚከናወን ሥራ ነው፡፡ ጌጡ የሚሠራው ብዙ ጊዜ በባለሙያዎች ፍላጐት ሲሆን ዕቃው በትዕዛዝ የሚሠራ ከሆነ ደግሞ እንደ አሠሪዎቹ ፍላጐት ይወሰናል፡፡ በመስክ ቆይታየ የቁሶችን የአጊያጊጥ ሁኔታ ከባለሙያዎች ቤት፣ ከተጠቃሚዎች ቤት፣ እንዲሁም ገበያ ላይ ተዘዋውሬ

ተመልክቻለሁ፡፡ በምልክታየም የቁሶቹ የአጊያጊያጥ አይነት እና መጠን እንደ ዕቃዎቹ መጠንና አገልግሎት የተለያየ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ይኸውም ትንሽ መጠን ያላቸውና ለቡና ማፍሊያና እና ለቡና ሥነ-ሥርዓት ማጀቢያ የሆኑ ቁሶች /የጣን ማጨሻ እና ጀበና /ከሌሎች ቁሶች በተሻለ ሁኔታ ጌጣጌጥ ይበዛባቸዋል፡፡ የጀበና ጌጥ የሚሠራው ባብዛኛው አንገቱ ላይ እና ከአንገቱ ወረድ ብሎ በሚገኘው የአካል ክፍሉ/ደረቱ/ ላይ ነው፡፡ የጌጦቹ ዓይነት የሚሠራባቸው ነገሮችም ሸምበቆ፣ ቅጠል እና እጅ መሆኑን ከባለሙያዎቹ የቃል መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የማጨሻዎች ልዩነት የመጣው ከተጠቃሚዎች /ከፈላጊዎች/ እምነት ልዩነት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል ፡፡ ይኸውም በአካባቢው ያለው የኦርቶዶክስ እና የሙስሊም እምነት ተከታይ ማህበረሰብ ተመሳሳይ ጌጥ ያለባቸውን /ጌጥ ብዙም ያልበዛባቸው ናቸው/ ሲጠቀም በጥንቆላ የሚተዳደሩ ሠዎች የሚጠቀሙበት ማጨሻ ግን በመጠንም በአይነትም የተለየ ነው፡፡ ይህ የማጤሻ ዓይነት የጠንቋይ ጀበና ተብሎ እንደ ተገለፀው ባለብዙ አንዲር ጀበና ገበያ ላይ የማይታይ ሲሆን የሚሠራውም በትዕዛዝ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ለጠንቋዮች የሚሆን ጀበናና እና የጣን ማጤሻ በመስራት የሚታወቁት ወ/ሮ አበባ እንዲህ ይላሉ፡፡

> *ባለአውሊያዎችማ ምን የማይሉት ነገር አለ፡፡ የጣን ማጨሻውን ቁመት በጉልበት ልክ፣ በደረት ልክ አንዳንድ ጊዜ ደሞ ተጉልበት ግርጌ አርገሽ ሥሪው ይላሉ፡፡ ወርዱም ሌላው ሠው ተሚጠቀምበት ሶስት እጥፍ ይሆናል፡፡ በዚየ ላይ የሠነደሉ መለኮሻ የሌላው ሠው ሁለት ሶስት ነው፡፡ የእነሱ ግን ተሰደሰት እስከ ሰላሳ የሠንደል መለኮሻ ቀዳዳ ያስደርጉበታል፡፡ (ቃለ መጠይቅ ግንቦት 05፣ 2003 ዓም)*

እኔም ከባለሙያዋ ቤት በትዕዛዝ ተሠርቶ የአሰሪዋን መምጣት የሚጠባበቀውን ማጤሻ ለማየት ችያለሁ፡፡ እኔ ያየሁት ጠንቋዮች ከሚያሠሩት የጣን ማጤሻ ትንሹን ነው፡፡ የዚህ ማጤሻ ቁመት 30 ሴ.ሜ ሲሆን፣ የእሳቱ ማድረጊያ ስፋት ደግሞ 20 ሴ.ሜ ነው፡፡ የሠንደል መሰኪያዎቹ ስድስት ሲሆኑ እግሩ ላይ ደግሞ ዓይን ለመሳብ ሲባል ሁለት ዙር የተሠመረ መስመር አለ፡፡ የጠንቋዮች እጣን ማጨሻዎች እንደመጠናቸው በቤት ውስጥ የሚቀመጡበት ቦታም የተለያየ ነው፡፡ ይኸውም ትልቁ እንደ እማ አበባ ገለባ ቁመቱን በደረታቸው ልክ አድርገው

የሚሰሩት በር ላይ የሚቀመጥ ሲሆን ስሙም በረኛ ነው። መካከለኛው ደግሞ ከወጪ በር ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ከሚገኝ ሌላ በር ውስጥ ይቀመጣል። ማጤሻዎች ሌላው ማህበረሰብ ከሚጠቀምባቸው የጣን ማጤሻዎች በቁመት፣ በስፋት እና በሰንደል መሰኪያ ብዛት ይለያል። ሌላው ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸው የጣን ማጤሻዎች የእሳት ማድረጊያ ስፋት በአማካኝ 6 ሳ.ሜ ቁመቱ ደግሞ አምስት ሳ.ሜ ነው። የሠንደል መሰኪያዎች ቀዳዳ ብዛት ደግሞ ከሁለት እስከ አራት ሊደረስ የሚችል ሲሆን ብዛቱም በተጠቃሚዎቹ ፍላጐት ይወሠናል።



(ፎቶግራፍ 26) ጠንቋይ ያልሆኑ የሚጠቀሙበት ማጤሻ



(ፎቶግራፍ 27) የጠንቋዮች ማጤሻ

ጠንቋዮች የሚጠቀሙበት የጣን ማጤሻ ቅርጽና መጠን የሚወሰነው እላያቸው ላይ ባለው ዛር/አውሊያ/ ትዕዛዝ እንደሆነ እማ አበባ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ።

> *እነሱ የሚሰሩት ሸክናውም አንዲሩ ብዙ ነው መጠኑም ትልቅ ነው። ሠንደል መለኮሻው ብዙ ነው። ያው አውሊያቸው እንደሚየዝዛቸው ዛሬ 7፡00 ሰዓት ላይ በባለሰባት አንዲረ ሸክና አፍላልኝ፤ በባለ አሰሩ መለኮሻ ደሞ ሠንደል አርዝሀ አቋድሰኝ? ስለሚሏቸው ተሌላቸው ያሠራሉ። አንዱ አውሊያቸው ደሞ እነሱ አምላካቸው ብዙ አይደል! በባለ ስድስት፣ በባለሶስቱ አንዲር ሸክና በባለ ሠላሳው መለኮሻ ይላቸዋል። የዛን ጊዜም ተሌላቸው ያሠራሉ ታለቸውም በአላቸው ይጠቀማሉ። ብዛቱን ሚያዝዛቸው ላያቸው ላይ ያለው አውሊያ ነው። (ቃለ መጠየቅ፣ ግንቦት 06፣ 2003 ዓ.ም)*

ባለሙያዋ ከሠጡኝ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በጥንቆላ የሚተዳደሩ ሠዎች የሚጠቀሙበትን የእጣን ማጤሻ እና ጀበና ቅርጽና ጌጥ የሚወሰነው በጥንቆላ ስራ እነዲሰማሩ ያስቻላቸው መንፈስ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በባለሰባቱ አንዲር

ጀበና ቡና የሚፈላው ከሌሊቱ ሠባት ሠዓት መቋደስ ለሚፈልግ ዛር እንደሆነ እማ አበባ ነግረውኛል።

በሌላ በኩል ሌላው ማህበረሰብ /በጥንቆላ የማይተዳደረው /የሚጠቀምባቸው ጀበናዎች እና የእጣን ማጨሻዎች ከሌሎች ቁሶች /ከማድጋ፣ ከጋን፣ ከድስት/ በተለየ መንገድ ጌጣቸው የበዛ መሆኑ ቀደም ብሎ ተብራርቷል። ጌጣቸው ለምን በዛ? ብዬ የጠየቅኋት የአካባቢው ተወላጅ ወ/ሮ ምንታምር ገዛኸኝ እንዲህ በማለት መልስ ሠጠችኝ

> *ጌጡማ ያው የቡና ማፍያ ስለሆነ ነው። ቡና ደሞ እኛ ብቻ ሳንሆን፣ ቡናው ሲፈላ ቡናው ጠርቷቸው የሚመጡ የማይታዩ እንግዶች /ዛሮች/ አሉ ይባላል። እነሱ ቡናውን የሚቀምሱት የቡና ማፍያው ማቅረቢያ መጠን ማጨሻው ዕቃ ደስ የሚል ተሆነ ነው። ታለበለዚያ ደስ ሳይላቸው ተቀረ ቡናውን ሳይቀመሱ ተበሳጭተው ከቤት ውስጥ አንዱን "ወግተው (ጐንጠው) ይሄዳሉ ይባላል። (ቃለ መጠየቅ፣ ሚያዚያ 18፣ 2003 ዓ.ም)*

ወ/ሮ ምንታምር ሌሎች የአካባቢው ተወላጆች ጨምረው የነገሩኝ መረጃ እንደሚያሳየው የአካባቢው ማህበረሰብ የቡና ማፍሊያዎችን ጌጣጌጥ ማብዛት ቡና ለሠዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች ቡና የሚወዱ ረቂቅ መናፍስት ጭምር ይጠጡታል ተበሎ ሥለሚታሰብ እና እነሱን ለማስደስት በማሠብ የሚደረግ መሆኑን ለማወቅ ችያለሁ።

በዚህ አካባቢ ጌጣጌጥ የሚበዛበት ሌላው ቁስ ገንቦ ነው። ይህ ቁስ ሆድ፣ አንገት፣ መቅጃ የሚመስል ነገር ግን ለመቅዳት የማያገልግል አንድ ጆሮ እና አንድ አንገት አለው። ገንቦ አሠራሩ እንደማድጋ ሲሆን ከማድጋ የሚለየው ማድጋ ሁለት እና ከዚያ በላይ ጆሮ ሲኖረው ገንቦ ግን አንድ ጆሮ ብቻ አለው። አገልግሎቱም ለመያዣነት/ለመሸከም/ ነው። የጌጣጌጡ መገኛ ብዙዎቹ ረዥም አንገቱ ላይ ሲሆን ከጆሮው ወረድ ብለው ደግሞ ሁለት ዙር ጌጦች አሉት። እንዲሁም ጡት የሚመስሉ አራት ጉጦችም ዙሪያውን ይገኙበታል።

ገንቦ ከሌሎች የመጠጥ/የፈሳሽ ነገር/ መያዣዎች በተለየ ሁኔታ ጌጣጌጡ ሊበዛ የቻለበት ምክንያት ቁሱ ቀደም ባሉት ጊዜያት /በኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት/ ይሰጥ ከነበረው ከፍተኛ የሆነ ባህላዊ አገልግሎት ጋር የተያያዘ ነው። ይኸውም

ገንቦ በዚያ ዘመን ከነበሩ መሳፍንቶች እና የተከበሩ ሠዎች ቤት ብቻ የሚገኝ ሲሆን ለጠጅና ለጠላ ማቅረቢያ በመሆን ያገለግል የነበረ የቁስ አይነት ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ የተከበሩ ሠዎች ሌላ የተከበረ ሰው በእንግድነት ወደ እነሱ ቤት በሚመጣበት ጊዜ እና የተከበረን ሰው ሲጠይቁ ለተጠየቂው ሠው ያላቸውን ክብር እና ፍቅር ለመገለጽ ሲባል በገንቦ ጠላ ወይም ጠጅ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የጌጦቹ ብዛትም ከዚህ አገልግሎቱ ጋር የተያየዘ ሲሆን ዓላማውም የገንቦው ተጠቃሚ የሆኑትን ደግሞ በገንቦ ጠላ ተይዞ ለሚጠየቀው ሰው ያለን የሚሰጡትን ክበር እና ፍቅር ለማሳየት እንዲሁም በዕቃው ውበት ለማስደሰት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ገልጸዋል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ የገንቦ አገልግሎት በዘመኑ ከነበሩት መሳፍንቶች ጋር የተያያዘ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ለዚህ መሠል አገልግሎት ሲውል አይታይም፡፡ ተፈላጊነቱም አናሳ በመሆኑ በሰፊው ጥቅም ላይ ሲውልም አይታይም፡፡ ነገር ግን ባጉና የሚገኙትት የሸክላ ባለሙያ ወ/ሮ መልካም ጤናው የገንቦን ወቅታዊ አገልግሎት “ገንቦ አሁን የሚፈልገው የለም፡፡ ባለአውሊያዎች እና አንድ አንድ ሠዎች ደሞ ለቅዱስ ዩሐንስ ነጭ ጠላ ማድረጊያ ስሪልኝ ብለው ያሠራሉ እንጂ አልሠራም ትቸዋለሁ፡፡ ሚገዛው ሰለሌለ ኪሳራ ነው ሚሆንብኝ” (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 20፣ 2003 ዓ.ም)

ወ/ሮ መልካም የተባሉት መረጃ አቀባይ ባለአውሊያዎች ገንቦን የሚጠቀሙት መንፈሳቸው በዚያ እንዲገለገሉ ሰለሚየዝዛቸው ሲሆን ሌሎች ሠዎች ደግሞ ለቅዱስ ዮሐንስ /ለእንቁጣጣሽ/ ነጭ ጠላ ማድረጊያነት የሚመርጡተ ቆሌያቸውን ለማስደሰት መሆኑን ጨምረው ነግረውኛል፡፡

በአካባቢው የሚበጁት የገንቦ አይነቶች ሁለት አይነት ሲሆኑ ልዩነታቸውም በመጠናቸው ወይም በመያዝ አቅማቸው ነው፡፡ ትንሹ የገንቦ አይነት የግብር ገንቦ ሲባል ተለቅ ያለው ደግሞ አሳዳሪ በመባል ይታወቃል፡፡ አሳዳሪ የሚባለው ቤት ውስጥ ተቀምጦ ለክበር በዓላት ቀን የተከበሩ እንግዶች ማስተናገጃነት የሚያገለግል ሲሆን የግብር ገንቦ በማንኛውም ቀን የቤተሰብ አባላት ጠላ እና ጠጅ አቅረበው የሚጠቀሙበት ነው፤ እንዲሁም የቤተሰብ አባላት ወደ ሥራ /አረም ማረም፤

ጉልጓሎ፤ መውቃት ወዘት/ በሚሄዱበት ጊዜ ጠላ ወደ ሥራ ቦታ ለመውሰድ የሚያገለግል የገንቦ አይነት ነው፡፡ የግብር ገንቦ በማንኛውም ሠው ቤት ሊገኝ አሳዳሪ የሚባለው ግን በመሳፍንቶች ቤት ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡ አባ ገላው አበጀ የተባሉት የ85 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ የገንቦን ዓይነቶችና ሥሞች እንዲሁም አገልግሎቶች እንዲህ በማለት አጫውተውኛል፡፡

> *ገንቦ ማለት ሁለት መልክ አለው፡፡ አንዱ ትልቅ ሲሆን ስሙም አሳዳሪ ይባላል፡፡ ትንሹ ደሞ የገብር ገንቦ ነው ምንለው፡፡ አሳዳሪ ተማንም ጢሠኛ ቤት ውስጥ አይገኝም፡፡ ተደጃዝማች፣ ተፊታውራሪ፣ተጉበዝ አለቃ እና ነጭ ለባሽ ቤት ነው የሚገኝ ስሙም ተአሳዳሪ ቤት ውስጥ የሚገኝ የክብር ዕቃ በመሆኑ ነው አሳዳሪ የተባለ መጠኑም ወደል ነው፡፡ /ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 09፣ 2003 ዓ.ም/*



(ፎቶግራፍ 28) ማእዘንት ላይ የተቀመጠ ገንቦ

ከማስጌጥ ቀጥሎ የሚከናወነው የሸክላ ሥራ ሂደት ማድረቅ ነው፡፡ የማድረቁ ሥራ የሚከናወነው በሁለት አይነት መንገድ ሲሆን አንደኛው በነፋስ ሁለተኛው ደግሞ በፀሐይ ነው፡፡ አንድ ቁስ ተሠርቶ አስፈላጊው ጌጥ ከተደረገበት በኋላ ቤት ውስጥ በአፉ ተደፍቶ ይቀመጥና በንፋስ ብቻ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ የሚደፋበት ምክንያትም ለመድረቅ ካለው ምቹነት የተመረጠ የአቀማመጥ ብልሃት መሆኑን ባለሙያዎች ነግረውኛል፡፡ አንድ ቁስ ቤት ውስጥ በነፋስ ለመድረቅ የሚወስደው ጊዜ እንደ ዕቃው መጠን የተለያየ ነው፤ ትንሽ መጠን ያላቸው ዕቃዎች በአንድ ቀን እና በሁለት ቀን ሲደርቁ ትልልቆቹ ግን እስከ ስምንት ሊቆዩ ይችላሉ።ክረምት ከሆነ ደግሞ ከሳምንትም ሊረዝም ይችላል፡፡ ቁሶቹ መድረቃቸው ከታወቀ ወደ ውጭ ይወጡና በደንብ በተጠረገና ከቆሻሻ በፀዳ መሬት ላይ ለአንድ ቀን ሙሉ በፀሐይ እንዲደርቁ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ፀሐይ ላይ ከመደረጋቸው በፊት ቤት ውስጥ

በነፋስ በትክክል መድረቃቸው መረጋገጥ መቻል አለበት፡፡ ሳይደርቁ ፀሐይ ላይ ከተደረጉ ግን ይሰነጠቃሉ፡፡

ባለሙያዎቹ ቤት ውስጥ እንዲደርቁ የተቀመጡትን ቁሶች በተገቢው መንገድ መድረቃቸውን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙበት ብቸኛው አማራጭ በጥፍራቸው ወጋ አድርጎ በማየት መሆኑን ገልፀውልኛል፡፡ ይህንንም የአሠራር ዘዴ ከረዥም ጊዜ ልምዳቸው የአገኙት እንጂ በስልጠና ወይም በሌላ መንገድ የለመዱት አለመሆኑን ጨምረው ገልፀውልኛል፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ የሆኑት እና ጀኳ ዮሐንስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚኖሩት ወይዘሮ ውበት የማድረቅን ሂደት እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፡፡

> *አንድ ዕቃ ወጥነን ሰንጨርስ ቤት ውስጥ ትንሽ ተሆነ ሁለት ቀን አንድ ቀን፣ ትልቅ ተሆነ ደሞ እስተ ሳምንት ክረምት ተሆነ እስተ ሁለት ሳምንት ድረስ ተደፍቶ ይቀመጣል፡፡ ጋን ትልቅ በመሆኑ እስተ ሁለት ሳምንት ይቆያል፡፡ ተዚያ በኋላ በእጃችን ሚጠን አይተን በጥፍራችን ጭቃው ተሚጠ ታልመጣ ደርቋል ማለት ነው፤ ጭቃው ተጥፍራችን ጋር ተመጣ ደሞ ይቀረዋል ማለት ነው፡፡ ተደርቀ በኋላ በጋ ተሆነ እና ሙሉ ቀን ጠሃይ ተሆነ አንድ ቀን ሙሉ ሲከርክር ይውላል ክረምት ተሆነ ግን ሁለት ቀን ይቆያል ተዚያ ምሽት እንተኩሠዋለን፡፡* (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ20፣ 2003 ዓ.ም)



(ፎቶግራፍ 29) ከቤት ውጪ በመድረቅ ላይ ያሉ የላቀች ምድጃዎች

5.1.5 የሸክላ ቁሶችን መተኮስ

ይህ በባለሙያዎቹ የሸክላ አሠራር ሂደት የመጨረሻው ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሂደት በኋላም በአካባቢው አጠራር "ማሟሸት" የሚባል ሂደት መኖሩን ቀደምደ ሲል ተገልፏል፡፡ ቁሶቹ የሚሟሹበት ጥሬ ዕቃ የሸክላ ቁሱ እንደሚሠጠው የአገልግሎት አይነት ይለያያል፡፡ ይኸውም ለቡና ማፍያ የሚያገለግል ከሆነ ጀበናው እሳት ላይ ተጥዶ በደንብ ከጋለ በኋላ የቡና አተላ ይጨምርበታል፡፡ ከዚያ በኋላ ቢያንስ ለአንድ ሠዓት ያህል እንዲንተከተክ ይደረጋል፡፡ ይህ ድርጊት ከተከናወነ በኋላ ጀበናው አገልግሎት መስጠት ይጀምራል፡፡ ይህ ሳይሆን ቢቀር እና ጀበናው ውስጥ በቀጥታ ውሃ ከተጨመረበት ይሠበር እና ከአገልግሎት ውጭ ይሆናል፡፡

ጀበናን የማሟሸት ሂደት ይህን የሚመስል ገጽታ ሲኖረው የድስት እና የማድጋ ዘሮች የሚሟሹበት ሂደት ደግሞ የተለየ ነው፡፡ እነዚህን ቁሶች ለሥራ ዝግጁ ለማድረግ መጀመሪያ ኩበት ወይም የበቆሎ "ቆረቆንዳ" እና ሌሎችም እንጨቶች /በአጭር በአጭሩ እየተቆረጡ/ ማድጋው ወይም ድስቱ ውስጥ ይጨመራሉ፡፡ ከዚያም እሳት ይጨመርባቸውና እየጨሱና እየነደዱ ሸክላውን እንዲያጠነክሩት ይደረጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከግማሽ ቀን በላይ /ቢያንስ ለስምንት ሠዓት ያህል/ ከቆዩ በኋላ ከውስጣቸው የገባው እሳት እና እንጨት ወጥቶ እንዲቀዘቅዙ ይደረጋሉ፡፡ ከዚያም በቀዝቃዛ ውሃ ታጥበው አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ፡፡ 09



(ፎቶግራፍ 30) ድሰት ሲሟሽ

መተኮስ የሚባለው የሸክላ ሥራ ሂደት የሚከናወነው ከባለሙያዎች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ በቋሚነት ተዘጋጅቶ በተቀመጠ ጉድጓድ ውስጥ ነው። ጥናቱ በአተኮረባቸው አካባቢዎች የሚኖሩት ሸክላ ሠሪዎች ቁሶችን ሠርተው፣ አስጊጠው፣ ከዚያም በነፋስና በፀሐይ ካደረቋቸው በኋላ ቁሶቹ የበለጠ ጠንካራ እንዲሆኑ እና አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ እንዲሆኑ በእሳት ይተኩሷቸዋል። የሸክላ ቁሶችን ለመተኮስ ሠፋ ብሎ የተቆፈረ ጉድጓድ፣ እንጨት፣ ኩበት፣ ሸቦ እና ጭድ ያስፈልጋሉ። እነዚህ ነገሮች ከተዘጋጁ በኋላ ለመተኮሰ የተዘጋጁት ቁሶች እንደመጠናቸው በአንድ ላይ ሠብሰብ ብለው እና ተደርደረው ከስር እንጨትና ኩበት፣ ከዚያ ሸክላዎች፤ በሸክላዎች ላይ ደግሞ ሸቦ እና ጭድ ተጨምሮባቸው እሳት ይጨመርባቸዋል።

አንድ ጊዜ የሚተኮሱት ዕቃዎች መጠናቸው ተመሳሳይ መሆን አለበት። ከዚህ ውጪ ግን ትንንሽ መጠን ያላቸው ከትልቆቹ ጋር ተቀላቅለው ከተተኮሱ ትንንሾቹ ቶሎ ስለሚበስሉ ትልልቆቹ ደግሞ ከግዘፈታቸው የተነሳ ለመብሠል ብዙ ጊዜ ስለሚያስፈልጋቸው ትንሾቹ በእሳት ብዛት ይጐዳሉ። ስለዚህ ሁሉም እንደ እየአቅማቸው ሠብሰብ ብለው ይተኮሳሉ። ወ/ሮ መልካም ጤናው ቁሶችን ለመተኮስ የሚፈጀው ጊዜ ከ10-12 ሠዓት እንደሆነ ይገልፃሉ። "ማልዳ አንድ ሠዓት ላይ ለመተኮስ ጉድጓድ ውስጥ የተደረጉ ዕቃዎች ቀኑን ሙሉ ውለው ኾምበር ዘቅዘቅ ስትል ወደ 12፡00 ሠዓት አካባቢ ይወጣሉ። ማታ አንድ ሠዓት አካባቢ ተገቡ ደግሞ ወፍ ጭጭ ሲል ተነስተን ተጉርጓድ እናወጣቸዋለን።" በማለት ይገልጹታል። (ቃለመጠይቅ ግንቦት 01፣ 2003 ዓ.ም)

የተተኮሱት ቁሶች በተገቢው መንገድ ተገቢውን እሳት ማግኘታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ከጉድጓድ እየወጡ ለተተኮሱ ሸክላዎች መቀመጫነት በተዘጋጀው ጐጆ ቤት ውስጥ ተደርድረው ይቀመጣሉ። ከዚያም በማግስቱ ትንንሽ ከሆነ ከሸምበቆ በተሠራ ቅርጫት ማድጋ እና ጋን ከሆኑ ደግሞ በጀርባ ታዝለው ወደ ገበያ ይሄዳሉ።

በወረዳው የሸክላ ገበያ ቀናት ማክሰኞ እና ቅዳሜ ናቸው። ባለሙያዎችም ከእነዚህ ቀኖች አንድ ቀን ቀድመው ሰኞ እና አርብ የደረቁ ሸክላዎቻቸውን በመተኮስ ለገበያ ያቀርባሉ። ባለሙያዎቹ ከሸክላ ሥራ በተጨማሪ የግብርና ሥራን ጐን

ለጐን ስለሚሠሩ የሸክላ ቁሶችን በተጠቀሱት ቀናት ሁል ጊዜ ያለማቋረጥ ላያቀርቡ ይችላሉ።።

5.2 የሸክላ ውጤቶች ጠቀሜታና ወቅታዊ ሁኔታ

በቡሬ ወረዳ ቁጥራቸው በርከት ያሉ የሸክላ ቁስ አይነቶች ይገኛሉ።። ቁሶቹ እንደአይነታቸው አገልግሎታቸውም ሠፋ ያለ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው።። ሆኖም ከመስክ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የሸክላ ቁሶች የአገልግሎት ደረጃ ቀደም ካሉት ጊዜያት ይልቅ አሁን እየቀነሰ መጥቷል ።። በዚህ አካባቢ ቀደም ባሉት ዘመናት ምን አልባትም የፋብሪካ ውጤት የሆኑት ቁሶች በስፋት መመረት ከመጀመራቸው አስቀድሞ መጠነ ሠፊ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ቁሶች እንዳሉ ቢታወቅም፤ በዚህ ወቅት ግን መመረትም ሆነ አገልግሎት መሰጠት ያቆሙ ቁሶች ያሉ መሆናቸውን በመስክ ቆይታዬ ተዘዋውሬ ካያኋቸው ቀበሌዎች ለማወቅ ችያለሁ።።

በዚህ ክፍል ቁሶቹን ከጥንት እስከ ዛሬ የሚበጁና ጥቅም የሚሰጡ፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት መጠነ ሠፊ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ በአሁኑ ወቅት መሠራትም ሆነ አገልግሎት መሰጠት የአቆሙ፣ ጥቅም ላይ የመዋላቸው ደረጃ በመቀነሱ በትዕዛዝ የሚሠሩ፤ እንዲሁም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሠራት የጀመሩና በሰፊው አገልግሎት ላይ እየዋሉ የሚገኙ ቁሶች በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች በመከፋፈል እንመለከታለን።።

5.2.1 እስካሁን የሚመረቱ እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ቁሶች

በዚህ ወረዳ ባህላዊ የሸክላ ሥራዎች መሰራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ /ምንም እንኳን መቼ መሠራት እንደጀመሩ የሚገልጽ መረጃ ባይገኝም/ እነሱን ሊተካ የሚችል የፋብሪካ ውጤት የሆነ ቁስ ቢመረትም በባለሙያዎቹ እየተመረቱ አገልግሎታቸው ሳይቋረጥ አሁን ድረስ የዘለቁ ቁሶች ይገኛሉ።። ከእነዚህም ውስጥ ጋን፣ ማድጋ፣ ቧድና፣ሸንክላ፣ ምጣድ፣ ድስት፣ ቶፋ፣ ድንጉኝ የሚባሉት ቁሶቹ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ።። ከላይ እንተደገለፀው የእነዚህን ቁሶች አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ ሊተካ የሚችል ቁስ በዘመናዊ መንገድ ቢመረትም፣ ነገር ግን ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ካላቸው የረዥም ጊዜ ቁርኝት የተነሳ በቀላሉ ከአገልግሎት ውጪ ሊሆኑ አይቻሉም።።

ምክንያቱም እነዚህ ቁሶች ለወረዳው ነዋሪ ማህበራዊ ወይም የቤት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ማህበረሰቡ አቅሙ በፈቀደው መጠን መሠረታዊ ፍላጐቱን አሟልቶ እንዲኖር ከሚያስችሉት ቁሶች መካከል ዋነኛዎቹ በመሆናቸው ነው፡፡ ወደፊት ሠፋ አድርገን እንደምናየው ቁሶቹ ለዚህ አካባቢ ማህበረሰበ ከቤት ውስጥ አገልግሎት በተጨማሪ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ማንነቱን እንዲገልጽ በማስቻልም በከፍተኛ ደረጃ ጠቅመውታል፡፡ ቁሶቹ አገልግሎት መስጠታቸውን ሳያቆሙ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደተወደዱ ሊቀጥሉ ያስቻላቸው ሌላው ምክንያት ደግሞ በእነዚህ ቁሶች የተዘጋጀው/የተሠራው/ ምግብ እና መጠጥ በዘመናዊ ቁሶች /በላስቲክ፣ ከብረት እና ከቆርቆሮ ቁሶች ከተሠራው ምግብ የተሻለ ጣዕም እና በረከት አለው ተብሎ የሚታመን መሆኑ ነው፡፡

5.2.2 መሰራትና ማገልገል ያቆሙ የሸክላ ቁሶች

በአካባቢው መሠራት እና አገልግሎት መስጠት የአቆሙ ቁሶች ናቸው ተብለው በመረጃ አቀባዮች የተገለፁት ቁሶች ስያሜ ረዥት፣ አጋላ፣ ማሠሮ እና የሸክላ ስኒ /ፍንጃል/ ናቸው፡፡ የእነዚህን ቁሶች አገልግሎት ስናይም ረዥት በፋብሪካ የሚመረተውንና ብረት ምጣድ ተብሎ የሚጠራው ቁስ ምትክ ሲያገለግል የነበረ ቁስ ነው፡፡ ይኸውም ረዥት በወቅቱ የተለያዩ ጥራጥሬዎችን ለመቁላት ቂጣ እና ሌሎች የዳቦ ዘሮችን ለመጋገር የሚያስችል ቁስ ነበር፡፡ አጋለ ደግሞ ሥጋ፣ ንፍሮ ፣ እንዲሁም ለማርሳ/ለክክ/ ወጥ መስሪያ በመሆን ሠፋ ያለ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ቁስ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው ሲበጅም ሆነ ሲሰራ አይታይም፡፡ ምክንያቱም ከአጋላ በተሻለ ሁኔታ በአጭር ጊዜ፣ በትንሽ የማገዶ እንጨት የሚፈለገውን ምግብ ለማዘጋጀት የማያስችል ጉርድ በርሚል /ጐላ/ ተብሎ የሚጠራ ከበርሚል ቁራጭ የሚሠራ ዘመናዊ ቁስ በመምጣቱ ነው፡፡ ማሠሮ በመባል የምትጠራዋ ቁስ ደግሞ ለድቁስ/አዋዜ/ ማስቀመጫ /ለጉችማነት የምታገለግል/ ቁስ ስትሆን ሸንክላ በመባል ከምትጠራው የማድጋ ዘር ጋር በመጠንና በቅርጽ ተቀራራቢ ስትሆን ልዩነታቸውም ሸንክላ ሁለት ጀሮ ብቻ ሲኖራት ማሠሮ ግን አራት ጀሮ ያላት የሸክላ ዕቃ ነች፡፡

የረዥትን፣ የአጋላንንና የማሠሮን ጥቅም በሚመለከት በቡሬ ወረዳ ተወልዳ ያደገችው ወ/ሮ መድሃኒት ዘገየ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡

የሸህላማ ጥቅሙም አይነቱም ብዙ ነበር። ረኽት የሚባል ነበር እናንተ አልደረሳችሁበተም እንጅ እኔ ሰዳር ደረቆት የተቆላው በእሱ ነበር። ሉጋላ እንኳ በእናንተ እድሜም ነበር። የንፍሮ መቀቀያ፣ የሲጋ መቀቀያ፣ የማርሳ ወጥ መሰሪየ እናደርገው ነበር። አሁን ጮላ መጥቶ አሰተወን እንጅ፣ ማሠሮም ያው ለድቁስ ጉችማ ነበረች። እሷን እንኳ ቅልና ጮማ ጉችማ ማድረግ ሰንጀምር ኢህአዴግ ተገባ ወዲህ ነው የቀረች። (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 17፣ 2003) ።

ቀደም ባሉት ጊዜያት አገልግሎት ሲሠጥ የነበረ እና በዚህ ወቅት መበጀት የአቆመ እና ከአገልግሎት ውጪ የሆነው ሌላው ቁስ የሸክላ ስኒ /ፍንጃል/ ነው። ይህ ቁስ ለቡና መጠጫነት ያገለግል የነበረ ቁስ ነው። መጠኑም ሆነ ቅርጹ በዚህ ወቅት ለቡና መጠጫ የሚያገለግሉትና መያዣ ጆሮ የሌላቸውን በፋብሪካ የሚመረቱ ስኒዎችን የሚመስል ገጸታ እንዳለው መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል። በዘመናዊ መንገድ ከሚመረቱት ጆሮ የሌላቸው ሥኒዎች የሚለየው የተሠራበት ንጥረ ቁስ አፈር መሆኑና በተለየዩ ቀለማት አለማሸብረቁ ነው።

እነዚህ ከላይ የተገለፁት አራት የሸክላ ቁሶች ጥናቱ በአተኮረበት አካባቢ ለረኽም ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት ግን ባለመ.ያዎቹም የሚገዛቸው ሠው ባለመኖሩ አያበጇቸውም፤ እነሱም አይጠቀመ.ባቸውም። ማህበረሰቡም ከእነሱ የተሻለ ውበት እና መጠን ያላቸውን የፋብሪካ ምርቶች በማግኘቱ አይፈልጋቸውም። በመሆኑም ከማሠሮ ውጪ ሌሎችን ከገበያም ሆነ ከተጠቃሚዎች ቤት ማግኘት ስላልተቻለ ቅርፃቸውን በቪዲዮም ሆነ በፎቶ ቀረፃ ለማስቀመጥ አልተቻለም። ማሠሮ የተበላችዋን ዕቃ ግን ሻኳ ዮሃንስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ከሚኖሩት የ70 ዓመት አዛውንት ቤት ውስጥ ስላገኘኋት ምስሏን በፎቶ ለመያዝ ችያለሁ።



(ፎቶግራፍ 31) ማሰሮ

እስካሁን በወረዳው ቀደም ባሉት ጊዜያት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ እና አሁንም በመስጠት ላይ የሚገኙ እንዲሁም ድሮ ሲያገለግሉ የነበሩ እና አሁን ደግሞ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ቁሶችን ምንነትና ተግባራት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ የነበራቸው ተፈላጊነት ቀንሶ በትዕዛዝ የሚሠሩ ቁሶችን ምንነትና ተግባራት እንመለከታለን፡፡

5.2.1.3 ተፈላጊነታቸው በመቀነሱ በትዕዛዝ ብቻ የሚሠሩ የሸክላ ቁሶች

እነዚህ ቁሶች በመጥፋትና በመረሳት ላይ የሚገኙ የሸክላ ቁሶች ናቸው፡፡ በትዕዛዝ የሚሠሩት ቁሶች የሚሰጡት አገልግሎት በፋብሪካ በተመረቱ ቁሶች በመተካቱና እንዲሁም የእነዚህ ቁሳች ባህላዊ አገልግሎት አሁን በሚገኘው ማህበረሰብ ዘንድ ችላ መባሉ ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ቁሶችም በአካባቢው ስያሜ መሠረት ፅዋ፣ግንቦ እና ቤተ-ሞገስ በመባል ይጠራሉ፡፡ ጽዋ ለጠላ መጠጫነት የሚያገለግል በተለይም ቤተክርስያን ለሚከሠኑ የጽዋ ማህበራት /ለማርያም፣ ለገብርኤል ለመድሃኒዓለም ወዘተ/ መጠጫ በመሆን ለረዥም ጊዜ ሲያገለግል የቆየ ቁስ ነው፡፡ የጽዋ አካላዊ ገጽታ ሲታይ ከአፋ ሠፋ ያለ፣ ከታች ጠበብ ያለ እግር ያለው ከቀንድ የሚሠሩ ዋንጫዎችን የሚመስል ቅርጽ የያዘ ዕቃ ነው፡፡ ይህ ቁስ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ ስናይ ግን ከላይ የተገለፀውን ማህበራዊ አገልግሎት ሲሰጥ አይታይም፡፡ ምክንያቱም የጽዋን አገልግሎት የሚተካና በክብደት እና በውበት እንዲሁም ካለው ጥንካሬ

አንፃር የተሻለ ገጽታ ይዞ የተሠራው ነጭ ኩባያ በፋብሪካ ተመርቶ በሰፊው መሠራጨቱ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ወቅት የጽዋ አገልግሎት ለሠርግ ሥርዓት መከወኛ ብቻ ሲሆን የሚሠራውም በሠርግ ወቅት በሠርገኞች ትዕዛዝ መሆኑን ከባለሙያዎች እና ከተጠቃሚዎች በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ገንቦ እና ቤተሞገስ ደግሞ የነበራቸው ጥንታዊ አገልግሎት የተጠቃሚዎችን ክብርና ዝና ከማሳየት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ወቅት እነዚህ ሁለት ቁሶች ይህን አገልግሎታቸውን የሚሰጡበት ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁለት ቁሶች የሚሠሩት በትዕዛዝ ነው፡፡ አገልግሎታቸውን ሥናይም ገንቦ ጌጣጌጥ ሥለሚበዛበት አንድ አንድ ሰዎች ለበዓል ጠላ ማቅረቢያ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ቤተ-ሞገስ ደግሞ በጠንቋዮች ቤት አናት ላይ በመሆን ቤቱ የእነሱ መሆኑን በትዕምርትነት የሚገልጽ ሲሆን በትዕዛዝ እንዲሠራ የሚያደርጉትም ጠንቋዮች ብቻ ናቸው፡፡ እንደ ቀድሞው ጊዜ በሐብታሞችና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተለየ ክብር በሚሠጣቸው ግለሰቦች ቤት አናት ላይ በመሆን ክብርን ሲገልጽ አይታይም፡፡


5.2.1.4 በቅርቡ መሠራት የጀመሩና በሠፊው አገልግሎት መስጠት ላይ ያሉ ቁሶች በወረዳው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሠራት የጀመሩና ለገጠሩም ሆነ ለከተማው ማህበረሰብ ሰፋ ያለ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ቁሶች አሉ፡፡ የቁሶች አገልግሎት ከሠል እና እንጨት በማንደድ ለተለየዩ ምግቦችና መጠጦች ማብሠያ /ማዘጋጃ/ መሆን ነው፡፡ ቁሶቹ መሠራት ከመጀመራቸው በፊት የነበረውን ክብረት እና ከቆርቆሮ የሚሠራውን ፈርሜሎ የተባለ የከሠል ማንደጃ የተኩ ናቸው፡፡

እነዚህ ቁሶች ሶስት አይነት መልክ /አካላዊ ገጽታ/ አላቸው፡፡ ሁለቱ የማንደጃ አይነቶች ተቀራራቢ ገጽታ ሲኖራቸው ለቁሶች/ለድስቶች፣ ብረት ድስቶች፣ ማንቆርቆሪያዎች/ መጣጃ የሚሆን ጉልቻ በመጨመር እና ባለመጨመር ብቻ ይለያያሉ፡፡ ሁለቱም የከሰል ማንደጃዎች ሲሆኑ መጠናቸውም ተመሳሳይ ነው፡፡ ምግብ ለማብሠል የሚጣዱባቸው ቁሶችም የእነሱን መጠን እና የመሸከም ችሎታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ማንደጃዎች መካከለኛ እና ትናንሽ በሆኑ ድስቶች ወጥ ይሠራባቸዋል፣ ውሃ ይሞቅባቸዋል፣ ከዚህም በተጨማሪ


በአካባቢው የሚሠሩት ጀበናዎች ከእነሱ የመሸከም አቅም ጋር ተመጣጣኝ በመሆናቸው እነዚህ ቁሶች በአብዛኛው ለቡና ማፍያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

እነዚህ ማንደጃዎች የእሳት ወይም የከሠል ማስቀመጫ ክፍል ሲኖራቸው፣ የዚህ ክፍል የታችኛው ወለል/ቂጣቸው/ ላይ ለአየር ማስገቢያ እና ለአመድ ማራገፊያ የሚሆን ወንፊት የሚመስል ክፍል አላቸው፡፡ ከዚህ ክፍላቸው ጋር ተያይዞ ደግሞ መሬት ላይ እንዲቆሙ የሚያስችላቸው እግር ሲኖራቸው እግራቸው ላይም ለአየር ማስገቢያ የሚሆን አራት ማዕዘን ወይም ክብ ቅርጽ ያለው ክፍተት አላቸው፡፡ /ከእነዚህ ሁለት ተመሳሳይ ገጽታ ካላቸው ማንደጃዎች ውስጥ አንደኛዋ ለእሳት ማስቀመጫ ክፍሏ ላይ ሶስት ጉጦች አሏት፡፡ የጉጦቹ አገልግሎትም የሚዘጋጀውን ምግብ ወይም መጠጥ የያዘውን ቁስ ማስቀመጥ ሲሆን ጉልቻ በመባል ይጠራሉ፡፡ ሌላኛዋ ግን እነዚህ ክፍሎች የሌሏት ስትሆን በዚች ማንደጃ የሚጣደው ነገር በቀጥታ እሳቱ ላይ ያርፋል ወይም ይቀመጣል፡፡ ቁሶች በአካባቢው ማህበረሰብ ላቀች የሚባል ስያሜ ያላቸው ሲሆን ሁለቱን ለይቶ መጥራት ካስፈለገም ባለጉልቻዋ ላቀች እና ጉልቻ የሌላት ላቀች እንደሚባሉ የሸክላ ባለሙያዎች እና ተጠቃሚው ማህበረሰብ ይገልፃል፡፡

ላቀች የሚለውን ስያሜ ያገኙት ከሚሰጡት አገልግሎት ማለትም ከፍጥነታቸው፣ ከዋጋቸው ርካሽነት /በአማካይ አምስትና ስድስት ብር መሆናቸው/፣ ከከሠል ቆጣቢነታቸው አንፃር ቀደም ብሎ በወረዳው አገልግሎት ሲሰጥ ከነበረው የብረት ወይም የቆርቆሮ ማንደጃ ተሽለው በመገኘታቸው ነው፡፡



(ፎቶግራፍ 32) ጉልቻ የሌላት ላቀች



(ፎቶግራፍ 33) ጉልቻ ያላት ላቀች

ሶስተኛው አይነት የማንደጃ ዓይነት ተንከርተት ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን ስያሜው ተንቀሳቃሽ ምድጃ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ተንከርተት አገልግሎቱ ለእንጨት ማንደጃ ሲሆን የስያሜው መነሻም አግራሞት /መደነቅ መሆኑን/ የቁሱ ተጠቃሚዎች አስረድተውኛል። ይህ ቁስ ከመምጣቱ በፊት ምድጃ በመሆን ያገለግል የነበረው መሬት ሲሆን ለጉልቻነት የማያገለግሉትም ሶስት ድንጋዮች ወይም ከሸክላ የሚሠሩ ምዝ በመባል የሚተወቁት ጉልቻዎች ናቸው። ይህ ምድጃ መሬት ላይ የሚዘጋጅ በመሆኑ አንድ ቦታ ላይ ብቻ በቋሚነት የሚያገለግል ነው። ተንከርተት ግን ከዚህ በተቃራኒው ከቦታ ቦታ እንደልብ በማንቀሳቀስ በተፈለገው ቦታ ለመስራት የሚያገለግል ምድጃ ነው። በመሆኑም ቁሱ እንግዳ የሆነበት አንድ አርሶ አደር ተንከርተት ብሎ ሰየመው፣ ከዚያም ስያሜው ከአንዱ ወደ አንዱ እየተዛመተ ቁሱ ተንከርተት የሚለውን ስያሜ ያዘ እንጅ የመጀመሪያ ስሙ የእንጨት መቆጠቢያ እንደነበር የሸክላ ባለሙያዎች ይገልፃሉ።

ይህ ማንደጃ ከእነ ላቀች ከፍ ያለ መጠን የለው ሲሆን በትልልቅ ድሰቶችና ብረት ድስቶች ወጥ ለመስራት፣ ውሃ ለማፍላት ወዘተ ያገለግላል። ከዚህም በተጨማሪ እንጨት የሚቆጥብ እና የማገዶ እንጨቱ በቀላሉ እንዲያያዝ ስለሚረዳ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተወዳጅነትንና ተፈላጊነትን አትርፏል። ባለሙያዎችም ከሌሎች ቁሶች በበለጠ በስፋት እያበጁ ለገበያ ያቀርቡታል። እኔም ቡሬ ገበያ በመሄድ ባደረግሁት ተደጋጋሚ ምልከታ ቁሱ ያለውን ሠፊ አቅርቦት ለማየት ችያለሁ።



(ፎቶግራፍ 34) ገበያ ላይ ለሽያጭ የቀረቡ ተንከርተቶች

ተንከርተት ሁለት ቦታ ላይ የተቀጠሉ ጉልቻዎች አሉት አንድ ቦታ /በአንድ ዙር/ የሚቀጥሉት ጉልቻዎች ሶስት ሲሆኑ የሁለቱ ቦታ ጉልቻዎች አጠቃላይ ብዛት ስድስት ነው የመጀመሪያዎቹ ሶስት ጉልቻዎች ከእሳት ማስቀመጫ ክፍሉ ጫፍ ላይ የሚቀጠሉ ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም ለትናንሽ ብረት ምጣዶች መጣጃነት ነው፡፡ ሁለተኛ ዙር ላይ የሚቀጥሉት ጉልቻዎች ከላይኞቹ ዝቅ ብለው የሚገኙ ሲሆን ለሸክላ ድስት ለብረት ድስት፣ ለማንቆርቆሪያዎች እና ለጀበናዎች መጣጃ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ፡

እስካሁን ከቀረበው ማብራሪያ እና ትንተና ጥናቱ በአተኮረበት አካባቢ የሚበጁ ቁሶችን ወቅታዊ ሁኔታ አይተናል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ከላስቲክ፣ ከብረት፣ ከቆርቆሮ እና ከሌሎች ጥሬ እቃዎች በስፋት በመመረታቸው ሳቢያ የጠፉ እና በመጥፋት ጐዳና ላይ የሚገኙ ቁሶች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5.3 የሸክላ ቁሶች ጠቀሜታ

በወረዳው በባህላዊ መንገድ የሚበጁት የሸክላ ቁሶች ለአካባቢው ማህበረሰብም ሆነ ለባለሙያዎች ከጥንት ጀምረው እስከዛሬ ከፍተኛ ጥቅም በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ጥቅማቸውም ከዕለት ምግብና መጠጥ ከማዘጋጃነት ጀምሮ ባህልን እምነትን፣ ክብርንና ዝናን እስከ መግለጽ ይዘልቃል፡፡በመሆኑም ቁሶቹ የሚሰጡትን አገልግሎት መሠረት አድርጐ በመመደብ እንደሚከተለው ትንተና ይደረግባቸዋል፡፡

ቁሶቹ የሚሰጡት ማህበራዊ አገልግሎት እና በሌላ በኩል ደግሞ ባህልን፣ እምነትን፣ እና ክብርን በመግለጽ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ይብራራል።

5.3.1 የሸክላ ቁሶች ማህበራዊ ጠቀሜታ

በጥቂቱም ቢሆን ቀደም ብሎ በቀረበው ንዑስ ርዕስ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአካባቢው ባለሙያዎች የሚዘጋጁ የሸክላ ቁሶች ቤት ውስጥ ለምግብ ማዘጋጃነት እና ለማብሰያነት፣ የሚጠጡ ነገሮችን ለማዘጋጀት እና ለመያዣነት እንዲሁም ለምግብ እና መጠጥ ማቅረቢያነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን ተመልክተናል። ይህን ጉዳይ እንደሚከተለው በዝርዝር እናያለን።

5.3.1.1 ለጠላ እና ጠጅ ማዘጋጃና ማቅረቢያ የሚሆኑ ቁሶች

በአካባቢው ጠላ በጣም የሚወደድ እና በተለይም በአመት በዓል ወቅት ከሁሉም ቤት የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ ነው። የዚህ መጠጥ ባህላዊነት የሚጀምረው በአዘገጃጀት ሂደቱ ብቻ ሳይሆን ለማዘጋጃነት በሚውሉት ቁሶችም ጭምር ነው። በመሆኑም በዚያ አካባቢ ጠላን ለማዘጋጀትና ለመጥመቅ ታስበው በባህላዊ መንገድ የሚሠሩ የሸክላ ቁሶች ይገኛሉ። እነሱም ጋን፣ ቧድና፣ ማድጋ፣ ሽንክላ፣ እና ገንቦ በመባል ይጠራሉ።

እነዚህ ቁሶች ከገንቦ በስተቀር ለውሃ እና ለጠላ መያዣ በመሆን ድርብ ተግባር ያከናውናሉ። ጋንና ቧድና ጠላ እና ጠጅ ለመጠጀት /ለመጠንሰስ እና "ለመሾም" የሚያገለግሉ ሲሆን ሽንክላ፣ ማድጋ እና ገንቦ ደግሞ ቤት ውስጥ ለአንድ ጊዜ መጠጥ የሚሆን ጠላ ለማቅረብ፣ እንዲሁም ቤተ-ክርስትያን ውስጥ ለሚከናወን ማህበር ጠላ ለመውሰድ ያገለግላሉ። ማድጋ ከዚህ በተጨማሪ ለአረቄ ማውጫነትም ያገለግላል። እንዴት ያገለግላል? የሚለውን በሚቀጥለው ንዑስ ርዕስ በዝርዝር እንመለከታለን።

የእነዚህን ቁሶች መጠንና አካላዊ ገጽታ ስንመለከት ጋን ከሁሉም የሚበልጥ ሲሆን ቧድና ደግሞ ከጋን አነስ ያለ ከማድጋ ደግሞ ከፍ ያለ ነው። ጋንና ቧድና አፋቸው ሠፊ ሲሆን ቧድና ከጋን አንፃር ሲታይ ጠበብ ያለ አፍ አለው። ሁለቱም ሁለት ጀሮ፣ ሠፋ ያለ አፍ፣ ማተብ እና ሁለት ጡት የሚመስሉ ጉጦች አጠር ካለው አንገታቸው ወረድ ብሎ ደረታቸው ላይ ይገኛል። ማድጋ እና ሽንክላ ደግሞ

ቅርፃቸው በሙሉ ተመሳሳይ ሲሆን ከመጠን አንፃር ሲታዩ ግን ማድጋ ከፍ ይላል፡፡ ገንቦ ከዚህ ከሶስቱ ከጋን፣ ከቧድና እና ከማድጋ አነስ ያለ መጠን ሲኖረው ከሸንክላ ጋር ተቀራራቢ አለው ፡፡ ነገር ግን ጌጥ የበዛበትና ከሁሉም የተሻለ ውበት የአለው ሲሆን ከአገልግሎት አንፃር ሲታይ ደግሞ ጠላ እና ጠጅ ከማቅረብ ያለፉ ተግባር አለው፡፡



(ፎቶግራፍ 35) ሸንክላዎች



(ፎቶግራፍ 36) ቧድና



(ፎቶግራፍ 37) ጋን

5.3.1.2 ለአረቄ ማውጫ የሚያገለግሉ የሸክላ ቁሶች

አረቄ ልክ እንደጠላ በአካባቢው የሚወደድ እና የሚዘወተር ባህላዊ የመጠጥ አይነት ነው፡፡ ማዘጋጃ/ማውጫ/፣ ቁሶች ብዙዎቹ /ከሁለቱ በስተቀር/ ከሸክላ የተሠሩ ቁሶች መሆናቸውን በመስክ ምልከታዬ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ አረቄ ለማውጣት የሚውሉት ቁሶች አገልግሎታቸው እንደ ጠላ በተናጠል ሳይሆን በህብረት ነው፡፡ ማለትም አንደኛው ዋና ሌላኛው ክዳን ሌላኛው ደግሞ ተቀባይ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ቁሶቹ ውስጥ አንደኛው ለጠላ ማዘጋጃ ተብሎ የተገለፀው ማድጋ ሲሆን ለአረቄ የሚሆነው ማድጋ ግን እንዲሁ ከገበያ ታይቶ የሚገዛ ሳይሆን በትዕዛዝ የሚሠራ ነው፡፡ ሌሎች ለዚህ መጠጥ ማዘጋጃነት የሚውሉት ቁሶች ዋዳት እና ጐራሽ በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ቁሶች በትነት መልክ ወጥቶ በተዘጋጀው ሸምበቆ አቋርጠ ኩዳ ውስጥ የሚጠራቀመውን አረቄ እንዲቀዘቅዝ የሚያደርግ ውሃ በመያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

የሁለቱን ቁሶች የአሠራር ሁኔታ ስናይ ግን ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይኸውም ጐራሽ በአረቄ አውጪ ሴቶች ከወገቡ በታች ከተሠበረ ማድጋ የሚዘጋግ ሲሆን ዋዳት ግን በባለሙያዎች ለአረቄና ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ተበሎ የሚዘጋጅ ነው፡፡ የጐራሽ አገልግሎት ከላይ የተገለፀው ብቻ ሲሆን ዋዳት ግን ለምግብ መብያ፣ ለሊጥ ማቡኪያ በመሆን አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ጥንታዊ ዕቃ ነው፡፡ ዋዳት ትንሽ እና ትልቅ ተብሎ ይከፈላል፡፡ ትንሹ ዋዳት ከላስቲክ እና ከሌሎች ንጥረ ቁሶች የተሠሩ ሠሃኖች ከመመረታቸው በፊት ለምግብ መብያነት ሲያገለግል የነበረ ሲሆን ትልቁ ዋዳትም እንደዚሁ ከእንጨት እና ከኘላስቲክ የተሠሩ የሊጥ ማቡኪያዎች ከመግኘታቸው በፊት ሊጥ ሲቦካባቸው የነበሩ ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት ግን እነዚህ የዋዳት ተግባሮች ተረት ሆነዋል፡፡ በመሆኑም የወቅቱ የዋዳት ተግባር ለአረቄ ኩዳ ማቀዝቀዣ የሚሆን ውሃ በመያዝ ብቻ ተወስኗል፡፡ የዋዳትን አገልግሎት በሻኳ ዮሐንስ ቀበሌ ገበሬ/ማህበር የሚኖሩት እና ከ20 ዓመተ ላይ አረቄ በማውጣት የሚተዳደሩት ወ/ሮ ምንታምር ገዛኸኝ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ ፡፡

> *ዋዳትማ ድሮ ብዙ ጥቅም ነበረው፡፡ እኔ ሀጣን ሳለሁ እንጀራ በወጥም ሆነ የተፈተፈተ ወተት በዋዳት ነበር ምንበላ ሸጋ ሸጋ ዋዳቶች ነበሩ እኛ ቤት፡፡ ትልቁ ዋዳት ደሞ ለበሆ ማቡኪያ ነበር፡፡ ኋላ የእንጨት ገበታ ተዘየ በኋላ ደግሞ የብላስቲክ ሳፋዎች ተመጡ በኋላ ቀሩ እንጂ በሱ ነበረ ምናባካ፡፡ አሁን ደሞ ጐራሽ ቀረና ትልቁ ድሮ ለቡሆ*

ማቡኪያ የነበረው አሁን ለአረቄ ማውጫ ሆኗል። እኔም ጐራሽ ሰራው አሰቸጋሪ ስለሆነ በዋዳት ማውጣት ከዠመርሁ አራት አመቴ ነው።
(ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 17፣ 2003)

ሌላኛዋ የአረቄ ማውጫ ቁስ መድፊየ ተብላ ትጠራለች። መድፊያ ከሸክላ ስኒ ቀጥላ የምትገኝ ትንሽ መጠን ያላት ቁስ ናት።አገልግሎቷ የአረቄውን ጥንስስ በያዘውና እሳት ላይ በተጣደው ማድጋ ላይ በመክደን መገጠም ነው። አከዳደንዋ የመድፊያው አፍ እና የማድጋው አፍ በመገጣጠም /ከማድጋው ምንም አይነት አየር ወደ ውጪ እንዳይወጣ ተደርጐ/ነው። ቁሷን ከማድጋ ዘር ሊያስመድባት የሚችለው ነገር አፍ እና ሆድ ስላላት ነው። በሌላ በኩል ግን ምንም የሚያመሳስላቸው ገጽታ የለም። ምክንያቱም እንደ ማድጋ ጀሮ፣ አንገት፣ የላትም። ከዚህም በተጨማሪ እንዳይወጣ የታፈነው ትነት አረቄ ሆኖ በጠብታ መልክ ወደ ኮዳው እንዳይተላለፍ ታልሞ የተሠራ እና ጠብታውን ወደ ኮዳው የሚወስደውን ሽምበቆ ማስገቢያ የሚሆን ከቂጧ ከፍ ብሎ ከወገቧ ዝቅ ብሎ የተሠራ ክፍተት/ቀዳዳ/ አላት። ይህም ገጽታዋን ከሌሎች የፈሳሽ ነገሮች መያዣ ቁሶች ይለያታል።



(ፎቶግራፍ 38) ለአረቄ ማውጫ የሚጠቅሙ የሸክላ ቁሶች

5.3.1.3 ለወጥ መስሪያ፣ ለወተት፣ለውሃ ማፍሊያና ማሞቂያ የሚያገለግሉ የሸክላ ቁሶች

ጥናቱ በአተኮረበት ወረዳ ለወጥ መስሪያ በመሆን የሚያገለግለት የድስት ዘሮች ናቸው፡፡ የድስት ዘሮች በቅርፃቸው፣ በአሠራር ሂደታቸው ተመሳሳይ ሲሆኑ የሚያለያያቸው ደግሞ መጠናቸው ወይም የመያዝ አቅማቸው ነው፡፡ ከመጠናቸው መለያየት የተነሳም የሚሠራባቸው የወጥ አይነትና እና መጠን የተለያየ ነው፡፡ ይኸውም ትንንሽ ድስቶች ሽሮና ሌሎች ከአትክልት የሚዘጋጁ ወጦች ሲሰሩባቸው መካከለኛ መጠን ያላቸው ደግሞ ለዶሮ ወጥ መስሪያና ለሌሎች በዛ ተደርገው ለሚሠሩ ወጦች ያገለግላሉ፡፡ ትልቅ ድስት /ሠታቴ/ ደግሞ በማህበር፣ በሠርግ ጊዜ ሥጋ ወጥ መስሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡ በመሆኑም በአንድ ሰው ቤት ውስጥ እንደ ሠዎቹ የአመጋገብ ልማድና የኢኮኖሚ አቅም አንዳቸው ወይም ደግሞ ሁሉም ሊገኙ እና ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

በዚህ አካባቢ ከወጥ መስሪያ ድስቶች በተጨማሪ ውሃ ለማሞቅ /"ለመወዘት"/ ወተት ለማፍላት፣ ህፃናት ልጆች/የስድስት እና የሰባት አመት ሴት ህፃናት/ ውሃ መቅጃነት፣ ለሴቶች ጠዋት ጠዋት ንጽህና መጠበቂያ /ለግብር ውሃ መውጫ/በመሆን የሚያገለግሉ ትንንሽ የሸክላ ቁሶች ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ቁሶች መጠን ሲታይ ከዚህ በፊት የአረቄ መድፊያ ተብላ የተገለፀችውን ዕቃ የሚመስል ገጽታ ሲኖራቸው፣ ከመጠን አንፃር ሲታዩ ግን ልዩነቱ ባይሠፋም ከእሷ በዛ ያለ መጠን ያለው ፈሳሽ የመያዝ አቅም አላቸው፡፡

ቁሶቹ ድንጉኝ እና ቶፋ ተብለው የሚጠሩ ሲሆን የሁለቱ የመያዝ አቅም በንጽጽር ሲታይ ድንጉኝ ከቶፋ የአነሰ አቅም አላት፡፡ ይኸውም ድንጉኝ ለገመድ ማስገቢያ የሚሆን ጆሮ የሌላት ሲሆን ቶፋ ግን እንደ ማድጋ እና ሸንካላ ሚዛናዊ ቦታ ላይ የተቀመጡ ጆሮዎች አሏት፡፡ በዚህም ምክንያት ቶፋ ህፃናት ሴቶች ከምንጭ ውሃ ቀድተው ለማምጣት የምትጠቅም ሲሆን ድንጉኝ ግን ጆሮ ስለሌላት ለዚህ ጥቅም አትውልም፡፡ ድንጉኝ በጆሮ ትክ ጡት የሚመስሉ ሁለት ጉጦች ይደረጉባታል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ሁለቱም መግላሊት የሚባል ክዳን ሲኖራቸው ሁለቱም ለውሃ ማሞቂያ፣ ለወተት ማፍሊያ፣ ጥዋት ጥዋት ደግሞ ለሴቶች ንጽህና መጠበቂያ

በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ድንጉኝ ግን ከእነዚህ ጥቅሞች በተጨማሪ ዘመናዊ ሳህኖች ከመምጣታቸው በፊት ቤተ-ክርስትያን ውስጥ ለሚከወን ማህበር ወይም ሠንበቴ ወጥ መውሰጃ በመሆን ታገለግል ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የአካባቢው ማህበረሰብ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተመረቱትን እና ለአያያዝ ምቹ የሆኑ ከፕላስቲክ የተሠሩ ሳህኖችን በመጠቀም ድንጉኝን ለማህበር ወጥ መውሠጃ በማድረግ ሲጠቀምባት አይታይም፡፡

የዚች ቁስ ከዚህ አገልግሎት ውጪ መሆን ግን ያስከተለው ሌላ የዕሴት መናጋት መኖሩን ወ/ሮ መድኃኒት ዘገየ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ “ድንጉኝ ድሮ ቤት ውሰጥ ብዙ ትጠቅም ነበር፡፡ ተዚያ ውጭ ደሞ “ደብር” ለማህበር ወጥ መውሠጃችን ነበረች፡፡ አሁን ግን ይሄ የላስቲክ ጮማ ተለቀቀ ድንጉኝ ቀረ እና በእሱ ሆነ ሁሉ ነገር፤ አሁን ግን ቁሶች እባካችሁ ወጥ በድንጉኝ አምጡ እያሉ በየወሩ ይለፈልፋሉ፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 14፣ 2003 ዓ.ም)

እኔም የቁሶች ጥያቄ ከምን እንደመነጨ ስጠይቃቸው

> *አይ ልጄ የእኛ አገር ሰው አርቲፊሻል ያታልለዋል እና ማህበሩ ተጠጥቶ ሲያልቅ አንዱ የአንዱ ሠሀን እየሠረቀ እየለወጠ አስቸገረ፡፡ ተዚያ በረከት ለማግኘት የሽደው ሠው ድብድብና ጠብ ይጀምራል፡፡ እሄ ሲያስመርራቸው ነው ቁሶች በድንጉኝ አምጡ የኛው ይሻላል እሱ ነው ቀጣፊ ማያደርገን ይላሉ፡፡ (እንደላይኛው) በማለት መልሰውኛል፡፡*

ከወ/ሮ መድሃኒት ንግግር መረዳት እንደሚቻለው የሸክላ ቁሶች ከቤት ውስጥ ከሚሠጡት አገልግሎት በተጨማሪ መልካም ማህበራዊ እሴቶችን በመጠበቅም የጐላ አስተዋጽኦ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

5.4 የሸክላ ቁሶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

የቁሶችን ጠቀሜታ ከኢኮኖሚ አንፃር ስናየው በዋናነት ለባለሙያዎች ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከመስክ ከተገኘ መረጃዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለሙያዎች ምንም እንኳን ከደርግ ሥርዓተ በኋላ እንደሌላው ማህበረሰብ /ባለሙያ እንዳልሆነው/ መሬት እኩል ተካፍሎ ቢሰጣቸውም፤ ኑሮዋቸው ግን ከእጅ ወደ አፍ የዘለለ አይደለም።

ከግብርና ስራ በሚተርፋቸው ጊዜ እና ቁሶቹ እንደሚሸጡበት የገበያ ቀን ከሳምንት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ለገበያ በማቅረብ ከችግራቸው እንደሚላቀቁ እና ቁሶቹን መስራታቸው ከሚመጣባቸው አስከፊ ችግር ያዳናቸው መሆኑን እማ ውበት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ሸክላውን ታልሠራሁ እርሻውማ ለበጋ እንጀራም አይሆነኝ፡፡ እሱን ጉልበቴ እንደፈቀድልኝ እየሠራሁ እየሸጥሁ ለአሻቦ፣ ለሸሮ፣ ለበርበሬ ታላደረግሁ አስቸጋሪ ነው፡፡ በሠው ደጃፍ መቆም አጋዱኝ ማለት ይመጣል እና ጉልበቴን ተዚያ የባሰ ታልደክመኝ አልተወውም፡፡ መስራቴን ታቆምሁ ጉሮሮዬን ዘጋሁ ማለት ነው፡፡* (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 21፣ 2003 ዓ.ም)

ወ/ሮ አበባ የተባሉት የሸክላ ባለሙያም እንደዚሁ ሥራው በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም ሸክላውን ካልሠሩ ኑሯቸው የባሠ ችግር እንደሚገጥመው ይናገራሉ፡፡

> *ሥራው በጣም ያስቸግራል፡፡ ያው ቀን ሥሰራ ተዋልሁ ማታ እጀን፣ ወገቤን ይቆረጥመኛል ውጋት ያረገኛል፡፡ በዚያ ላይ ቲቪ አለብኝ፤ ታርሶ የሚገኘው እህል ስለማያቆጭ አመመኝ፣ ደክመኝ ብዬ ብተወው ጠም ማደር ይመጣል ብዬ ነው፤ ቢጨንቀኝ ትልልቁን ትቼ ትንንሾቹን /ጀበና፣ ማንደጃ/ እየሠራሁ ባይሆን ተእጀ ወደ አፍ እያደረግሁ እኖራለሁ፤ ልጆቼንም አሳድጋለሁ* (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 21፣ 2003 ዓ.ም)

የሸክላ ቁሶች ጠቀሚታ በሸክላ ባለሙያዎች ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሙያውን የመስራት ችሎታ ሳይኖረው በብዙ ድካም ተሠርተው ገበያ ላይ የቀረቡትን የሸክላ ሥራ ውጤቶች እየገዛ የሚጠቀመውን ማህበረሰብም የካትታል፡፡ ጥቅሙም ከቁሶቹ ዋጋ ርካሽነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ማለትም የሸክላ ቁሶች ዋጋ በፋብሪካ ከሚመረቱ ቁሶች ጋር ሲነፃፀር አነስ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የኢኮኖሚ አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን የሸክላ ዕቃዎችን መርጠው በመግዛት ለማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች መከወኛ ያደርጓቸዋል፡፡ ከዚህ ዘርፈ ብዙ የሆነ ጥቅም አንፃር ሲታይ ቁሶች እየሠጡት ያሉት አገልግሎት በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

5.5 የሸክላ ቁሶች ባህላዊ ፋይዳ

ጥናቱ በአተኮረበት አካባቢ የሚበጁት የሸክላ ቁሶች ቤት ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ ባህላዊ መግለጫ በመሆንም ያገለግላሉ፡፡ ባህላዊ አገልግሎት በመስጠት ከዚህም ጋር ተያይዞ የግለሰቦችን ኢኮኖሚያዊ እና

ማህበራዊ ደረጃ በመግለጽ የሚታወቁ ቁሶች አሉ፡፡ እነሱም ጋን፣ ቧድና፣ ገንቦ እና ጽዋ ናቸው፡፡

በአካባቢው ከሚሠሩ ቁሶች ውስጥ ጋንና ቧድና በትልቅነታቸው ተወዳዳሪ የላቸውም፡፡ቀደም ብሎ እነዚህ ሁለት ቁሶች አገልግሎታቸው ጠላ ለመጠንሰስ /ለመጠጀት/ እንዲሁም ለመሸም መሆኑ ተገልጿል፡፡ እነዚህ ሁለት ቁሶች ከሚሰጡት ሁለት ዋና ዋና አገልግሎት ውስጥ መሸም የሚባለው ጉዳይ ትልቅ ባህላዊ አገልግሎት ነው፡፡ መሸም ማለት ቀደም ብሎ እንደተገለፀው አንድ ሰው /ቤተሰብ/ ለማህበር ወይም ለሠርግ በሚደግስበት ወቅት የቤተሰቡ ቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሆኑ ሠዎች ጠላ በጋንና በቧድና በመውሰድ የሚያደርጉት እርዳታ/ትብብር/ ነው፡፡

የባህላዊ ክዋኔውን አከዋወን ስናይ ጀሚዎች እንደ ሠርግ አዘጋጆች ከሠርጉ ቀን ቀደም ብለው ጠላ እና እንጀራ ያዘጋጃሉ፡፡ ከዚያም የሠርጉ ቀን የሚሸመት በቧድና ከሆነ ከቤታቸው በቧድና ሞልተው ለሁለት በእንጨት ተሸክመው ወደ ሠርጉ ቦታ ወስደው ያስረክባሉ፡፡ ከዚያም የወሰዱትን ጠላ ቤተሰብ ሳይሆን እነሱ ራሳቸው እየቀዱ የቧድናው ጠላ እስከሚያልቅ እየቀዱ ያስተናግዳሉ፡፡ የሚሸመት በጋን ከሆነ ደግሞ ጋን ከቧድና የበለጠ የመያዝ አቅም ስላለው /ትንሹ ጋን ቢያንስ ሁለት ቧድና ይይዛል/ በጋን ሙሉ ጠላ ተሸክሞ መውሰድ ስለሚያስቸግር ባዶውን ጋን በመውሰድ ቀድሞ በተዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፡፡ ከዚያም ጀሚዎቹ ጋኑ እስከሚሞላ ድረስ በቧድና እያመላለሱ ጠላውን በጋኑ ይሞሉታል፡፡

ከዚህ ክዋኔ ጋር ተያይዞ ከእምነት ጋር የሚባል እና የሚከወን ሌላ ክዋኔም እንዳለ ከቃል መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም ጀሚዎች ጠላ በቧድና እያመላለሱ ለመሙላት ሲጥሩ የጋኑ ይዘት ሁለት ቧድና ከአምስት ሊትር ቢሆን አምስት ሊትሩን ጠላ ከሠርግ አዘጋጆች መሙላት ወይም ደግሞ የቀረው ትንሽ በመሆኑ ጐዶሎ እንደሆነ እናስተናግድ ማለት አይችልም፡፡ በመሆኑም ጀሚዎቹ ከሌላቸው ወይም ቤታቸው ሩቅ ከሆነ ስለጐደለብን እናንተ ሙሉልን ካሉ በአዘጋጆቹ ነቀፌታና አሽሙር ይደርስባቸዋል፣ ወይም ደግሞ ጐዶሎውን እየቀዳን እናስተናግድ ካሉ ጐዶሎ የመጥፎ አጋጣሚ ትዕምርት በመሆኑ የአላቸው አማራጭ ከሌላቸው

ገዝተው ቤታቸው ካለ ደግሞ ቤታቸው በመሄድ የቀረውን ጠላ መጠን ያህል በሚይዝ ዕቃ አምጥተው ጋኑን መሙላት ነው።

ለመሸም የሚወስደውን ጠላ የሚሸከሙት ወንዶች ሲሆኑ በቧድናው ጆሮ ገመድ በማስገባት አንገቱን ጨምረው አስረው እርፍ በሚባል እንጨት ለሁለት በትከሻቸው ተሸክመው ወደ ሠርጉ ቤት ይወስዱታል። በመሆኑም በዚያ አካባቢ በዚህም መሠረት ቧድና ተሸክመው የሚሄዱ ሁለት ወንዶች መንገድ ላይ ከታዩ ለመሸም እንደሚሄዱ ይታወቃል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ሠው ሠርግ ወይም ማህበር ለሚያዘጋጅ ወዳጅ ወይም ዘመድ ብዙ ቁጥር ባላቸው ቧድናዎች ወይም ደግሞ በትልቅ ጋን ከሸመ ለአዘጋጆቹ ያለውን ፍቅርና ቀረቤታ እንዲሁም የእሱን ሀብት እና ማህበራዊ ደረጃ ይገልፃል። ምክንያቱም በዚያ አካባቢ በብዙ ቧድና /ከአራት እስከ አምስት ቧድና/ ወይም ደግሞ በትልቅ ጋን የሚሸም ሠው ሃብታም እና የተሻለ ማህበራዊ ደረጃ ያለው ተደርጐ ስለሚወሰድ ነው።

ከጋን ጋር የተያያዘውን የማህበራዊ እና ደረጃ የክብር ጉዳይ ወ/ሮ ምንታምር ገዛኸኝ "የአለው ሠው ለሚወደው እና ለቅርብ ዘመዱ በወደል ጋን ወይም በብዙ ቧድና ይሸማል። የሌለው ተሆነ ደግሞ ያው ተሚቀር እንደ ሀቅሙ በሸንክላም በማድጋም እንደአሉታው ይሸማል" *(ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ* 16፣ 2003 ዓ.ም.) ብለውኛል።ከዚሁ ከመሸም ጋር ተያይዞ የሚባል ሌላም ነገር አለ። ይኸውም አንድ ሰው በአንድ ወቅት ለአንድ ወዳጁ ወይም ዘመዱ ከሸመ፤ የተሸመለት ቤተሰብ በመሸም ብድሩን ካልመለሠ በመካከላቸው በሃገር ሽማግሌ እስከ መካሠስ የዘለቀ ፀብ ይፈጠራል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሸመው ሠው ብድሩ ሊመለስለት ስለሚፈለግ መዳር ሳይፈልግ ልጅ እስከመዳር የሚደርስበት ሁኔታ እንዳለ የአካባቢ ተወላጅ የሆኑ መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ። "ይሄ አሁን በመጣው በጐማ በርሚል የሚደረግ ጠላ ያስታውቃል ውሃ ውሃ ነው እሚል በዚያ ላይ ጠሐይ ስለማይችል ጠላው ተሎ "ይቆመጭራል" ይሞቃል፣ እንዲያው ምንም ቢሆን የአባቶቻችን ጋን ይሻላል" *(ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ* 15፣ 2003 ዓ.ም)

የ50 ዓመቱ የኔሁን ዘገየ የጋንን ተመራጭነት ከመሸም ጋር አያይዘው እንደሚከተለው ይገልጹታል። "ሌላው ቀርቶ ሲሸም እንኳ እከሌ አራት ወይም አምስት

ቧድና ወይም ጋን ጠላ ሾመ ሲባል ነው አንጅ 5 የጎማ በርሚ ጠላ ሾመ ሲባል ደስ አይልም። ለንግግርም አይመች 5 ጐማ ብሎ ጠላ ጥሩ አይመጣም እዚያው እንደለመድነው በጋን ጠላ ነው እንጅ በጐማ ጠላ ተሾመ ሲባል አያስደስትም።" (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 15፣ 2003 ዓ.ም) በአጠቃለይ ከላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ጋንና ቧድና ከማህበረሰቡ ባገኙት የክብር፣ የፍቅር እና የምልኪ መገለጫነት እና የአገልግሎት ተመራጭነት አንፃር፣ እነሱን ሊተካ የሚችል የፋብሪካ ውጤት የሆነ ዕቃ ቢኖርም እስከዚህ ወቅት ድረስ ከአገልግሎት ውጪ ሳይሆኑ በመመረት እና ጥቅም በመስጠት ላይ ሊገኙ ችለዋል።

ሌላው ባህላዊ አገልግሎት በመስጠት የሚታወቀው ቁስ "ገንቦ" ነው። ገንቦ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ለመግለጽ እንደተሞከረው በጌጣጌጥ ብዛት ግንባር ቀደም ቁስ ነው። አገልግሎቱ፣ በተለይም በዘመነ ሐይለ ስላሴ በመሳፍንቶች ቤት ውስጥ ብቻ የተገደበ መሆኑ ተገልጿል። በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን በትዕዛዝ የሚሠራ እና በማንኛውም ሠው ቤት ሊገኝ የሚችል ቁስ ቢሆንም፣ የአካባቢው ሰው ይህን ቁስ በሚያይበት ጊዜ በቀደምት ጊዜ የተከበሩ ሠዎች መገልገያ እንደነበር ይገልፃሉ። በመሆኑም አሁንም ከሌሎች የፈሳሽ ነገሮች መያዣ ቁሶች የተለየ ክብር ሲሰጠው ይስተዋላል። ቤት ውስጥ የሚቀመጠውም እንደማነኛውም የማድጋ ዘሮች በተገኘው ቦታ ሳይሆን በተመረጠ እና ከፍ ባለ ቦታ ላይ ከጭቃ በሚሠራውና ማዕዘንት ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ መሆኑን ከመስክ ቆይታየ ለማረጋገጥ ችያለሁ። የዚህ ቁስ መቀመጫ በገጠር ከላይ በተገለፀው ማዕዘንት በሚባለው ለእሱ የተዘጋጀ ቦታ ላይ ሲሆን ከተማ ደግሞ ከዕቃ መደርደሪያ ብፌ ላይ ዳንቴል ለብሶ በመቀመጥ ለቤት ማሰዋቢያ በመሆን ያገለግላል።

በሶስተኛነት ባህላዊ አገልግሎት በመስጠት የሚታወቀው ቁስ ጽዋ ሲሆን በመጠንም ሆነ በአገልግሎትም ከላይ ከተገለፁት ቁሶች የተለየ ገጽታ አለው። ጽዋ ሆድ እና እግር ማቆሚያ እንዲሁም አፍ የሚባሉ ክፍሎች ያሉት የዋንጫ ቅርጽ ያለው ለጠላ መጠጫነት የሚያገለግል ቁስ ነው። የዚህ ጽዋ ማህበራዊ ተግባር ለመጠጫነት ሲሆን ነገር ግን ከዚህ ያለፈ ባህላዊ ተግባርም አለው።

ይኸውም ጽዋ በአካባቢው ማህበረሰብ የሠርግ ሥነ ሥርዓት በመሰበር የወግ ማዕረግ ማሳያ ይሆናል። ይህ ቁስ የወግ ማዕረግ ማሳያ የመሆኑን ሂደት ስናይ በመጀመሪያ ቁሱ ለዚህ ተግባር የሚዘጋጀው የሚዳረው ወንድ ልጅ ከሆነ እና የሚያገባውም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆን ብቻ ነው። በመሆኑም የምትሞሸረው ሴት ከሆነች ወይም ደግሞ ወንድ ሆኖ ለሁለተኛ ጊዜ የሚያገባ ከሆነ የጽዋ ሠበራ ሥርዓቱ አይከናወንለትም። ለምን ይህ እንደሆነ ስጠይቅ ግን የአገኘሁት ምላሽ "ያው ባህላችን ነው ሌላ ነገር የለውም" የሚል ነው። በዚህም ምክንያት ስርዓቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚያገባ ወንድ ልጅ ብቻ መከወኑን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ማገኘት አልቻልሁም።

የጽዋ ሠበራ ሥርዓቱ የሚከወነው ሙሽራው ወደ ሙሽሪት ለመሄድ ከቤቱ ሲወጣ ነው። በዚህም ጊዜ ለዚህ ዓላማ የተገዛው አዲስ ሸክላ የጠላ ድፍድፍ ተሞልቶ ሙሽራው እንዲይዘው ይደረጋል። ከዚያም ለተለያዩ የእህል ዘሮች መውቀጫ የሚያገለግል ሙቀጫ ይዘጋጅና ሚዜዎቹ ሙቀጫውን ዙሪያውን ከበው ሽመል /ዱላ/ ይዘው ይቆማሉ። ከሚዜዎቹ አንዱ ድፍድፍ የተመላበትን ጽዋ ይዞ የቆመውን ሙሽራ ትከሻው ላይ አድርጐ ከሌሎች ሚዜዎች ጋር ሙቀጫውን ይዞራል። በዚህ መሠረት ሙቀጫውን መዞር ከጀመረ ሶስተኛ ዙር ሲሞላቸው ሙሽራው የያዘውን ጽዋ ሙቀጫው ውስጥ ይጥልና በያዘው ሽመል አንድ ጊዜ ይመታዋል /ይወቅጠዋል/። ከዚያም ሚዜዎቹ በሙሉ በያዙት ሽመል ጽዋውን በትብብር ድቅቅ እስከሚል ይወቅጡታል። ከዚያ በኋላ ሙሽራው ከሚዜው ትከሻ ወርዶ ወደ ሙሽራዋ ቤት ጉዞ ይጀምራል።

ይህ የጽዋ ሠበራ ሥነ-ሥርዓት ከክብረ ንጽህና መውሰድ ጋር የተያያዘ ነው። ይኸውም ጽዋው እና ድፍድፉ ልጅቷንና ክብረ ንጽህናዋን የሚወክሉ ሲሆኑ ዱላው ደግሞ ልጁን ይወክላል። የጽዋው መሰበርም ልጁ የሚፈጽመውን የክብረ ንጽህና መውሰድ ብቃት ለማመልከት እና ወሬ ለመፍጠር የሚደረግ ሥርዓት መሆኑን አባ ገላው እንዲህ በማለት ከሌሎች ቀደምት አባቶች የሰሙትን ይገልፃሉ።

በኛ አካባቢ ተጥንት ጀምሮ እስታሁን ድረስ ወንድ ልጅ "ቁንጅናውን" ሲያገባ ጥዋ ይሠብራል። ጥዋ ሠበራ ወግ ማዕረግ ነው። ሙሽራው ለመጀመሪያ ጊዜ ተሴት ጋር ስለሚገናኝ እንዳይፈራ እንደ ጥዋው ሳትፈራ ሠብረህ ወንድነትህን አሳይ በማለት ለልጁ ድፈረት ለመስጠት ነው ይላሉ አንዳንድ አባቶች። (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 07፣ 2003 ዓ.ም)

በአጠቃላይ ባህላዊ አገልግሎት የሚሰጡ በማለት ከቀረቡት አራት ቁሶች ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው የሸክላ ቁሶች ማህበረሰቡ በጫነባቸው ባህላዊ እሴት ለማህበረሰቡ ባህላዊ ማንነት መገለጫ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን መገንዘብ ይችላል። በዚህ አገልግሎታቸውም ምክንያት ማህበራዊ አገልግሎታቸው በሌሎች የፋብሪካ ውጤት በሆኑት ቁሶች በመተካቱ ገበያ ላይ የመቅረብ ዕድላቸው እየጠበበ ቢመጣም ነገር ግን የተሸከሙትን ባህላዊ እሴት የሚተካ ቁስ ባለመገኘቱ ዘመን ተሻግረው ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ እስከዚህ ዘመን መዝለቅ ችለዋል።

5.6 የሸክላ ባለሙያዎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ

ጥናቱ ባተኮረበት አካባቢ የሚገኙት የሸክላ ባለሙያዎች ማህበራዊ ደረጃ ስናይ ከዘመነ ደርግ በፊት አስከፊ ገጽታ ነበረው። አስከፊነቱም ማህበረሰቡ ከሰጣቸው ስያሜ ይጀምራል። በዚህ አካባቢ የሸክላ ባለሙያ የሆኑ ሠዎች ሸማኔ እና ደበላንሳ ተብለው ይጠራሉ። ከመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት በዚህ አካባቢ ብረት በመቀጥቀጥ፣ሸማ በመስራት፣ እና ሸክላ በመስራት የሚተዳደሩ ሠዎችን በጥቅሉ ሸማኔ በማለት ይጠሯቸዋል። የሸክላ ባለሙያዎችን ግን ደበላንሳ የሚል ተጨማሪ ስያሜ አላቸው።

ማህበረሰቡ የእነዚህን የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ክብር የሚነካው ክብረ-ነክ ስያሜ በመስጠት ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ማለትም ከማህበር፣ ከዕቁብ፣ ከዕድር፣ከጋብቻ፣ ከክርስትና በማግለልም ጭምር ነው። ይህ የመገለል ሁኔታ ግን በጊዜ ሂደት መሉ በመሉም ባይሆን እየተቀረፈ የመጣ ይመስላል። ከተጠቃሚዎችም ሆነ ከባለሙያዎች የአገኘሁት መረጃ እንደሚያሳየው በሃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ከፍተኛ የሆነ መገለል ሲደርስባቸው የነበረ ሲሆን ከላይ ከተገለፁት ማህበራዊ ተቋማት መሉ በመሉ የተገለሉ እና እንደሌላው ማህበረሰብ እኩል

የማይታዩ መሆናቸውን መሪጌታ ዘማሪያምና ሌሎችም ያካባቢው ያገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡

ከዘመነ ደርግ ጀምሮ ግን የባለሙያዎች የመገለል ደረጃ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ይኸውም በማህበር፣ በዕቁብ እና በዕድር በመገናኘት ባለሙያ ካልሆነው ማህበረሰብ ጋር ያለቸውን ቅርበት አሻሽለዋል፡፡ በጋብቻ በኩል ግን አሁንም ድረስ በቂ ነው የሚባል ለውጥ አይታይም፡፡ አሁንም ድረስ ማህበረሰቡ ከባለሙያዎች ጋር መጋባት አይፈልግም፤ ባለሙያዎችም እንዲሁ ከዘራቸው ውጪ ማግባት አይፈልጉም፡፡ ከቃል መረጃዎች መረዳት እንደቻልኩት የሸክላ ባለሙያዎች ከሸማ ሠራተኞች ውጪ ከሌሎች የእደ ጠበብ ሰራተኞች ጋርም ሆነ ባለሙያ ካልሆነው ማህበረሰብ ጋር ፊፅሞ መጋባት አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም ራሳቸውን ከሌሎች በተሻለ ንፁሆች አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ እማ ውበት ፡፡ “በጋብቻ የራሳችንን አቻችንን ሸማ የሚሠራ ሰው ፈልገን ነው የምንጋባ፣ ፋቂ ባሪያ ተሆነ አንጋባም፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 08፣ 2003) ብለውኛል፡፡ እኔም ከባለሙያዋ ስሜታዊ ንግግር በመነሳት ከቆዳ ባለሙያዎች ጋር ብትጋቡ ምን ችግር አለው? በአልኳቸው ጊዜ “ምን አልሁሽ ተጣርተን፣ የጠራውን ዘር ፈልገን ነው እንጅ ተእነሱ ጋር ደሞ ምን አገናኝቶን ሸማኔ ሲለን ይውላል እንጅ እኛስ የተጣራን ነን” በማለት ስሜታቸውን ገልጸዋል፡፡የአካባቢው ማህበረሰብም የዕደ ጥበብ ባለሙያዎቹ የራሳቸውን የሙያ ባልደረባ ፈልገው እንደሚጋቡ ይገልፃሉ፡፡

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት የአካባቢው ተወላጅ አቶ የኔሁን ዘገዬ “ማህበር፣ ጋብቻ ምናምን ሸማኒዎችም ፋቂዎችም ዘሮቻቸውን ፈልገው ከሩቅ አገር ሂደው ነው የሚጋቡት እንጅ በቅርብ ካለው ጨዋማ አይገናኙም፡፡ እኛም አንፈልጋቸውም፤ እነሱ ዘራቸውን ስለሚያውኩ ደፍረው አይመጡም፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 17፣ 2003) ሲሉ ሃሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

ሻይ ቤት ውስጥ ያገኘሁትና በዚህ ዙሪያ ያለውን አመለካከት እንዲነግረኝ የጠየኩት ወጣት እንዲህ ሲል ይናገራል፡፡ “እኔ ዘንድሮ አንዷን የሸማኔ ጎን ያላትን ብር አላት የሚል ወሬ ሰምቼ ላገባት ነበር፡፡ኋላ ግን ሳስበው ብወልድስ ልጄ የሸማኔአሰብኩ፡፡ በዚያ ላይ እኔ የባላባት ዘር ነኝ ለምን ዘሬን አበላሻለሁ ብዬ ተውኩት፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 08፣ 2003 ዓ.ም) ከላይ የቀረቡት መረጃዎች ባለሙያዎች ከደርግ ዘመነ

መንግስት ወደዚህ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነት የተሻለ ለውጥ ቢታይበትም በጋብቻ በኩል ያለው ችግር ግን እስከ አሁን ድረስ አለመቀረፉን ያሳያሉ፡፡

ሆኖም ግን በዚህ ወቅት በጋብቻ በኩል ያለው ችግር በትንሹም ቢሆን እየተቀረፈ መሆኑን አመላካች ፍንጮች አሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ መልካም አለማየሁ የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡

> *ድሮ ዘራቸውን ፈልገው ነበር የሚጋቡ፣ ተጨዋ ጋር አይገናኙም ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ልጆች ትምህርት እየወሰዱ ስለሆነ ተፋቅረው ተናት ተአባታቸው ፍቃድ ውጪ ይጋባሉ፡፡ አንዳንዱ ደሞ ባይማርም ሙያቸውን እያለ መጋባት ጀምሯል፡፡ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 17፣ 2003)*

ከወ/ሮ መልካም ቃል መረዳት እነደሚቻለው የተማሩት ልጆች የእደጥበብ ስራዎችን አስፈላጊነት በመረዳትም ይሁን ሳይረዱ ነገር ግን ፍቅርን አስቀድሙው ፀንቶ የቆየውን የጋብቻ ገደብ እየጣሱ ከባለሙያ ልጆች ጋር እየተጋቡ መሆኑንያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዶቹ የሙያው ጥቅም ገብቷቸው የቆየውን አጥንት ቆጥሮ የመጋባት ባህል ንቆ በመተው ጋብቻ እየፈፀሙ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ይህ ደግሞ በባለሙያዎች እና ቁሶችን በሚጠቀመው ማህበረሰብ መካከል የነበረውን የሻከረ ግንኙነት ስለሚያለሰልስ በባህላዊ የሸክላ ሙያው ቀጣይነት ላይም አወንታዊ አሰተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል፡፡

ከዚህ ከባለሙያዎቹ ማህበራዊ ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የባለሙያዎቹ የመሬት ባለቤትነት ነው፡፡ ባለሙያዎቹ በቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የራሳቸው የሆነ መሬት ያልነበራቸው እና ከአንድ ባለሙያ ካልሆነ /ባላባት ተብሎ ከሚጠራ ሰው ጋር/ ተጠግተው በመቀመጥ በእጃቸው እየሠሩ በሚሸጧቸው ቁሶች ብቻ የሚተዳደሩና ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ መሆናቸውን የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚመለከት ወ/ሮ መድሀኒት ዘገዬ “ድሮማ ምን መሬት አላቸው ከአንድ ሀብታም ባላባት ቤት ጎን ጐጆ ይሠራሉ ተዚያ በእጃቸው እየሠሩ ነው የሚተዳደሩት፡፡ አንዳንዶቹ ደሞ ሳይታወቁ ከጨዋዎች ይዋለዱና በምሽታቸው ሠበብ መሬት ያገኛሉ፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 11፣ 2003 ዓ.ም) ይላሉ፡፡

መሪጌታ ዘማሪያም ደግሞ "ድሮማ መሬት የላቸውም መሬት በአባት ስለሆነ ሸማኔዎች መሬት አሰያገኙም ነበር። በእጃቸው እየሠሩ ነው ተእጅ ወደ አፍ የሚሉት" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 08፣ 2003 ዓ.ም) ።በማለት ያስረዳሉ።

5.6.1 የሸክላ ስራ ሙያ ለመዳ

በዚህ ክፍል በቡሬ ወረዳ ባጉና ሃና እና ሻኳ ዮሃንስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ሸክላ በመስራት ኑሮዋቸውን የሚመሩ ባለሙያዎች ሸክላ የመስራት ጥበብን ከየትና እንዴት እንዳገኙት እንመለከታለን።

ሸክላ ባለሙያዎቹ ሙያውን መሰራት የለመዱት ቤተሰቦቻው ሲሰሩ በመመልከት ነው። በጥናቱ በተካተቱት ዘጠኝ ባለሙያዎች ውስጥ ስድስቱ ከእናቶቻቸው ሶስቱ ደግሞ ከአማቶቻቸው በማየት መስራት እንደጀመሩ ገልፀውልኛል። የለመዳ ሁኔታቸውም የሚጀምረው የሸክላ አፈር ቁፋሮ በማገዝ ከዚያም የተቆፈረውን አፈር ተሸክሞ በማምጣት ሲሆን፣ ከዚያ በመቀጠል ያሉትን ሂደቶች ደግሞ የመስሪያ ቁሳቁሶችን በማቀራረብ እናቶቻቸው ወይም አማቶቻቸው ሲሠሩ ቁጭ ብለው በመመልከትና ለብቻቸው መለማመጃ የሚሆን ጭቃ ተሰጥቷቸው ደጋግመው በመሞከር ሙያውን መስራት እንደጀመሩ ይናገራሉ።

ሙያውን እንዴት እንደለመዱት የጠየኳቸውት እማ ውበት የሚከተለውን ነግረውኛል።

> *የዕድሜ ልክ ሰራዬ ነው። ጮጆ ብዬ ከወጠንሁ ጀምሮ የምሰራው እሱን ነው። ይሄው ባል አግብቼ ሻኳ ቀበሌ መኖር ከጀመርሁ እንኳን 28 ዓመቴ ነው። የለመደሁት ተእናቴ ነው። እናቴ ትሠራ ነበር ያው እሷን እያየሁ መስራት ጀመርሁ እሰታሁን የነፍስ ማሳደሪያ አድርጌዋለሁ። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 21፣ 2003 ዓ.ም)*

የባጉና ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ለ20 ዓመት ያህል ሸክላ በመስራት ሲተዳደሩ የቆዩት እማአበባ በዚህ ሙያ አምስት ወንድ እና ሁለት ሴት ልጆችን ማሳደጋቸውን ይገልፃሉ። ሙያውን የለመዱትም አያታቸው ሲሰሩ አይተው መሆናቸውን ይገልፃሉ። (*ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20፣ 2003 ዓ.ም*)

ሙያውን መስራት ከጀመረች አንድ አመት ያሳለፈችው የ25 ዓመቷ ቦሠና መኮንንም የለመደችበትን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጻለች "የለመድሁት ቅርብ ጊዜ ነው። ገና አንድ ዓመቴ ነው። መስራት የጀመርሁት እናቴ የሸሀላ ባለሙያ ብተሆንም እሱን ትታ ግብርና ሰራ ሰለምትሰራ ከእሷ አለመድኩም። ተድሬ ከቲያቲያ ወደ ባጉና ሰመጣ አማቴ ማንደጃና ማድጋ ሥለምትሠራ ለእሷ ጭቃ እያቀረብሁ፣ እየቆፈርሁ፣ ስትሠራ እያየሁ አሁን ማንደጃና ማድጋ መስራት ችያለሁ። ሌላ ነገር ግን ሲሰራ ስላላየሁ አለመድሁም። ታየሁ ግን መልመዴ አቀርም"(ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20፣ 2003 ዓ.ም)

ከላይ ከቀረቡት የሶስት ሰዎች ተሞክሮ ሸክላ ሰራ በልጅነት ጊዜ ወይም ከአደጉ በኋላ ሙያውን ከሚሠራ ቤተሰብ በማየት የሚለመድ ጥበብ መሆኑ ልብ ይሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የሸክላ ስራ ከቤተሰብ በተጨማሪ በስልጠናም ሊለመድ እንደሚችል ሻኳ ዮሀንስ ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩት እማ ውበት በመጀመሪያ ከእናታቸው በማየት የለመዱትን ሸክላ ሥራ በስልጠና ደግሞ ሌሎች አዳዲስ ቁሶችን መስራት መልመዳቸውን እንዲህ ይገልጹታል።

> *መጀመሪያ ተእናቴ እያየሁ ከጥንት ጀምረው የሚሠሩትን ጋን፣ ማድጋ፣ ምጣድ፣ ድስት ኩስኩስት/ጀበና/ እሠራ ነበር ቅርብ ጊዜ /ከ2 ዓመት በፊት/ ደሞ ጥቃቅንና እንዱስትሪ ቡሬ /03/ ወስደው አሠልጥነውን ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ እና የእንጀራ መጋገሪያ ደግሞ ፈጠነችን በብሎኬት አሠልጠኑን እኔም እነሱ ታሳዩን ጨምሬ ለማገዶ ቆጣቢው እግር ተላይ ደሞ ሁለተኛ የብረትምጣድ ጉልቻ አድርጌ አሳምሬ እየሠራሁ በደና ዋጋ እየሸጥሁ ነው። /ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 19፣ 2003 ዓ፣ም/*

በእነዚህ ሁለት ቀበሌዎች ከሚኖሩ የሸክላ ባለሙያዎች ልምድ ሙያው አንድም የሚሠሩ ሠዎችን በመመልከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በስልጠና ሊገኝ የሚችል ጥበብ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

5.6.2 የሸክላ ሙያ ላይ የተጋረጡ ችግሮች

የአካባቢው ማህበረሰብ ባለሙያዎቹ የሚሰራቸውን ቁሶች እየተጠቀመ ቢገኝም ጉልበታቸውን ጊዜያቸውን ሰውተው አሳምረው በተፈለገው ጊዜ ለሚያቀርቡላቸው የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ያለው አመለካከት አሉታዊ ነው።

ይኸውም ለመስክ ሥራው በተዘዋወርኩባቸው አካባቢዎች እንዳየሁት ባለሙያዎቹ ክብር የሌላቸውና ባለሙያ ካልሆነው ማህበረሰብ ያነሱ መሆናቸውን የአካባቢው ማህበረሰብ በተደጋጋሚ ይገልፃል። ከመረጃ አቀባዮች መካከል አባ ገላው አበጀ የሚከተለውን ነግረውኛል።

> *ጨዋዎች ከእጅ ሠሪዎች ጋር በጋብቻ፣ በማህበር በእድር አንገናኝም። እንዲያውም በኃይለ ስላሴ ጊዜ እንኳን ለመጋባት እነሱ በበለፀበት ዕቃም አንበላም ነበር። እንዲያው ይቅር ብለን ብንጋባ እንኳ የአባቶቻችን አጥም ይፈሃል። እስተ ሰባት ጉልበት ንጡህ የጨዋ ዘር ነው ተፈልጐ ነው የምንጋባ እንጅ ተፋቂ ተሸማኔ ጋር መጋባት መዋለድ ዘር ያበላሻል። ግን ያው ተጋብቻ ላይ የአባት ጉዳይ ሁኖ ነው እንጅ እነሱ ተሚሠሩት እኛ የማንካው ዕቃ እንኳን የለም መተኛው፣ መብያው፣ መጠጫው፣ ሁሉ ነገር እነሱ የሠሩት ነው።* (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 08፣ 2003 ዓ.ም)

ከአዛውንቱ ንግግር መረዳት እንደሚቻለው ባለሙያዎቹ በጋብቻም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳች የተገለሉ እና እንዲቀላቀሉ የማይፈልጉ ናቸው፤ የሚለው መጥፎ አመለካከት በማህበረሰቡ ዘንድ ፀንቶ የቆየ መሆኑንና ወደፊትም ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል ያመላክታል።

በዚህ አካባቢ የሚሠራው ባህላዊ የሸክላ ሙያ ያጋጠመው ሌላው ለችግር ከሙያው ባህሪ የመነጨ ነው። የሸክላ የአሠራር ሂደቱ ከፍተኛ የሆነ ጉልበትና ጊዜ የሚጠይቅ ስራ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ስራው ሙሉ በሙሉ በእጅ እና በእግር የሚሠራ በመሆኑ እና ባለሙያዎቹ አጋዥ መሳሪያዎችን አለመጠቀማቸው ነው። ይህንንም በሚመለከት በቃለመጠይቁ የተካተቱት ሁሉም የሸክላ ባለሙያዎች ሥራችሁን እንዳትሠሩ ያደረጋችሁ ችግር ካለ ግለፁልኝ ባልኳቸው ጊዜ የአቅም እና የጉልበት ማነስ ችግርሰ እንዳጋጠማቸው በተደጋጋሚ ገልፀውልኛል። በዚህም ምክንያት ከዚህ ባነሰ ጉልበት ሊሰራ የሚችል እና የተሻለ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ከተገኘ ሙያውን ለመተው ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸውንም ጨምረው ገልፀዋል።

በሸክላ ቁሶች ላይ ተጽኖ በማሳደር የሸክላ ቁሶችን የመመረት ደረጃ እና የተፈላጊነት መጠን በመቀነስ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ አስተዋጽኦ እያደረሰ የሚገኘው የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ ቁሶች በሰፊው መመረት መጀመራቸው ነው።

የመስክ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዚህ አካባቢ የሚመረቱ ባህላዊ የሸክላ ቁሶች የሚሰጡትን ማህበራዊ /የቤት ውስጥ/ አገልግሎት ሊተኩ የሚችሉ እና በዘመናዊ መንገድ ከፕላስቲክ፣ ከብረት፣ ከቆርቆሮ እና ከሌሎች ጥሬ ዕቃዎች የሚመረቱ ቁሶች ተበራክተዋል፡፡ እነዚህ ቁሶች ደግሞ ከሚመረቱባቸው ጥሬ ዕቃ እና ከማምረቻ ዘዴዎች አንፃር ከሸክላ ቁሶች የተሻለ ምቾት አላቸው፡፡ ማለትም በአጭር ጊዜ በትንሽ ማገዶ ምግብ ለማዘጋጀት፣ እንዲሁም የተለያዩ ነገሮችን በቀላሉ ለመያዝና ለማንቀሳቀስ ያስችላሉ፡፡ በዚህ የተነሳ የአካባቢው ማህበረሰብ የፋብሪካ ውጤት የሆኑት ቁሶች ከመመረታቸው በፊት በከፍተኛ ደረጃ ሲጠቀምባቸው የነበራቸውን የሸክላ ቁሶች ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ወደ ጐን በመተው በዘመናዊ ቁሶች መጠቀም ጀምሯል፡፡

ይህ ደግሞ በባህላዊ መንገድ እየተበጁ ለባለሙያዎች የገቢ ምንጭ በመሆን፣ ለአካባቢው ሰው ደግሞ ከቤት ውስጥ አገልግሎት ባለፈ ባህላዊ መገለጫ በመሆን የሚያገለግሉት ቁሶች የወደፊት ዕጣ ፋንታ ከአገልግሎት ውጪ መሆኑን ያመለክታል፡፡

6.ያታዊ ተሳትፎ በባህላዊ የሸክላ እና የቆዳ ሥራ

በዚህ ክፍል በቡሬ እና በወንበርማ ወረዳ በሚገኙ ባለሙያዎች መካከል የሚታየው ያታዊ የስራ ድርሻ ክፍፍል ይዳሰሳል። በመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት ሁለቱ ሙያዎች በተለያዩ ያታዎች የሚሠሩ ናቸው። ይኸውም የሸክላ ሥራ ሙሉ በሙሉ በሴቶች ብቻ የሚሠራ ሲሆን የቆዳ ስራ ደግሞ በአብዛኛው በወንዶች የሚሠራ ነው።የሸክላ ሙያ ውስጥ ወንዶች በምንም ዓይነት መንገድ የማይሳተፉ ሲሆን ፣በቆዳ ሙያ ውስጥ የሚሳተፉት በብዛት ወንዶች ሲሆኑ ሴቶችም የቤት ቁሳቁሶችን በተለይም የስፌት ዕቃዎችን በማስጌጥ ይሳተፋሉ።

ሁሉም የሸክላ ባለሙያዎች ወንዶች በምን አይነት መንገድ ያግዟችኋል? የሚል ጥያቄ ሲቀርብላቸው የሚሠጡት መልስ በአግራሞት የተሞላ እና በፌዝና በሳቅ የታጀበ ነው። ይህን ጥያቄ ካቀረብኩላቸው ባለሙያዎች ውስጥ የ 25 ዓመቷ ወ/ሮ በሠና መኮንን አንዷ ነች። እሷም የሚቀጥለውን አግራሞት ያዘለ መልስ ሰጥታኛለች። " ሆ! ምን አርገሙ ሊረዳኝ ነው? ገሉን ሊፈጨው ነው ጭቃውን ሊሸከም? ኧረ እሱ አለመደውም፤ ልጄም ወንድ ነው፤ ሴት ብትሆን እንኳ አለማምዳት ነበር፤ ለነገሩ እሷ እያየች አተወውም እንጂ፤ እኔ የማላውቀውን እያየሁ አይደል የለመድሁት" (ቃለ መጠይቅ ሚያዚያዚያ 20/08/03)

ቁልፍ መረጃ አቀባዬ እማ ውበት ሸክላ ሲሰሩ ከቤተሰብ ውስጥ የሚያግዝዎትው አለ? ብየ ስጠይቃቸው "ማንም የሚረዳኝ የለም ሴት ልጅ የለኝም ልጆቼ ወንዶች ናቸው። ወንድ ምን ሊያደርግ ነው ከሆነለትም ሸማ መስራቱ ይሻለው ነበር እሱንም ቢሆን ተማሪ ስለሆኑ እሺ ብለው አይሰሩም። ደሞ ወንድ ሸህላውን ሊተኩስ ነው ጭቃ ሊጠፈጥፍ ፣ ወይስ ገል ሊፈጭ ጐታ እንኳን እሽ ብለው ጭቃ ነክተው እይሠሩም።" (ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 18፣ 2003) ብለውኛል።

በባጉና ሃና ቀበሌ ውበትና ጥራት ያላቸውን ዕቃዎችን በመስራት የሚታወቁት ወይዘሮ አበባም መረጃዎቹን ባሰባሰብኩበት ወቅት ባለቤታቸው በሞት የተለያቸው ሲሆን ከመሞቱ በፊት ይረዳቸው የነበረው ሸመናና ግብርና በመስራት እንጂ ሸክላ ስትሠራ አንድም ቀን አግዟቸው እንደማያውቅ እና እሳቸውም እንደማይፈልጉ

ገልጸዋል። ምክንያቱም ሽክላ ስራ ስለሆነ እናቶችም ለሴቶች እንጂ ለወንዶች ባለማውረሳቸው ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች የሽክላ ሥራ ሙሉ በሙሉ ከወንዶች ጣልቃ ገብነት ውጪ የሚሠራ ሙያ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ባለሙያዎቹም በአግራሞት ከተሞላው መልሳቸው ሙያው የእነሱ ብቻ መሆኑን አምነው የመቀበላቸው ደረጃ ከፍ ያለ በመሆኑ ወንዶች ያግዟችሁ ቢባሉ እንደ ነውር የሚቆጥሩት ይመስላል። ከዚህም ባለፈ ሙያውን የሴቶች ጉዳይ ብቻ አድርገው በማሠባቸው የወንዶችን ጣልቃ ገብነት ሊቃወሙ ይችላሉ ብሎ መገመትም ይቻላል።

በባህላዊ የቆዳ ሥራ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ሙያው የወንዶች ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። በመስክ ምልከታዬም ሆነ ከቃል መረጃዎች ለማረጋገጥ እንደቻልኩት ቆዳውን ከገበያ በመግዛት፣ ወንዝ ውስጥ በመዘፍዘፍ፣ ከወንዝ አውጥቶ በመወጠር እና በመፋቅ በአጠቃላይ እስከ መተልተል እና መስፋት ባለው የሥራ ሂደት ውስጥ ሴቶች ጣልቃ ሲገቡ አይታዩም። አቶ ሽታ ደነቀው የተባሉት የቆዳ ባለሙያ ሴቶች በቆዳ ሥራ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> *ሴቶችማ ምንም አይሠሩም፤ አይሆንላቸውም ሊያሸ ነው የተዘፈዘፈውን ተወንዝ አውጥተው ሊፍቁ ባይሆን እነሱ እኛ ሥራውን ሁሉ ጨርሰን ዥንዲ አውጥተን፣ አለሳልሰን ስንሠጣቸው። እነሱ እየቆራረጡ ቁና፣ ላደን፣ አገልግል ይለጉማሉ። አንቀልባውን ቀለም ይቀባሉ፤ በዛጐል ያሳምራሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 05፣ 2003 ዓ.ም)*

እኔም ምንትዋብ ልመንህ የተባሉትን የአቶ ሽታ ደነቀው ባለቤት በቆዳ ሥራ ውስጥ ያላቸን ድርሻ እንዲገልጹልኝ ስጠይቃቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል።

> *ቆዳው ተለሳልሶ ከተሠጠን አንቀልባ ተሆነ ሌላ ስራ ከሌለን ሁለት አንቀልባ በአንድ ቀን እናደርሳለን። የሚለጐም ዕቃ ተሆነ ደግሞ እንደ ዕቃው ዓይነት በአንድ ቀን አንድም ብዙም እንሠራለን። ስንለጉም ዕቃው ላይ ቆዳውን እያለበስን በወስፌ እየወጋን በሲርና በጭፋር እንሠፋዋለን። ተዚያ ውጪ ቆዳ መንከር እና መፋቅ እንኳ የኛ ስራ አይደለም። ሁኖልን እንስራ ብንል እንኳ ሰው መሳቂያ ነው የሚያረጉን (ቃለ መጠይቅ ግንቦት 6/2003 ዓም)*

በአጠቃላይ ለአብነት ከተጠቀሱት ሠዎች የቃል መረጃ እና ከሌሎችም የመስክ መረጃዎች ለማየት እንደተቻለው ጥናቱ በአተኮረባቸው ሁለት ወረዳዎች ውስጥ ሸክላ የሴቶች ሙያ በመሆን ከጥንት እስከዛሬ ድረስ የዘለቀ ሲሆን የቆዳ ሥራ ደግሞ በወንዶች የሚከናወን የዕደ ጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ ሆኖም በሁለቱ ሙያዎች ውስጥ የሚታየውን ያታዊ ተሳትፎ በንጽጽር ሥናይ፣ ሸክላ ሙሉ በሙሉ ከወንዶች ጣልቃ ገብነት ውጪ በሴቶች ብቻ የሚሠራ ሲሆን፤ የቆዳ ሙያ ላይ ግን ምንም እንኳ ብዙው ክፍል በወንዶች የሚሰራ ቢሆንም በተወሰን ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ ይታይበታል፡፡

7. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች

7.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የቆዳና የሸክላ ሥራ ውጤቶችን የአሠራር ሂደትና ጠቀሜታ በመመርመር ማሳየት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የባለሙያዎችን ህይወት በመዳሰስ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደረጃቸውን በማሳየት የአሉበትን ሁኔታ ማሳወቅም ሌላው የጥናቱ ዋና ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህን ዋና ዓላማዎችና ሌሎችን ንዑሳን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስም በመስክ ቆይታየ ምልከታንና ቃለ መጠይቅን በዋነኛ መረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ በእነዚህ ሁለት ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ትወራዎች አንፃር ተተንትነው ከሚከተሉት የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ተደርሷል፡፡

የሸክላ እና የቆዳ ሥራ ውጤቶች በስፋት ሲመረቱ እና አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ቁሶች ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሁለቱም ቁሶች የመመረት እና አገልግሎት የመስጠት ደረጃ እያሽቆለቆለ መጥቷል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት የሸክላ ባለሙያዎች ሃያ ሁለት የሚደርሱ የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ሲያመርቱ የነበረ ሲሆን በዚህ ወቅት ግን አስራ ሶስት ቁሶችን ብቻ በማበጀት ለገበያ እንደሚያቀርቡ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

የቆዳ ባለሙያዎችም እንደዚሁ ሃያ ሶስት የሚደርሱ የቆዳ ውጤቶችን ሲያበጁ የነበረ ሲሆን፤ በዚህ ወቅት ግን ሠባት አይነት ዕቃዎችን ብቻ ያመርታሉ፡፡ ከሰባቱ ውስጥም አራቱ ወቅት ጠብቀው በሠርግ እና በእርሻ ሥራ ወቅት ብቻ የሚበጁ ናቸው፡፡

ለሁለቱም ቁሶች የምርት ዓይነት መቀነስ ምክንያት የሆኑት ማህበረሰቡ ለባለሙያዎች ያለው አሉታዊ አመለካከት፤ የፋብሪካ ቁሶች በሠፊው መመረት መጀመራቸው፤ እንዲሁም የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር እና የሙያዎቹ አድካሚነት ይጠቃሳሉ፡፡

በሁለቱ ወረዳዎች የሚበጁት የሸክላ እና የቆዳ ቁሶች ከቀዳሚ ተግባራቸው በተጨማሪ የተጠቃሚ ግለሠቦችንና የማህበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል እንዲሁም ማህበራዊ ደረጃ በመግለጽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ይህ አገልግሎታቸውም ካላቸው ቅርጽ፣ መጠን፣ ቀለም እና ከብዛታቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአካባቢው በጥንቆላ የሚተዳደሩ ሠዎች ለየት ያለ /ያልተለመደ/ ቅርጽ እና ጌጣጌጥ የበዛባቸውን የሸክላ ቁሶች ይጠቀማሉ፡፡ ሌላው ማህበረሰብም እንደዚሁ ጌጥ የበዛባቸውን የቡና ማፍያ ጀበናዎች ከመናፍስት/ከዛር መንፈስ/ ጋር በማያያዝ ይጠቀማል፡፡ እንዲሁም ትልልቅ ጋንና ቧድናንም ለሀብት መገለጫ በማድረግ ከቤት ውስጥ አገልግሎት በተጨማሪ የማህበራዊ ደረጃ ወይም የክብሩ መገለጫ ያደርጋል፡፡

የቆዳ ቁሶችም እንደዚሁ በመጠናቸው እና በቀለማቸው የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያሳያሉ፡፡ በዚህ አካባቢ ለዚህ አገልግሎት ከሚውሉት ውስጥ አገዛ እና ላምነት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሁለቱም የዕደ ጥበብ ሥራዎች ተከታታይ ሂደቶችን በማለፍ የሚሠሩ ናቸው፡፡ ይኸውም የሸክላ ስራ አምስት ተከታታይ የሥራ ሂደቶችን አልፎ የሚሠራ ሲሆን የቆዳ ሥራ ደግሞ በስምንት ሂደቶች ይከናወናል፡፡

በሁለቱም ዘርፎች የሚተገበሩት ተከታታይ ሂደቶች በዘፈቀደ የሚከናወኑ ሳይሆን የባለሙያዎችን ክህሎት እና አቅም የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በሸክላ ሥራ ሂደት የሚተገበሩት ሂደቶች ከአንዱ /ከማስጌጥ/ በስተቀር በሌሎች ሁለም ቁሶች ላይ የሚተገበሩ እና አይቀሬ ናቸው፡፡ የቆዳ ቁሶችን ሥንመለከት ግን አንዳንድ ቁሶች ላይ ለምሳሌ ላምነት እና ገርንዲ ላይ ሁሉም ሂደቶች አይከናወኑባቸውም፡፡በሁለቱ ቁሶች የሚከናወኑት ሂደቶች ጉልበትን የሚጠይቁ ሲሆን ከሸክላ ሥራ የሸክላ አፈር መቆፈር እና ከገል ጋር ቀላቅሎ የማቡካት ሃደቶች በጣም አድካሚ ሲሆኑ፤ ከቆዳ ደግሞ ማልፋት ወይም ማሸት የሚባለው ሂደት ከሌሎች የበለጠ አድካሚ መሆኑን በጥናቱ ታውቋል፡፡

የሸክላ እና የቆዳ ቁሶች ከሚሠጧቸው ማህበራዊ እና ባህላዊ አገልግሎቶች በተጨማሪ ለባለሙያዎቹ የገቢ ምንጭ በመሆን የሚሠጡት አገልግሎት ቀላል አይደለም፡፡ ዋጋቸው ተመጣጣኝ በመሆኑ ደግሞ አብዛኛውን ዝቅተኛ ኑሮ የሚመራውን ማህበረሰብ የኢኮኖሚ አቅሙ በሚፈቅደው መጠን አየገዛ እንዲጠቀም አስችለውታል፡፡

ጥናቱ በአተኮረበት አካባቢ የሚኖሩት ባለሙያዎች ህይወት ሲታይ ከሌላው ማህበረሰብ የተገለሉ እና በአካባቢው በሚከወኑ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች የመሳተፍ ዕድላቸውም አነስተኛ ነው፡፡ ከተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት፣ ከማህበር፣ ከዕቁብ፣ ከጋብቻ ወዘተ በመገለል ከፍተኛ ሥነ ልቦናዊ ጫና ሲደርስባቸው ቆይቷል፤ አሁንም እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡ ሆኖም ይህ አይነቱ ድርጊት በቂ ባይባልም እየተቀረፈ እና የተወሰኑ መሻሻሎች እየታዩበባ መሆኑ በተኮረበትጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ከባለሙያዎች ህይዎት ጋር ተያይዞ የተደረጉ ጥናቶች ባለሙያዎች ቡዳ እየተባሉ እንደሚገለሉ ገልፀዋል።ይህ ጥናት በአተኮረበት አካባቢ የሚኖሩ ባለሙያዎች በዚህ መንገድ ሲገለሉ አይታዩም። ምክንያቱም በአካባቢውአን ሰው ቡዳ የሚባለው ዘር ካለበት ብቻ ነው እንጂ የእደ ጥበብ ስራ ስለሚሰራ ብቻ ቡዳ አይባልም።

ቀደምት ጥናቶች የባለሙያዎችን ህይወት በመዳሰስ ቡዳዎች ናቸው ተብለው ስለሚታሰቡ የሚገለሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህ ጥናት ባተኮረበት አካባቢ የሚገኙ ባለሙያዎች ግን ቡዳ እንደማይባሉ ተረጋግጧል፡፡ ምክንያቱም በዚህ አካባቢ አንድ ሰው ቡዳ የሚባለው በዘሩ የቡዳ መንፈስ አለበት ተብሎ ከታመነ ብቻ እንጂ የእደጥበብ ሥራ ስለሚሰራ ብቻ ቡዳ ተብሎ አይገለልም፡፡

በሁለቱ ሙያዎች የሚታየውን ፆታዊ ተሳትፎ ስናይ የሸክላ ሥራ ሙሉ በሙሉ በሴቶች የሚከናወን ሲሆን የቆዳ ሥራ ደግሞ በወንዶች የሚሰራ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ባለሙያዎችን የተለያዩ አጋጣሚዎች ተጠቅሞ ሲያገሏቸው እና ሲያንቋሸሻቸው ቢታይም ቁሶቹን ግን ለማህበራዊ፣ እና ለተለያዩ ባህላዊ እና

ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በስፋት ይጠቀምባቸዋል፡፡ ማህበረሰቡ ለባለሙያዎችና ለቁሶች ያለውን አመለካከት ስናይ ተቃራኒና ሚዛናዊ ያልሆነ ነው፡፡ የሙያው ውጤቶች የሆኑትን ቁሶች አጣጥሞ በመጠቀም ባለሙያዎችንና ሙያውን ማንቋሸሽ የአካባቢው ማህበረሰብ የረኸም ጊዜ ልምድ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሁለቱን ሙያዎች ሁኔታ ስንመለከት የቆዳ ሥራ በአጋጠመው የጥሬ አቅርቦት ችግር /የጉሎ ዋጋ መናር/ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ተፈላጊነት በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነሱ የመቅረት አዝማሚያ ይታይበታል፡፡ የሸክላ ሙያ ግን ቁሶቹ ገበያ ላይ ያላቸው ተፈላጊነት በአንፃራዊነት የተሻለ ስለሆነ የመበጀት እድሉ ሠፋ ያለ ሲሆን የሙያው ቀጣይ ህልውናም የተሻለ ተስፋ አለው፡፡

ሁለቱ ወረዳዎች በእነዚህ የዕደ ጥበብ ሥራዎች ዙሪያ እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴ ሲታይ ቡሬ ወረዳ ለሁለቱም ሙያዎች ጥሩ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም የወረዳው ከተማ አስተዳደር ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ከጥቃቅን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር በተመባበር ለሸክላ ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት እንዲሁም ከሌላ አገር ዘመናዊ የሸክላ ቁሶችን በሞዴልነት በማምጣት እና ለባለሙያዎች በማሳየት፣ አዳዲስ ቁሶች እንዲሰሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ ለቆዳ ባለሙያዎችም የሚሰሩበት ቤት በመስጠት እያበረታታቸው ይገኛል፡፡ የወንበርማ ወረዳ ግን በሸክላ ሙያ ዙሪያ ምንም ያደረገው ነገር የሌላ ሲሆን ለቆዳ ባለሙያዎች ግን ምንም እንኳን ባይሳካም ሥልጠና እና የመስሪያ ቦታ የመስጠት ሙከራ ማድረጉን ከባለሙያዎች እና ከወረዳው ኃላፊዎች የተገኙ መረጃዎች አሳይተዋል፡፡

7.2 የይሁንታ ሃሳብ

የሸክላ እና የቆዳ ቁሶች ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጡት ማህበራዊ እና ባህላዊ አገልግሎት ከፍተኛ መሆኑን ከትንተናው እና ከጥናቱ ግኝቶች ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእነዚህ ጠቃሚ ቁሶች ባለቤት የሆኑት ባለሙያዎች ህይወት አሳዛኝ መሆኑንም ለማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በእነዚህና ሌሎች ችግሮች ሳቢያ በአሁኑ ጊዜ የቁሶቹ አገልግሎት ላይ የመዋል እና የመበጀት ደረጃ ቀንሷል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለም ቁሶቹ በዚያ አካባቢ ሊጠፉ የሚችሉበት እድል የሠፋ ነው፡፡ ችግሩ

ከመስፋፋቱ በፊት የሚመለከታቸው የወረዳው አስተዳደሮችና መስሪያ ቤቶች የሚከተሉትን መፍትሄዎች ቢተገብሩ የተሻለ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

- የማህበረሰቡን መጥፎ አመለካከት ለመቀየር የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ቢሰጥ፣
- የሁለቱም ወረዳዎች ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ባህላዊ ቁሶችን በሚመለከት ያደረገው ምንም አይነት ጥናትም ሆነ የማስተዋወቅ ሥራ ባለመኖሩ ወደ ፊት በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን ደከም ያለ እንቅስቃሴ ቢያሻሽል፣
- ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የወረዳው አስተዳደሮችና የቢሮ ኃላፊዎች እንደገለፁት በባዛሮች ላይ የሚያደርጉትን የዕደ ጥበብ ሥራዎችን የማስተዋወቅ ሥራ በሌሎች መንግስታዊ እና ማህበራዊ ተቋማት ዕድሉ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ቢያመቻቹ፣
- የወረዳው ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ከጥቃቅን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት የጀመሩትን የባለሙያዎቹን ሥራ የማሻሻል ሥልጠና እና የመስራያ ቦታ አቅርቦት አሻሽለው ቁሶቹ በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤት በሆኑ መሳሪያዎች እንዲሠሩ ቢያደርጉ፡፡

ዋቢ ጽሁፎች

ሀብታሙ እንግዳው፡፡ “በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሻሞ ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒያለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2001፡፡

ሄለን አላምረው፡፡ “ባህላዊ ሽመናና የቆዳ ስራ በደምበጫ አካባቢዋ፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999፡፡

ራሄል ወርቁ፡፡ “የቅመም አቀማመም ብልሃቶችና አሰያየማቸው ከማህበረሰባዊ ስነ ልሳን አኳያ ሲቃኝ፡፡” ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993፡፡

ብርሃነ ትንሳኤ ወልደ ሰንበት፡፡ “የሽማኔና የማዕድ ቤት ዕቃዎች ስያሜ፡፡” ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1968፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ “ባህላዊ የቤት እቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ፡፡” ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993፡፡

ታምራት ሀይሉ፡፡ “የብራና መፃህፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣2000፡፡

ታሪኩ ሰብስቤ፡፡ “የወላይታ ብሂረሰብ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ፎክሎራዊ ገፅታ፡፡” ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000፡፡

አስቴር ሙሉ፡፡ “ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣2000፡፡

አበበ መርዕድ። "በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 2000።

ዓብዩ አስማማው። "የቤት ውስጥ መገልገያና ማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን የአርጎባ ልዩ ወረዳ።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 2000 ዓ.ም።

ዓብይ ፍትህዓወቅ። "የግብርናና ተግባረድ ስያሜዎች።" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1963።

እንዳልካቸው ደሳለኝ። "የምሁር ጉራጌ ባህላዊ ምግቦች አውዳዊ ትንተና።" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2001።

ከተማ ደስታ። "የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ የስራ መሳሪያዎች ስያሜ።" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2004።

ውብሸት አሰፋ። "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል።" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1978።

ደረጀ ቤተ። "በጣርማ በር ወረዳ የሚበቅሉ የእህል ዘሮችና ቃል ግጥሞች።" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2001።

ደረጀ ስዩም። "ከተጉለት እና ቡልጋ አውራጃ የተሰበሰቡ የሽማኔን ህይወት የሚያንፀባርቁ ስነቃላዊ ግጥሞች ጥናት።" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ

የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1982፡፡

ደስታ ሎሬንስ፡፡ "የከምባታ ህብረተሰብ ባለእጆች እና ስነ ቃሎቻቸው፡፡" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1982፡፡

Ames, L. Kenneth. "Meaning in Artifacts: Hall Furnishings in Victoria America." In Journal of Interdisciplinary History; Vol IX; No. 1, PP. 19-46; 1978.

Berterame, Stefeno and Lordan Magni. " Potter Between Adaptation and Survival in the Beles Resettlement Area (Ethiopia)" in Resettlement and Rural Development in Ethiopia; Paolo Dieci and Claudio Viezzoli (eds). Italy; France Angle, Milano: 1992.

Cleary, Ann MC. "Methods and Theory of Material Culture Studies." Course note on line at — URL: http://WWW.bliklist.Com art aide/ theories/ (n.d).

Dorson, M. Richard (ed.); Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press 1972.

Gallagher, J "The Prepation of Hides with Stone Tools in South Central Ethiopia." Journal of Ethiopia Studies. V. 12, No 1, 1974.

Gedef Abawa. "An Ethno Archeological Investigation of Pottery Making Among Traditional Potters of Gonder" Addis Ababa University Development Archeology, MA Thesis, 2005.

Glassie, Henry. Folkloristic Study of the American Artifact: Objects and objectives" In Hand book of American Folklore. Ricahrd M. Dorson (ed). Bloomington: India University Press, 1983.

Leveron, Andreano. "Production of Pottery in the Development of the Beles valley." In Resettlement and RUral development in Ethiopia. Paolo Dieci and Claudio Vicezzoli; (eds). Italy; France Angeli, Milano, 1992.

Marchese, Ronald T. "Material Culture The Shape of Things Around us. Edition. Mayo (ed). Bowling Green, Bowling Green state university Popular Press, 1984.

Pankrust, Alula "Decline, Survival and Development of Class Comparisons of Tanning, Iron Work, Potters, Wood Work and Weaving with particular Reference to South Western Ethiopia" Ethiopia journal of development research, Addis Ababa University, Vol 22, No 2, 2000.

Prown, Jules David. "Mind in Matter An Introdcution to Material Culture Theory and Method. On line Availble at: WWW.http:// Jstor org/ about/ terms/ Html. 1982.

Roberts, E warren. "Folk Crafts" In Folklore and Folk life: An Introduction. Dorson, Richard's ed; Chicago and London: The University of Chicago Press. 1972.

Schlereth Thomas. Artifacts and the American Past. Online. Available at: WWW.http:// Btnep. Org. 1980.

_____ "Material Culture Research and Historical Explanation" on line http//: WWW.jstor. Org

Silver man. Ray mond A. (ed). Ethiopian Traditions of Creativity. East Lasting: Michigan State University Museum, 1999.

Takle Meride. "Gender Culture Pottery as Women Activity in Ethiopia: A Case Study of Selected Sites in Addis Ababa and is Surroundings."

Addis Ababa University School of graduate studies, MA Thesis in Ethiopia studies, 2002.

Tsehai Berhane Selassie "Gender and Occupational Potters in Wolayta Imposed Feminist and Mysterious Survival Ethiopia." In Gender Issues in Ethiopia. Addis Ababa University, institute of Ethiopian studies, 1991. "

Vlach, John Michael. "Folk Crafts Men." In Hand Book of American Folklore. Richard M. Dorson (ed). Bloomington: Indiana University press, 1983

Yodor, Don. "Folk cookery." In Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press. 1972.

አባሪ 1

ለዕደ ጥበብ ሠራተኞች የቀረቡ የቃል መጠይቆች

1. ሙሉ ስም
2. ዕድሜ
3. የጋብቻ ሁኔታ
4. የቤሰብ ብዛት
5. የገቢ ምንጭ
6. የመኖሪያ አካባቢ
7. ሙያውን መስራት የጀመራችሁት ከመቼ ጀምሮ ነው?
8. ሙያውን እንዴት ለመዳችሁት?
9. የሙያችሁ ውጤት የሆኑትን ቁሶች ለመስራት ምን ምን መሳሪያዎች ትጠቀማላችሁ?
10. በመሳሪያዎቻችሁ ተጠቅማችሁ ቁሶችን ለመሥራት ምን ምን ጥሬ ዕቃዎችን ትጠቀማላችሁ?
11. ለቁሶቹ መስሪያ የሆነውን ጥሬ ዕቃ (ቆዳ ወይም የሸክላ አፈር) ከየት ታገኛላችሁ)?
12. ቁሶችን እንዴት ትሰራላች? ቅደም ተከተሉ ምን ይመስላል?
13. አፈሩ የማን ነው? አፈሩን በም አይነት መሳሪያ (ዕቃ) ታመጡታላችሁ? ለምን?
14. ቁሶችን ለመስራት ምን መሳሪያዎች ትጠቀማላችሁ?
15. አንድ ቁስ ተሠርቶ ለገበያ ለመቅረብ ስንት ቀን ይፈጃል?
16. ቁሶችን መቼ መቼ ትሰራላቹሁ?
17. የገበያው ሁኔታ እንዴት ነው?
18. ቁሶች የት ትሸጣላችሁ?
19. ብዙ ጊዜ ትልልቅ ዕቃዎችን ነው ወይስ ትንንሾችን የምትሰሩት? ለምን?
20. የምትሰሯቸውን ቁሶች ዋጋ በዝርዝር ብትነግሩኝ?
21. ድሮ ስትሰሯቸው የነበሩ እና አሁን የተዋችኋቸው ቁሶች አሉ? ከአሉ ለምን?

22.በዚህ ወቅት ተፈላጊ የሆነው ዕቃ የትኛው ነው? ድሮስ? ለምን?

23.ሙያችሁን ትወዱታላችሁ?

24. አልወድም ከሆነ ለምን?

25. ስትሰሩ ከቤተሰብ ውስጥ ማን ይረዳችኋል? ሴት/ወንድ?

26. ለልጆቻችሁ እንዴት ታለማምዳላችሁ? አናለማምድም ከሆነ ለምን?

27.ሙያችሁን በአግባቡ እንዳትሰሩ እንቅፋት የሆነባችሁ ነገር ምንድነው?

28.በተመሳሳይ የእጅ ሙያ ላይ የተሰማራችሁ ሰዎች ተደራጅታችሁ እንድትሰሩ ያገዛችሁ የመንግስት አካል አለ?

29.ካለ እንዴት ሰራችሁ ከሌለ ለምን?

30.በአካባቢያችሁ የሚኖረው ባለሙያሁ ያልሆነው ማህበረሰብ ለእናንተ እና ለሙያችሁ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

አባሪ 2

ለታሪክ አዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ለሀይማኖት መሪዎች እና ለተጠቃሚዎች የቀረቡ የቃል መጠይቆች

ሙሉ ስም

ዕድሜ

መኖሪያ አካባቢ

የሥራ ድርሻ

1. ቡሬ ዳሞት የሚለው ስያሜ ከየት መጣ?
2. የቡሬ ወረዳ ማህበረሰብ ማህበራዊ ህይወት ምን ይመስላል? የመረዳዳት የመደጋገፍ ባህል አለው?
3. የቡሬ ወረዳ ማህበረሰብ የሀይማኖት ሁኔታ እንዴት ይገለፃል?
4. የወረዳ እጅ ሠሪዎች (ባለሙያዎች) በተለይ የቆዳና የሸክላ ባለሙያዎች የትውልድ ቦታቸው የት ነው?
5. ከወረዳው ውጪ ከሆኑ ከየት መጡ? እንዴት መጡ?
6. በልዩ ቀበሌው ይኖሩ የነበሩ አሁን አገር የለቀቁ ሸክላ እና ቆዳ ሠሪዎች አሉ?
7. ከአሉ አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል?
8. የኢኮኖሚ ደረጃቸውስ?
9. ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው የማህበር፣ ዕቁብ፣ የጋብቻ ሁኔታ እንዴት ነው?
10. እነዚህ ቁሶች በዚህ አካባቢ መቼ መሠራት ጀመሩ?
11. በዚህ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው የሸክላና የቆዳ ቁሶች ምን ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊና ማህበራዊ አገልግሎት አላቸው?
12. የሸክላ ባለሙያዎችች እና ቆዳ ስሪዎች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል?
13. እዚህን ሁለት ቁሶች ቤታችሁ ውስጥ ትገለገሉባቸዋላችሁ?
14. ከተጠቀማችባሁቸው ከድሮ እና ከአሁን መቼ በብዛት ትጠቀማላችሁ? የትኞቹን ቁሶች? ስትጠቀሙባቸው ቆይታችሁ አሁን የተዋችሁዋቸው ቁሶች ይኖሩ ይሆን? ከአሉ የትኞቹ? ለምን

15. የቆዳ እና የሸክላ ቁሶችን ከየትና እንዴት ታገኛለህ/ታገኛላችሁ

አባሪ 3

ለቡሬ እና ወንበርማ ወረዳ አስተዳደር ሀላፊዎች እና የባህል ቢሮ ባለሙያዎች የቀረበ የቃል መጠይቅ

1. በወረዳው ምን ያህል ቀበሌዎች ይገኛሉ?
2. የወረዳው መገኛ ቦታ እና መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ
3. የወረዳው የህዝብ መጠንና ህዝቡ የሚከተለው የእምነት ዓይነት
4. የህዝቡ የኢኮኖሚ መሠረት ልማት የገቢ ምንጭ?
5. የአካባቢው የአየር ንብረት ሁኔታ ምን ይመስላል?
6. የእጁ ሙያ ለሀገር ዕድገት ያለው አስፈላጊነት ምንድን ነው?
7. የእጅ ባለሙያዎች (በተለይ ባህላዊ የቆዳ እና የሸክላ ባለሙያዎች) በወረዳው በየትኛው ክፍል ይገኛሉ?
8. የባለሙያዎችን የሙያ ክህሎት ለማሻሻል ምን አይነት ድጋፍ ተደርጓል?
9. ወደፊት ባለሙያዎችን በሙያቸው ተጠቃሚ ለማድረግ ምን የታቀደ ነገር አለ?
10. የወረዳው ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸው እና መለያው የሆኑ ቁሶች አሉ ብለው ያምናሉ?
11. ካሉ እነሱን ለመጠበቅና ባህላዊ ጥቅማቸውን ለማጉላት ምን ተደርጓል?
12. በቁሳዊ ባህል ዙሪያ ጥናቶች ተደርገው ያውቃሉ?
13. ወረዳው በቁሶች ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ አካላትን በማበረታት በኩል ያለው አስተዋፅኦ ምን ይመስላል?

አባሪ 4

መረጃ የሠጡ የቡሬ እና ወንበርማ ወረዳ አስተዳደር እና ሀላፊዎች ዝርዝር

ተ.ቁ	ስም	ፆታ	ዕድሜ	የሥራ ድርሻ	መኖሪያ አካባቢ	የሰጡት የመረጃ አይነት
1	ወ/ሮ ወለት ይፋ	ሴት	28	የቡሬ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ፅ/ቤት ሀላፊ	ቡሬ	ባለሙያዎች መገኛ፣ ቀበሌ፣ በሁለቱ ሙያዎቹ ዙሪያ ስለአደረጉት አስተዋፅኦ
2	መስፍን አበጀ	ወንድ	35	የቡሬ ወረዳ አስተዳደር ክትል ከተንቲባ	ቡሬ	የእጅ ሙያ ለሀገር ዕድገት ያለው አስተዋፅኦ እና የዕደጥበብ ሥራዎችን በሚመለከት ወረዳው ያለውን ዕቅድ
3	ግርማ ታፈሰ	ወንድ	30	የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትና ዕደ ጥበባት ስራዎች አፈሰር	ቡሬ	በዕደጥበብ ሥራዎች ዙሪያ በተለይም በሸክላ እና በቆዳ ዙሪያ ወረዳው ያለውን እንቅስቃሴ
4	አለማየሁ ሞላ	ወንድ	25	የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ኦፊሰር	ቡሬ	ስለ ወረዳው አጠቃላይ ገፅታ
5	ወ/ሮ አሊማ ሃሚድ	ሴት	26	በአ/ብ/ክ/መ በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን የሥርዓት ፆታ ስርፀትና ክትትል የሥራ ሂደት	ቡሬ	ወረዳው በሸክላ እና በቆዳ ስራዎች ዙሪያ ያደረገው ፆታዊ አስተዋፅኦ
6	አለማየሁ መርድ	ወንድ	30	የቡሬ ወረዳ ኮሙኒኬሽን ጉዳዩች ባለሙያ	ቡሬ	ቢሮው በሁለቱ የዕደ ጥበብ ዘርፎች ዙሪያ ያለውግንዛቤ
7	የሸዋስ ተመስገን			የጥቃቅን ንግድና ኢንዲስትሪ ስራዎች ማስፋፊያ	ቡሬ	የሸክላ ባለሙያዎችን የሚመለከት መረጃ

8	ምህረት ዘሪሁን	ወንድ	27	የሥነ-ፅሁፍና ቲያትር አፈሰር	ሸንዲ	በቆዳ እና በሸክላ ዙሪያ ሼንደ ወረዳው በቁሶች ዙሪያ ያለው ግዛቤ
9	አወቀ መሠረት	ወንድ	27	የወንበርማ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት የሙዚቃና ውዝዋዜ አፈሰር	ሸንዲ	በዕደ ጥበብ ሥራዎች ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችንና ወረዳው በቁሶች ዙሪያ ያለው ግንዛቤ
10	ሀብታሙ በውቀት	ወንድ	25	በወንበርማ ወረዳ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮ ፅ/ቤት የፕሬስ ስራዎች ዜናና ፕሮግራም የሥራ ሂደት ባለሙያ	ሸንዲ	በዜናና በመፅሄቶች ላይ ስራዎችን የዕደ ጥበብ ሥዎችን የማስተዋወቅ ሥራ
11	ማማሩ ሙላት	ወንድ	25	የወንበርማ ወረዳ ሚሊሻ ፅ/ቤት የትጥቅ እና ጦር መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት ፈፃሚ እና አስተባባሪ	ሸንዲ	ወረዳው ያደረገውን የዕደ ጥበብ ሥራዎች የማስተዋወቅ ሥራ
12	የአብሥራ መላኩ	ሴት	26	የወንበርማ ወረዳ ባህል ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ	ሸንዲ	ወረዳው በሸክላ እና በቆዳ ቁሶች ዙሪያ ያደረገው ጥናታዊ ፅሁፍ

አባሪ 5

የሸክላ እና የቆዳ ባለሙያ የሆኑ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

ተ.ቁ	ስም	ፆታ	ዕድሜ	ዝርዝር የስራ ድርሻ	መኖሪያ አካባቢ	የሠጠው/ችው የመረጃ አይነት
1	ወንዴ አንባው	ወንድ	67	የቆዳ ባለሙያ	ባጉና ሀና	ስለቆዳ ሥራ (በተለይም ስለሻጉንዲ የአሰራር ሂደት እና ስለ ቆዳ ባሙያዎች ማህበራዊ ህይወት
2	ሽታ ደነቀው	ወንድ	35	የቆዳ ባለሙያ	ሸንዲ	ስለቆዳ ቁሶች የአሰራር ሂደት እና ያታዊ የስራ ድርሻ ሥለ ቆዳ ቁሶች ገበያ ሁኔታ
3	በላይ ደነቀው	ወንድ	25	የቆዳ ባለሙያ	ሸንዲ	የቆዳ ቁሶች ለመዳ እና የቆዳ ቁሶችን የአጋጠመ የጥሬ ዕቃ ችግር
4	ደነቀው አባተ	ወንድ	50	የቆዳ ባለሙያ	ሸንዲ	ለቆዳ ባለሙያዎች መንግስት ያደረገውን አስተዋፅኦ ስለቁሶ የአሰራር ሂደር
5	ይበልጣል ሹመቴ	ወንድ	25	የቆዳ ባለሙያ	ሸንዲ	ሥለመጫኛ እና ምራን የአሰራር ሂደት
6	አስማማው ተረፈ	ወንድ	25	የቆዳ ባለሙያ	ዋንጫ ሰፈር	ሙያ ለመዳ የቁሶች የገበያ ሁኔታ የቁሶች የአሰራር ሂደት
7	ታደሰ ወንድይራድ	ወንድ	70	የቆዳ ባለሙያ	ባጉና ሃና	ሥለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት

8	ምንትዋብ ልመንህ	ሴት	40	የቆዳ ባለሙያ	ሸንዲ	ሥለ መለጎም (የሥፌት ዕቃዎችን ማጌጥ)
9	አበባ ደመላሽ	ሴት	40	የሸክላ ባለሙያ	ባጉና ሀና	የሸክላ ስራ ሂደት፤ የጠንቋይ ጀበናና ማጨሻ፤ ስለ ጠንቋዮች ሸክላ አጠቃቀም
10	ውበት ከበደ	ሴት	40	የሸክላ ባለሙያ	ሸኳ ዮሐንስ	ስለ ባለሙያዎ ማህበራዊ ህይወት፣ ስለቁሶች አሰራር እና ሸክላ አፈር አይነት
	መልካምጤናው	ሴት	60	የሸክላ ባለሙያ	ባጉና ሃና	ሥለ መሥረያ ቁሶች እና ስለቁሶች አሰራር
12	ምንትዋብ ስማቸው	ሴት	35	የሸክላ ባለሙያ	ባጉና ሃና	የሸክላ አፈርን ለሥራ ማዘጋጀት እና ንፅሕና ፈላጊነት
13	ቦሰና መኮነን	ሴት	25	የሸክላ ባለሙያ	ባጉና ሃና	የማንደጃንና የሸክላን የአሰራር ሂደት እንዲሁም ከሸክላ ቁሶች ጋር ተያይዞ የሚነገርን የባለሙያዎች እምነት
14	ታሪክ አያሌው	ሴት	45	የሸክላ ባለሙያ	ባጉና ሀና	ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት
15	ሙሉ ኩራባቸው	ሴት	40	የሸክላ ባለሙያ	ሻኳ ዮሐንስ	ስለ ቶፋ እና ድንጉኝ አሰራር
16	ዓለሚቱ የኔአለም	ሴት	30	የሸክላ ባለሙያ	ሻኳ ዮሐንስ	ስለ ሙያ ለመዳ
17	ማስረሻ ሙላቱ	ሴት	55	የሸክላ ባለሙያ	ሻኳ ዮሐንስ	ስለ ሸክላ ቁሶች ገበያ ሁኔታ

አባሪ 6

መረጃ የሠጡ የሀገር ሽማግሌዎች

ተ.ቁ	ስም	ያታ	ዕድሜ	የሥራ ድርሻ	የሰጡት የመረጃ ዓይነት
1	ገላው አበጀ	ወንድ	80	ግብርና	ስለባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት፣ ስለቁሶች ጥቅም፣ ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት፣ ስለቡሬ ወረዳ ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜ
2	መርጌታ ዘማሪያም	ወንድ	60	መርጌታ	ስለ ቆዳ እና የሸክላ ቁሶች ቤተክርስቲያናዊ አገልግሎት
3	አባ አማረ ተሰማ	ወንድ	65	ግብርና	ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት፣ ስለ ቡሬ ወረዳ ታሪክና ስያሜ

አባሪ 7

የሸክላ ቁሶች አይነት እና አካላዊ ገፅታ

የሸክላ ቁሶች ቀላዊ መጠሪያ		ስፋት በሳ.ሜ	ቁመት በሳ.ሜ	የአፍ ስፋት በሳ.ሜ	የአንገት ሥፋት በሳ.ሜ	የአንገት ርዝመት በሳ.ሜ	የመያዝ አቅም በሊትር	ዋጋ በብር
ፅዋ								
ድንጉኝ		22	7	12	11	2	1	ከ2-3
ቶፋ		30	12	13	12	3	2 ሊትር ከግማሽ	4
የጣን ማጨሻ								
	የጠንቋዮች ማጨሻ ትልቁ	30	60	4	12	3		45
	የሌላው ማህበረሰብ	8	6	3	3	3		ከ3-4
ጀበና /ኩስኩስት	የጠንቋይ	22		3	3	4	2 ሊትር ተኩል	ከ30-40
	የሌላው ማህበረሰብ	20	5	3	3	3	2 ሊትር	ከ3-6
ገንቦ	አሳደሪ	45	22	5	25	6		15
	የግብር	40	19	6	6	10		10
ድስት	ሰታቴ	50	10	35	33	2	5	20
	መካከለኛ	ከ35-40	9	30	32	1	3 ተኩል	15
	የግብር	30	ከ7-8	28	28	1	3	7
	ትንሽ	20	4	15	20	1	1 ተኩል	5
ማንደጃ	ላቀች	30	25	30	40	1	5	5
	ተንከርተት	35	30	35	10	3	5	5
ማሠሮ	30	30	21	5	4	4	5	ገበያ ላይ አይቀርብም
ሽንክላ	41	41	25	7	4	5	10	10
ማድጋ		45	26	8	6	4	35	25
ቧድና		55	25	10	5	4	50	60
ጋን		120	60	25	7	5	130	150
ዋዳት	ትልቁ	40	8	50	-	-	5	10
	ትንሹ	25	6	26	-	-	1-2	15

አባሪ 8

ባለሙያ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች

ተ.ቁ	ስም	ፆታ	ዕድሜ	የሥራ ድርሻ	መኖሪያ አካባቢ	የሰጡት የመረጃ አይነት
1	መድሀኒት ዘገየ	ሴት	47	ግብርና	ሻኳ ዮሐንስ	ስለ ቁሶች ጥቅም እና ስለባለሙያዎች የህይወት ልምድ
2	ባይህ ግዛቸው	ወንድ	60	ግብርና	ከበሳ አቦ	
3	ምንታምር ገዜ	ሴት	47	ግብርና	ከበሳ አቦ	ስለቆዳ ቁሶች ቀለም ስለባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት፤ ስለ ለምድ አገልግሎት
4	መልካም ዓለማየሁ	ሴት	40	ግብርና	ከበሳ አቦ	ስለ ባለሙያዎች ወቅታዊ የጋብቻ ሁኔታ
5	የኔሁን ዘገየ	ወንድ	55	ግብርና	ከበሳ አቦ	ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት እና ስለ ጋን ባህላዊ ጥቅም
6	አበበ መልኬ	ወንድ	27	ነጋዴ	ቡሬ ከተማ	ስለ ባለሙያዎ ጋብቻ ሁኔ
7	መቅደስ አረፍ አይኔ	ሴት	40	የቤት እመቤት	ቡሬ ከተማ	ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት
8	ምንተስኖ በቀለ	ወንድ	30	ነጋዴ	ቡሬ ከተማ	ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት
9	ቢዘንጋው አናጋው	ወንድ	40	ግብርና	ቡሬ ከተማ	ስለ ጀበርናና ዝናር ጥቅም
10	ወ/ሮ ዕፁብ ድንቅ ውለታው	ሴት	39	መምህር	ቡሬ ከተማ	ስለባለሙያዎች የጋብቻ ሁኔታ
11	ሙላት አላምረው	ወንድ	45	መምህር	ቡሬ ከተማ	ስለ ቆዳና ሸክላ ቁሶች ጥቅምና ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት

አባሪ 9




1. የአቶ በላይ ደነቀው ታናሽ ወንድም ቆዳ ሲፍቅ



2. ወ/ሮ መልካም ጤናው ስለ ሸክላ ቁሶች የገበያ ሁኔታ ሲገልጹ




3. ወ/ሮ ውበት የሸክላ ቁሶችን መወጠኛ እቃ ይዘው




4.አቶ ሽታ ደነቀው ለዝንዲ መስሪያ የሚሆን ቆዳ ሲያሹ




5. ከግራ ወደቀኝ ድንጉኝ እና የአረቄ ማድጋ ክዳን ወይም መድፊያ



6. አጎዛ ሲቃቃ (ሲወጠር)



7. ከጭቃ የተሰራ የጀበና መወጠኛ ቁስ



8. ወ/ሮ አበባ የሸክላ አፈር ሲፈጩ




9. ቶፋ እና ክዳኑ(መግላሊት)



10.ወ/ሮ ምንትዋብ ልመንህ ስለመለጎም ሲያስረዱ



11. አጥኝዋ የጽዋ እቃ ይዛ



12. ዋዲያቶች

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ የእኔ ወጥ ሥራ ነው። ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴንም አረጋግጣለሁ።

Degiyew Tilahun

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ 2003 ዓ.ም

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ማሚያ ጽሁፍ የእኔ ወጥ ሥራ ነው። ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርስቲ የዲግሪ ማሚያ ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴንም አረጋግጣለሁ።

Desalew T. Tahir

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ 2003 ዓ.ም